፮፡ የምትነድድ፡ እሳት፡ ናቸው ። እነሆ ÷ በፊቱ፡ ተጽፎአል ፦ ኃጢአታችሁንና፡ የአበቶቻችሁን፡ ኃጢአት፡ በአንድ፡ ላይ፡ ወደ፡ ብብታቸው፡ ፍዳ፡ አደርጌ፡ እመልሰለሁ፡ እንጂ፡ ዝም፡ አልልም ÷ ይላል፡ እግዚአብሔር፡ ፯፡ በተራሮችም፡ ላይ፡ ስላጠኑ ÷ በኮረብቶችም፡ ላይ፡ ስለ፡ ሰደቡኝ ÷ ስለዚህ፡ አስቀድመው፡ የሠሩትን፡ ሥራቸውን፡ በብብታቸው፡ እሰፍራለሁ ።

፰፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ይላል ፦ ወይን፡ በዘለላው፡ በተገኘች፡ ጊዜ ፦ በረከት፡ በእርስዋ፡ ላይ፡ አለና፡ አታጥፉት፡ እንደሚባለው ÷ ሁሉን፡ እንዳላጠፋ፡ ስለ፡ ባሪያዎቼ፡ እንዲሁ፡ ፱፡ አደርጋለሁ ። ከያዕቆብም፡ ዘርን፡ ከይሁዳም፡ ተራሮቼን፡ የሚወርሰውን፡ አወጣለሁ ፤ እኔም፡ የመረጥኋቸው፡ ይወርሱአታል ÷ ባሪያዎቼም፡ በዚያ፡ ይኖራሉ ። ሳሮንም፡ የበጎች፡ ማሰማርያ ÷ የአኮርም፡ ሸለቆ ፡ የላሞች፡ መመሰማያ፡ ፲፡ ለፈለጉኝ፡ ሕዝቤ፡ ይሆናል ። እናንተን፡ ግን፡ እግዚአብሔርን፡ የተዋቸሁ፡ ቅዱሱንም፡ ተራራዬን፡ የረሳችሁትን ÷ ጉድ፡ ለተባለ፡ ጣዖትም፡ ማዕድ፡ ያዘጋጃችሁትን ÷ እድል፡ ለተባለ፡ ጣዖትም፡ የወይን፡ ጠጅ፡ ለመጠጥ፡ ፲፪፡ ቀኮርን፡ የቀዳችሁትን ÷ እድላችሁን፡ ለሰይፍ፡ አደርገዋለሁ ÷ ሁላችሁም፡ ለመታረድ፡ ትጐነበሳላችሁ፡ በፊቴም፡ ክፉ፡ ነገርን፡ አደረጋችሁ ÷ ያልወደድሁትንም፡ መረጣችሁ፡ እንጂ፡ በጠራሁ፡ ጊዜ፡ አልመለሳችሁልኝምና ÷ በተናገርሁም፡ ጊዜ፡ አልሰማችሁኝምና ።

፲፫፡ ስለዚህ፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ይላል ፦ እነሆ ÷ ባሪያዎቼ፡ ይበላሉ፡ እናንተ፡ ግን፡ ትራባላችሁ፡ እነሆ ÷ ባሪያዎቼ፡ ይጠጣሉ ፡ እናንተ፡ ግን፡ ትጠማላችሁ፡ እነሆ ÷ ባሪያዎቼ፡ ደስ፡ ይላቸዋል፡ እናንተ፡ ግን፡ ታፍራላችሁ፡ ፲፬፡ እነሆ ÷ ባሪያዎቼ፡ ከልባቸው፡ ደስታ፡ የተነሣ፡ ይዘምራሉ ÷ እናንተ፡ ግን፡ ከልባችሁ፡ ጎዝን፡ የተነሣ፡ ትጮኻላችሁ ÷ መንፈሳችሁም፡ ስለ፡ ተሰበረ፡ ወዮ፡ ትላላችሁ ። ፲፭፡ ስማችሁንም፡ ለተመረጡት፡ ሕዝቤ፡ እርግማን፡ አድርጋችሁ፡ ጥተዋላችሁ ÷ ጌታ፡ እግዚአብሔርም፡ ይገድላችኋል ÷ ባሪያዎቹንም፡ ፲፮፡ በሌላ፡ ስም፡ ይጠራቸዋል ። እንዲሁም፡ በም ድር፡ ላይ፡ የተባረከ፡ በእውነት፡ አምላክ፡ ይባረክል ÷ በምድርም፡ ላይ፡ የማለ፡ በእውነት፡ አምላክ፡ ይምላል፡ የቀድሞው፡ ጭንቀት፡ ተረስቶአልና ÷ ከዓይኔም፡ ተሰውሮአልና ። ፲፯፡ እነሆ ÷ አዲስ፡ ሰማይና፡ አዲስ፡ ምድር፡ እፈጥራለሁና፡ የቀደመውትም፡ አይታሰቡም ÷ ፲፰፡ ወደ፡ ልብም፡ አይገቡም ። ነገር፡ ግን፡ በፈጠርሁት፡ ደስ፡ ይበላችሁ፡ ለዘላለምም፡ ሐሤት፡ አደርጉ፡ እነሆ ÷ ኢየሩሳሌምን፡ ለሐሤት፡ ፲፱፡ ሕዝብዋንም፡ ለደስታ፡ እፈጥራለሁና ። እኔም፡ በኢየሩሳሌም፡ ሐሤት፡ አደርጋለሁ፡ በሕዝቤም፡ ደስ፡ ይለኛል፡ ከዚያም፡ ወዲያ፡ የል

ቀሰ፡ ድምፅና፡ የዋይታ፡ ድምፅ፡ አይሰማበትም ። ፳፡ ከዚያም፡ ወዲያ፡ ጥቂት፡ ዘመን፡ ብቻ፡ የሚኖር፡ ሕፃን ÷ ወይም፡ ዕድሜውን፡ ያልፈጸመ፡ ሽማግሌ፡ አይገኝም ፡ ጕልማሳው፡ የመቶ፡ ዓመት፡ ሆኖት፡ ይሞታልና ÷ ኃጢአተኛውም፡ የመቶ፡ ዓመት፡ ሆኖት፡ የተረገመ፡ ይሆናልና ። ፳፩፡ ቤቶችንም፡ ይሠራሉ፡ ይቀመጡባቸውማል ፡ ወይኑንም፡ ይተክላሉ፡ ፍሬውንም፡ ይበላሉ ። ፳፪፡ ሌላ፡ እንዲቀመጥበት፡ አይሠሩም ÷ ሌላም፡ እንዲበላው፡ አይተክሉም ፡ የሕዝቤ ፡ ዕድሜ፡ እንደ፡ ዛፍ፡ ዕድሜ፡ ይሆናልና ÷ እኔም ፡ የመረጥኋቸው፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ረጅም ፡ ዘመን፡ ደስ፡ ይላቸዋልና ። ፳፫፡ እነርሱ፡ ከነልጆቻቸው፡ የእግዚአብሔር፡ ቡራኩን፡ ዘር፡ ናቸውና ፡ በከንቱ፡ አይደክሙም፡ ለጥፋትም፡ አይወልዱም ። ፳፬፡ እንዲህም፡ ይሆናል ፡ ሳይጠሩ፡ እመልስላቸዋለሁ ÷ ገና፡ ሲናገሩ ፡ እሰማለሁ ። ፳፭፡ ተኵላና፡ ጠቦት ፡ በአንድነት፡ ይሰማራሉ ÷ አንበሳም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ይበላል ÷ የእባብም ፡ መብል ፡ ትቢያ ፡ ይሆናል ። በተቀደሰው፡ ተራራዬ ፡ ሁሉ ፡ አይጐዱም ÷ አያጠፉምም ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፷፮ ።

፩፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ÷ ምድርም ፡ የእግሬ ፡ መረገጫ ፡ ናት ፤ የምትሠሩልኝ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? የማርፍበትስ ፡ ስፍራ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ፪፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ እጄ ፡ ሠርታለችና ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የእኔ ፡ ናቸው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ ትሑት ÷ መንፈሱም ፡ ወደ ፡ ተሰበረ ÷ በቃሌም ፡ ወደሚንቀጠቀጥ ፡ ሰው ፡ እመለከታለሁ ። ፫፡ በሬን ፡ የሚያርድልኝ ፡ ሰውን ፡ እንደሚገድል ፡ ነው ፡ ጠቦት ፡ ገብቶ ፡ የሚሠዋ ፡ የውሻውን ፡ አንገት ፡ እንደሚሰብር ፡ ነው ፡ የእህልን ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርብ ፡ የአሳማን ፡ ደም ፡ እንደሚያቀርብ ፡ ነው ፡ ዕጣንን ፡ የሚያሥታውስ ፡ ጣዖትን ፡ እንደሚባርክ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የገዛ ፡ መንገዳቸውን ፡ መረጡ ፡ ነፍሳቸውም ፡ በርኵሰታቸው ፡ ደስ ፡ ይላታል ። ፬፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የተሰለቀባቸውን ፡ እመርጣለሁ ÷ የፈሩትንም ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለሁ ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረጉ ÷ ያልወደድሁትንም ፡ መረጡ ፡ እንጂ ። በጠራሁ ፡ ጊዜ ፡ አልመለሱልኝምና ÷ በተናገርሁም ፡ ጊዜ ፡ አልሰሙኝምና ።

፭፡ በቃሉ ፡ የምትንቀጠቀጡ ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፦ የጠሉአችሁ ፡ ስለ ፡ ስሜም ፡ ያገለሩአችሁ ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ ፦ ደስ ፡ ታችኹን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ብለዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያፍራሉ ። ፮፡ የጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ከከተማ ÷ ድምፅም ፡ ከመቅደስ ÷ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ፍዳን ፡ የሚያመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቶአል ።

፯፡ ሳታምጥ ፡ ወለደች ፡ ምጥም ፡ ሳያገኛት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ። ፰፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቶአል ? እንዲህስ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አይቶአል ? በውኑ ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ታምጣለችን ? ወይስ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ይወለዳልን ? ጽዮን ፡ እንዳማጠች ፡ ወዲያው ፡ ልጆችዋን ፡ ወልዳለችና ። ፱፡ በውኑ ፡ ወደ ፡ መውለድ ፡ የማደርስ ፡ እኔ ፡ አላስወልድምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የማስወልድስ ፡ ማኅፀንን ፡ እኔ ፡ እዘጋለሁን ? ይላል ፡ አምላክሽ ።

፲፡ እናንተ ፡ የምትወድዱአት ፡ ሁሉ ÷ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋር ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ÷ ስለ ፡ እርስዋም ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ እናንተም ፡ የምታለቅሱላት ፡ ሁሉ ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ በደስታ ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ÷ ትጠቡ ፡ ዘንድ ፡ ከማጽናናት ፡ ዋኖ ፡ ጡት ፡ ትጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ጠጥታችሁ ፡ በክብርዋ ፡ ሙላት ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ። ፲፩፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እነሆ ÷ ሰላምን ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ የአሕዛብንም ፡ ክብር ፡ እንደሚጐርፍ ፡ ፈሳሽ ፡ እመልስላታለሁ ፡ ከዚያም ፡ ትጠባላችሁ ÷ በጫንቃ ፡ ላይ ፡ ይሸከሙአችኋል ፡ በጕልበትም ፡ ላይ ፡ እያስቀመጡ ፡ ያቀማጥሉአችኋል ። ፲፪፡ እናት ፡ ልጅዋን ፡ እንደ ፡ ምታጽናና ፡ እንዲሁ ፡ አጽናናችኋለሁ ÷ በኢየሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ትጽናናላችሁ ። ፲፫፡ ታያላችሁ ÷ ልባችሁም ፡ ሐሤት ፡ ታደርጋለች ÷ አጥንታችሁም ፡ እንደ ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡ ትበቅላለች ፡ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ለሚፈሩት ፡ ትታወቃለች ÷ በጠላቶቹም ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ።

፲፬፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጥቱን ፡ በቍጣ ÷ ዘለላውንም ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ከእሳት ፡ ጋር ፡ ይመጣል ÷ ሰረገሎቹም ፡ እንደ ፡ ወውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይሆናሉ ። ፲፭፡ እግዚአብሔርም ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በእሳትና ፡ በሰይፉ ፡ ይፈርዳል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ተመግተው ፡ የሞቱት ፡ ይበዛሉ ። በመከከላቸው ፡ ያለውን ፡ አንዱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ገነቱ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰውነታቸውን ፡ የሚቀድሱና ፡ የሚያነጹ ÷ የአሪያንም ፡ ሥጋ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገርንም ፡ አይጥንም ፡ የሚበሉ ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፲፯፡ ሥራቸውንና ፡ አሳባቸውን ፡ አውቄአለሁና ፡ አሕዛብንና ፡ ልሳናትን ፡ ሁሉ ፡ የምሰበስብበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ÷ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡ ክብሬንም ፡ ያያሉ ። ፲፰፡ በመካከላቸውም ፡ ምልክት ፡ አደርጋለሁ ÷ ከእነርሱም ፡ የዳኑትን ፡ ዝናዬን ፡ ወዳልሰሙ ÷ ክብሬንም ፡ ወዳላዩ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ወደ ፡ ፋጥ ፡ ወደ ፡ ሉድ ፡ ወደ ፡ ሞሳሕ ፡ ወደ ፡ ቶቤል ፡ ወደ ፡ ያዋን ፡ በሩቅ ፡ ወዳሉ ፡ ደሴቶች ፡ አልከትራቸዋለሁ ÷ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ክብሬንም ፡ ይናገራሉ ። ፲፱፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍርባናቸውን ፡ በጥሩ ፡ ሰቃ ፡ አደርገው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደሚያመጡ ÷ እንዲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ይዘን ፡ ዘንድ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ከብሬንም ፡ ይናገራሉ ፡ በሰረገሎች ፡ በአልጋዎችና ፡ በበቅሎች ፡ በጠያሮ ፡ ግመሎችም ፡ ላይ ፡ አደርገው ÷ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጡአቸዋል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፳፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ እንዲሆኑ ፡ ከእነርሱ ፡ እወስዳለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፳፩፡ እኔ ፡ የምሠራው ፡ አዲስ ፡ ሰማይና ፡ አዲስ ፡ ምድር ፡ ከፊቴ ፡ ጸንተው ፡ እንደሚኖሩ ÷ እንዲሁ ፡ ዘራችሁና ፡ ስማችሁ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፳፪፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ በየመባቻውና ፡ በየሰንበቱ ፡ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ዘወትር ፡ ይመጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፳፫፡ ወጥተውም ፡ በእኔ ፡ ያመፁብኝን ፡ ሰዎች ፡ ሬሳቸውን ፡ ያያሉ ፡ ትላቸው ፡ አይሞትምና ÷ እሳታቸውም ፡ አይጠፋምና ፡ ለሥጋ ፡ ለባሽም ፡ ሁሉ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ ይሆናሉ ።

ትንቢተ ኤርምያስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፡ በብንያም ፡ አገር ፡ በዓናቶት ፡ ከነበሩ ፡ ካህናት ፡ የሆነ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ የኤርምያስ ፡ ቃል ። ፪፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሞጽ ፡ ልጅ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ በመንግሥቱ ፡ በአሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣለት ። ፫፡ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ ዘመን ÷ እስከ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ፍጻሜ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ተማረከችበት ፡ እስከ ፡ አም ስተኛው ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

፬፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ ፭፡ በሆድ ፡ ሳልሠራህ ፡ አውቄሃለሁ ÷ ከማኅፀንም ፡ ሳትወጣ ፡ ቀድሼሃለሁ ÷ ለአሕዛብም ፡ ነቢይ ፡ አድርጌሃለሁ ። ፮፡ እኔም ፦ ወዮ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ÷ እነሆ ÷ ብላቴና ፡ ነኝና ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አላውቅም ፡ አልሁ ። ፯፡ እግዚአብሔርም ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ወደምሰድህ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ትሄዳለህና ÷ የማዝዝህንም ፡ ሁሉ ፡ ትናገራለህና ፦ ብላቴና ፡ ነኝ ፡ አትበል ። ፰፡ እኔ ፡ አድንህ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ፡ ከፊታቸው ፡ አትፍራ ÷ ይላል ፡ እግዚ

፪፡ አብሔር ። እግዚአብሔርም ፡ እኛን ፡ ዘርግቶ ፡ አፈን ፡ ዳሰሰ ÷ እግዚአብሔርም ፡— እነሆ ÷
፩፡ ቃሌን ፡ በአፍህ ፡ ውስጥ ፡ አኑሬአለሁ ፡ እነሆ ÷ ትንቅልና ፡ ታፈርስ ፡ ዘንድ ÷ ታጠፋና ፡ ትገለ
ብጥ ፡ ዘንድ ÷ ትሠራና ፡ ትተክል ፡ ዘንድ ፡ በአ
ሕዛብና ፡ በመንግሥታት ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ አደርጌ
ሃለሁ ፡ አለኝ ።
፲፩፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡— ኤርም
ያስ ፡ ሆይ ÷ ምን ፡ ታያለህ ? አያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
መጣ ። እኔም ፡— የለውዝ ፡ በትር ፡ አያለሁ ፡
፲፪፡ አልሁ ። እግዚአብሔርም ፡— እጾመው ፡
ዘንድ ፡ በቃሌ ፡ እተጋለሁና ፡ መልካም ፡ አይተ
ሃል ፡ አለኝ ።
፲፫፡ ሁለተኛም ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡—
ምን ፡ ታያለህ ? አያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ።
እኔም ፡— የሚፈላ ፡ አፍላል ፡ አያለሁ ÷ ፊቱም ፡
፲፬፡ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ነው ፡ አልሁ ። እግዚአብሔ
ርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡— ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ክፋ ፡
ነገር ፡ በምድሪቱ ፡ በተቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
፲፭፡ ይገለጣል ። እነሆ ፡ እኔ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትን ፡
የመንግሥታትን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ እጠራለሁ ÷
ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡
እያንዳንዳቸውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ መግ
ቢያ ፡ በዙሪያዋ ፡ በቅጥርዋ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በይ
ሁዳም ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ዙፋኖቻውን ፡
፲፮፡ ያስቀምጣሉ ። ስለ ፡ ክፋታቸውም ፡ ሁሉ ÷
እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፡ ለሌሎችም ፡ አማልክት ፡
ስላጠኑ ፡ ለእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ÷
፲፯፡ ፍርዴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እናገራለሁ ። አንተ ፡
ግን ፡ ወገብህን ፡ ታጠቅ ÷ ተነሥም ÷ ያዘዝሁህ
ንም ፡ ሁሉ ፡ ንገራቸው ፡ በፊታቸው ፡ እንዳላስ
፲፰፡ ፈራህ ፡ አትፍራቸው ። እነሆ ፡ በምድሪቱ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ በይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በአለቆች
ዋና ፡ በክህናትዋ ፡ ላይ ፡ በምድሪቱም ፡ ሕዝብ ፡
ላይ ፡ እንደ ፡ ተመሸገ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ብረትም ፡
ዓምድ ፡ እንደ ፡ ናስም ፡ ቅጥር ፡ ዛሬ ፡ አድርጌሃ
፲፱፡ ለሁ ። ከእንተ ፡ ጋር ፡ ይዋጋሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡
አድንህ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ፡
ድል ፡ አይነሡህም ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን
፪፡ ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ሂድ ÷ በኢየሩሳሌም ፡
ጆሮ ፡ ጩኸ ÷ እንዲህም ፡ በል ፡— እግዚአብ
ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የብላቴንነትሽን ፡ ምሕ
ረት ፡ የታጨሽበትንም ፡ ፍቅር ÷ በምድረ ፡ በዳ ፡
ዘር ፡ በልተዘራበት ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተከተል
፫፡ ሽኝ ፡ አስቤአለሁ ። እስራኤል ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነበረ ÷ የቡቃያውም ፡ በኵራት ፡
ነበረ ፤ የበሉት ፡ እንደ ፡ በደለኞች ፡ ይቈጠራሉ ÷
ክፉም ፡ ነገር ፡ ያገኛቸዋል ÷ ይላል ፡ እግዚአ
ብሔር ።
፬፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ወገ
ኖች ፡ ሁሉ ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ፭፡
አባቶቻችሁ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቁ ÷ ከንቱነት
ንም ፡ የተከተሉ ÷ ከንቱም ፡ የሆኑ ፡ ምን ፡ ክፋት ፡
አግኝተውብኝ ፡ ነው ? እነርሱም ፡— ከግብጽ ፡ ፮፡
ምድር ፡ ያወጣን ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ በባድማ ፡
ጕድጓድም ፡ በለበት ፡ ምድር ÷ በውኃ ፡ ጥምና ፡
በሞት ፡ ጥላ ፡ ምድር ፤ ማንም ፡ በማያልፍበ
ትና ፡ ማንም ፡ በማይቀመጥበት ፡ ምድር ፡ የመ
ራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ አለ ? አላሉም ።
ፍሬዋንና ፡ በረከትዋንም ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፯፡
ፍሬያማ ፡ ምድር ፡ አገባኋችሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በገ
ባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ምድሬን ፡ አረከሳችሁ ÷ ርስቴ
ንም ፡ አጐሳቈላችሁ ። ካህናቱም ፡— እግዚአ ፰፡
ብሔር ፡ ወዴት ፡ አለ ? አላሉም ÷ ባለ ፡ አፈቶ
ችም ፡ አላወቁኝም ፤ ገዢዎችም ፡ ዐመፁብኝ ÷
ነቢያትም ፡ በበኣል ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ÷ የማይ
ረባንም ፡ ነገር ፡ ተከተሉ ።
ስለዚህ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እከራከራለሁ ÷ ፱፡
ከልጆቻችሁም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እከራከራለሁ ።
ወደ ፡ ኪቲም ፡ ደሴቶች ፡ እለፋና ፡ ተመልከቱ ÷ ፲፡
ወደ ፡ ቄዳርም ፡ ላኩና ፡ እጅግ ፡ መርምሩ ÷ እን
ደዚህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ አንደ ፡ ሆነ ፡ እዩ ።
በውኑ ፡ አማልክት ፡ ያልሆኑትን ፡ አማልክቱን ፡ ፲፩፡
የለመጣቸው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አለን ? ነገር ፡
ግን ፡ ሕዝቤ ፡ ክብሩን ፡ ለማይረባ ፡ ነገር ፡ ለወጠ ።
ሰማያት ፡ ሆይ ÷ በዚህ ፡ ተደነቁ ÷ እጅግም ፡
ደንግጡና ፡ ተንቀጥቀጡ ፡ ይላል ፡ እግዚአብ ፲፪፡
ሔር ። ሕዝቤ ፡ ሁለቱን ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ አድር
ገዋልና ፡ እኔን ፡ የሕያውን ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ትተ
ውኛል ÷ የተቀደዱትንም ፡ ጕድጓዶች ፥ ውኃ
ውን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉትን ፡ ጕድጓ
ዶች ÷ ለራሳቸው ፡ ቆፍረዋል ።
በውኑ ፡ እስራኤል ፡ ባሪያ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ ፲፬፡
የቤት ፡ ውላጅ ፡ ነውን ? ስለ ፡ ምን ፡ ብገዘዘ ፡
ሆነ ? የአንበሳ ፡ ደቦሎች ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አገሡ ÷ ፲፭፡
ድምፃቸውንም ፡ ሰጡ ፡ ምድሩንም ፡ በድማ ፡
አደረጉ ÷ ከተሞቹም ፡ ተቃጠሉ ፡ የሚቀመጥ
በቸውም ፡ የለም ። የሜምፎስና ፡ ተፍናኤስ ፲፮፡
ልጆች ፡ አስነወሩሽ ፡ አላገጡብሽም ። ይህ ፡ ፲፯፡
ሁሉ ፡ የሆነብሽ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተውሽ ፡ አይደለ
ምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክሽ ። አሁ ፲፰፡
ንስ ፡ የሺሖርን ፡ ውኃ ፡ ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በግ
ብጽ ፡ መንገድ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለሽ ? የኤፍራ
ጥስንም ፡ ውኃ ፡ ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በአሦር ፡ መን
ገድ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለሽ ? ክፋትሽ ፡ ይገሥጽ ፲፱፡
ሻል ፡ ክዳትሽም ፡ ይዘልፍሻል ፤ እምላክሽንም ፡
እግዚአብሔርን ፡ የተውሽ ፡ እኔንም ፡ መፍራት ፡
የሌለብሽ ፡ ክፋና ፡ መራራ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
እወቂ ÷ ተመልከቺ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ።
ከዋንት ፡ ጀምሬ ፡ ቀንበርሽን ፡ ሰብሬአለሁ ፡ ፳፡
እስራትሽንም ፡ ቈርጫለሁ ፤ አንቺም ፡— አላገ
ለግልም ፡ አልሽ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡
ከረብታ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከለምለምም ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡

በታች ፡ ለማመንዘር ፡ ተጋደምሽ ። እኔ ፡ የተ ፳፩፡
መረጠች ፡ ወይን ፡ ፍጹምም ፡ እውነተኛ ፡ ዘር ፡
አድርጌ ፡ ተከልሽ ፡ ነበር ፡ እንቺ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡
የእንግዳ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ ሆነሽ ፡ እንዴት ፡ ተለ
ወጥሽብኝ ? በእንዶድ ፡ ብትታጠቢም ÷ ለራ ፳፪፡
ስሽም ፡ ሳሙና ፡ ብታበዢ ÷ በእኔ ፡ ፊት ፡ በኃ
ጢአትሽ ፡ ረክሰሻል ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔር ። እንቺስ ፡— አልረከስሁም ፡ በእሊም ፳፫፡
ንም ፡ አልተከተልሁም ፡ እንዴት ፡ ትያለሽ ?
በቁላ ፡ ያለውን ፡ መንገድሽን ፡ ተመልከቺ ፡
ያደረግሽውንም ፡ እወቂ ፡ በመንገድም ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ ተለቀቀች ፡ እንደ ፡ ፈጣን ፡ ግመል ፡ ሆነ
ሻል ፡ በምኞትዋ ፡ ነፋስን ፡ እንደምታሸትት ÷ ፳፬፡
በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡
አህያ ፡ ነሽ ፡ ከምኞትዋ ፡ የሚመልሳት ፡ ማን ፡
ነው ? የሚሹአት ፡ ሁሉ ፡ አይደክሙም ÷ በወ
ራትዋ ፡ ያገኙአታል ። እግርሽን ፡ ከሸክላ ፡ መን ፳፭፡
ገድ ፡ ጕሮሮሽንም ፡ ከውኃ ፡ ጥም ፡ ከልክዪ ፡
አንቺ ፡ ግን ፡— እጨክናለሁ ÷ እንግዶችን ፡ ወድ
ጀአለሁና ÷ አከተላቸዋለሁም ፡ አልሽ ።
ሴባ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያፍር ፡ እን ፳፮፡
ዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ እነርሱና ፡ ንጉሦቻ
ቸውም ፡ አለቆቻቸውም ፡ ካህናቶቻቸውም ፡
ነቢያቶቻቸውም ፡ ያፍራሉ ። ግንዱን ፡— አንተ ፡ ፳፯፡
አባቴ ፡ ነህ ፡ ድንጋዩንም ፡ — አንተ ፡ ወለድኸኝ ፡
ይላሉ ፡ ፊታቸውንም ፡ ሳይሆን ፡ ጀርባቸውን ፡
ሰጡኝ ÷ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ተነሥ
ተህ ፡ እድነን ፡ ይላሉ ። ለአንተ ፡ የሠራሃቸው ፡
አማልክትህ ፡ ግን ፡ ወዴት ፡ ናቸው ? ይሁዳ ፡
ሆይ ÷ አማልክትህ ፡ እንደ ፡ ከተሞችህ ፡ ቍጥር ፡
እንዲሁ ፡ ናቸውና ፡ ይነሡ ፡ በመከራህም ፡ ጊዜ ፡
ያድኑህ ።
ከእኔ ፡ ጋር ፡ የምትከራከሩ ፡ ለምንድር ፡ ነው ? ፳፱፡
ሁላችሁ ፡ ዐምፃችሁብኛል ፡ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ። ልጆቻችሁን ፡ በከንቱ ፡ ቀሥፈዋችሁ
ለሁ ፡ ተግሣጽን ፡ አልተቀበሉም ፡ ሰይፋችሁ ፡
እንደሚሰብር ፡ አንበሳ ፡ ነቢያቶቻችሁን ፡ በል ፴፡
ቶአል ። ትውልድ ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ ተመልከቱ ። በውኑ ፡ ለእስራኤል ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ ወይስ ፡ የጨለማች ፡ ምድር ፡ ሆንሁብኝን ?
ሕዝቤስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡— እኛ ፡ ፈርጥጠናል ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ አንመለስም ፡
ይላል ? በውኑ ፡ ቆንጆ ፡ ጌጥዋን ፡ ወይስ ፴፩፡
ሙሽራ ፡ ዝርግፍ ፡ ጌጥዋን ፡ ትረሳለችን ? ሕዝቤ ፡
ግን ፡ የማይቈጠር ፡ ወራት ፡ ረስቶኛል ። ፍቅ
ርን ፡ ለመሻት ፡ መንገድሽን ፡ እንዴት ፡ ታቀኛ
ለሽ ! ስለዚህ ፡ ለክፋዎች ፡ ሴቶች ፡ እንኳ ፡ መን
ገድሽን ፡ አስተምረሻል ። በእጆችሽም ፡ የንጹ ፴፪፡
ሐን ፡ ደሙች ፡ ይም ፡ ተገኝቶአል ። በእነዚህ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ በግልጥ ፡ አገኘሁት ፡ እንጂ ፡ በስ
ውር ፡ ፈልጌ ፡ አላገኘሁትም ። አንቺ ፡ ግን ፡—
ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ በእውነት ፡ ቍጣው ፡ ከእኔ ፡ ተመ
ልሶአል ፡ አልሽ ። እነሆ ፡— ኃጢአት ፡ አልሠራ ፴፫፡
ሁም ፡ ብለሻልና ፡ በፍርድ ፡ እከስስሻለሁ ። መን

ይላል፣ እግዚአብሔር ። በእምላክሽ፣ በእግዚአብሔር፣ ላይ፥ እንዳመፅሽ ÷ መንገድሽንም፣ ከለመለመ፣ ዛፍ፣ ሁሉ፣ በታች፣ ለእንግዶች፣ እንደ ፣ ዘረጋሽ ÷ ቃሌንም ፣ እንዳልሰማሽ ፣ ኃጢአትሽን፣ ብቻ ፣ እወቂ ፣ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። ከዳተኞች ፣ ልጆች ፣ ሆይ ÷ እኔ ፣ ባላችሁ ፣ ነኝና ፣ ተመለሱ ፥ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዱንም ፣ ከአንዲት ፣ ከተማ ፣ ሁለቱንም ፣ ከአንድ ፣ ወገን ፣ ኣወስዳችኋለሁ ÷ ወደ ፣ ጽዮንም ፣ አመጣችኋለሁ ፣ እንደ ፣ ልቤም ፣ በግ ፣ ጠባቆችን ፣ አሰጣችኋለሁ ÷ በእውቀትና ፣ በማስተዋልም ፣ ይጠብቁአችኋል ። በበዛችሁም ፣ ጊዜ ፣ በምድርም ፣ ላይ ፣ በረባችሁ ፣ ጊዜ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ÷ በዚያ ፣ ዘመን ፣ — የእግዚአብሔር ፣ የቃል ፣ ኪዳን ፣ ታቦት ፣ ብለው ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ አይጠሩም ፣ ልብ ፣ አያደርጉትም ÷ አያስቡትምም ÷ አይሹትምም ÷ ከእንግዲህ ፣ ወዲህም ፣ አይደረግም ። በዚያም ፣ ዘመን ፣ ኢየሩሳሌምን ፣ የእግዚአብሔር ፣ ዙፋን ፣ ብለው ፣ ይጠሩአታል ÷ አሕዛብም ፣ ሁሉ ፣ ወደ ፣ እርስዋ ፣ ይሰበሰባሉ ፣ ከእንግዲህም ፣ ወዲህ ፣ ክፉውን ፣ እልከኛ ፣ ልባቸውን ፣ ተከትለው ፣ አይሄዱም ። በዚያም ፣ ዘመን ፣ የይሁዳ ፣ ቤት ፣ ወደ ፣ እስራኤል ፣ ቤት ፣ ይሄዳል ፤ በአንድም ፣ ሆነው ፣ ከሰሜን ፣ ምድር ፣ ርስት ፣ አድርጌ ፣ ለአባቶቻቸው ፣ ወደ ፣ ሰጠኋት ፣ ምድር ፤ ይመጣሉ ።

እኔ ፣ ግን ፦ ከወንዶች ፣ ልጆች ፣ ጋር ፣ እንዴት ፣ አደርግሻለሁ ? ያማረችውንስ ፣ ምድር ፣ የከበረችውን ፣ የአሕዛብን ፣ ሠራዊት ፣ ርስት ፣ እንዴት ፣ አሰጥሻለሁ ? ብዬ ፣ ነበር ። ደግሞ ፦ — አባቴ ፣ ብለሽ ፣ ትጠሪኛለሽ ፣ እኔንም ፣ ከመከተል ፣ አትመለሽም ፣ ብዬ ፣ ነበር ። የእስራኤል ፣ ቤት ፣ ሆይ ÷ ሚስት ፣ ባልዋን ፣ እንደምታታልል ፣ እንዲሁ ፣ አታለላችሁኝ ፣ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። የእስራኤል ፣ ልጆች ፣ መንገዳቸውን ፣ አጣምመዋልና ÷ አምላካቸውንም ፣ እግዚአብሔርን ፣ረስተዋልና ፣ በወናዎች ፣ ከረብቶች ፣ላይ ፣ የልመናቸውና ፣ ልቅሶአቸው ፣ ድምፅ ፣ ተሰማ ።

ከዳተኞች ፣ ልጆች ፣ ሆይ ÷ ተመለሱ ÷ ከዳተኝነታችሁንም ፣ እፈውሳለሁ ። እነሆ ÷ አንተ ፣ አምላካችን ፣ እግዚአብሔር ፣ ነህና ፣ ወደ ፣ አንተ ፣ እንመጣለን ። በእውነት ፣ የከረብቶችና ፣ የተራሮች ፣ ፍጅት ፣ ከንቱ ፣ ናት ፤ በእውነት ፣ የእስራኤል ፣ መዳን ፣ በአምላካችን ፣ በእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ከትንሽነታችን ፣ ጀምሮ ፣ የአባቶቻችን ፣ ድካም ÷ በጎቻቸውንና ፣ ላሞቻቸውን ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ልጆቻቸውንም ÷ አፍረት ፣ በልቶባቸዋል ። ከትንሽነታችን ፣ ጀምሮ ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ እኛና ፣ አባቶቻችን ፣ በአምላካችን ፣ በእግዚአብሔር ፣ ላይ ፣ ኃጢአት ፣ ሠርተናልና ÷ የአምላካችን ንም ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣ አልሰማንምና ፣ በእፍረታችን ፣ እንጋደም ÷ ውርደታችንም ፣ ይክደነን ።

ምዕራፍ ፬ ።

እስራኤል ፣ ሆይ ÷ ብትመለስ ÷ ወደ ፣ እኔ ፣ ተመለስ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ ርኵሰትህን ፣ ከፊቴ ፣ ብታስወግድ ÷ ባትናወጥም ÷ ሕያው ፣ እግዚአብሔርን ! ብለህም ፣ በእውነትና ፣ በቅንነት ፣ በጽድቅም ፣ ብትምል ÷ አሕዛብ ፣ በእርሱ ፣ይባረካሉ ፣ በእርሱም ፣ይመካሉ ።

እግዚአብሔር ፣ ለይሁዳና ፣ ለኢየሩሳሌም ፣ ሰዎች ፣ እንዲህ ፣ ይላልና ፦ ዋኔቱን ፣ እርሻ ፣ አረሱ ፣ በእሾህም ፣ላይ ፣ አትዝሩ ። እናንተም ፣ የይሁዳ ፣ ሰዎች ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ የምትኖሩ ፣ ሆይ ÷ ስለ ፣ ሥራችሁ ፣ ክፋት ፣ ቊጣዬ ፣ እንደ ፣ እሳት ፣ እንዳይወጣ ፣ የሚያጠፋውም ፣ ሳይኖር ፣ እንዳያቃጥል ÷ ለእግዚአብሔር ፣ ተገረዙ ፣ የልባችሁንም ፣ ሸለፈት ፣ አስወግዱ ።

በይሁዳ ፣ ዘንድ ፣ ተናገሩ ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ ላይ ፣ አውሩና ፦ — በአገሪቱ ፣ላይ ፣ መለከት ፣ ንፉ ፣ በሉ ፤ ጮኻችሁም ፦ — ሁላችሁ ፣ ተሰብሰቡ ፣ ወደ ፣ ተመሸጉትም ፣ ከተሞች ፣ እንግቢ ፣ በሉ ። ከሰሜን ፣ ክፋ ፣ ነገርንና ፣ ጽኑ ፣ ጥፋትን ፣ አመጣለሁና ፣ ወደ ፣ ጽዮን ፣ ዓላማን ፣ አንሡ ፣ ሽሹ ÷ አትዘግዩ ። እንበሳ ፣ ከጭፍቅ ፣ ዱር ፣ ወጥቶአል ÷ አሕዛብንም ፣ የሚዘርፍ ፣ ተነሥቶአል ፤ ምድር ፣ ሽን ፣ በድማ ፣ያደርግ ፣ ዘንድ ፣ ከስፍራው ፣ ወጥቶአል ÷ ኵተሞች ፣ሽም ፣ ሰው ፣ የሌለባቸው ፣ ፍርስራሾች ፣ ይሆናሉ ። የእግዚአብሔር ፣ ጽኑ ፣ ቊጣ ፣ ከእኛ ፣ ዘንድ ፣ አልተመለሰምና ፣ ማቅ ፣ ልበሱ ÷ አልቅሱም ፣ ዋይም ፣ በሉ ። በዚያም ፣ ቀን ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ÷ የንጉሡና ፣ የመኳንንቱ ፣ ልብ ፣ ይጠፋል ÷ ካህናቱም ፣ ይደነ ቃሉ ፣ ነቢያቱም ፣ ይደነግጣሉ ።

እኔም ፦ — ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሆይ ÷ ወዮ ÷ አንተ ፣ ሰይፍ ፣ እስከ ፣ ነፍስ ፣ ድረስ ፣ በደረሰ ፣ ጊዜ ፦ — ሰላም ፣ ይሆንላችኋል ፣ ብለህ ፣ ይህን ፣ ሕዝብና ፣ ኢየሩሳሌምን ፣ እጅግ ፣ አታለልህ ፣ አልሁ ።

በዚያ ፣ ጊዜ ፣ ለዚህ ፣ ሕዝብና ፣ ለኢየሩሳሌም ፦ — ለማበጠር ፣ ወይም ፣ ለማጥራት ፣ ሰይሆን ፣ የሚያቃጥል ፣ ነፋስ ፣ በምድረ ፣ በዳ ፣ ካሉ ፣ ከወናዎች ፣ ኮረብቶች ፣ ወደ ፣ ወገኔ ፣ ሴት ፣ ልጅ ፣ ይመጣል ፤ ስለ ፣ እኔ ፣ ጽኑ ፣ የሆነ ፣ ነፋስ ፣ ከእነዚህ ፣ ይመጣል ፣ ይበላል ። አሁንም ፣ እኔ ፣ ደግሞ ፣ ፍርዴን ፣ በእነርሱ ፣ላይ ፣ እናገራለሁ ። እነሆ ÷ እንደ ፣ደመና ፣ይወጣል ÷ ሰረገሎቹም ፣ እንደ ፣ ዐውሎ ፣ ነፋስ ፣ ፈረሶቹም ፣ ከንስር ፣ ይልቅ ፣ ፈጣኖች ፣ ናቸው ። ጠፍተናልና ፣ ወድልን ። ኢየሩሳሌም ፣ ሆይ ÷ ትድኚ ፣ ዘንድ ፣ ልብሽን ፣ ከክፋ ፣ ነገር ፣ እጠቢ ። ክፉ ፣ አሳብ ፣ የሚኖርብሽ ፣ እስከ ፣ መቼ ፣ ድረስ ፣ ነው ? የተናጋሪ ፣ ድምፅ ፣ ከዳን ፣ ዘንድ ፣ ይናገራልና ÷ ከኤፍሬምም ፣ ኮረብቶች ፣ መከራን ፣ ያወራልና ። ለአሕዛብ ፣ አሰሙና ፦ — እነሆ ÷ ጠበቂዎች ፣ ከሩቅ ፣ አገር ፣ ይመጣሉ ፤ በይሁዳም ፣ ከተሞች ፣ ላይ ፣ ይጮኻሉ ፣ ብላችሁ ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ላይ ፣ አውሩ ። በእኔ ፣ ላይ ፣ ዓመፀኛ ፣ ሆናለችና ፣ በዙሪያዋ ፣ ከብበው ፣ እንደ ፣ እርሻ ፣ ጠባቂዎች ፣ ሆነውበታል ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። መንገድሽና ፣ ሥራሽ ፣ ይህን ፣ አድርጎብሻል ፣ ይህ ፣ ክፋትሽ ፣ መራር ፣ ነው ÷ ወደ ፣ ልብሽም ፣ ደርሶአል ።

አንጀቴ ! አንጀቴ ! ልቤ ፣ በጣም ፣ ታምሞአል ÷ በውስጤም ፣ ልቤ ፣ ታውከብኛል ፤ ነፍሴ ፣ ሆይ ÷ የመለከትን ፣ ድምፅና ፣ የሰልፍን ፣ ውከታ ፣ ሰምተሻልና ፣ ዝም ፣ እል ፣ ዘንድ ፣ አልችልም ። መከራ ፣ በመከራ ፣ ላይ ፣ ተጠርቶአል ፤ ምድርም ፣ ሁሉ ፣ ተበዝብዛለችና ፤ በድንገትም ፣ ድንኳኔ ፣ በቅጽበት ፣ ዓይንም ፣ መጋረጃዎቼ ፣ ጠፉ ። ዓላማውን ፣ የምመለከት ÷ የመለከቱንስ ፣ ድምፅ ፣ የምሰማ ፣ እስከ ፣ መቼ ፣ ነው ? ሕዝቤ ፣ ሰንፈዋልና ፣ አላወቁኝም ፤ ሰነፎች ፣ ልጆች ፣ ናቸው ÷ ማስተዋልም ፣ የላቸውም ፤ ክፉ ፣ ነገርን ፣ ለማድረግ ፣ ብልሃተኞች ፣ ናቸው ÷ በጎ ፣ ነገርን ፣ ማድረግ ፣ ግን ፣ አያውቁም ።

ምድሪቱን ፣ አየሁ ÷ እነሆም ፣ ባዶ ፣ ነበረች ፣ አንዳችም ፣ አልነበረባትም ፤ ሰማያትንም ፣ አየሁ ÷ ብርሃንም ፣ አልነበረባቸውም ። ተራሮችን ፣ አየሁ ÷ እነሆም ÷ ተንቀጠቀጡ ÷ ኮረብቶችም ፣ ሁሉ ፣ ተናወጡ ። አየሁ ÷ እነሆም ÷ ሰው ፣ አልነበረም ÷ የሰማይም ፣ ወፎች ፣ ሁሉ ፣ ሸሽተው ፣ ነበር ። አየሁ ÷ እነሆም ÷ ፍሬያማ ፣ እርሻ ፣ ምድረ ፣ በዳ ፣ ሆነች ÷ ከተሞችም ፣ ሁሉ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ፊት ፣ ከጽኑ ፣ ቊጣው ፣ የተነሣ ፣ ፈርሰው ፣ ነበር ።

እግዚአብሔርም ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ — ምድር ፣ ሁሉ ፣ በድማ ፣ ትሆናለች ÷ ነገር ፣ ግን ፣ ፈጽሜ ፣ አላጠፋትም ። ስለዚህ ፣ ምድር ፣ ታለቅሳለች ÷ በላይም ፣ሰማይ ፣ይጨቍራል ፤ ተናግሬአለሁና ÷ አስቤአለሁም ፣ አልጸጸትም ፣ ከእርሱም ፣ አልመለስም ። ከፈረሰኞችና ፣ ከቀስተኞች ፣ ድምፅ ፣ የተነሣ ፣ ከተማ ፣ ሁሉ ፣ ሸሽታለች ፤ ወደ ፣ ችፍግ ፣ ዱርም ፣ ይገባሉ ፣ በቋጥኝ ፣ ላይም ፣ ይወጣሉ ፤ ከተማ ፣ ሁሉ ፣ ተለቅቃለች ፣ የሚቀመጥበትም ፣ ሰው ፣ የለም ። አንቺም ፣ የተበዘበዝሽ ፣ ሆይ ÷ ምን ፣ ታደርጊአለሽ ? ቀይ ፣ በለበስሽ ፣ ጊዜ ÷ በወርቅ ፣ አንበርም ፣ በጌጥሽ ፣ ጊዜ ÷ ዓይንሽንም ፣ በሰው ፣ በተኳልሽ ፣ ጊዜ ÷ በከንቱ ፣ ታጌጪ ለሽ ፤ ውሽሞችሽ ፣ አቃለሉሽ ÷ ነፍስሽን ፣ ይሹአታል ። እንደምታምጥ ፣ የበኵርዋንም ፣ እንደምትወልድ ፣ ሴት ፣ ድምፅ ፣ ሰምቻለሁና ፤ የጽዮን ፣ ሴት ፣ ልጅ ፣ ድምፅ ፣ በድክም ፣ ይሰልላል ÷ እጆችዋንም ፦ ተዘረጋለችና ፦ — ተገድለው ፦ ከሞቱት ፣ የተነሣ ፣ ነፍሴ ፣ ዝላለችና ፣ ወዮልኝ ! አለች ።

ምዕራፍ ፭ ።

በኢየሩሳሌም ፣ መንገድ ፣ እየተመላለሳችሁ ፣ ሩጡ ÷ ተመልከቱም ÷ አመቁም ÷ በአደባባይ ዋም ፣ ፈልጉ ፣ ፍርድን ፣ የሚያደርገውን ፣ እውነትንም ፣ የሚሻውን ፣ ሰው ፣ ታገኙ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ይቅር ፣ እላታለሁ ። እነርሱም ፦ — ሕያው ፣ እግዚአብሔርን ፣ ቢሉ ፣ የሚምሉት ፣ በሐሰት ፣ ነው ። አቤቱ ÷ ዓይንህ ፣ እውነትን ፣ የምትመለከት ፣ አይደለችምን ? አንተ ፣ ቀሥፈሃቸዋል ፣ ነገር ፣ ግን ፣ አላዘኑም ÷ ቀጥቅጠሃቸውማል ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ተግሣጽን ፣ እንቢ ፣ አሉ ፤ ፊታቸውን ፣ ከድንጋይ ፣ ይልቅ ፣ አጠንክረዋል ፤ ይመለሱ ፣ ዘንድ ፣ እንቢ ፣ አሉ ።

እኔም ፦ — የእግዚአብሔርን ፣ መንገድና ፣ የአምላካቸውን ፣ ሕግ ፣ አላወቁምና ፣ እነዚህ ፣ በእውነት ፣ ድሆችና ፣ ሰነፎች ፣ ናቸው ፤ ወደ ፣ ታላላቆቹ ፣ እሄዳለሁ ፣ እናገራቸውማለሁ ፣ የእግዚአብሔርን ፣ መንገድና ፣ የአምላካቸውን ፣ ሕግ ፣ ያውቃሉና ፣ አልሁ ። እነዚህ ፣ ግን ፣ ቀንበሩን ፣ በአንድነት ፣ ሰብረዋል ÷ እስራቱንም ፣ ቈርጠዋል ። ስለዚህ ፣ ኃጢአታቸው ፣ በጣዖት ፣ አልና ÷ የከዳታቸውም ፣ ብዛት ፣ ጸንቶአልና ፣ ስለዚህ ፣ አንበሳ ፣ ከዱር ፣ ወጥቶ ፣ ይሰብራቸዋል ÷ የበረሀም ፣ ተኵላ ፣ ያጠፋቸዋል ÷ ነብርም ፣ በከተሞቻቸው ፣ ላይ ፣ ይተጋል ÷ ከዚያም ፣ የሚወጣ ፣ ሁሉ ፣ ይነጠቃል ።

በእነዚህ ፣ ነገሮች ፣ ይቅር ፣ የምልሽ ፣ እንዴት ፣ አድርጌ ፣ ነው ? ልጆችሽ ፣ ትተውኛል ፣ አማልክትም ፣ በልሆኑ ፣ ምለዋል ፤ ከጠገብኋቸውም ፣ በኋላ ፣ አመነዘሩ ፣ በጋለሞቶቹም ፣ ቤት ፣ ተሰበሰቡ ። እንደ ፣ ተቀለቡ ፣ ፈረሶች ፣ ሆኑ ፤ እያንዳንዳቸውም ፣ ከባልንጀሮቻቸው ፣ ሚስቶች ፣ ኋላ ፣ አሽካኩ ። በውኑ ፣ ስለ ፣ እነዚህ ፣ ነገሮች ፣ አልቀጣቸውምን ? ይላል ፣ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፣ እንደዚህ ፣ ባለ ፣ ሕዝብ ፣ ላይ ፣ አትበቀልምን ?

ወደ ፣ ቅጥርዋ ፣ ወጥታችሁ ፣ አፍርሱ ÷ ነገር ፣ ግን ፣ ፈጽማችሁ ፣ አታጥፉ ፤ ለእግዚአብሔር ፣ አይደሉምና ፣ ቀርንጫፍዋን ፣ ውሰዱ ። የእስራኤል ፣ ቤትና ፣ የይሁዳ ፣ ቤት ፣ በእኔ ፣ ላይ ፣ እጅግ ፣ ወንጅለዋል ፣ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። እነርሱም ፦ — እርሱ ፣ አይደለም ÷ ክፉ ፣ ነገር ፣ አይመጣብንም ፣ ሰይፍንና ፣ ራብንም ፣ አናይም ፣ ነቢያትም ፣ ነፋስ ፣ ይሆናሉ ÷ የእግዚአብሔርም ፣ ቃል ፣ በእነርሱ ፣ ዘንድ ፣ የለም ÷ እንዲህም ፣ ይደረግባቸዋል ፣ ብለው ፣ እግዚአብሔርን ፣ ክደዋል ።

ስለዚህም ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ — በዚህ ፣ ቃል ፣ ተናግራችኋልና ፣ እነሆ ÷ በአፍህ ፣ ውስጥ ፣ ቃሌን ፣ እሳት ፣ ይህንም ፣ ሕዝብ ፣ እንጨት ፣ አደርጋለሁ ÷ ትበላቸውማለች ። የእስራኤል ፣ ቤት ፣ ሆይ ÷ እነሆ ÷ ሕዝብን ፣ ከሩቅ ፣ አመጣባችኋለሁ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ ኃያል ፣ ጥንታዊ ፣ ሕዝብ ፣ ነው ÷ ቋንቋቸውንም ፣ የማታውቀው ፣ የሚናገሩትንም ፣ የማታስተውለው ፣ ሕዝብ ፣ ነው ። የፍላጻቸውም ፣ ሰገባ ፣ እንደ ፣ ተከፈተ ፣

መቃብር ፡ ነው ÷ ሁሉም ፡ ኃያላን ፡ ናቸው ።
፮ መከርሀንና ፡ እንጀራሀን ፡ ይበላሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሀንም ፡ ይበሉአቸዋል ፤ በጎችህንና ፡ ላሞችሀንም ፡ ይበላሉ ፡ ወይንህንና ፡ በለስህንም ፡ ይበላሉ ፤ የምትታመናቸውን ፡ የተመሸጉ ፡ ከተሞችን ፡ በሰይፍ ፡ ይደበድባሉ ።
፯ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ ፈጽሚ ፡ አላጠፋችሁም ።
፱ እንዲህም ፡ ይሆናል ፡ እናንተ ፡ — አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አደረገብን ? ብትሉ ÷ አንተ ፡ — እንደ ፡ ተዋችሁኝ ፡ በአገራችሁም ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ እንዳመለካችሁ ÷ እንዲሁ ፡ ለእናንተ ፡ ባልሆነ ፡ አገር ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ትገዛላችሁ ፡ ትላቸዋለህ ።
፳ ይህን ፡ በያዕቆብ ፡ ቤት ፡ አውሩ ÷ በይሁዳም ፡ አሰሙ ፡ — እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ ልብ ፡ ቢሶች ÷ ዓይን ፡ አያላችሁ ፡ የማታዩ ÷ ጆሮም ፡ አያላችሁ ፡ የማትሰሙ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ÷ ይህን ፡ ስሙ ።
፳፪ በውኑ ፡ እኔን ፡ አትፈሩምን ? ከፊቴስ ፡ አትደነግጡምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳያልፍና ፡ አሸዋን ፡ በዘላለም ፡ ትእዛዝ ፡ ለባሕር ፡ ዳርቻ ፡ አደርጌአለሁ ፡ ሞገዱም ፡ ቢናወጥ ፡ አያሸንፍም ፡ ቢጮኽም ፡ አያልፍብትም ። ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ የሸፈተና ፡ ያመፀ ፡ ልብ ፡ አላቸው ፡ ፳፬ ሀምባዋል ፡ ሄደውማል ። በልባቸውም ፡ — የፊ ተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ገና ፡ በጊዜው ፡ የሚሰጠውን ÷ ለመከር ፡ የተመደቡትን ፡ ወራት ፡ የሚጠብቅልንን ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንፍራ ፡ አላሉም ። ፳፭ አንዚህን ፡ አስቀርታለች ÷ ኃጢአታችሁም ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከለከለቻችሁ ። ፳፮ በሕገኬ ፡ መካከል ፡ ከፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተዋል ፡ እንደ ፡ አጥማጆችም ፡ ያይበሰ ፡ ወጥመድንም ፡ ይዘረጋሉ ፡ ሰዎችንም ፡ ያጠምዳሉ ። ፳፯ ቀፎ ፡ ወፍ ችን ፡ እንደሚሞላ ፡ እንዲሁ ፡ ቤታቸው ፡ ሸንገላን ፡ ሞልታለች ፡ እንዲሁም ፡ ከብረዋል ፡ በለጠጎችም ፡ ሆነዋል ። ፳፰ ወፍረዋል ፡ ሰብተውማል ÷ ክፋታቸውንም ፡ ያለ ፡ ልክ ፡ አብዝተዋል ፡ የድሀ ፡ አደጎች ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ እንዲሆን ፡ አልተመዋገቱላቸውም ÷ የችግረኞችንም ፡ ፍርድ ፡ ፳፱ አልፈረዱላቸውም ። በውኑ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አልቀሥፍምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አትበቀልምን ?
፴ የምታስደንቅና ፡ የምታስደነግጥ ፡ ነገር ፡ ፴፩ በምድር ፡ ላይ ፡ ሆኖለች ፡ ነቢያት ፡ በሐሰት ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡ ካህናትም ፡ በእነዚህ ፡ እድ ፡ ይገዛሉ ÷ ሕዝቤም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ይወድዳሉ ፡ በፍጻሜውስ ፡ ምን ፡ ታደር ጋላችሁ ?

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

እናንተ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ÷ ክፋ ፡ ነገር ፡ ፩ ታላቅም ፡ ጥፋት ፡ ከሰሜን ፡ ይጐበኛልና ፡ ከኢ የሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ሽሹ ÷ በቴቁሔ ፡ መለከቱን ፡ ንፉ ÷ በቤትሐካረም ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ አንሡ ። የተዋበች ፡ ውብና ፡ የተሰነቀለች ፡ የጽዮንን ፡ ፪ ልጅ ፡ አጠፋለሁ ። ፫ እረኞችና ፡ መንጮቻቸው ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ይመጣሉ ÷ በዙሪያዋም ፡ ድንኳኖቻቸውን ፡ ይተክሉባታል ÷ እያንዳንዱም ፡ በስፍራው ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራል ። ፬ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አዘጋጁ ፡ ተነሡ ÷ በቀ ትርም ፡ እንውጣ ። ቀኑ ፡ መሽቶአልና ÷ የማታ ውም ፡ ጥላ ፡ ረዝሞአልና ፡ ወዮልን ። ፭ ተነሡ ፡ በሌሊትም ፡ እንውጣ ÷ አዳራሾችዋንም ፡ እና ፍርስ ። ፮ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ ይላልና ፡ — ዛፎችዋን ፡ ቍረጡ ÷ በኢየ ሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ አፈርን ፡ ደልድሉ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ የምትቀጡፍ ፡ ናት ፡ መከከልዋ ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፯ ጕድጓድ ፡ ውኃ ፡ እን ደሚፈልቅ ÷ እንዲሁ ፡ ክፋትዋ ፡ ከእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ ይፈልቃል ፤ ግፍና ፡ ቀሚያ ፡ በእር ስዋ ፡ ዘንድ ፡ ይሰማል ÷ ደዌና ፡ ቍስልም ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አለ ። ፰ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ÷ ነፍሴ ፡ ከአንቺ ፡ እንዳትለይ ÷ አንቺንም ፡ ባድ ማና ፡ ወና ፡ እንዳላደርግሽ ÷ ተማሪዋን ፡ ተቀ በዩ ።
፱ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ሰው ፡ ወይኑን ፡ እንደሚቃርም ÷ እንዲሁ ፡ ከእስራ ኤል ፡ የቀሩትን ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃርሙአቸዋል ፤ እጅ ህንም ፡ እንደ ፡ ለቃሚ ፡ ወደ ፡ እንቅብ ፡ ዘር ጋ ። ፲ ይሰሙኝስ ፡ ዘንድ ፡ ለማን ፡ እናገራለሁ ? ለማ ንስ ፡ አስጠነቅቃለሁ ? እነሆ ÷ ጆሮአቸው ፡ ያል ተገረዘች ፡ ናት ፡ ለመስማትም ፡ አይችሉም ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለስድብ ፡ ሆኖ ባቸዋል ፡ ደስም ፡ አያሰኛቸውም ። ፲፩ ስለዚህ ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ተሞልቻለሁ ፡ ከመታ ገሥ ፡ ደክሚአለሁ ፡ በሚዳ ፡ በሕፃናት ፡ ላይ ፡ በጕልማሶችም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በአንድነት ፡ አፍ ስሰው ፡ ባል ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ሽማግሌውም ፡ ከጎበዙ ፡ ጋር ፡ ይያያዛልና ። ፲፪ እጀን ፡ በምድር ፡ ዘሚኖሩ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለሁና ፡ ቤቶቻቸው ፡ እር ሻዎቻቸውም ፡ ሴቶቻቸውም ፡ በእንድነት ፡ ለሌሎች ፡ ይሆናሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፲፫ ከታናሹ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡ ስስትን ፡ ያስባሉና ÷ ከነቢዩም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ካህኑ ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋሉና ። ፲፬ የሕዝቤንም ፡ ስብራት ፡ በጥቂቱ ፡ ይፈውሰሉ ፡ ሰላም ፡ ሳይሆን ፡ — ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይላሉ ። ፲፭ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ አፍረዋልን ? ምንም ፡ አላፈሩም ÷ አፍረትንም ፡ አላወቁም ፡ ስለዚህ ፡

ከሚወድቁ ፡ ጋር ፡ ይወድቃሉ ፡ በጐበኘኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይዋረዳሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፲፮ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — በመን ገድ ፡ ላይ ፡ ቁሙ ፡ ተመልከቱም ፡ የቀደመች ውንም ፡ መንገድ ፡ ጠይቁ ፡ መልካሚቱ ፡ መን ገድ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እወቁ ÷ በእርስ ዋም ፡ ላይ ፡ ሂዱ ÷ ለነፍሳችሁም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛ ላችሁ ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ — እንሄድባትም ፡ አሉ ። ፲፯ እኔም ፡ — የመለከቱን ፡ ድምፅ ፡ አድምጡ ፡ ብዬ ፡ ጠባቆችን ፡ ሾምሁባችሁ ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ — አናደምጥም ፡ አሉ ። አሕዛብ ፡ ሆይ ÷ ስለዚህ ፡ ስሙ ፡ ማኅበር ፡ ሆይ ÷ እነዚያ ፡ የሚያገኛቸ ውን ፡ እወቁ ። ፲፰ ምድር ፡ ሆይ ÷ ስሚ ፡ እነሆ ÷ ቃሉን ፡ ስላልሰሙ ፡ ሕጌንም ፡ ስለ ፡ ጣሉ ÷ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የአሳባቸውን ፡ ፍሬ ፡ ከፉን ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለሁ ። ፲፱ ስለ ፡ ምንስ ፡ ከሳባ ፡ ዕጣንን ÷ ከሩቅም ፡ አገር ፡ ቀረፋን ፡ ታቀ ርቡልኛላችሁ ? የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታ ችሁን ፡ አልቀበለውም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕታች ሁም ፡ ደስ ፡ አያሰኘኝም ። ፳ ስለዚህ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — እነሆ ÷ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ አደርጋለሁ ፡ አባቶችና ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይሰናከሉባቸዋል ÷ ጎረ ቤትና ፡ ባልንጀራም ፡ ይጠፋሉ ።
፳፩ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — እነሆ ÷ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ አገር ፡ ይመጣል ። ታላቅ ፡ ሕዝ ብም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣል ። ፳፪ ቀስትንና ጦርን ፡ ይይዛሉ ፡ ጨካኞች ፡ ናቸው ÷ ምሕረትም ፡ አያደርጉም ፡ ድምፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ይተም ማል ÷ በፈረሶችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፡ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ። ፳፫ ወሬውን ፡ ሰምተናል ÷ እጃችን ፡ ደክማለች ፡ ምጥ ፡ ወላድን ፡ ሴት ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡ ይዘናል ። ፳፬ የጠላት ፡ ሰይፍና ፡ ድንጋጤ ፡ ከብ በዋችኋልና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ አትውጡ ፡ በመንገ ድም ፡ ላይ ፡ አትሂዱ ። ፳፭ የሕዝቤ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ ማቅ ፡ ልበሺ ፡ በአመድም ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለዪ ፡ አዋፊ ፡ በላያችን ፡ በድንገት ፡ ይመጣብናልና ፡ ለአንድያ ፡ ልጅ ፡ እንደሚደረግ ፡ ልቅሶ ፡ መራሪ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሺ ።
፳፮ መንገዳቸውን ፡ እንድታውቅና ፡ እንድትፈ ትን ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ፈታኝ ፡ አድርጌሃለሁ ። እነርሱ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ዓመፀኞች ፡ ናቸው ፡ በጠማማነት ፡ ይሄዳሉ ፡ ናስና ፡ ብረት ፡ ናቸው ፡ ሁሉ ፡ ርኵሰትን ፡ ያደርጋሉ ። ፳፯ ወናፉ ፡ አናፋ ፡ እርሳሱም ፡ በእሳት ፡ ቀለጠ ፡ አንጥረኛውም ፡ መልሶ ፡ በከንቱ ፡ ያቀልጠዋል ፤ ንጡሕ አትሆኖች ፡ አልተወገዱም ። ፳፰ እግዚአብሔር ፡ ጥሎአቸዋ ልና ፡ የተጣለ ፡ ብር ፡ ብለው ፡ ይጠሩአቸዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ፪ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ ቁም ፡ ይህንም ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ተናገር ፡ — እግዚአብሔርን ፡ ልታመ ልኩ ፡ በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ፡ ይሁዳ ፡ ያላችሁ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ። ፫ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — መንገዳችሁንና ፡ ሥራችሁን ፡ አሳ ምሩ ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ አሳድራችኋለሁ ። ፬ የእ ግዚአብሔር ፡ መቅደስ ÷ የእግዚአብሔር ፡ መቅ ደስ ÷ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያላችሁ ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ አትታመኑ ። ፭ መን ገዳችሁንና ፡ ሥራችሁን ፡ ፈጽማችሁ ፡ ብታሳ ምሩ ÷ በሰውና ፡ በጎረቤቱ ፡ መከከል ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ብትፈርዱ ÷ መጻተኛውንና ፡ ድሀ ፡ አደ ጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ በትገፉ ÷ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ በታፈስሱ ÷ ከፉም ፡ ሊሆንባ ችሁ ፡ እንግዶችን ፡ አማልክት ፡ በትከተሉ ÷ ከዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ በሰ ጠኋቸው ፡ ምድር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አሳድራች ኋለሁ ።
፰ እነሆ ÷ በማትረቡበት ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ ታምና ችኋል ። ፱ ትሰርቃላችሁ ÷ ትገድላላችሁ ÷ ታመ ነዝራላችሁ ÷ በሐሰትም ፡ ትምላላችሁ ÷ ለበአ ልም ፡ ታጥናላችሁ ÷ የማታውቋቸውንም ፡ እንግ ዶች ፡ አማልክት ፡ ትከተላላችሁ ፡ መጣችሁም ÷ ፲ ስሜም ፡ በተጠራበት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በፊቴ ፡ ቆማችሁ ፡ — ይህን ፡ አስጸያፊ ፡ የሆን ፡ ነገርን ፡ ሁሉ ፡ አላደረግንም ፡ አላችሁ ። ፲፩ ይህስ ፡ ስሜ ፡ የተጠራበት ፡ ቤት ፡ በዓይናችሁ ፡ የሌበች ፡ ዋሻ ፡ ሆኖአልን ? እነሆ ÷ እኔ ፡ አይቻለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፲፪ ነገር ፡ ግን ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስሜን ፡ ወዳሳደ ርሁበት ፡ በሴሎ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ስፍራዬ ፡ ሂዱ ÷ ከሕዝቤም ፡ ከእስራኤል ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ያደ ረግሁበትን ፡ እዩ ። ፲፫ አሁንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ስላደረጋችሁ ÷ በማለዳም ፡ ተነሥቼ ፡ በተናገርኋችሁ ፡ ጊዜ ፡ ስላልሰማችሁ ÷ በጠራ ኋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ስላልመለሳችሁ ፡ ስለዚህ ፡ ፲፬ በሴሎ ፡ እንዳደረግሁ ፡ እንዲሁ ፡ ስሜ ፡ በተጠ ራበት ፡ በምትታመኑበት ፡ ቤት ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችሁም ፡ በሰጠኋችሁ ፡ ስፍራ ፡ አደር ጋለሁ ። ፲፭ የኤፍሬምንም ፡ ዘር ፡ ሁሉ ÷ ወንድሞ ቻችሁን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጣልሁ ÷ እንዲሁ ፡ ከፊቴ ፡ አጥላችኋለሁ ።
፲፮ እንግዲህም ፡ አልሰማህሁምና ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ልመናና ፡ ጸሎት ፡ አታድርግ ፡ አትማልድላቸው ። ፲፯ እነርሱስ ፡ በይ ሁዳ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደ ባበይ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አታይምን ? ፲፰ ይ ቄጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ እንጐቻ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ለሌሎችም ፡ አማልክት ፡ የመ ጠጥ ፡ ቍርባን ፡ እንዲያፈስሱ ፡ ልጆች ፡ እን ጨት ፡ ይሰበስባሉ ÷ አባቶችም ፡ እሳት ፡ ያነድ ዳሉ ፡ ሴቶችም ፡ ዱቄት ፡ ይለውሰሉ ። ፲፱ እኔን ፡ ያስቈጣሉን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፊታቸ

፳ ውስ፡እፍረት፡አይደለምን? እንግዲህም፡ጌታ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እነሆ፥ ቀጣዩና፡መዓቱ፡በዚህ፡ስፍራ፡ላይ፥ በሰውና፡በእንስሳ፡ላይ፥ በዱር፡ዛፎችና፡በምድር፡ፍሬ፡ላይ፡የፈሰሰል፡ይነድዳል፥ አይጠፋምም።

፳፩ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦ለሴላ፡መሥዋዕታችሁ፡የሚቃጠለውን፡መሥዋዕታ ፳፪ ችሁን፡ጨምሩ፥ ሥጋውንም፡ብሉ። ከግብጽ፡ምድር፡ባወጣኋችሁ፡ቀን፡ስለሚቃጠል፡መሥዋዕትና፡ስለ፡ሌላ፡መሥዋዕት፡ለአበቶቻችሁ፡አልተናገርኩሁምና፥ አላዘዝኋቸውምና። ፳፫ ነገር፡ግን፦ቃሌን፡ስሙ፥ እኔም፡አምላክ፡እሆናችኋለሁ፡እናንተም፡ሕዝብ፡ትሆኑኛላችሁ፡መልክም፡ይሆንላችሁ፡ዘንድ፡ባዘዝኋችሁ፡መንገድ፡ሁሉ፡ሂዱ፡ብዬ፡በዚህ፡ነገር፡ ፳፬ አዘዝኋቸው። ነገር፡ግን፡በክፉ፡ልባቸው፡አሳብና፡አልሰማኝነት፡ሄዱ፡ወደ፡ፊትም፡ሳይሆን፡ወደ፡ኋላቸው፡ሄዱ፡እንጂ፡አልሰሙም፡ ፳፭ ጆሮአቸውንም፡አላዘነበሉም። አባቶቻችሁ፡ከግብጽ፡ምድር፡ከወጡበት፡ቀን፡ጀምሮ፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፥ በየዕለቱ፡እየማለድሁ፡ባሪያዎቼን፡ነቢያትን፡ሁሉ፡ልኬብችሁ፡ነበር። ፳፮ ነገር፡ግን፡አንገታቸውን፡አደነደኑ፡እንጂ፡አልሰሙኝም፡ጆሮአቸውንም፡አላዘነበሉም፡አባቶቻቸውም፡ከደረጉት፡ይልቅ፡የባሰ፡አደረጉ።

፳፯ በዚህም፡ቃል፡ሁሉ፡ትነግራቸዋለህ፥ ነገር፡ግን፡አይሰሙህም፡ትጠራቸው፡ማለህ፥ ፳፰ ነገር፡ግን፡አይመልሱልህም። አንተም፦የአምላኩን፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ያልሰማ፥ ተግሣጽንም፡ያልተቀበለ፡ሕዝብ፡ይህ፡ነው፡እውነት፡ጠፍቶአል፡ከአፋቸውም፡ተቈርጦአል፡ትላቸዋለህ።

፳፱ እግዚአብሔር፡የቀኣጣውን፡ትውልድ፡ጥሎ አልና፥ ትቶታልምና፡ጠጕርሽን፡ቍረጪ፥ ጣዖቱም፥ በወናዎች፡ከረብቶችም፡ላይ፡ ፴ አሙሽ። የይሁዳ፡ልጆች፡በፊቴ፡ክፉን፡ነገር፡ሠርተዋል፡ይላል፡እግዚአብሔር፡ያረክሱትም፡ዘንድ፡ስሜ፡በተጠራበት፡ቤት፡ ፴፩ ርኵሰታቸውን፡አኑረዋል። እኔም፡ያላዘዝሁትንና፡በልቤ፡ያላሰብሁትን፥ ወንዶችና፡ሴቶች፡ልጆቻቸውን፡በእሳት፡ያቃጥሉ፡ዘንድ፡በኔኖም፡ልጅ፡ሽለቆ፡ያለችውን፡ ፴፪ የቶፌትን፡መስገጃዎች፡ሠርተዋል። ስለዚህ፥ እነሆ፥ ስፍራ፡ከማጣት፡የተነሣ፡በቶፌት፡ይቀበራሉና፡የእርድ፡ሽለቆ፡ይባላል፡እንጂ፡ ፴፫ ቶፌት፡ወይም፡የኔኖም፡ልጅ፡ሽለቆ፡ዳግመኛ፡የማይባልበት፡ዘመን፡ይመጣል፥ይላል፡ ፴፬ እግዚአብሔር። የዚህም፡ሕዝብ፡ሬሳ፡ለሰማይ፡ወፎችና፡ለምድር፡አራዊት፡መብል፡ ፴፭ ይሆናል፥ የሚያስፈራራቸውም፡የለም። ምድረቱም፡ባድማ፡ትሆናለችና፡ከይሁዳ፡ከተሞችና፡ከኢየሩሳሌም፡አደበባይ፡የእልልታን፡ ድምፅና፡የደስታን፡ድምፅ፥የወንድ፡ሙሽራን፡ድምፅና፡የሴት፡ሙሽራን፡ድምፅ፡አጠፋለሁ።

ምዕራፍ፡፰

፩ በዚያን፡ዘመን፥ይላል፡እግዚአብሔር፥የይሁዳን፡ነገሥታት፡አጥንትና፡የመኳንንቶቹን፡ ፪ አጥንት፥የካህናቱን፡አጥንትና፡የነቢያቱን፡አጥንት፥የኢየሩሳሌምንም፡ሰዎች፡አጥንት፡ከመቃብራቸው፡ያወጣሉ። በወደዱአቸውና፡ባመለኩአቸው፥በተከተሉአቸውና፡በፈለጉአቸው፥በሰገዱላቸውም፡በፀሐይና፡በጨረቃ፡ ፫ በሰማይም፡ሠራዊት፡ሁሉ፡ፊት፡ይዘረጉአቸዋል፤ እያከማቹአቸውም፡አይቀብሩአቸውም፥ በምድርም፡ፊት፡ላይ፡እንደ፡ጕድፍ፡ይሆናሉ። እኔም፡ባሳደድኋቸው፡ስፍራ፡ሁሉ፡የቀሩ፥ከዚህች፡ክፉ፡ወገን፡የተረፉ፡ቅሬታዎች፡ሁሉ፥ከሕይወት፡ይልቅ፡ሞትን፡ይመርጣሉ።

፬ እንዲህም፡ትላቸዋለህ፦እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦የወደቁ፡አይነሡምን?የሳተ፡አይመለስምን?እንግዲህ፡ይህ፡የኢየሩሳሌም፡ሕዝብ፡ዘወትር፡ስለ፡ምን፡ወደ፡ ፭ ኋላው፡ይመለሳል?ተንኰልን፡ይዘአል፡ሊመለስም፡እንቢ፡ብሎአል። አደመጥሁ፡ሰማሁም፡ቅንን፡ነገር፡አልተናገሩም፤ ማናቸውም፡ስለ፡ኃጢአቱ፡የገባ፡የለም፡ወደ፡ሰልፍም፡እንደሚሮጥ፡ፈረስ፡እያንዳንዱ፡በየመንገዱ፡ይሄዳል። ፮ ሽመላ፡በሰማይ፡ጊዜዋን፡አውቃለች፡ዋኖስና፡ጨረባ፡ዋልያም፡የመምጣታቸውን፡ጊዜ፡ይጠብቃሉ፤ ሕዝቤ፡ግን፡የእግዚአብሔርን፡ፍርድ፡አላወቁም።

፯ እናንተስ፦ጥበበኞች፡ነን፡የእግዚአብሔርም፡ሕግ፡ከእኛ፡ጋር፡ነው፡እንዴት፡ትላላችሁ?እነሆ፥የጸሐፊ፡ብርዕ፡ሐሰተኛ፡ነው፡በሐሰትም፡አድርጎአል። ጥበበኞች፡አፍረዋል፡ደንግጠውማል፡ተማርከውማል፤እነሆ፥የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ጥለዋል፤ምን፡ዓይነት፡ጥበብ፡አላቸው? ፱ ከታናሹ፡ጀምሮ፡እስከ፡ታላቁ፡ድረስ፡ሁሉ፡ስስትን፤ያስበሉትና፡ከነቢይም፡ጀምሮ፡እስከ፡ካህኑ፡ድረስ፡ሁሉ፡በተንኰል፡ያደርጋሉና፡ስለዚህ፡ሚስቶቻቸውን፡ለሌሎች፡እርሻቸውንም፡ለሚወርሱባቸው፡እሰጣለሁ። የሕዝቤንም፡ሴት፡ልጅ፡ ፲ ስብራት፡በጥቂቱ፡ይፈውሳሉ፤ሰላም፥ሰላ ሆን፡—ሰላም፡ሰላም፡ይላሉ። አስጸያፊ፡ ፲፩ ነገርን፡ስለ፡ሠሩ፡አፍረዋልን?ምንም፡አላፈሩም፡እፍረትንም፡አላወቁም፤ስለዚህ፡ከሚወድቁ፡ጋር፡ይወድቃሉ፡በጕበኝኝታው፡ጊዜ፡ይዋረዳሉ፤ይላል፡እግዚአብሔር። ፲፪ ፈጽሚ፡አጠፋችኋለሁ፡ይላል፡እግዚአብሔር፤በወይን፡ላይ፡ፍሬ፡በበለስ፡ዛፍ፡ላይ፡በለስ፡አይሆንም፡ቅጠልም፡ይረግፋል፤ የሚያልፋቸውንም፡ሰጠኋቸው።

፲፫ ዝም፡ብለን፡ለምን፡እንቀመጣለን?እግዚአብሔርን፡ስለ፡በደልን፡አምላካችን፡እግዚአብሔር፡አጥፍቶናልና፡የሐሞትንም፡ውኃ፡አጠጥቶናልና፡ተሰብስባችሁ፡ወደ፡ተመሸጉ፡ከተሞች፡እንግባ፡በዚያም፡እንጥፋ። ፲፬ ሰላምን፡በተስፋ፡ተጠባበቅን፡መልካምም፡አልተገኘም፤መጠንን፡በተስፋ፡ተጠባበቅን፡እነሆም፡ድንጋጤ፡ሆነ። ፲፭ የፈረሶቹ፡ድምፅ፡ከዳን፡ተሰማ፡ከአርበኞች፡ፈረሶች፡ማሸካካት፡የተነሣ፡ምድር፡ሁሉ፡ተንቀጠቀጠች፤መጡም፡ምድሪቱንና፡በእርስዋም፡ያለውን፡ሁሉ፡ከተማይቱንና፡የተቀመጡበትንም፡በሉ። እነሆ፡እስማት፡የማይከለክላቸውን፡እባቦችንና፡እፉኝቶችን፡እሰድድባችኋለሁ፤እነርሱም፡ይነድፉአችኋል።

፲፰ ኀዘኔ፡የማይድንና፡ነው፥ልቤም፡በውስጤ፡ደክሞአል። እነሆ፥—እግዚአብሔር፡በጽዮን፡የለምን?ወይስ፡ንጉሥዋ፡በእርስዋ፡ዘንድ፡የለምን?የሚል፡የወገኔ፡ሴት፡ልጅ፡ ፲፱ ጩኸት፡ድምፅ፡ከሩቅ፡አገር፡ተሰማ። በተቀረጹ፡ምስሎቻቸውና፡በባዕድ፡ከንቱነት፡ያስቈጡኝ፡ስለ፡ምንድር፡ነው?መከሩ፡አልፎአል፥ በጋው፡ዐልፎአል፥እኛም፡አልዳንም። ፳ በሕዝቤ፡ሴት፡ልጅ፡ስብራት፡እኔ፡ተሰብሬአለሁ፡ጠቍሬማለሁ፤አድናቆትም፡ይዞኛል። ፳፩ በገለዓድ፡የሚቀባ፡መድኃኒት፡የለምን?ወይስ፡በዚያ፡ሐኪም፡የለምን?የወገኔ፡ሴት፡ልጅ፡ፈውስ፡ስለ፡ምን፡አልሆነም?

ምዕራፍ፡፱

፩ ተወግተው፡ስለ፡ሞቱ፡ስለ፡ሕዝቤ፡ሴት፡ልጅ፡ሰዎች፡ሌሊትና፡ቀን፡አለቅስ፡ዘንድ፡ራሴ፡ውኃ፥ዓይኔም፡የእንባ፡ምንጭ፡በሆነልኝ፤ ፡ሁሉም፡አመንዝሮች፡የአታላዮች፡ጉባኤ፡ናቸውና፡ሕዝቤን፡እተዋቸው፡ዘንድ፡ከእነርሱም፡እለይ፡ዘንድ፡በምድረ፡በዳ፡የመንገደኞች፡ማደሪያን፡ማን፡በሰጠኝ?ምላሳቸውን፡ስለ፡ሐሰት፡እንደ፡ቀስት፡ገተሩ፤በምድር፡በረቱ፡ነገር፡ግን፡ለእውነት፡አይደለም፤ከክፋት፡ወደ፡ክፋት፡ይሄዳሉና፡እኔንም፡አላወቁምና፥ይላል፡እግዚአብሔር። ፬ ወንድምም፡ሁሉ፡ያሰናክላልና፥ባልንጀራም፡ሁሉ፡ያማልና፡እናንተ፡ሁሉ፡ከባልንጀሮቻችሁ፡ተጠንቀቁ፥በወንድሞቻችሁም፡አትታመኑ። ሰውም፡ሁሉ፡ባልንጀራውን፡ያታልላል፡በእውነትም፡አይናገርም፤ሐሰትን፡መናገርንም፡ምላሳቸው፡ተምሮአል፥ክፋንም፡ለማድረግ፡ይደክማሉ። ፮ ማደሪያህ፡በሽንገላ፡መካከል፡ነው፥ከሽንገላም፡የተነሣ፡እኔን፡ያውቁኝ፡ዘንድ፡እንቢ፡ብለዋል፥ይላል፡እግዚአብሔር።

፯ ስለዚህ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እነሆ፥አቀልጣቸዋለሁ፡እፈትናቸውማለሁ፡ስለ፡ሕዝቤ፡ሴት፡ልጅ፡ክፋት፡ከዚህ፡ሌላ፡የማደርገው፡ምንድር፡ነው?

፰ ምላሳቸው፡የተሳለ፡ፍላጻ፡ነው፡ሽንገላን፡ይናገራሉ፡ሰው፡ከባልንጀራው፡ጋር፡በሰላም፡ይናገራል፥በልቡ፡ግን፡ያደባበታል።

፱ በውኑ፡ስለዚህ፡ነገር፡አልቀሥፍምን?ይላል፡እግዚአብሔር፡ነፍሴስ፡እንደዚህ፡ባለ፡ሕዝብ፡ላይ፡አትበቀልምን?

፲ ለተራሮች፡ልቅሶን፡ለምድረ፡በዳ፡ማሰማርያዎችም፡ዋይታን፡አነሣለሁ፥ሰው፡እንዳያልፍባቸው፡በእሳት፡ተቃጥለዋልና። ሰዎችም፡የከብቱን፡ድምፅ፡አይሰሙም፤ከሰማይ፡ወፎች፡ጀምሮ፡እስከ፡እንሰሳ፡ድረስ፡ሸሽተው፡ሄደዋል። ፲፩ ኢየሩሳሌምንም፡የፍርስራሽ፡ክምር፡የቀበሮም፡ማደሪያ፡አደርጋታለሁ፥የይሁዳንም፡ከተሞች፡ሰው፡የማይቀመጥበት፡በድማ፡አደርጋቸዋለሁ።

፲፪ ይህን፡የሚያስተውል፡ጠቢብ፡ሰው፡ማን፡ነው?ያወራስ፡ዘንድ፡የእግዚአብሔር፡አፍ፡ለማን፡ተናገረ?ሰው፡እንዳያልፍበት፡ምድርስ፡ስለ፡ምን፡ጠፋች፥እንደ፡ምድረ፡በዳስ፡ስለ፡ምን፡ተቃጠለች?

፲፫ እግዚአብሔርም፡እንዲህ፡አለ፦የሰጠኋቸውን፡ሕጌን፡ትተዋልና፥ቃሌንም፡አልሰሙምና፥ነገር፡ግን፡የልባቸውን፡ምኞትና፡አባቶቻቸው፡ያስተማሩአቸውን፡በኣሊምን፡ተከትለዋልና፡ስለዚህ፡የእስራኤል፡አምላክ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እነሆ፥ይህን፡ሕዝብ፡እሬትን፡አበላዋለሁ፡የሐሞትንም፡ውኃ፡አጠጣዋለሁ። ፲፬ እነርሱና፡አባቶቻቸውም፡በላወቁአቸው፡አሕዛብ፡መካከል፡እበትናቸዋለሁ፥እስክጠፋቸውም፡ድረስ፡በስተ፡ኋላቸው፡ሰይፍን፡አሰድድባቸዋለሁ።

፲፭ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እንዲመጡ፡አልቃሾችን፡ሴቶችን፡ጥሩ፡እንዲመጡም፡ወደ፡ብልሃተኞች፡ሴቶች፡ላኩ፥ዓይኖቻችንም፡እንባ፡እንዲያፈስሱ፡የዓይናችንም፡ሽፋሽፍቶች፡ውኃን፡እንዲያፈልቁ፡ፈጥነው፡ለእኛ፡ልቅሶውን፡ይያዙ። ፲፮ በጽዮን፡እንዴት፡ተበዘበዝን!ምድርንም፡ትተናልና፥ቤቶቻችንንም፡አፍርሰዋልና፡እኛ፡ሞት፡ወደ፡መስኮታችን፡ደርሶአል፡ወደ፡አዳራሻችንም፡ውስጥ፡ገብቶአል። ፲፯ የሰውም፡ሬሳ፡እንደ፡ጕድፍ፡በእርሻ፡ላይ፡ወንጭም፡እንደማይሰበሰበውም፡ከአጫጆች፡በኋላ፡እንደሚቀር፡ቃርሚያ፡ይወድቃል።

፲፰ እነሆ፥አቀልጣቸዋለሁ፡እፈትናቸውማለሁ፡ስለ፡ሕዝቤ፡ሴት፡ልጅ፡ክፋት፡ከዚህ፡ሌላ፡የማደርገው፡ምንድር፡ነው?

፲፱ ምላሳቸው፡የተሳለ፡ፍላጻ፡ነው፡ሽንገላን፡ይናገራሉ፡ሰው፡ከባልንጀራው፡ጋር፡በሰላም፡ይናገራል፥በልቡ፡ግን፡ያደባበታል።

፳ በውኑ፡ስለዚህ፡ነገር፡አልቀሥፍምን?ይላል፡እግዚአብሔር፡ነፍሴስ፡እንደዚህ፡ባለ፡ሕዝብ፡ላይ፡አትበቀልምን?

፳፩ ለተራሮች፡ልቅሶን፡ለምድረ፡በዳ፡ማሰማርያዎችም፡ዋይታን፡አነሣለሁ፥ሰው፡እንዳያልፍባቸው፡በእሳት፡ተቃጥለዋልና። ሰዎችም፡የከብቱን፡ድምፅ፡አይሰሙም፤ከሰማይ፡ወፎች፡ጀምሮ፡እስከ፡እንሰሳ፡ድረስ፡ሸሽተው፡ሄደዋል። ፳፪ ኢየሩሳሌምንም፡የፍርስራሽ፡ክምር፡የቀበሮም፡ማደሪያ፡አደርጋታለሁ፥የይሁዳንም፡ከተሞች፡ሰው፡የማይቀመጥበት፡በድማ፡አደርጋቸዋለሁ።

፳፫ ይህን፡የሚያስተውል፡ጠቢብ፡ሰው፡ማን፡ነው?ያወራስ፡ዘንድ፡የእግዚአብሔር፡አፍ፡ለማን፡ተናገረ?ሰው፡እንዳያልፍበት፡ምድርስ፡ስለ፡ምን፡ጠፋች፥እንደ፡ምድረ፡በዳስ፡ስለ፡ምን፡ተቃጠለች?

፳፬ እግዚአብሔርም፡እንዲህ፡አለ፦የሰጠኋቸውን፡ሕጌን፡ትተዋልና፥ቃሌንም፡አልሰሙምና፥ነገር፡ግን፡የልባቸውን፡ምኞትና፡አባቶቻቸው፡ያስተማሩአቸውን፡በኣሊምን፡ተከትለዋልና፡ስለዚህ፡የእስራኤል፡አምላክ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እነሆ፥ይህን፡ሕዝብ፡እሬትን፡አበላዋለሁ፡የሐሞትንም፡ውኃ፡አጠጣዋለሁ። ፳፭ እነርሱና፡አባቶቻቸውም፡በላወቁአቸው፡አሕዛብ፡መካከል፡እበትናቸዋለሁ፥እስክጠፋቸውም፡ድረስ፡በስተ፡ኋላቸው፡ሰይፍን፡አሰድድባቸዋለሁ።

፳፮ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል፦እንዲመጡ፡አልቃሾችን፡ሴቶችን፡ጥሩ፡እንዲመጡም፡ወደ፡ብልሃተኞች፡ሴቶች፡ላኩ፥ዓይኖቻችንም፡እንባ፡እንዲያፈስሱ፡የዓይናችንም፡ሽፋሽፍቶች፡ውኃን፡እንዲያፈልቁ፡ፈጥነው፡ለእኛ፡ልቅሶውን፡ይያዙ። ፳፯ በጽዮን፡እንዴት፡ተበዘበዝን!ምድርንም፡ትተናልና፥ቤቶቻችንንም፡አፍርሰዋልና፡እኛ፡ሞት፡ወደ፡መስኮታችን፡ደርሶአል፡ወደ፡አዳራሻችንም፡ውስጥ፡ገብቶአል። ፳፰ የሰውም፡ሬሳ፡እንደ፡ጕድፍ፡በእርሻ፡ላይ፥ማንም፡እንደማይሰበስበውም፡ከአጫጆች፡በኋላ፡እንደ፡ሚቀር፡ቃርሚያ፡ይወድቃል።

እግዚአብሔር ፤ እንዲህ ፤ ይላል ፦ ጠቢብ ፤ በጥበቡ ፤ አይመካ ፥ ኃያልም ፤ በኃይሉ ፤ አይ መካ ፥ ጠጋም ፤ በብልጥግና ፡ አይመካ ፤ ነገር ፥ ግን ፤ የሚመካው ፦ ምሕረትንና ፥ ፍር ድን ፥ ጽድቅንም ፤ በምድር ፤ ላይ ፤ የማደርግ ፤ እኔ ፤ እግዚአብሔር ፤ መሆኔን ፤ በማወቁና ፤ በማስተ ዋሉ ፤ በዚህ ፤ ይመካ ፤ ደስ ፤ የሚያሰኙኝ ፤ እነ ዚህ ፤ ናቸውና ፥ ይላል ፤ እግዚአብሔር ።

አሕዛብ ፤ ሁሉ ፤ ያልተገረዙ ፤ ናቸውና ፥ የእ ስራኤልም ፤ ቤት ፤ ሁሉ ፤ ልባቸው ፤ ያልተገረዘ ፤ ነውና ፥ የተገረዙትን ፤ ሁሉ ፥ ግብጽንና ፤ ይሁ ዳን ፥ ኤዶምያስንም ፤ የአሞንንም ፤ ልጆች ፤ ሞዓ ብንም ፤ በምድረ ፤ በዳም ፤ የተቀመጡትን ፤ ጠጒ ራቸውን ፤ በዙሪያ ፤ የተላጩትን ፤ ሁሉ ፥ በለ መገረዛቸው ፤ እነርሱን ፤ የምቀጣበት ፤ ዘመን ፤ እነሆ ፤ ይመጣል ፥ ይላል ፤ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፤ ፲ ።

እናንተ ፤ የእስራኤል ፤ ቤት ፤ ሆይ ፥ እግዚአ ብሔር ፤ በእናንተ ፤ ላይ ፤ የተናገረውን ፤ ቃል ፤ ስሙ ። እግዚአብሔር ፤ እንዲህ ፤ ይላል ፦ የአሕዛብን ፤ መንገድ ፡ አትማሩ ፥ ከሰማይ ፥ ምል ክትም ፤ አትፍሩ ፥ አሕዛብ ፤ ይፈሩታልና ። የአ ሕዛብ ፤ ልማድ ፤ ከንቱ ፤ ነውና ፤ ዛፍ ፤ ከዳር ፤ ይቁረጣል ፥ በሠራተኛም ፤ እጅ ፤ በመጥረቢያ ፤ ይሠራል ። በብርና ፤ በወርቅ ፤ ያስጌጡታል ፥ እንዳይናወጥም ፤ በችንካርና ፥ በመዶሻ ፤ ይቸ ነክሩታል ። እንደ ፤ ተቀረጸ ፤ ዓምድ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፤ አይናገሩም ፤ መራመድም ፤ አይቻ ላቸውምና ፥ ይሸከሙአቸዋል ። ክፉ ፤ መሥራ ትም ፤ አያቻላቸውምና ፥ ደግሞም ፡ መልካም ፤ ይሠሩ ፤ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፤ አትፍሩአቸው ።

አቤቱ ፥ እንደ ፤ አንተ ፤ ያለ ፤ የለም ፤ አንተ ፡ ታላቅ ፤ ነህ ፤ ስምህም ፤ በኃይል ፤ ታላቅ ፤ ነው ። የአሕዛብ ፤ ንጉሥ ፤ ሆይ ፥ በአሕዛብ ፤ ጥበበ ኞች ፤ ሁሉ ፡ መካከል ፤ በመንግሥታቸውም ፡ ሁሉ ፤ እንደ ፤ አንተ ፤ ያለ ፤ ስለሌለ ፥ አንተን ፤ መፍራት ፤ ይገበልና ፥ አንተን ፤ የማይፈራ ፡ ግን ፤ ነው ፡ ? በእንድ ፤ ጊዜ ፤ ሰንፈዋል ፥ ደን ቀሎአልማል ፡ ጣዖታት ፤ የሚያስተምሩት ፡ የእ ንጨት ፤ ነገር ፤ ብቻ ፤ ነው ። የሠራተኛና ፥ የእ ንጥረኛ ፤ እጅ ፤ ሥራ ፤ የሆነ ፤ ከተርሴስ ፡ ጥፍ ጥፍ ፤ ብር ፤ ከአፈዝም ፤ ወርቅ ፤ ይመጣል ፤ ልብሳቸውም ፡ ሰማያዊና ፡ ቀይ ፤ ግምጃ ፤ ነው ፥ ሁሉም ፤ የብልሃተኞች ፤ ሥራ ፤ ናቸው ። እግ ዚአብሔር ፤ ግን ፤ እውነተኛ ፤ አምላክ ፤ ነው ፤ እርሱም ፡ ሕያው ፡ አምላክና ፡ የዘላለም ፤ ንጉሥ ፤ ነው ፡ ከቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ትንቀጠቀ ጣለች ፥ አሕዛብም ፡ መዓቱን ፤ አያችሉም ።

እናንተም ፦ ሰማያንና ፡ ምድርን ፡ ያልፈ ጠሩ ፡ እነዚህ ፤ አማልክት ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ከሰማያም ፡ በታች ፡ ይጠፋሉ ፡ ትሉአቸዋላ ችሁ ።

ምድርን ፡ በኃይሉ ፡ የፈጠረ ፥ ዓለሙን ፡ በጥ በቡ ፡ የመሠረተ ፡ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡ የዘረጋ ፡ አርሱ ፡ ነው ። ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ ውኖች ፡ በሰማይ ፡ ይሰበሰባሉ ፥ ከምድርም ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፡ ለዝናብም ፡ መብረቅን ፡ ያደርጋል ፥ ነፋስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛ ግብቱ ፡ ያወጣል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እውቀት ፡ አጥቶ ፡ ሰንፎአል ፥ አንጥረኛም ፡ ሁሉ ፡ ከቀረ ጹ ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡ አፍሮአል ፡ ቀልመ ፡ የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፥ እስትንፋ ስም ፡ የላቸውምና ። እነርሱ ፡ ምናምንቴና ፡ የቀ ልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፡ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠ ፋሉ ። የያዕቆብ ፤ እድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ እነ ዚህ ፡ አይደለም ፡ እርሱ ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነውና ፡ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፤ ነገድ ፡ ነውና ፡ ስሙ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጥሽ ፡ ሆይ ፥ ዕቃ ሽን ፡ ከመሬት ፡ ሰብስቢ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ ይላልና ፦ እነሆ ፥ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩ ትን ፡ እስከ ፡ ሰማቸው ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እመ ነጭፋቸዋለሁ ፥ አስጨንቃቸውማለሁ ።

ስለ ፡ ስብራቴ ፡ ወዮልኝ ! ቍስሌም ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፦ በእውነት ፡ የመከራ ፡ ቍስሌ ፡ ነው ፡ እርሱንም ፡ መሸከም ፡ ይገባኛል ፡ አልሁ ። ድንኳኔ ፡ ተበዘበዘ ፡ አውታሬም ፡ ሁሉ ፡ ተቁ ረጠ ፡ ልጆቼም ፡ ከእኔ ፡ ወጥተው ፡ አይገኙም ፤ ድንኳኔንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚዘረጋ ፡ መጋረጃዎችንም ፡ የሚያነሣ ፡ የለም ። እረኞች ፡ ሰንፈዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አልጠየቁት ምና ፡ አልተከናወነላቸውም ፥ መንጎቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ተበትነዋል ። የወሬን ፡ ድምፅ ፡ ስሙ ፥ እነ ሆም ፥ የይሁዳን ፡ ከተሞች ፡ በድማና ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ጽኑ ፡ ሽብር ፡ መጥቶአል ።

አቤቱ ፥ የሰው ፡ መንገድ ፡ ከራሱ ፡ እንዳይ ደለ ፡ አውቃለሁ ፥ አካሄዱንም ፡ ለማቅናት ፡ ከሚራመድ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። አቤቱ ፥ ቅጣኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳታዋርደኝ ፡ በመጠ ፥ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በቍጣ ፡ አይሁን ። ያዕቆብን ፡ በልተ ውታልና ፥ ውጠውትማልና ፥ አጥፍተውትማ ልና ፥ ማደሪያውንም ፡ አፍርሰዋልና ፡ በማያው ቁህ ፡ አሕዛብ ፡ ስምህንም ፡ በማይጠሩ ፡ ወገ ኖች ፡ ላይ ፡ መዓትህን ፡ አፍስስ ።

ምዕራፍ ፤ ፲፩ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስማ ፥ ለይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በአ የሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ተናገር ፥ እንደዚህም ፡ በላቸው ፡ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ከብ ረት ፡ ምድጃ ፡ በወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ ያዘዝሁትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ የማይ ሰማ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፤ አልሁም ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ ያዘዝኋችሁንም ፡ ሁሉ ፡ አድርጉ ፤ እን ዲሁም ፡ እናንተ ፡ ሕዝብ ፡ ትሆኑኛላችሁ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናችኋለሁ ። ይህም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈስሰውን ፡ ምድር ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ የማልሁ ትን ፡ መሐላ ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እኔም ፦ አቤቱ ፥ አሜን ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።

እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ይህ ችን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ከተሞችና ፡ በአ የሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ አድርገውትም ። አባቶቻችሁን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣሁበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ እያስጠነቀቅሁ ፦ ቃሌን ፥ ስሙ ፡ በማለት ፡ አስጠንቅቄአቸው ፡ ነበር ። እነርሱ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በክፋ ፡ ልባቸው ፡ እልከ ኛነት ፡ ሄዱ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙም ፡ ጆሮአቸ ውንም ፡ አላዘነበሉም ፡ ስለዚህ ፡ ያዘዝኋቸውን ፡ እነርሱም ፡ ያላደረጉትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ አመጣሁባቸው ።

እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ በይ ሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አድማ ፡ ተገኝቶአል ። ቃሌንም ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ወዳሉ ፡ ወደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ኃጢአት ፡ ተመለሱ ፡ ያመልኩአቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንግዶ ችን ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፤ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ያደረግሁ ትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፈረሱ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ ሊያመልጡት ፡ የማይችሉትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለሁ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ይጮኻሉ ፡ እኔም ፡ አልሰማቸ ውም ። በይሁዳም ፡ ከተሞችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ሄደው ፡ ወደሚያጥኑላቸው ፡ አማል ክት ፡ ይጮኻሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከቶ ፡ አያድኑአቸውም ። ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አማልክትህ ፡ እንደ ፡ ከተሞችህ ፡ ቍጥር ፡ እን ዲሁ ፡ ናቸው ፡ እንደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መንገ ዶች ፡ ቍጥር ፡ ለኃውረኛ ፡ ነገር ፡ መሠዊያ ፥ እር ሱም ፡ ለበኣል ፡ ታጥኑበት ፡ ዘንድ ፡ መሠዊያ ፥ አድርጋችኋል ። አንተም ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ ከመከራቸው ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ አልሰማቸውምና ፡ ስለ ፡ እነር ሱም ፡ ጩኸትና ፡ ልመና ፡ አታድርግ ።

ወዳጄ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ አላት ፡ ስእ ለት ፡ ወይም ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ ከፋትሽን ፡ ከአንቺ ፡ ያስወግዳልን ? ወይስ ፡ በእነዚህ ፡ ታመ ልጫለሽን ? እግዚአብሔር ፡ ስምሽን ፡ — በመ ልካም ፡ ፍሬ ፡ የተዋበች ፡ የለመለመች ፡ የወ ይራ ፡ ዛፍ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፡ በጽኑ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ጩኸት ፡ አሳትን ፡ አነደደበት ፡ ቅርንጫ ፎችዋም ፡ ተሰብረዋል ። ለበኣልም ፡ በማጠና ቸው ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ለራሳቸው ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ስለ ፡ እስራኤልና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ቤት ፡ ክፋት ፡ የተከለሽ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ተናግሮብሻል ።

እግዚአብሔርም ፡ አስታወቀኝ ፥ እኔም ፡ አወ ቅሁ ፥ ሥራቸውንም ፡ ገለጥህልኝ ። እኔም ፡ ለመ ታረድ ፡ እንደሚነዳ ፡ እንደ ፡ የዋህ ፡ በግ ፡ ጠበት ፡ ሆንሁ ፡ እነርሱም ፡ — ዛፉን ፡ ከፍሬው ፡ ጋር ፡ እንቍረጥ ፥ ስሙም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እን ዳይታሰብ ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ፡ እናጥፋው ፡ ብለው ፡ ምክርን ፡ እንዳሰቡብኝ ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ። ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትፈትን ፡ በቅ ንም ፡ የምትፈርድ ፡ አቤቱ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክርክሬን ፡ ገልጠሙልሃለሁና ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡ በቀልህን ፡ ለይ ። ስለዚህም ፡ — በእጃችን ፡ እንዳትሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ አትናገር ፡ ብለው ፡ ነፍስህን ፡ ስለሚሹ ፡ ስለ ፡ ኖሩቶት ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ አቀጣቸዋለሁ ፤ ጎበዛዝቶቻ ቸው ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታሉ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ በራብ ፡ ይሞታሉ ፤ በምጐበኛ ቸውም ፡ ዓመት ፡ በኖሩቶት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለሁና ፡ ማንም ፡ ከእነርሱ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።

ምዕራፍ ፤ ፲፪ ።

አቤቱ ፥ ከእንተ ፡ ጋር ፡ በተምዋገትሁ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነህ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ልናገር ። የኃጢአተኞች ፡ መን ገድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይቃናል ? በደልንስ ፡ ለሚያ ደርጉ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ደኅንነት ፡ ይሆናል ? ተክለሃቸዋል ፡ ሥር ፡ ሰድደዋል ፡ አድገዋል ፡ አፍርተውማል ፡ በአፋቸው ፡ አንተ ፡ ቅርብ ፡ ነህ ፥ ከልባቸው ፡ ግን ፡ ሩቅ ፡ ነህ ። አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አውቀኸኛል ፡ አይተኸኛል ፥ ልቤንም ፡ በፊትህ ፡ ፈትነሃል ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ ለመታረድ ፡ ጕትተህ ፡ ለያቸው ፥ ለመታረድም ፡ ቀን ፡ አዘጋጃቸው ። ምድሪቱ ፡ የምታለቅሰው ፥ የአገሩ ፡ ሣርስ ፡ ሁሉ ፡ የሚደርቀው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? የተቀመጡበት ፡ ሰዎች ፦ ፍጻ ሜያችንን ፡ አያይም ፡ ብለዋልና ፡ ስለ ፡ ክፋታ ቸው ፡ እንስሶችና ፡ ወፎች ፡ ጠፍተዋል ።

ከእግረኞች ፡ ጋር ፡ በሮጥህ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ቢያደክሙህ ፥ ከፈረሶች ፡ ጋር ፡ መታገል ፡ እን ይቲ ፡ ትችላለህ ? በሰላምም ፡ ምድር ፡ ታምነህ ፡ ብትቀመጥ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ እንዴት ፡ ታደርጋለህ ? ወንድሞችህና ፡ የአባትህ ፡ ቤት ፡ እነርሱ ፡ ዋሹ ፡ ሙሾ ፡ አሉልህ ፡ ስለዚህ ፡ በኋላህም ፡ ጮኸው ፡ ሞልተዋልና ፡ በመልካምም ፡ ቢናገሩህም ፡ አት ታመናቸው ።

ቤቴን ፡ ትቼአለሁ ፡ ርስቴንም ፡ ጥያለሁ ፥ ነፍ ሴም ፡ የምትወድዳትን ፡ በጠላቶችዋ ፡ እጅ ፡ አሳ ልፈ ፡ ሰዋቸለሁ ። ርስቴ ፡ በዱር ፡ እንዳለ ፡ አንበሳ ፡ ሆናብኛለች ፤ ድምፅዋን ፡ አንሥታብኛለች ፡ ስለዚህ ፡ ጠልቻታለሁ ። ርስቴ ፡ እንደ ፡ ዝንጕርጕር ፡ አሞራ ፡ ሆነችብኝን ? አሞሮችስ ፡ በዙሪያዋና ፡ በላይዋ ፡ ሆነዋልን ? ሂዱ ፥ የም ድር ፡ አራዊትን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቡ ፥ ይበሉም ፡

፲፡ ዘንድ፡አምጡአቸው ። ብዙ፡እረኞች፡የወ
ይኑን፡በታዬን፡አጥፍተዋል÷እድል፡ፈንታ
ዬንም ፡ረግጠዋል ፤ የአምሮቴን፡እድል፡
፲፩፡ ፈንታ፡ምድረ፡በዳ፡አድርገውታል ። በድማ፡
አድርገውታል÷ፈርሶም ፡ወደ፡እኔ፡ያለቅ
ሳል ፤ ምድር፡ሁሉ፡በድማ፡ሆናለች፡በል
፲፪፡ ቡም፡የሚያስበት፡የለም ። በወናዎች፡ከረ
ብቶች፡ሁሉ፡ላይ፡በገዘባጮች፡መዋተዋል÷
የእግዚአብሔር፡ሰይፍ፡ከምድር፡ዳር፡ጀምሮ፡
እስከ፡ምድር፡ዳር፡ድረስ፡ይበላልና ፤ለሥጋ፡
፲፫፡ ለባሽ፡ሁሉ፡ሰላም፡የለም ። ስንዴን ፡ዘሩ፡
እሾህንም፡አጨዱ ፤ ደከሙ÷ምንም ፡አልረ
ባቸውም ፡ስለ፡እግዚአብሔር ፡ጽኑ፡ቍጣ፡
ከፍሬያችሁ፡ታፍራላችሁ ።
፲፬፡ እግዚአብሔር፡ለሕዝቤ ፡ለእስራኤል፡ያወ
ረስኩትን፡ርስት፡ለሚነኩት፡ክፉዎች፡ጕረቤ
ቶች፡ሁሉ፡እንዲህ፡ይላልና ፥— እነሆ÷ከም
ድራቸው፡እነቅላቸዋለሁ÷የይሁዳንም፡ቤት፡
፲፭፡ ከመካከላቸው፡እነቅለዋለሁ ።ከነቀልኋቸውም፡
በኋላ ፡መልሼ ፡እምራቸዋለሁ÷እያንዳንዱ
ንም ፡ወደ ፡ርስቱ ፡እያንዳንዱንም ፡ወደ ፡
፲፮፡ ምድሩ ፡እመልሳለሁ ። በበእል ፡ያምሉ ፡
ዘንድ ፡ሕዝቤን ፡እንዳስተማሩ ፡በስሜ ፥—
ሕያው ፡እግዚአብሔርን ! ብለው ፡ይምሉ ፡
ዘንድ ፡የሕዝቤን ፡መንገድ፡በትጋት፡ቢማሩ÷
በዚያን፡ጊዜ ፡በሕዝቤ ፡መካከል ፡ይመሠረ
፲፯፡ ታሉ ።ቢያሰሙኝ፡ግን፡ያንን፡ሕዝብ፡ፈጽሜ፡
እነቅለዋለሁ፡አጠፋውማለሁ÷ይላል፡እግዚ
አብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩፡ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ይለኛል ፥— ሂድ÷
ከተልባ ፡እግር ፡የተሠራችን ፡መታጠቂያ፡
ለአንተ፡ግዛ÷ወገብህንም፡ታጠቅበት፡በው
፪፡ ኃውም፡ውስጥ፡አትንከራት ። እንደ፡እግዚ
አብሔርም፡ቃል፡መታጠቂያን፡ገዛሁ፡ወገቤ
፫፡ ፬፡ ንም፡ታጠቅሁበት ። ሁለተኛም፡ጊዜ፡ኾኖ፡የገ
ዛሃትን፡በወገብህ፡ያለችውን፡መታጠቂያ፡
ወስደህ፡ተነሥ÷ወደ፡ኤፍራጥስም፡ሂድ÷
በዚያም፡በተሰነጠቀ፡ዓለት፡ውስጥ፡ሸሽጋት፡
የሚል፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡መጣልኝ ።
፭፡ እግዚአብሔርም፡እንዳዘዘኝ፡ሄድሁ፡በኤፍራ
፮፡ ጥስም፡አጠገብ፡ሸሽግኋት ። ከብዙ፡ቀንም፡
በኋላ፡እግዚአብሔር፡ተነሥተህ፡ወደ፡ኤፍ
ራጥስ፡ሂድ÷በዚያም፡ትሸሽጋት፡ዘንድ፡
ያዘዝሁህን፡መታጠቂያ፡ከዚያ፡ውስጥ፡ውሰድ፡
፯፡ አለኝ ። እኔም፡ወደ፡ኤፍራጥስ፡ሄድሁ፡ቆፈ
ርሁም÷ከሸሸግሁበትም፡ስፍራ፡መታጠቂያ
ይቱን፡ወሰድሁ ። እነሆም÷መታጠቂያይቱ፡
ተበላሽታ፡ነበር÷ለምንም፡አልረባችም ።
፰፡ የእግዚአብሔርም፡ቃል፡ወደ፡እኔ፡እን
፱፡ ዲህ፡ሲል፡መጣ ፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡
ይላል ፥— እንዲሁ፡የይሁዳን፡ትዕቢት፡ታላ
ቁንም፡የኢየሩሳሌምን፡ትዕቢት፡አበላሻለሁ ።

፩፡ ቃሌን፡ይሰሙ፡ዘንድ፡እንቢ፡የሚሉ÷በል
በቸውም ፡እልከኝነት፡የሚሄዱ÷ያመልኩአ
ቸውና፡ይሰግዱላቸው፡ዘንድ፡ሌሎችን፡አማ
ልክት፡የሚከተሉ፡እነዚህ፡ክፉ፡ሕዝብ፡አን
ዳች፡እንደማትረባ፡እንደዚች፡መታጠቂያ፡
፲፡ ይሆናሉ ። መታጠቂያ ፡በሰው ፡ወገብ ፡ላይ ፡
እንደምትጣበቅ÷እንዲሁ ፡ሕዝብና ፡ስም ፡
ምስጋናና፡ክብር፡ይሆኑልኝ፡ዘንድ ፡የእስራ
ኤልን ፡ቤት፡ሁሉ፡የይሁዳንም ፡ቤት፡ሁሉ፡
ከእኔ ፡ጋር፡አጣብቄአለሁ÷ይላል፡እግዚአብ
ሔር፡ነገር፡ግን፡አልሰሙም ።

፲፩፡ ስለዚህ፡— የእስራኤል፡አምላክ፡እግዚአብ
ሔር፡እንዲህ፡ይላል ፥— ማድጋ፡ሁሉ፡የወ
ይን፡ጠጅ፡ይሞላል፡ብለህ፡ትነግራቸዋለህ፡
እነርሱም ፥— ማድጋ፡ሁሉ፡የወይን፡ጠጅ፡
እንዲሞላ፡በውኑ፡እኛ፡እናውቅምን ? ይሉ
፲፪፡ ሃል ። አንተም ፡እንዲህ፡ትላቸዋለህ ፥— እግ
ዚአብሔር፡እንዲህ፡ይላል ፥— እነሆ÷በዚህች፡
ምድር፡የሚኖሩትን፡ሁሉ÷በዳዊት፡ዙፋን፡
የሚቀመጡትን፡ነገሥታት፡ካህናቱንም ፡ነቢ
ያቱንም ፡በኢየሩሳሌምም ፡የተቀመጡትን ፡
፲፫፡ ሁሉ ፡በስካር ፡እሞላቸዋለሁ ። ሰውንም ፡
በሰው ፡ላይ÷አባቶችንና፡ልጆችን፡በአንድ፡
ላይ÷እቀጠቅጣቸዋለሁ÷ይላል ፡እግዚአብ
ሔር፡አጠፋቸዋለሁ፡እንጂ፡አልራራም÷አላ
ዝንም ÷አልምርም ።

፲፬፡ ስሙ÷አድምጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ተናግሮ
አልና፡አትታበዩ ። ሳትጨልም፡እግራችሁም፡
፲፮፡ በጨለመችው ፡ተራራ ፡ላይ ፡ሳትሰናከል ÷
በተስፋ፡የምትጠብቁትን፡ብርሃን፡ሰሞት፡
ጥላና፡ለድቅድቅ፡ጨለማ፡ሳይለውጠው፡ለአ
ምላካችሁ፡ለእግዚአብሔር፡ክብርን፡ስጡ ።
፲፯፡ ይህን፡በትሰሙ፡ነፍሴ፡ስለ ፡ትዕቢታችሁ፡
በስውር ፡ታለቅሳለች ። የእግዚአብሔርም ፡
መንጋ፡ተማርኮአልና፡ዓይኔ፡ታነባለች÷እን
ባንም ፡ታፈስሳለች ።

፲፰፡ ለንጉሡና፡ለንጉሥ፡እናት፡ለእቴጌይቱ ፥—
የክብራችሁ፡አክሊል ፡ከራሳችሁ ፡ወርዶአ
ልና ፡ተዋርዳችሁ፡ተቀመጡ፡በል ። የደቡብ፡
፲፱፡ ከተሞች ፡ተዘግተዋል ÷ የሚከፍታቸውም ፡
የለም ፤ ይሁዳ ፡ሁሉ ፡ተማርኮአል÷ፈጽሞ፡
ተማርኮአል ።

፳፡ ዓይናችሁን ፡አንሥታችሁ፡እነዚህን፡ከሰ
ሜን፡የሚመጡትን፡ተመልከቱ፡ለአንቺ፡የተ
ሰጠ፡መንጋ÷የተዋበ፡መንጋሽ÷ወዴት፡
አለ ? ወዳጆችሽ፡እንዲሆኑ፡ያስተማርሻቸ
፳፩፡ ውን፡በራስሽ፡ላይ፡አለቆች፡ባደረጋቸው፡
ጊዜ፡ምን፡ትያለሽ ?እንደ፡ወላድ፡ሴት፡ምጥ፡
አይዝሽምን ? በልብሽም ፥— እንዲህ፡ያለ፡
፳፪፡ ነገር፡ስለ፡ምን፡ደረሰብኝ ? ብትዪ÷ከኃጢአ
ትሽ፡ብዛት፡የተነሣ፡የልብስሽ፡ዘርፍ፡ተገል
ጦአል ፡ተረከዝሽም ፡ተገፍፎአል ። በውኑ፡
፳፫፡ ኢትዮጵያዊ፡መልኩን፡ወይስ፡ነብር፡ዝንጉ
ርጕርኑትን፡ይለውጥ፡ዘንድ፡ይችላልን ? በዚ

፩፡ ያን ፡ጊዜ ፡ክፋትን ፡የለመዳችሁ፡እናንተ፡
፪፡ ደግሞ ፡በን ፡ለማድረግ ፡ትችላላችሁ ። ስለ
ዚህ፡እንደሚያልፍ፡እብቅ፡በምድረ፡በዳ፡
፫፡ ነፋስ፡እበትናቸዋለሁ ። ረስተሽኛልና ÷በሐ
ሰትም ፡ታምነሻልና ፡ዕጣሽ፡የለካሁልሽም ፡
እድል፡ፈንታ፡ይህ፡ነው÷ይላል፡እግዚአብ
፭፡ ሔር ።ስለዚህም ፡የልብስሽን ፡ዘርፍ፡በፊ
፮፡ ትሽ፡አገልጣለሁ ፡እፍረትሽም ፡ይታያል ።
፯፡ እስጸያፊ ፡ሥራሽን ÷ምንዝርናሽን ÷ማኸክ
ትሽን ÷የግልሙትናሽንም፡መዳራት፡በኮረብ
፰፡ ቶች፡ላይ፡በሜዳም፡አይቻለሁ ።ኢየሩሳሌም፡
ሆይ ÷ወዮልሽ ! ለመንጻት፡እንቢ፡ብለሽል፡
፱፡ ይህስ፡እስከ፡መቼ፡ነው ?

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩፡ ወደ ፡ኤርምያስ፡ስለ ፡ድርቅ ፡የመጣው ፡
፪፡ የእግዚአብሔር፡ቃል ፡ይህ፡ነው ። ይሁዳ፡
አለቀሰች÷ደጆችዋም ፡በዶ ፡ሆኑ ፡በምድ
ርም ፡ላይ ፡ጨለሙ ፡የኢየሩሳሌም፡ጩኸት፡
፫፡ ከፍ፡ከፍ ፡ብሎአል ። ታላላቆችም ፡ብላቴና
ቻቸውን ፡ወደ፡ውኃ፡ሰደዱ ፤ ወደ፡ጕድጓድ፡
መጡ ፡ውኃም ፡አላገኙም ÷ዕቃቸውንም ፡
ባዶውን ፡ይዘው ፡ተመለሱ፡አፈሩም ፡ተዋረ
፬፡ ዱም ፡ራሳቸውንም ፡ተከናነቡ ። በምድር ፡
ላይ ፡አልዘነበምና ፡መሬቱ፡ስንጥቅጥቅ፡ስለ፡
ሆነ ፡አራሾች ፡አፈሩ ፡ራሳቸውንም ፡ተከና
፭፡ ነቡ ። ዋላ ፡ደግሞ ፡በምድረ፡በዳ፡ወለደች÷
፮፡ ሣርም ፡የለምና ፡ግልገልዋን፡ተዋች ።የሜዳ፡
አህዮችም ፡በወና ፡ከረብታ ፡ላይ ፡ቆመዋል÷
እንደ ፡ቀበሮም ፡ወደ ፡ነፋስ፡አለከለኩ ፡ልም
ላሜም ፡የለምና ፡ዓይኖቻቸው ፡ጠወለጉ ።

፯፡ አቤቱ ÷ኃጢአታችን ፡ብዙ ፡ነውና ÷በአ
ንተም ፡ላይ ፡ኃጢአት፡ሠርተናልና ፡ኃጢአ
ታችን ፡ይመሰክርብናል ፡ነገር ፡ግን ፡ስለ ፡
፰፡ ስምህ ፡ብለህ ፡አድርግ ። አንተ ፡የእስራኤል ፡
ተስፋ ፡ሆይ ፡በመከራም ፡ጊዜ ፡የምታድነው ÷
በምድር ፡እንደ ፡እንግዳ ÷ወደ ፡ማደሪያ ፡
ዘወር ፡እንደሚል ፡መንገደኛ ፡ስለ ፡ምን ፡ትሆ
፱፡ ናለህ ? እንዳንቀላፋ ፡ሰው ÷ያድንም ፡ዘንድ ፡
እንደማይችል ፡ኃያል ፡ስለ ፡ምን ፡ትሆናለህ?
አንተ ፡ግን ፡አቤቱ ፡በመካከላችን ፡ነህ ፡
እኛም፡በስምህ፡ተጠርተናል ፡አትተወን ።

፲፡ እግዚአብሔር ፡ለዚህ ፡ሕዝብ ፡እንዲህ ፡
ይላል ፥— መቅበዝበዝን ፡ወድደዋል ፡እግራ
ቸውንም ፡አልከለከሉም ፡ስለዚህ ፡እግዚአብ
ሔር፡በእነርሱ፡ደስ፡አይለውም÷በደላቸው
ንም ፡አሁን ፡ያስባል ፡ኃጢአታቸውንም ፡
፲፩፡ ይቀጣል ።እግዚአብሔርም ፥—ለዚህ፡ሕዝብ፡
፲፪፡ ስለ ፡መልካም ፡አትጸልይላቸው ። በጾሙ፡
ጊዜ ፡ጸሎታቸውን ፡አልሰማም ፤ የሚቃጠለ
ውን፡መሥዋዕትና፡የእህሉን፡ቍርባን፡በቀ
ረቡ፡ጊዜ፡አልቀበላቸውም፡በሰይፍና፡በራብ፡
በቸነፈርም፡አጠፋቸዋለሁ፡አለኝ ።

፲፫፡ እኔም ፥— ጌታ፡እግዚአብሔር፡ሆይ÷ወዮ !
እነሆ ÷ነቢያት ፥— በእውነት፡ሰላምን፡በዚህ፡
ስፍራ ፡እሰጣችኋለሁ፡እንጂ ፡ሰይፍንና ፡አታ
ዩም ÷ራብም ፡አያገኛችሁም ፡ይሉአቸዋል ፡
አልሁ ። እግዚአብሔርም፡እንዲህ፡አለኝ ፥— ፲፬፡
ነቢያቱ፡ውሸት ፡በስሜ ፡ትንቢት፡ይናገራሉ ፡
እላክኋቸውም ÷አላዘዝኋቸውም ÷አልተናገ
ርኋቸውም ፤ የውሸቱን ፡ራእይ ፡ምዋርትንም ፡
ከንቱንም ፡ነገር ፡የልባቸውንም ፡ሽንገላ፡ይሰ
ብኩላችኋል ። ስለዚህ፡እግዚአብሔር፡በስሜ ፡ ፲፭፡
ትንቢት፡ስለሚናገሩ ፡ነቢያት ፥— በዚህች ፡
አገር ፡ሰይፍና ፡ራብ ፡አይሆንም ፡ስለሚሉ ፡
ስላላክኋቸው ፡ነቢያት ፡እንዲህ፡ይላል ፥— እነ
ዚያ ፡በሰይፍና ፡በራብ ፡ይጠፋሉ ። ትንቢት ፡ ፲፮፡
የሚናገሩላቸውም ፡ሰዎች ፡ከራብና ፡ከሰይፍ፡
የተነሣ ፡በኢየሩሳሌም ፡አደባባይ ፡ይበተናሉ ፡
ክፋታቸውንም ፡አፈስስባቸዋለሁና ፡እነርሱ
ንና ፡ሚስቶቻቸውን ፡ወንዶችና ፡ሴቶች፡ልጆ
ቻቸውንም ፡የሚቀብራቸው ፡አይገኝም ። እን ፲፯፡
ደዚህም ፡ብለህ ፡ትነግራቸዋለህ ፥— የወገኔ ፡
ልጅ ፡ድንግሊቱ ፡በታላቅ፡ስብራትና ፡እጅግ፡
ክፉ ፡በሆነ ፡ቍስል ፡ተሰብራለችና ፡ዓይኖቼ ፡
ሌሊትና ፡ቀን ፡ሳያቋርጡ ፡እንባ ፡ያፍስሱ ።
ወደ ፡ሜዳ ፡ብወጣ÷እነሆ ፡በሰይፍ፡የሞቱ ፡ ፲፰፡
አሉ ፡ወደ ፡ከተማም ፡ብገባ÷እነሆ ፡በራብ፡
የከሱ ፡አሉ ፡ነቢዩና ፡ካህኑም ፡ወደማያው
ቁት ፡አገር ፡ሄደዋልና ።

በውኑ፡ይሁዳን፡ፈጽመህ፡ጥለኽዋልን ? ነፍ ፲፱፡
ስህስ ፡ጽዮንን ፡ጠልታታለችን ? ስለ ፡ምን ፡
መታኸን ? ፈውስስ ፡ስለ ፡ምን ፡የለንም ? ሰላ
ምን ፡በተስፋ ፡ተጠባበቅን ÷መልካምም ፡አል
ተገኘም ፡ፈውስን ፡በተስፋ ፡ተጠበቅን ÷እነ
ሆም ÷ድንጋጤ ፡ሆነ ። አቤቱ ፡በእንተ ፡ላይ ፡ ፳፡
ኃጢአትን ፡ሠርተናልና ፡ክፋታችንንና ፡የአ
ባቶቻችንን፡በደል፡እናውቃለን ። ስለ ፡ስምህ፡ ፳፩፡
ብለህ ፡አትናቀን ÷የክብርህንም ፡ዙፋን ፡አታ
ስነውር ፤ ከእኛ ፡ጋርም ፡ያደረግኸውን ፡
ቃል ፡ኪዳንህን ፡አስብ ፡እንጂ ፡አታፍርብ ፡
በውኑ ፡በአሕዛብ ፡ጣዖታት ፡መከከል ፡ያዘ ፳፪፡
ንብ ፡ዘንድ ፡የሚችል ፡ይገኛልን ? ወይስ ፡
ሰማይ ፡ዝናብ ፡ማፍሰስ ፡ይችላልን ? አቤቱ ፡
አምላካችን ፡ሆይ ፡አንተ ፡እይደለህምን ?
አንተ ፡ይህን ፡ነገር ፡ሁሉ ፡አድርገሃልና ፡ስለ
ዚህ ፡አንተን ፡በተስፋ ፡እንጠበበቃለን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩፡ እግዚአብሔርም ፡እንደዚህ ፡አለኝ ፡— ፡
ሙሴና ፡ሳሙኤል ፡በፊቴ ፡ቢቆሙም ፡ልቤ ፡
ወደዚህ ፡ሕዝብ ፡አይዘነበልም ፡ከፊቴ ፡ጣላ
ቸው ፡ይውጡ ። እነርሱም ፥— ወዴት ፡እን ፪፡
ውጣ ፡ቢሉህ ÷አንተ ፥— እግዚአብሔር ፡እን
ዲህ ፡ይላል ፥— ለሞት ፡የሆነ ፡ወደ ፡ሞት ÷
ለሰይፍም ፡የሆነ ፡ወደ ፡ሰይፍ ÷ለራብም ፡
የሆነ ፡ወደ ፡ራብ ÷ለምርኮም ፡የሆነ ፡ወደ ፡
ምርኮ፡ትላቸዋለህ ። ሰይፍን፡ለመግደል፡ውሾ ፫፡

ችንም ፡ ለመጕተት ፡ የሰማያትንም ፡ ወፎች ፡ የምድርንም ፡ አራዊት ፡ ለመብላትና ፡ ለማጥፋት ÷ አራቱን ፡ ዓይነት ፡ ጥፋት ፡ አዝዝባቸዋለሁ ፥ ፱ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ልጅ ፡ ምናሴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስላ ደረገው ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ መከከል ፡ ለመከራ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁ ። ፲፭ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ÷ የሚራራልሽ ፡ ማን ፡ ነው ? የሚያዝንልሽስ ፡ ማን ፡ ነው ? ወይስ ፡ ስለ ፡ ደኅንነትሽ ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው ? አንቺ ፡ አኔን ፡ ጥለሽል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ ወደ ፡ ኋላሽም ፡ ተመልሰሻል ፡ ስለዚህ ፡ እጀን ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ዘርግቼ ፡ አጥፍቼሻለሁ ፡ ከይቅርታ ፡ ደክሜአለሁ ። ፮ ፡ በአገርም ፡ ደጆች ፡ ውስጥ ፡ በመንሽ ፡ አበጥሬ አቸዋለሁ ፡ የወላድ ፡ መካን ፡ አድርጌአቸዋለሁ÷ ሕዝቤንም ፡ አጥፍቼአለሁ ፡ ከመንገዳቸውም ፡ ፯ ፡ አልተመለሱም ። መበለቶቻቸውም ፡ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ በዝተውብኛል ፤ በብላቴኖች ፡ እናት ፡ ላይ ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ አጥፊውን ፡ አም ጥቻለሁ ፡ ጣርንና ፡ ድንጋጤን ፡ በድንገት ፡ አም ፰ ፡ ጥቼበታለሁ ። ሰባት ፡ የወለደች ፡ ደክማለች ÷ ነፍስዋንም ፡ አውጥታለች ፤ ቀን ፡ ገና ፡ ሳለ ፡ ፀሐይዋ ፡ ገብታባታለች ፤ አፍራለች ፡ ተዋርዳማ ለች ። የተረፉትንም ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ።

፱ ፡ እናቴ ፡ ሆይ ÷ ወዮልኝ ! ለምድር ፡ ሁሉ ፡ የክርክርና ፡ የጥል ፡ ሰው ፡ የሆንሁትን ፡ ወለድሽኝ ፡ ለማንም ፡ አላበደርሁም ÷ ማንም ፡ ለእኔ ፡ አላበደረም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ይረግመኛል ። እግ ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ለደ ኅንነትህ ፡ አጸናሃለሁ ፤ በእውነት ፡ በመከራና ፡ በጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ ጠላትህ ፡ እንዲለምንህ ፡ አደር ፲፪ ፡ ገዋለሁ ። በውኑ ፡ ብረትን ÷ የሰሜንን ፡ ብረት ÷ ናስንም ፡ የሚሰብር ፡ አለን ?

፲፫ ፡ በዳርቻህ ፡ ሁሉ ፡ ስላለ ፡ ኃጢአትህ ፡ ሁሉ ፡ ባለጠግነትህንና ፡ መዝገብህን ፡ ለመበዝበዝ ፡ በከንቱ ፡ አሰጣለሁ ። የምታቃዋላችሁ ፡ አሳት ፡ ከቀሣፍ ፡ ትነድዳለችና ፡ ከጠላቶችህ ፡ ጋር ፡ ወደማታውቀው ፡ ምድር ፡ አሳልፍሃለሁ ።

፲፭ ፡ አቤቱ ÷ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ አስበኝ ፡ ጐብኝኝም ፡ የሚያሳድዱኝንም ፡ ተበቀላቸው ፡ እንጂ ፡ አትታገሣቸው ፤ ስለ ፡ አንተ ፡ ስድብን ፡ ፲፮ ፡ እንደ ፡ ታገሥሁ ፡ እወቅ ። ቃልህ ፡ ተገኝቶአል ፡ እኔም ፡ በልቼዋለሁ ፡ አቤቱ ÷ የሠራዊት ፡ አም ላክ ፡ ሆይ ÷ በስምህ ፡ ተጠርቻለሁና ፡ ቃልህ ፡ ሐሤትና ፡ የልብ ፡ ደስታ ፡ ሆነኝ ። በዋዘኞችና ፡ ፲፯ ፡ በደስተኞች ፡ ጉባኤ ፡ አልተቀመጥሁም ፤ ቀኣጣን ፡ ሞልተህብኛልና ፡ በእጅህ ፡ ፊት ፡ ለብቻዬ ፡ ተቀመጥሁ ። ስለ ፡ ምን ፡ ሕመሜ ፡ አዘወተረኝ ? ፲፰ ፡ ቍስሌስ ፡ ስለምን ፡ የማይፈወስ ፡ ሆነ ? ስለ ፡ ምንስ ፡ — አልኸርም ፡ ኦሳ ፡ ውኑ ፡ እንደ ፡ ሐሰ ተኛ ፡ ምንጭ ÷ እንዳ ፡ ያሉ ፡ ነች ፡ ውኃ ፡ ትሆን ኖለህን ?

፲፱ ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — ብትመለስ ፡ እመልስሃለሁ ፡ በፊቴም ፡ ትቆማለህ ፤ የከበረውንም ፡ ከተዋረደው ፡ ብትለይ ፡ እንደ ፡ አፌ ፡ ትሆናለህ ፤ እነርሱ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይመለሳሉ ÷ አንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አትመለስም ። ፳ ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ የተመሸገ ፡ የናስ ፡ ቅጥር ፡ አደርግሃለሁ ፤ ይዋጉሃል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለማዳን ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ፡ አያሸንፉህም ። ይከፉ ፡ ፳፩ ፡ ሰዎችም ፡ እጅ ፡ እታደግሃለሁ ÷ ከጨካኞችም ፡ ጡጫ ፡ እቤዝሃለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ፪ ፡ ሰል ፡ መጣ ፦ — በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ሚስት ፡ አታ ግባ ÷ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ አይሁኑ ፫ ፡ ልህ ። እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ተወለዱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ÷ ስለ ፡ ወለዱአቸውም ፡ ስለ ፡ እናቶቻቸው ÷ በዚህ ችም ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ወለዱአቸው ፡ ስለ ፡ አባቶች ፬ ፡ ቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ — በክፉ ፡ ሞት ፡ ይሞ ታሉ ፡ አይለቀስላቸውም ፡ አይቀበሩምም ÷ በመሬትም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይሆናሉ ፡ በሰ ይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ÷ ሬሳቸውም ፡ ለሰ ማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይሆናሉ ።

፭ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰላሜን ÷ ቸርነትንና ፡ ምሕረትን ÷ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አስ ወግጀአለሁና ፡ ልቅሶ ፡ ወዳለበት ፡ ቤት ፡ አት ግባ ÷ ታለቅስም ፡ ታዝንም ፡ ዘንድ ፡ አትሂድ ። ፮ ፡ ታላላቆችና ፡ ታናናሾች ፡ በዚህች ፡ ምድር ፡ ይሞታሉ ፡ አይቀበሩም ፡ ሰዎችም ፡ አያለቅሱ ላቸውም ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ገላን ፡ አይነጩላ ቸውም ፡ ራስንም ፡ አይላጩላቸውም ። ፯ ፡ ሰዎችም ፡ ስለ ፡ ሞቱት ፡ ለማጽናናት ፡ የእዝን ፡ እንጀራ ፡ አይቈርሱላቸውም ÷ ስለ ፡ አባታቸው ፡ ስለ ፡ እናታቸውም ፡ የመጽናኛት ፡ ጽዋ ፡ አያጠጡአቸውም ። ፰ ፡ ከቤላና ፡ ትጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደ ፡ ግብዣ ፡ ቤት ፡ አትግባ ። ፱ ፡ የእስራኤል ፡ አም ላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ — እነሆ ÷ በዓይናችሁ ፡ ፈት ፡ በዘመና ችሁም ፡ የአልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፡ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ አስቀራለሁ ።

፲ ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በተ ናገርህ ፡ ጊዜ ፦ — ይህን ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አግዚአብሔር ፡ ተናገ ረብን ? በደላችንስ ፡ ምንድር ፡ ነው ? በአምላ ካችንስ ፡ በአግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የሠራነው ፡ ኃጢአታችን ፡ ምንድር ፡ ነው ? ፲፩ ፡ ቢሉህ ÷ አንተ ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለህ ፦ አባቶቻችሁ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፡ ነው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ ሌሎችንም ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፡ አመለኩአ ቸውም ፡ ሰገዱላቸውም ÷ እነርሱም ፡ ትተው ፲፪ ፡ ኛል ÷ ሕጌንም ፡ አልጠበቁም ፤ እናንተም ፡ ከአ ባቶቻችሁ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ አድርጋችኋል ፤ እን ሆም ÷ ሁላችሁ ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ልባችሁ ፡ እል ከኝንት ፡ ሄዳችኋል ፤ እኔንም ፡ አልሰማችሁም ። ፲፫ ፡ ስለዚህ ፡ ከዚህች ፡ ምድር ፡ እናንተና ፡ አባቶች ችሁ ፡ ወዳላወቃችኋት ፡ ምድር ፡ እጥላችኋለሁ ፤ ምሕረትንም ፡ አላደርግላችሁምና ፡ በዚያ ፡ ሌሎ ችን ፡ አማልክት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ታመልካላ ችሁ ።

፲፬ ፡ ስለዚህ ÷ እነሆ ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብ ሔርን ! ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመ ጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፦ — የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ካሳደ ዳቸውም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ይባላል ። ፲፭ ፡ እኔም ፡ ለአባቶቻ ቸው ፡ ወደ ፡ ሰጠኋት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ እመ ልሳቸዋለሁ ።

፲፮ ፡ እነሆ ÷ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆችን ፡ እሰድ ዳለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ እነርሱም ፡ ያጠምዱአቸዋል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ አዳ ኞችን ፡ እሰድዳለሁ ÷ እነርሱም ፡ ከየተራራ ውና ፡ ከየከረብታው ፡ ሁሉ ፡ ከየድንጋዩም ፡ ስንጣቂ ፡ ውስጥ ፡ ያድኑአቸዋል ። ፲፯ ፡ ዓይኔ ፡ በመ ንገዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ከፊቴም ፡ አልተ ሰወሩም ÷ ኃጢአታቸውም ፡ ከዓይኔ ፡ አልተሸ ሸገም ። ፲፰ ፡ ምድሬንም ፡ በተጠሉ ፡ በጣዖቶች ቸው ፡ ሬሳዎች ፡ አርክሰዋልና ፡ ርስቴንም ፡ አስጸያፊ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ሞልተዋልና ፡ አስ ቀድሜ ፡ የበደላቸውንና ፡ የኃጢአታቸውን ፡ ዕጥ ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ እከፍላቸዋለሁ ።

፲፱ ፡ አቤቱ ÷ ኃይሌ ÷ አምባዬ ÷ በመከራም ፡ ቀን ፡ መጠጊያዬ ፡ ሆይ ÷ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መጥተው ፡ — በእውነት ፡ አባቶ ቻችን ፡ ውሸትንና ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ የማይረባ ቸውንም ፡ ወርሰዋል ፡ ይላሉ ። ፳ ፡ በውኑ ፡ ሰው ፡ አማልክት ፡ ያልሆኑትን ፡ ለራሱ ፡ አማልክትን ፡ አድርጎ ፡ ይሠራልን ?

፳፩ ፡ ስለዚህ ÷ እነሆ ÷ አስታውቃቸዋለሁ ÷ በዚህች ፡ ጊዜ ፡ እጀንና ፡ ኃይሌን ፡ አስታውቃ ቸዋለሁ ፤ እነርሱም ፡ ስሜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩ ፡ የይሁዳ ፡ ኃጢአት ፡ በብረት ፡ ብርዕና ፡ በተ ሾለ ፡ ዕብነ ፡ አልማዝ ፡ ተጽፎአል ፤ በልባቸው ፪ ፡ ጽላትና ፡ በመሠዊያቸው ፡ ቀንዶች ፡ ተቀርጸ አል ። ልጆቻቸውም ፡ ከለመልሙ ፡ ዛፎች ፡ በታችና ፡ በረዘሙት ፡ ከረብቶች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፫ ፡ መሠዊያቸውንና ፡ የማምለኪያ ፡ ሀፀዳቸውን ፡ ያስባሉ ። በሚዳ ፡ ያለው ፡ ተራራዬ ፡ ሆይ ÷ ባለጠግነትህንና ፡ መዝገብህን ፡ ሁሉ ፡ የከረብ ታውን ፡ መስገጃዎችህም ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ በድ ፬ ፡ ንበሮችህ ፡ ሁሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ አሰጣለሁ ። አን

፭ ፡ ተም ፡ የሰጠሁህን ፡ ርስት ፡ ትለቅቃለህ ፡ ለዘላ ለምም ፡ በማታውቃትም ፡ ምድር ፡ ለጠላቶች ችሁ ፡ ባሪያ ፡ አደርግሃለሁ ፡ ለዘላለም ፡ የሚነ ድዱውን ፡ እሳት ፡ በቀጣዩ ፡ አንድዳችኋልና ።

፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በሰው ፡ የሚታመን ፡ ሥጋ ፡ ለብሹንም ፡ ከንጹ ፡ የሚያ ደርግ ፡ ልቡም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚመለስ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ነው ። ፯ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቊጥቋጦ ፡ ይሆናል ÷ መልካምም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አያይም ፤ ሰውም ፡ በሌለበት ÷ ጨው ፡ ባለበት ፡ ምድር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በደረቅ ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጣል ። ፰ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የታ መነ ፡ እምነቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ቡሩክ ፡ ነው ። ፰ ፡ በውኃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ተተ ከለ ፡ በወንዝም ፡ ዳር ፡ ሥሩን ፡ እንደሚዘረጋ ፡ ሙቀትም ፡ ሲመጣ ፡ እንደማይፈራ ፡ ቅጠሉም ፡ እንደሚለመልም ÷ በድርቅ ፡ ዓመትም ፡ እንደ ማይሠጋ ፡ ፍሬውንም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ዛፍ ፡ ይሆናል ።

፱ ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ተንኰለኛ ፡ እጅግም ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ማንስ ፡ ያውቀዋል ? ፲ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ÷ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ልብን ፡ እመረምራለሁ ፡ ሰላሊትንም ፡ እፈት ናለሁ ። ፲፩ ፡ ያልወለደችውን ፡ እንደምታቅፍ ፡ ቆቅ ÷ እንዲሁ ፡ በቅን ፡ ሳይሆን ፡ ባለጠግነትን ፡ የሚሰበስብ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ በእኩሌታ ፡ ዘመኑ ፡ ይተወዋል ÷ በፍጻሜውም ፡ ሰነፍ ፡ ይሆናል ።

፲፪ ፡ የመቅደሳችን ፡ ስፍራ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የከብር ፡ ዙፋን ፡ ነው ። አቤቱ ፡ ፲፫ ፡ የእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ሆይ ÷ የሚተዉህ ፡ ሁሉ ፡ ያፍራሉ ፡ ከእንተም ፡ የሚለዩ ፡ የሕይወትን ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተዋልና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ። አቤቱ ፡ ፲፬ ፡ ፈውሰኝ ፡ እኔም ፡ እፈወሰለሁ ፡ አድነኝ ፡ እኔም ፡ እድናለሁ ፡ አንተ ፡ ምስጋናዬ ፡ ነህና ። ፲፭ ፡ እነሆ ፦ የእግዚአብ ሔር ፡ ቃል ፡ ወዪት ፡ አለች ? አሁን ፡ ትምጣ ፡ ይሉኛል ። እኔም ፡ አንተን ፡ ተከትዬ ፡ አረኛ ፡ ፲፮ ፡ ከመሆን ፡ እልቸኰልሁም ÷ የመከራንም ፡ ቀን ፡ አልወደድሁም ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ ከከንፈሬ ፡ የወጣው ፡ በፊትህ ፡ ነበረ ። ፲፯ ፡ ለማስፈራራት ፡ አትሁንብኝ ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ መጠጊ ያዬ ፡ ነህ ። ፲፰ ፡ አሳፋሪቹ ፡ ይፈሩ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አል ፈር ፤ እነርሱ ፡ ይደንግጡ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አልደን ግጥ ፡ ክፉንም ፡ ቀን ፡ አምጣባቸው ÷ በሁለት ፡ እጥፍ ፡ ጥፋት ፡ አጥፋቸው ።

፲፱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ — ሂድ ÷ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በሚገቡበትና ፡ በሚወ ጡበት ፡ በሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ በር ፡ በኢየሩሳሌ ምም ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ቁም ፡ እንዲህም ፡ በላ ፳ ፡ ቸው ፦ — በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ÷ እና ንተ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ÷ ይሁዳም ፡ ሁሉ ÷ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ሁሉ ፡ የእግ ዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ። ፳፩ ፡ እግዚአብሔር ፡

እንዲህ ፣ ይላል ፦ ለራሳችሁ ፣ ተጠንቀቁ ÷ በሰንበትም ፣ ቀን ፣ ሸክም ፣ አትሸከሙ ÷ በኢ
፳፪ የሩሳሌምም ፣ በሮች ፣ አታግቡ ÷ ከቤቶቻች
ሁም ፣ በሰንበት ፣ ቀን ፣ ሸክምን ፣ አታውጡ ÷
ሥራንም ፣ ሁሉ ፣ አትሥሩበት ፣ አባቶቻችሁ
ንም ፣ እንዳዘዝሁ ፣ የሰንበትን ፣ ቀን ፣ ቀድሱ ።
፳፫ እነርሱ ፣ ግን ፣ አልሰሙም ፣ ጆሮአቸውን ፣ አላ
ዘነበሉም ÷ እንዳይሰሙና ፣ እንዳይገሠጹም ፣
አንገታቸውን ፣ አደነደኑ ።
፳፬ አኔን ፣ ፈጽሞ ፣ ብትሰሙ ÷ ይላል ፣ እግዚአ
ብሔር ÷ በሰንበትም ፣ ቀን ፣ በዚህች ፣ ከተማ ፣
በሮች ፣ ሸክም ፣ ባታገቡ ÷ የሰንበትንም ፣ ቀን ፣
ብትቀድሱ ፣ ሥራንም ፣ ሁሉ ፣ በትሠሩበት ÷
፳፭ በዳሞት ፣ ዙፋን ፣ ላይ ፣ የሚቀመጡ ፣ ነገሥታ
ትና ፣ መሳፍንት ፣ በሰረገሎችና ፣ በፈረሶች ፣
ላይ ፣ እየተቀመጡ ፣ በዚህች ፣ ከተማ ፣ በሮች ፣
ይገባሉ ፣ እነርሱና ፣ መሳፍንቶቻቸው ፣ የይሁ
ዳም ፣ ሰዎች ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ የሚቀመጡ ፣
ይገባሉ ÷ ይህችም ፣ ከተማ ፣ ለዘላለም ፣ የሰው ፣
፳፮ መኖሪያ ፣ ትሆናለች ። የሚቃጠለውን ፣ መሥ
ዋዕትና ፣ ሌላ ፣ መሥዋዕትን ፣ የእህሉንም ፣ ቍር
በን ፣ ዕጣኑንም ፣ የምስጋናውንም ፣ መሥዋዕት ፣
ይዘው ፣ ከይሁዳ ፣ ከተሞች ፣ ከኢየሩሳሌምም ፣
ዙሪያ ፣ ከብንያምም ፣ አገር ፣ ከቈላውም ፣ ከደ
ጋውም ፣ ከደቡብም ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣
፳፯ ቤት ፣ ይመጣሉ ። ነገር ፣ ግን ፣ የሰንበትን ፣ ቀን ፣
እንድትቀድሱ ÷ በሰንበትም ፣ ቀን ፣ ሸክምን ፣
ተሸክማችሁ ፣ በኢየሩሳሌም ፣ በሮች ፣ እንዳት
ገቡ ፣ የነገርኋችሁን ፣ በትሰሙኝ ÷ በበሮችዋ ፣
ላይ ፣ እሳትን ፣ አነድዳለሁ ÷ የኢየሩሳሌምንም ፣
አዳራሾች ፣ ትበላለች ÷ አትጠፋም ።

ምዕራፍ ፣ ፲፰ ።

፩ ፪ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ወደ ፣ ኤርምያስ ፣
የመጣ ፣ ቃል ÷ እንዲህም ፣ አለው ፦ ተነሥ
ተህ ፣ ወደ ፣ ሸክላ ፣ ሠሪው ፣ ቤት ፣ ውረድ ÷
፫ በዚያም ፣ ቃሌን ፣ አሰማሃለሁ ። ወደ ፣ ሸክላ ፣
ሠሪው ፣ ቤትም ፣ ወረድሁ ÷ እነሆም ÷ ሥራ
ውን ፣ በመንኰራኵር ፣ ላይ ፣ ይሠራ ፣ ነበር ።
፬ ከጭቃም ፣ ይሠራው ፣ የነበረ ፣ ዕቃ ፣ በሸክላ ፣
ሠሪው ፣ እጅ ፣ ተበላሸ ÷ ሸክላ ፣ ሠሪውም ፣ እንደ
ወደደ ፣ መልሶ ፣ ሌላ ፣ ዕቃ ፣ አድርጎ ፣ ሠራው ።
፭ የእግዚአብሔርም ፣ ቃል ፣ ወደ ፣ እኔ ፣ እን
፮ ዲህ ፣ ሲል ፣ መጣ ። የእስራኤል ፣ ቤት ፣ ሆይ ÷
ይህ ፣ ሸክላ ፣ ሠሪ ፣ እንደሚሠራ ፣ በውኑ ፣ እኔ ፣
በእናንተ ፣ ዘንድ ፣ መሥራት ፣ አይቻለኝምን ?
እነሆ ÷ ጭቃው ፣ በሸክላ ፣ ሠሪ ፣ እጅ ፣ እንዳለ ÷
፯ እንዲሁ ፣ እናንተ ፣ በእኔ ፣ እጅ ፣ አላችሁ ። ስለ
ሕዝብ ፣ ስለ ፣ መንግሥትም ፣ እነቅል ፣ አፈር
ስም ፣ አጠፋም ፣ ዘንድ ፣ በተናገርሁ ፣ ጊዜ ÷
፰ ይህ ፣ ስለ ፣ እርሱ ፣ የተናገርሁበት ፣ ሕዝብ ፣ ከክ
ፋቱ ፣ ቢመለስ ÷ እኔ ፣ አደርግበት ፣ ዘንድ ፣ ካሰብ
፱ ሁት ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ እጸጸታለሁ ። ስለ ፣ ሕዝብም ፣
ስለ ፣ መንግሥትም ፣ እሠራውና ፣ እተክለው ፣
ዘንድ ፣ በተናገርሁ ፣ ጊዜ ÷ በፊቴ ፣ ክፉን ፣ ነገር ፣ ፲
ቢያደርግ ፣ ቃሌንም ፣ በይሰማ ÷ እኔ ፣ አደርግ
ለት ፣ ዘንድ ፣ ስለ ፣ ተናገርሁት ፣ መልካም ፣ ነገር ፣
እጸጸታለሁ ። አሁን ፣ እንግዲህ ፣ ለይሁዳ ፣ ፲፩
ሰዎችና ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ለሚቀመጡ ፦ — እግ
ዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ — እነሆ ÷ ክፉ ፣
ነገር ፣ እፈጥርባችኋለሁ ÷ አሳብንም ፣ አስብባች
ኋለሁ ። አሁንም ፣ ሁላችሁ ፣ ከክፉ ፣ መንገዳ
ችሁ ፣ ተመለሱ ÷ መንገዳችሁንና ፣ ሥራችሁ
ንም ፣ አቅኑ ፣ ብለህ ፣ ተናገራቸው ። እነርሱ ፣ ፲፪
ግን ፦ — እንጨክናለን ፣ አሳባችንን ፣ ተከትለን ፣
እንሄዳለን ፣ ሁላችንም ፣ እንደ ፣ ክፉው ፣ ልባ
ችን ፣ እልከኝነት ፣ እናደርጋለን ፣ አሉ ።
፲፫ ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ —
በአሕዛብ ፣ መካከል ፦ — እንዲህ ፣ ያለ ፣ ነገር ፣ ማን ፣
ሰምቶአል ? ብላችሁ ፣ ጠይቁ ። የእስራኤል ፣
ድንግል ፣ በጣም ፣ የሚያስደነግጠውን ፣ ነገር ፣
አድርጋለች ። በውኑ ፣ የሊባኖስ ፣ በረዶ ፣ የም ፲፬
ድረ ፣ በዳውን ፣ ድንጋይ ፣ ይተዋልን ? ወይስ ፣
ከሩቅ ፣ የምትመጣው ፣ ቀዝቃዛይቱ ፣ ፈሳሽ ፣
ውኃ ፣ ትደርቃለችን ? ሕዝቤ ፣ ግን ፣ ረስተው
ኛል ፣ ለከንቱ ፣ ነገርም ፣ ዐጥነዋል ፣ ከመንገዱም ፣
ተሰናክለዋል ፣ ከቀድሞውም ፣ ጕዳና ፣ ርቀው ፣
ወዳልተሠራው ፣ ወደ ፣ ጠማማው ፣ መንገድ ፣
ፈቀቅ ፣ ብለዋል ። ምድራቸውን ፣ ለመደነቂ ፲፮
ያና ፣ ለዘላለም ፣ ማፍዋጫ ፣ አድርገዋል ፣ የሚ
ያልፍበት ፣ ሁሉ ፣ ይደነቃል ፥ ራሱንም ፣ ያነቃ
ንቃል ። በጠላት ፣ ፊት ፣ እንደ ፣ ምሥራቅ ፣ ፲፯
ነፋስ ፣ እበትናቸዋለሁ ÷ በጥፋታቸውም ፣ ቀን ፣
ጀርባዬን ፣ እንጂ ፣ ፊቴን ፣ አላሳያቸውም ።
፲፰ እነርሱም ፦ — ሕግ ፣ ከካህን ÷ ምክርም ፣ ከጠ
ቢብ ÷ ቃልም ፣ ከነቢይ ፣ አይጠፋምና ፣ ኑ ÷
በኤርምያስ ፣ ላይ ፣ አሳብን ፣ እናስብ ። ኑ ÷ በም
ላስ ፣ እንምታው ÷ ቃሉንም ፣ ሁሉ ፣ አናድ
ምጥ ፣ አሉ ።
፲፱ አቤቱ ÷ አድምጠኝ ÷ የክርክራንም ፣ ቃል ፣
ስማ ። ለነፍሴ ፣ ጕድጓድ ፣ ቂፍረዋልና ፣ በውኑ ፣ ፳
በመልካም ፣ ፋንታ ፣ ክፉ ፣ ይመለሳልን ? ስለ
እነርሱ ፣ በመልካም ፣ እናገር ፣ ዘንድ ፣ ቍጣህ
ንም ፣ ከእነርሱ ፣ እመልስ ፣ ዘንድ ፣ በፊትህ ፣
እንደ ፣ ቆምሁ ፣ አስብ ። ስለዚህ ፣ ልጆቻቸውን ፣ ፳፩
ለራብ ፣ ስጥ ፣ ለሰይፍም ፣ እጅ ፣ አሳልፈህ ፣ ስጣ
ቸው ÷ ሚስቶቻቸውም ፣ የወላጅ ፣ መካንና ፣
መበለቶች ፣ ይሁኑ ÷ ወንዶቻቸውም ፣ በሞት ፣
ይሞቱ ÷ ጕልማሶቻቸውም ፣ በሰልፍ ፣ ጊዜ ፣
በሰይፍ ፣ ይመቱ ። ሊይዙኝ ፣ ጕድጓድ ፣ ቆፍረ ፳፪
ዋልና ÷ ለእግሮቼም ፣ ወጥመድ ፣ ሸሽገዋልና ፣
ድንገት ፣ በላያቸው ፣ ጭፍራ ፣ በመጣህ ፣ ጊዜ ፣
ከቤታቸው ፣ ጩኸት ፣ ይሰማ ። አንተ ፣ ግን ÷ ፳፫
አቤቱ ÷ ይገድሉኝ ፣ ዘንድ ፣ በላዬ ፣ የመከሩ
ትን ፣ ምክር ፣ ሁሉ ፣ ታውቃለህ ፣ በደላቸውን ፣
ይቅር ፣ አትበል ፣ ኃጢአታቸውንም ፣ ከፊትህ ፣
አትደምስስ ፣ በፊትህም ፣ ይውደቁ ÷ በቍጣህ ፣
ጊዜ ፣ እንዲሁ ፣ አድርግባቸው ።

ምዕራፍ ፣ ፲፱ ።

፩ እግዚአብሔርም ፣ እንዲህ ፣ አለኝ ፦ — ሂድ ÷
ከሸክላ ፣ ሠሪ ፣ ገምበ ፣ ግዛ ÷ ከሕዝቡም ፣ ሽማ
ግሌዎችና ፣ ከካህናት ፣ ሽማግሌዎች ፣ ከአንተ ፣
፪ ጋር ፣ ውሰድ ፣ በክርሲት ፣ በር ፣ መግቢያ ፣ አጠ
ገብ ፣ ወዳለው ፣ ወደ ፣ ሄኖም ፣ ልጅ ፣ ሸለቆ ፣
ሂድ ÷ በዚያም ፣ የምነግርህን ፣ ቃል ፣ ተናገር ÷
፫ እንዲህም ፣ በል ፦ — የይሁዳ ፣ ነገሥታትና ፣ በኢ
የሩሳሌም ፣ የምትኖሩ ፣ ሆይ ÷ የእግዚአብሔ
ርን ፣ ቃል ፣ ስሙ ፣ የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠ
ራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ —
የሰማውን ፣ ሰው ፣ ጆሮ ፣ ጭው ፣ የሚያደርግ ፣
ክፉ ፣ ነገር ÷ እነሆ ÷ በዚህ ፣ ስፍራ ፣ አመጣለሁ ።
፬ ትተውኛልና ÷ ይህንም ፣ ስፍራ ፣ እንግዳ ፣ አድ
ርገውታልና ÷ እነርሱና ፣ አባቶቻቸውም ፣ ለማ
ያውቋቸው ፣ ለሌሎች ፣ አማልክት ፣ ዐጥነዋ
ልና ÷ የይሁዳም ፣ ነገሥታት ፣ ይህን ፣ ስፍራ ፣
፭ በንጹሕ ፣ ደም ፣ ሞልተዋልና ÷ እኔም ፣ ያላዘ
ዝሁትን ፣ ያልተናገርሁትንም ፣ ወደ ፣ ልቤም ፣
ያልገባውን ÷ የሚቃጠለውን ፣ መሥዋዕት ፣
አድርገው ፣ ለበኣል ፣ ልጆቻቸውን ፣ በእሳት ፣
ያቃጥሉ ፣ ዘንድ ፣ የበኣልን ፣ የከረብታውን ፣
መስገጃዎች ፣ ሠርተዋልና ፣ ስለዚህ ÷ እነሆ ÷
፮ ይህ ፣ ስፍራ ፣ የእርድ ፣ ሸለቆ ፣ ይባላል ፣ እንጂ ፣
ቶፌት ፣ ወይም ፣ የሄኖም ፣ ልጅ ፣ ሸለቆ ፣ ዳግ
መኛ ፣ የማይባልበት ፣ ዘመን ፣ ይመጣል ÷ ይላል ፣
፯ እግዚአብሔር ። በዚህም ፣ ስፍራ ፣ የይሁዳንና ፣
የኢየሩሳሌምን ፣ ምክር ፣ አፈርሰለሁ ÷ በጠላቶ
ቻቸውም ፣ ፊት ፣ በሰይፍና ፣ ነፍሳቸውን ፣ በሚ
ሹት ፣ እጅ ፣ እጥላቸዋለሁ ÷ ሬሳቸውንም ፣ ለሰ
ማይ ፣ ወፎችና ፣ ለምድር ፣ አራዊት ፣ መብል ፣
፰ አድርጌ ፣ እሰጣለሁ ። ይህችንም ፣ ከተማ ፣ ለመ ፳
ደነቂያና ፣ ለማፍዋጫ ፣ አደርጋታለሁ ፣ የሚያል
ፍበትም ፣ ሁሉ ፣ ስለ ፣ ተደረገበት ፣ መቅሠፍት ፣
ሁሉ ፣ ይደነቃል ፣ ከንፈሩንም ፣ ይመጥጣል ።
፱ የወንዶችና ፣ የሴቶች ፣ ልጆቻቸውንም ፣ ሥጋ ፣
አበላቸዋለሁ ÷ ሁሉም ፣ ጠላቶቻቸውና ፣ ነፍሳ
ቸውን ፣ የሚሹት ፣ በሚያስጨንቃቸው ፣ ጭን
ቀትና ፣ መከበብ ፣ የባልንጀሮቻቸውን ፣ ሥጋ ፣
ይበላሉ ።
፲ ገምቦውንም ፣ ከእንተ ፣ ጋር ፣ በሚሄዱ ፣ ሰዎች ፣
፲፩ ፊት ፣ ትሰብራለህ ÷ እንዲህም ፣ ትላቸዋለህ ፣ —
የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣
ይላል ፦ — የሸክላ ፣ ሠሪው ፣ ዕቃ ፣ እንደሚሰባ
በር ፣ ደግሞም ፣ ይጠገን ፣ ዘንድ ፣ እንደማይቻል ÷
እንዲሁ ፣ ይህን ፣ ሕዝብና ፣ ይህችን ፣ ከተማ ፣ እሰ
ብራለሁ ፣ የሚቀብሩበትም ፣ ስፍራ ፣ ሌላ ፣ የለ
ምና ፣ በቶፌት ፣ ይቀብራሉ ። እንዲሁ ፣ በዚህ ፣
ስፍራና ፣ በሚኖሩበት ፣ ላይ ፣ እደርጋለሁ ፣
፲፪ ይላል ፣ እግዚአብሔር ÷ ይህችንም ፣ ከተማ ፣
እንደ ፣ ቶፌት ፣ አደርጋለሁ ። የረከሱትም ፣ የኢ
የሩሳሌም ፣ ቤቶችና ፣ የይሁዳ ፣ ነገሥታት ፣
ቤቶች ፣ እንዲያ ፣ በሰገነታቸው ፣ ላይ ፣ ለሰማይ
፲፫ ሠራዊት ፣ ሁሉ ፣ ያጠኑባቸው ፣ ለሌሎችም ፣
አማልክት ፣ የመጠጥን ፣ ቍርባን ፣ ያፈሰሱባ
ቸው ፣ ቤቶች ፣ ሁሉ ÷ እንደ ፣ ቶፌት ፣ ስፍራ ፣
ይሆናሉ ።
፲፬ ኤርምያስም ፣ እግዚአብሔር ፣ ትንቢት ፣ ሊና
ገር ፣ ወደዚያ ፣ ልኩት ፣ ከነበረው ፣ ስፍራ ፣ ከቶ
ፌት ፣ መጣ ÷ በእግዚአብሔርም ፣ ቤት ፣ አደባ
ባይ ፣ ቆሞ ፣ ለሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ — የእስራኤል ፣ ፲፭
አምላክ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ —
ቃሌን ፣ እንዳይሰሙ ፣ እንገታቸውን ፣ አደንድ
ነዋልና ፣ እነሆ ÷ በዚህች ፣ ከተማና ፣ በመንደሮ
ችዋ ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣ የተናገርሁባትን ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣
ሁሉ ፣ አመጣለሁ ።

ምዕራፍ ፣ ፳ ።

፩ በእግዚአብሔርም ፣ ቤት ፣ የተሾመው ፣ አለቃ ፣
የካህኑ ፣ የኢሜር ፣ ልጅ ፣ ጳስኮር ፣ ኤርምያስ ፣
በዚህ ፣ ነገር ፣ ትንቢት ፣ ሲናገር ፣ ሰማ ። ጳስኮ ፪
ርም ፣ ነቢዩን ፣ ኤርምያስን ፣ መታው ÷ በእግ
ዚአብሔርም ፣ ቤት ፣ በነበረው ፣ በላይኛው ፣
በብንያም ፣ በር ፣ ባለው ፣ በእግር ፣ ግንድ ፣
፫ ውስጥ ፣ አኖረው ። በነጋውም ፣ ጳስኮር ፣ ኤር
ምያስን ፣ ከግንድ ፣ ውስጥ ፣ አወጣው ። ኤርምያ
ስም ፣ እንዲህ ፣ አለው ፦ — እግዚአብሔር ፣ ስም
ህን ፦ — ማጎርሚሳቢብ ፣ እንጂ ፣ ጳስኮር ፣ ብሎ ፣
፬ አይጠራህም ። እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላ
ልና ፦ — እነሆ ÷ ለራስህና ፣ ለወዳጆችህ ፣ ሁሉ ፣
ፍርሃት ፣ አደርግሃለሁ ፣ እነርሱም ፣ በጠላቶቻ
ቸው ፣ ሰይፍ ፣ ይወድቃሉ ፣ ዓይኖችህም ፣
ያያሉ ፣ ይሁዳንም ፣ ሁሉ ፣ በባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣
እጅ ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣለሁ ÷ እርሱም ፣ ወደ ፣
ባቢሎን ፣ ያፈልሳቸዋል ፣ በሰይፍም ፣ ይገድላ
ቸዋል ። የዚህችንም ፣ ከተማ ፣ ባለጠግነት ፣ ፭
ሁሉ ፣ ጥሪትዋንም ፣ ሁሉ ፣ ክብርዋንም ፣ ሁሉ ፣
የይሁዳንም ፣ ነገሥታት ፣ መዝገብ ፣ ሁሉ ፣ በጠ
ላቶቻቸው ፣ እጅ ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣለሁ ÷ እነር
ሱም ፣ ይበዘብዙአቸዋል ፣ ይዘውም ፣ ወደ ፣ ባቢ
ሎን ፣ ያፈልሱአቸዋል ። አንተም ÷ ጳስኮር ፣ ፮
ሆይ ÷ በቤትህም ፣ የሚኖሩት ፣ ሁሉ ፣ ተማርከ
ችሁ ፣ ትሄዳላችሁ ፣ አንተም ፣ በሐሰትም ፣ ትን
ቢት ፣ የተናገርህላቸው ፣ ወዳጆችህ ፣ ሁሉ ፣
ወደ ፣ ባቢሎን ፣ ትገባላችሁ ፡ በዚያም ፣ ትሞ
ታላችሁ ÷ በዚያም ፣ ትቀበሯላችሁ ።
፯ አቤቱ ÷ አታለልኸኝ ፣ እኔም ፣ ተታለልሁ ÷
ከእኔም ፣ በረታህ ፣ አሸነፍህም ፣ ቀኑን ፣ ሁሉ ፣
መሳቂያ ፣ ሆኛለሁ ÷ ሁሉም ፣ ያላግጡብኛል ።
፰ በተናገርሁ ፡ ቊጥር ፣ እጮኻለሁ ፣ ግፍና ፣ ጥፋት ፣
ብዬ ፣ እጮኻለሁ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ቃል ፣ ቀኑን ፣
ሁሉ ፣ ስድብና ፣ ዋዛ ፣ ሆኖብኛልና ። እኔም ፦ — ፱
የእግዚአብሔርን ፣ ስም ፣ አላነሣም ፣ ከእንግ
ዲህ ፣ ወዲህም ፣ በስሙ ፣ አልናገርም ፣ ብል ÷
በአጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፣ እንደ ፣ ገባ ፣ እንደሚነድድ ፣
እሳት ፣ ያለ ፣ በልቤ ፣ ሆነብኝ ፣ ደከምሁ ÷ መሸ
ከምም ፣ አልቻልሁም ። የብዙ ፣ ሰዎችን ፣ ስድብ ፣ ፲

ሰምቻለሁ ÷ ማስፈራራትም ፡ ከብበኛል ። መው
ደቁን ፡ የሚጠብቁ ፡ የሰላሚ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡—
ምናልባት ፡ ይታለል ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ እናሸንፈ
ውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ እርሱንም ፡ እንበቀል ፡
እንደ ፡ ሆነ ፥ ክሰሱት ፡ እኛም ፡ እንከስስዋለን ፡
ይላሉ ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኃያልና ፡
እንደ ፡ ጨካኝ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡
አሳዳጆቼ ፡ ይሰናከላሉ ፡ አያሸንፉም ፡ እጅ፡ሀና
ወንላቸውምና ፡ በጽኑ ፡ እፍረት ፡ ያፍራሉ ÷
ለዘላለምም ፡ በማይረሳ ፡ ጕስቁልና ፡ ይጐሰቍ
ላሉ ። አቤቱ ፥ ጻድቅን ፡ የምትመረምር ፡ ኵላ
ሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትመለከት ፡ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ ሆይ ÷ ክርክሬን ፡ ገልጬልሃለሁና ፡ በቀ
ልህን ፡ በላያቸው ፡ ለይ ። ለእግዚአብሔር ፡
ዘምሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመስግኑ ፡ የችግ
ረኛውን ፡ ነፍስ ፡ ከክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ እጅ ፡
አድኖአልና ።

የተወለድሁበት ፡ ቀን ፡ የተረገመች ፡ ትሁን ፡
እናቴ ፡ እኔን ፡ የወለደችበት ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡
አትሁን ። ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶልሃል ፡ ብለ፡
ለአባቴ ፡ የምሥራች ፡ ነግሮ ፡ ደስ ፡ ያሰኘው ፡
ሰው ፡ የተረገመ ፡ ይሁን ። ያም ፡ ሰው ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሳይጸጸት ፡ እንደ ፡ ገለጠባቸው ፡ ከተ
ሞች ፡ ይሁን ÷ በማለዳም ፡ ልቅሶን ፡ በቀት
ርም ፡ ጩኸትን ፡ ይስማ ፡ እናቴ ፡ መቃብር ፡
ትሆነኝ ፡ ዘንድ ፡ ማኅፀንዋም ፡ ዘወትር ፡ ይዘኝ ፡
ያቆይ ፡ ዘንድ ፡ በማኅፀን ፡ ውስጥ ፡ አልገደለኝ
ምና ። ድከምንና ፡ ጣርን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ዘመ
ኔም ፡ በእፍረት ፡ ታልቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡
ከማኅፀን ፡ ወጣሁ ?

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡
የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡
ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡— የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡ
ከደነፆር ፡ ይወጋናልና ፡ ስለ ፡ እኛ ÷ እባክህ ÷
እግዚአብሔርን ፡ ጠይቅ ፡ ከእኛም ፡ ይመለስ ፡
ዘንድ ፡ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
እንደ ፡ ተአምራቱ ፡ ሁሉ ፡ ያደርግ ፡ ይሆናል ፡
ብሎ ፡ የመልክያን ፡ ልጅ ፡ ጳስኮርንና ፡ ካህኑን ፡
የመዕሤያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስን ፡ ወደ ፡ ኤርም
ያስ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ሴዴቅያ
ስን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ የባ
ቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ በቅጥርም ፡ ውጭ ፡ የከበቡ
አችሁን ፡ ከለዳውያንን ፡ የምትወጉበትን ፡ በእ
ጃችሁ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ሠራችሁን ፡ እመልሰዋ
ለሁ ÷ እነዚያንም ፡ ወደዚህች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡
እሰበስባቸዋለሁ ። እኔም ፡ በተዘረጋች ፡ እጅና ፡
በብርቱ ፡ ክንድ ÷ በቍጣና ፡ በመዓት ፡ በታላ
ቅም ፡ መቅሠፍት ፡ እወጋችኋለሁ ። በዚህችም ፡
ከተማ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሁሉ ፡ ሰዎችንና ፡ እንስ
ሶችን ፡ እመታለሁ ÷ በጽኑም ፡ ቸነፈር ፡ ይሞ
ታሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡
የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከቸነፈርና ፡
ከሰይፍ ፡ ከራብም ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ የቀሩት
ንም ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ሕዝቡን ፡ በባቢሎን ፡
ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ እጅ ፡ በጠላቶቻቸ
ውና ፡ ነፍሳቸውንም ፡ በሚሹት ፡ እጅ ፡ አሳ
ልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ እርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡
ይመታቸዋል ፡ እያዝንላቸውም ÷ አይራራላቸ
ውም ÷ አያምራቸውም ።

ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ በል ፡— እግዚአ
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ በፊታችሁ ፡
የሕይወትን ፡ መንገድና ፡ የሞትን ፡ መንገድ ፡
አድርጌአለሁ ። በዚህች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ዘገይ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞ
ታል ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ከበቡአችሁ ፡ ወደ ፡ ከለ
ዳውያን ፡ የሚገባ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ÷
ነፍሱም ፡ ምርኮ ፡ ትሆንለታለች ። ለመልካም ፡
ሳይሆን ፡ ለክፉ ፡ ፊቴን ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡
አድርጌአለሁና ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ትሰ
ጣለች ፡ እርሱም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላታል ።

የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔ
ርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ። የዳሞት ፡ ቤት ፡ ሆይ ÷ እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ስለ ፡ ሥራችሁ ፡
ክፋት ፡ ቍጣዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እንዳይወጣና ፡
ማንም ፡ ሳያጠፋው ፡ እንዳይነድድ ÷ በማለዳ ፡
ፍርድን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ከእስጨ
ናቂው ፡ እጅ ፡ አድኑ ። እነሆ ÷ በሸለቆው ፡
ውስጥ ፡ በሜዳ ፡ ላይም ፡ በለው ፡ አምባ ፡ የም
ትቀመጡ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ በእንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡
እናንተም ፡— በእኛ ፡ ላይ ፡ የሚወርድ ፡ ወይም ፡
ወደ ፡ መሸሪያችን ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ? የም
ትሉ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ እንደ ፡
ሥራችሁም ፡ ፍሬ ፡ እቀጣችኋለሁ ፡ በዱርዋም ፡
ውስጥ ፡ እሳትን ፡ እነደ ፡ ዳስሁ ÷ በዙሪያዋም ፡
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ይበላል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ወደ ፡ ይሁዳ ፡
ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውረድ ፡ በዚያም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡
ተናገር ÷ እንዲህም ፡ በል ፡— በዳዊት ፡ ዙፋን ፡
የምትቀመጥ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ አንተና ፡
ባሪያዎችህ ፡ በእነዚህም ፡ በሮች ፡ የሚገባ ፡ ሕዝ
ብህ ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ። እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ፍርድንና ፡ ጽድ
ቅን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ከእስፈሩ
ቂው ፡ እጅ ፡ አድኑ ፡ መጻተኛውንና ፡ ድሀ ፡ አደ
ጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ አትበድሉ ÷ አታምፁብ
ቸውም ÷ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ አታ
ፍስሱ ። ይህንንም ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ÷ በዳ
ዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡ ፡ ነገሥታት ፡ በሰረ
ገሎችና ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ÷ በዚህ ፡
ቤት ፡ በሮች ፡ ይገባሉ ፡ እርሱም ፡ ባሪያዎቹም ፡
ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ይገባሉ ። ነገር ፡ ግን ፡
ይህን ፡ ቃል ፡ በትሰሙ ÷ ይህ ፡ ቤት ፡ ወና ፡ እን
ዲሆን ፡ በራሴ ፡ ምያለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ። እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— አንተ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡
እንደ ፡ ገለዓድና ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ራስ ፡ ነህ ÷
ነገር ፡ ግን ፡ በእርግጥ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማንም ፡
የማይቀመጥባቸውም ፡ ከተሞች ፡ አደርግሃ
ለሁ ። መማረያም ፡ የሚያዘጋጉ ፡ አጥፊዎች ፡
በአንተ ፡ ላይ ፡ እዘጋጃለሁ ÷ የተመረጡትንም ፡
የዝግባ ፡ ዛፎችህን ፡ ይቁርጣሉ ÷ በእሳትም ፡
ውስጥ ፡ ይጥሉአቸዋል ። ብዙ ፡ አሕዛብም ፡
በዚህች ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ ያልፋሉ ÷ ሁሉም ፡
ባልንጀሮቻቸውን ፡— እግዚአብሔር ፡ በዚህች ፡
ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ?
ይላሉ ። እነርሱም ፡— የእምላክቸውን ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ትተው ፡ ለሌሎች ፡
አማልክት ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፡ ስላመለኩአቸውም ፡
ነዋ ፡ ብለው ፡ ይመልሳሉ ።

ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለስምና ÷ የተወለ
ደበትንም ፡ አገር ፡ አያይምና ፡ ለሚወጣ ፡ እጅግ ፡
አልቅሱ ፡ እንጂ ፡ ለሞተ ፡ አታልቅሱ ፡ አትዘኑ
ለትም ። በአባቱ ፡ በኢዮስያስ ፡ ፋንታ ፡ ስለ ፡
ነገሠው ፡ ከዚህም ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ወጣው ፡ ስለ ፡
ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡
ሰሎም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡—
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አይመለስም ÷ በተማረ
ከበት ፡ አገር ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ፡ ይህችንም ፡
አገር ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያይም ።

ቤቱን ፡ በግፍ ፡ ሰገነቱንም ፡ በኀሰብ ፡ ለሚ
ሠራ ÷ ባልንጀራውንም ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡
ለሚያሠራ ÷ ዋጋውንም ፡ ለማይሰጠው ፡ ለራሴ ፡
ሰፊ ፡ ቤት ፡ ትልቅም ፡ ሰገነት ፡ እሠራለሁ ፡ ለሚል ÷
መስኮትንም ፡ ለሚያወጣ ÷ በገሣባም ፡ ሥራ ፡
ለሚያስጌጥ ÷ በቀይ ፡ ቀለምም ፡ ለሚቀባው ፡
ወዮለት ! በገሣባ ፡ እንጨት ፡ ስለምትወዳደር ፡
በውኑ ፡ ትነግሣለህን ? በውኑ ፡ አባትህ ፡ አይበ
ላምና ፡ አይጠጣም ፡ ነበርን ? ፍርድንና ፡ ጽድቅ
ንስ ፡ አያደርግም ፡ ነበርን ? በዚያም ፡ ጊዜ ፡ መል
ካም ፡ ሆኖለት ፡ ነበር ። የድሀውንና ፡ የችግረኛ
ውን ፡ ፍርድ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ÷ በዚያም ፡ ጊዜ ፡
መልካም ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ይህ ፡ እኔን ፡ ማወቅ ፡
አይደለምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ዓይንህና ፡
ልብህ ፡ ግን ፡ ለስስት ፡ ንጹሕ ፡ ደምንም ፡ ለማፍ
ሰስ ፡ ዓመፅንና ፡ ግፍንም ፡ ለመሥራት ፡ ብቻ ፡
ነው ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡
ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ኢዮአ
ቄም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ወንድሚ ፡ ሆይ ÷ ወዮ !
እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ፡ ወይም ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷
ወዮ ! እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ። እህያም ፡ እን
ደሚቀበር ፡ ይቀበራል ÷ ከኢየሩሳሌምም ፡ በር ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጐትቶ ፡ ይጣላል ።

ውሽሞችሽ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍተዋልና ፡ ወደ ፡
ሊባኖስ ፡ ውጥተሽ ፡ ጩኺ ፡ በባሳንን ፡ ላይ ፡
ድምፅሽን ፡ አንሺ ፡ በዓባሪምም ፡ ውስጥ ፡
ሀንሽ ፡ ጩኺ ። በደኅንነትሽ ፡ ጊዜ ፡ ተና
ገርሁሽ ፡ አንቺም ፡— አልሰማም ፡ አልሽ ።
ከሕፃንነትሽ ፡ ጀምሮ ፡ ቃሌን ፡ አለመስማ
ትሽ ፡ መንገድሽ ፡ ነው ። በግ ፡ ጠባቂዎች ፡
ሽን ፡ ሁሉ ፡ ነፋስ ፡ ይጠብቃቸዋል ÷ ውሽ
ሞችሽም ፡ ተማርከው ፡ ይሄዳሉ ፡ በዚያን ፡
ጊዜም ፡ ስለ ፡ ክፋትሽ ፡ ሁሉ ፡ ታፍሪያለሽ ፡ ትጐ
ሳቄይማለሽ ። አንቺ ፡ በሊባኖስ ፡ የምትቀ
መጪ ÷ በዝግባ ፡ ዛፍም ፡ ውስጥ ፡ ጎጆሽን ፡
የምትሠሪ ፡ ሆይ ÷ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡
ሕማም ፡ በያዘሽ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ታኒሪያለሽ !

እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢ
ዮአቄም ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያን ፡ የቀኝ ፡ እጇ ፡ ማኅ
ተም ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እንኳ ÷ ከዚያ ፡ እነቅልህ ፡
ነበር ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍስህንም ፡
ለሚሹት ፡ ለምትፈራቸውም ፡ እጅ ፡ ለባቢሎ፡
ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡
እሰጥሃለሁ ። እንትንም ፡ የወለደችህንም ፡ እና
ትህን ፡ ወዳልተወለዳችሁባት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡
እጥላችኋለሁ ÷ በዚያም ፡ ትሞታላችሁ ። ይመ
ለሱበትም ፡ ዘንድ ፡ ነፍሳቸው ፡ ወደምትመኟት ፡
ወደዚያች ፡ ምድር ፡ አይመለሱም ። በውኑ ፡
ይህ ፡ ሰው ፡ ኢኮንያን ፡ የተናቀና ፡ የተሰበረ ፡
የሸከላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ እርሱ ፡ ለእን
ዳች ፡ የማይረባ ፡ የሸከላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ? እር
ሱና ፡ ዘሩስ ፡ በማያውቋት ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ምን ፡
ተጥለው ፡ ወደቁ ? ምድር ፡ ሆይ ፡ ምድር ፡
ሆይ ÷ ምድር ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሚ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ከዚህ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ የሚከናወን ፡ በዳዊትም ፡
ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ በይሁዳም ፡ የሚነ
ግሥ ፡ እንግዲህ ፡ አይገኝምና ፡— መከን ፡ በዘመ
ኑም ፡ የማይከናወንለት ፡ ሰው ፡ ብላችሁ ፡ ጻፉ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

የማሰማርያዬን ፡ በጎች ፡ ለሚያጠፉና ፡ ለሚ
በትኑ ፡ እረኞች ፡ ወዮላቸው ! ይላል ፡ እግዚአ
ብሔር ። ስለዚህ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሕዝቤን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ እረኞች ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— በጎቼን ፡ በትኖችኋል ፡ አባ
ርራችኋቸውማል ፡ አልጐበኛችኋቸውምም ፡
እነሆ ÷ የሥራችሁን ፡ ክፋት ፡ እጐበኝባችኋ
ለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። የመንጋዬም ፡
ቀሪታ ፡ ከባረርኋትባቸው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
በረታቸው ፡ ሰብስቤ ፡ እመልሳቸዋለሁ ፡ እነር
ሱም ፡ ያፈራሉ ፡ ይበዙማል ። የሚጠብቋቸ
ውን ፡ እረኞች ፡ አስነሣላቸዋለሁ ÷ ዳግመኛም ፡
አይፈሩምና ፡ አይደነግጡም ÷ ከእነርሱም ፡
አንድ ፡ አይጐድልም ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

እነሆ ÷ ለዳዊት ፡ ጻድቅ ፡ ቍጥቋጥ ፡ የማስ
ነሣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፡ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ÷ እርሱም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ÷
ይከናወንለታልም ፡ በምድርም ፡ ፍርድንና ፡
ጽድቅን ፡ ያደርጋል ። በዘመኑም ፡ ይሁዳ ፡ ይድ
ናል ፡ እስራኤልም ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጣል ÷

የሚጠራበትም ፡ ስም ፡— እግዚአብሔር ፡ ድድ
ቃችን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።
፯ ስለዚህ ÷ እነሆ ፡— የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔ
ርን ፤ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመ
፰ ጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፡—
የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ዘር ፡ ከሰሜን ፡ አገርና ፡ ካሰ
ደድኋቸውም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ያወጣና ፡ የመራ ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ይባላል ፡ በምድራች
ውም ፡ ይቀመጣሉ ።
፱ ስለ ፡ ነቢያት ፡ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተሰብሮአል ፡
አጥንቶቼም ፡ ሁሉ ፡ ታውከዋል ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ የተነሣ ፡ ከቅዱስ ፡ ቃሉም ፡ የተነሣ ፡ የወ
ይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳሸነፈው ፡ እንደ ፡ ሰካራም ፡
፲ ሰው ፡ ሆኛለሁ ። ምድር ፡ ከአመንዝሮች ፡ ተሞ
ልታለችና ÷ ከመርገምም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡
አልቅሳለች ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ ማሰማርያ ፡ ደርቆ
አል ፡ አካሄዳቸው ፡ ክፉ ፡ ነው ÷ ብርታታቸ
፲፩ ውም ፡ ቅን ፡ አይደለም ። ነቢዩና ፡ ካህኑም ፡
ረክሰዋልና ÷ በቤቴም ፡ ውስጥ ፡ ክፋታቸውን ፡
፲፪ አግኝቻለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፡
መንገዳቸው ፡ በጨለማ ፡ እንዳለች ፡ እንደ ፡
ድጥ ፡ ስፍራ ፡ ትሆንባቸዋለች ÷ እነርሱም ፡
ፍግምግም ፡ ብለው ፡ ይወድቁበታል ፤ እኔም ፡
በምጐበኛቸው ፡ ዓመት ፡ ክፋ ፡ ነገርን ፡ እመጣ
ባቸዋለሁና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፲፫ በሰማርያ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ስንፍናን ፡ አይቻ
ለሁ ፤ በበኣል ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ÷ ሕዝ
፲፬ ቤንም ፡ እስራኤል ፡ ያስቱ ፡ ነበር ። በኢየሩሳ
ሌምም ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ የሚያስደነግጥን ፡ ነገር ፡
አይቻለሁ ፤ ያመነዝራሉ ፡ በሐሰትም ፡ ይሄዳሉ ፡
ማንም ፡ ከክፋቱ ፡ እንዳይመለስ ፡ የክፉ ፡ አድ
ራጊዎችን ፡ እጅ ፡ ያበረታሉ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡
ሰዶም ፡ የሚኖሩባትም ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ሆኑ
፲፭ ብኝ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— እነሆ ÷ ከኢየሩሳሌም ፡ ነቢያት ፡
ዘንድ ፡ ርኵሰት ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ
አልና ፡ እሬትን ፡ አበላቸዋለሁ ፡ የሐሞትንም ፡
ውኃ ፡ አጠጣቸዋለሁ ።
፲፮ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— ትንቢት ፡ የሚናገሩላችሁን ፡ የነቢያ
ትን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ፤ ከንቱነትን ፡ ያስተምሩ
አችኋል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ሳይሆን ፡
ከገዛ ፡ ልባቸው ፡ የወጣውን ፡ ራእይ ፡ ይናገራሉ ።
፲፯ ለሚንቁኝ ፡ ሁልጊዜ ፡— እግዚአብሔር ፡— ሰላም ፡ ይሆንላችኋል ፡ ብሎአል ፡ ይላሉ ፡
በልቡም ፡ እልከኝነት ፡ ለሚሄድ ፡ ሁሉ ፡— ክፉ ፡
፲፰ ነገር ፡ አያገኝችሁም ፡ ይላሉ ። ቃሉን ፡ ያደና ፡
ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡
የቆመ ፡ ማን ፡ ነውና ? ቃሉንስ ፡ ያደመጠ ፡ የሰ
ማስ ፡ ማን ፡ ነው ?
፲፱ እነሆ ÷ የእግዚአብሔር ፡ ሀውከ ፡ ነፋስ ÷ እር
ሱም ፡ ቍጣው ፡ ÷ የሚያገለባብጥ ፡ ሀውከ ፡
ነፋስ ፡ ወጥቶአል ፤ የዓመፀኞችን ፡ ራስ ፡ ይገለ
ባብጣል ። የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የልቡን ፡
፳ አሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመ
ለስም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ፈጽማችሁ ፡ ታስ
ተውሱታላችሁ ።
፳፩ እኔ ፡ ሳልልካቸው ፡ እነዚህ ፡
ነቢያት ፡ ሮጡ ፡ እኔም ፡ ሳልነግራቸው ፡ ትንቢ
፳፪ ትን ፡ ተናገሩ ። በምክሬ ፡ ግን ፡ ቢቆሙ ፡ ኖሮ ፡ ለሕዝቤ ፡ ቃሌን ፡ ባሰሙ ፡ ነበር ÷ ከክፋም ፡ መን
ገዳቸው ፡ ከሥራቸውም ፡ ክፋት ፡ በመለሱአ
ቸው ፡ ነበር ።
፳፫ እኔ ፡ የቅርብ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የሩቅ ፡
አምላክ ፡ አይደለሁም ። ሰው ፡ በስውር ፡ ቢሸ
፳፬ ሸግ ÷ እኔ ፡ አላየውምን ? ሰማይንና ፡ ምድር
ንስ ፡ የሞላሁ ፡ እኔ ፡ አይደለሁምን ? ይላል ፡
እግዚአብሔር ። አለምሁ ፡ አለምሁ ፡ እያሉ ፡
፳፭ በስሜ ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩትን ፡ የነቢያትን ፡
ነገር ፡ ሰምቻለሁ ። ትንቢትን ፡ በሐሰት ፡ በሚ
፳፮ ናገሩ ÷ የልባቸውንም ፡ ሽንገላ ፡ በሚናገሩ ፡
በነቢያት ፡ ልብ ፡ ይህ ፡ የሚሆነው ፡ እስከ ፡
መቼ ፡ ነው ? እነዚህ ፡ አባቶቻቸው ፡ ስለ ፡ በአል ፡
፳፯ ስሜን ፡ እንደ ፡ ረሱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ለባልንጀ
ራው ፡ በሚናገራት ፡ ሕልማቸው ፡ ሕዝቤ ፡
ስሜን ፡ ለማስረሳት ፡ ያስባሉ ። የሚያልም ፡
ነቢይ ፡ ሕልምን ፡ ይናገር ፤ ቃሌም ፡ ያለበት ፡
ቃሌን ፡ በእውነት ፡ ይናገር ። ገለባ ፡ ከስንዴ ፡
፳፰ ጋር ፡ ምን ፡ አለው ? በውኑ ፡ ቃሌ ፡ እንደ ፡
እሳት ÷ ድንጋዩንም ፡ እንደሚያደቅቅ ፡ መዶሻ ፡
፳፱ አይደለችምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለ
ዚህ ÷ እነሆ ÷ እያንዳንዱ ፡ ከባልንጀራው ፡
ዘንድ ፡ ቃሌን ፡ በሚሰርቁ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷
፴ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እነሆ ÷ ከምላሳቸው ፡
ትንቢትን ፡ እውጥተው ፡— እርሱ ፡ ይላል ፡
፴፩ በሚሉ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷ ይላል ፡ እግዚአ
ብሔር ። እነሆ ÷ ሐሰትን ፡ በሚያልሙ ፡ በሚ
፴፪ ናገሩም ፡ በሐሰታቸውና ፡ በድፍረታቸውም ፡
ሕዝቤን ፡ በሚያስቱ ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷
ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እኔም ፡ አልላክኋቸ
ውም ፡ አላዘዝኋቸውምም ፡ ለእነዚህም ፡ ሕዝብ ፡
በማናቸውም ፡ አይረቡአቸውም ÷ ይላል ፡ እግ
ዚአብሔር ።
፴፫ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብሎ
ቢጠይቅህ ፡ እንተ ፡— ሸክሙ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ÷
እጥላችሁማለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ትላ
፴፬ ቸዋለህ ። የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ የሚለ
ውን ፡ ነቢይንና ፡ ካህንን ፡ ሕዝብንም ፡ ያን ፡
፴፭ ሰውና ፡ ቤቱን ፡ እቀጣለሁ ። አንዱም ፡ አንዱ ፡
ለባልንጀራው ፡ እንዲህ ፡ አንዱም ፡ ለወንድሙ ፡
እንዲህ ፡ ይበል ፡— እግዚአብሔር ፡ የመለሰው ፡
ምንድር ፡ ነው ? እግዚአብሔርስ ፡ ምን ፡ ነገር ፡
፴፮ ተናገረ ? ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ቃሉ ፡ ሸክም ፡ ይሆን
በታልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብላችሁ ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትጥሩ ፡ የሠራዊትን ፡
ጌታ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕ
፴፯ ያውን ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ለመጣችኋልና ። ለነ

ቢያ ፡— እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ መለሰልህ ? እግ
ዚአብሔርስ ፡ የተናገረው ፡ ምንድር ፡ ነው ?
፴፰ ትላለህ ። ነገር ፡ ግን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡
ብትሉ ÷ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
እኔ ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ትበሉ ፡ ብዬ ፡
ልኬባችኋለሁና ÷ እናንተም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡—
፴፱ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብላችኋልና ፡ ስለዚህ ፡
እነሆ ÷ ፈጽሜ ፡ እረሳችኋለሁ ፡ እናንተንም ፡
ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችሁም ፡ የሰጠኋትን ፡
፵ ከተማ ፡ ከፊቴ ፡ እጥላለሁ ። የዘላለምንም ፡
ስድብ ፡ ከቶም ፡ ተረስቶ ፡ የማይጠፋውን ፡ የዘ
ላለምን ፡ እፍረት ፡ አመጣባችኋለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የይሁዳን ፡
ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንን ፡ የይ
ሁዳንም ፡ አለቆች ፡ ጠራቢዎችንና ፡ ብረተ ፡ ሠራ
ተኞችን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኮ ፡ ወደ ፡ ባቢ
ሎን ፡ ካፈለሰላቸው ፡ በኋላ ÷ እግዚአብሔር ፡ አሳ
፪ የኝ ÷ እነሆም ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡
ፊት ፡ ሁለት ፡ ቅርጫት ፡ በለስ ፡ ተቀምጠው ፡
፫ ነበር ። በአንደኛይቱ ፡ ቅርጫት ፡ አስቀድሞ ፡
እንደ ፡ ደረሰ ፡ በለስ ፡ የሚመስል ፡ እጅግ ፡ መል
ካም ፡ በለስ ፡ ነበረባት ፡ በሁለተኛይቱ ፡ ቅርጫት ፡
ከክፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡
፬ እጅግ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነበረባት ። እግዚአብሔ
፭ ርም ፡— ኤርምያስ ፡ ሆይ ÷ የምታየው ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? አለኝ ። እኔም ፡— በለስን ፡ አያለሁ ፡
እጅግ ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ በለስ ÷ ከክ
ፋቱም ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡
እጅግ ፡ ክፉ ፡ የሆነ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነው ፡ አልሁ ።
፮ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን
፯ ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እንደዚህ ፡
እንደ ፡ መልካሙ ፡ በለስ ÷ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡
ስፍራ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ምድር ፡ የሰደድሁ
ትን ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ ለበጐነት ፡ እመለከተ
፰ ዋለሁ ። ናይኔንም ፡ ለበጐነት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡
አደርጋለሁ ፡ ወደዚህችም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸ
ዋለሁ ፡ እሠራቸዋለሁ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሰቸ
ውም ፡ እተክላቸዋለሁ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላቸ
፱ ውም ። እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡
የሚያውቅ ፡ ልብ ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ በፍጹምም ፡
ልባቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሳሉና ፡ ሕዝብ ፡
ይሆኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናቸዋለሁ ።
፲ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ከክ
ፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፡
እንደ ፡ ክፉው ፡ በለስ ÷ እንዲሁ ፡ የይሁዳን ፡
ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ አለቆቹንም ፡ በዚህችም ፡
አገር ፡ የሚቀሩትን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅሬታ ፡
፲፩ በግብጽም ፡ አገር ፡ የሚቀመጡትን ፡ እጥላቸዋ
፲፪ ለሁ ። በማሳድዳቸውም ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ለስ
ድብና ፡ ለምሳሌ ፡ ለማላገጫና ፡ ለእርግማን ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡
፲፫ ለመበተን ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁ ። ለእነር
ሱና ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡
፲፬ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በመካከላቸው ፡ ሰይፍንና ፡
ራብን ፡ ቸነፈርንም ፡ እሰድዳለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

፩ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢ
ዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ÷ በባቢሎን ፡
ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ በመጀመሪያው ፡
፪ ዓመት ÷ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህ
፫ ንም ፡ ቃል ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ለይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለተቀመጡ ፡ ሁሉ ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፡— ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡
፬ ከአሞጽ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮስያስ ፡ ከአሥራ ፡ ሦስተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
ባሉት ፡ በእነዚህ ፡ በዘጠ ፡ ሦስቱ ፡ ዓመታት ፤
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፤
እኔም ፡ ማልጀ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናገርኋችሁ ፡
፭ ነገር ፡ ግን ፡ አልሰማችሁም ። እግዚአብሔርም ፡
ማልዶ ፡ ተነሥቶ ፡ በረያዎቹን ፡ ነቢያትን ፡ ወደ ፡
እናንተ ፡ ላከ ፡ እናንተም ፡ አላደመጣችሁም ፡
፮ ጆሮአችሁንም ፡ አላዘነበላችሁም ። እርሱም ፡— ሁላችሁ ፡ እናንተ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችሁና ፡ ከሥ
ራችሁ ፡ ክፋት ፡ ተመለሱ ፡ እግዚአብሔርም ፡
ከዘላለም ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶ
፯ ቻችሁ ፡ በሰጣትሁ ፡ ምድር ፡ ተቀመጡ ። ታመ
ልኩአቸውም ፡ ትሰግዱላቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌሎ
ችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ÷ ክፉም ፡ እንዳላ
ደርግባችሁ ፡ በእጃችሁ ፡ ሥራ ፡ አታስቈጡኝ ፡
፰ አለ ። ለእናንተ ፡ ጕዳት ፡ እንዲሆን ፡ በእጃችሁ ፡
፱ ሥራ ፡ አስቈጡኝ ፤ ዘንድ ፡ አልሰማችሁንም ÷
ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፡ የሠራዊት ፡
፲ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ቃሌን ፡
አልሰማችሁምና ፡ እነሆ ÷ ልኬ ፡ የሰሜንን ፡
፲፩ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ባሪያዬንም ፡ የባቢሎንን ፡
ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆርን ፡ እወስዳለሁ ÷ በዚህ
ችም ፡ ምድር ፡ በሚቀመጡበትም ፡ ሰዎች ፡
በዙሪያዋም ፡ ባሉ ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ አመጣቸዋለሁ ፡ ፈጽሜም ፡ አጠፋቸዋ
ለሁ ÷ ለመደነቂያና ፡ ለማፍዋጩም ፡ ለዘላለ
ምም ፡ በድማ ፡ አደርጋቸዋለሁ ። ከእነርሱም ፡
፲፪ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ÷
የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡
ድምፅ ÷ የወፍጮንም ፡ ድምፅ ፡ የመብራት
፲፫ ንም ፡ ብርሃን ፡ አስቀራለሁ ። ይህችም ፡ ምድር ፡
ሁሉ ፡ በድማና ፡ መደነቂያ ፡ ትሆናለች ፤ እነዚ
ህም ፡ አሕዛብ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰብ ፡ ዓመት ፡
ይገዛሉ ።
፲፬ ሰባው ፡ ዓመትም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ÷ የባቢ
ሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ያንን ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ኃጢአ
ታቸው ፡ እቀጣለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷
የከለዳውያንንም ፡ ምድር ፡ ለዘላለም ፡ በድማ ፡
አደርጋታለሁ ። በእርስዋም ፡ ላይ ፡ የተናገር
፲፭

ሁትን ፡ ቃሌን ፡ ሁሉ ÷ ማለት ፡ ኤርምያስ ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ የተናገረውን ፡ በዚህች ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ÷ በዚ
፲፬ ያች ፡ ምድር ፡ አመጣለሁ ። ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላላቆች ፡ ነገሥታት ፡ እነርሱን ፡ ያስገዙአቸ ዋል ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ አደራረጋቸውና ፡ እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ እከፍላቸዋለሁ ።

፲፭ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ ይለኛል ፦ የዚህን ፡ ቍጣ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጽዋ ፡ ከእጄ ፡ ውሰድ ፡ አንተንም ፡ የምሰ ድድባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አጠጣቸው ።
፲፮ ከምሰድድባቸውም ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ይጠጣሉ ፡
፲፯ ይወላገዳሉም ፡ ያብዳሉም ። ከእግዚአብሔ ርም ፡ እጅ ፡ ጽዋውን ፡ ወሰድሁ ÷ እግዚአብሔ ርም ፡ እኔን ፡ የሰደደባቸውን ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡
፲፰ አጠጣኋቸው ። ዛሬ ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ ሁሉ ፡ ባድማና ፡ መደነቂያ ፡ ማፍዋፏም ፡ እርግማ ንም ፡ አደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተሞች ፡ ነገሥታትዋንም ፡ አለቆ ችዋንም ፡ አጠጣኋቸው ። የግብጽንም ፡ ንጉሥ ፡
፲፱ ፈርዖንን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ አለቆቹንም ፡ ሕዝቡ ንም ፡ ሁሉ ÷ የተደባለቀውንም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ÷ የዖፅ ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ የፍልስ ጥኤም ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ፡ አስቀሎ ናንም ፡ ጋዛንም ፡ አቃሮንንም ፡ የአዛጦንንም ፡
፳ ቀሬታ ÷ ኤዶምያስንም ÷ ሞዓብንም ÷ የአሞን
፳፩ ንም ፡ ልጆች ÷ የጢሮስን ፡ ነገሥታትም ፡ ሁሉ ÷ የሲዶናን ፡ ነገሥታትም ፡ ሁሉ ÷ በባሕር ፡ ማዶ ፡
፳፪ ያለች ፡ የደሴት ፡ ነገሥታትንም ÷ ድዳንንም ÷ ቴማንንም ÷ ቡዝንም ÷ ጠጕራቸውንም ፡ የሚ
፳፫ ቈርጡትን ፡ ሁሉ ÷ የዓረብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚቀመጡ ፡ የድብ
፳፬ ልቅ ፡ ሕዝብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ የዘምሪ ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ የኤላም ፡ ነገሥታትንም ፡
፳፭ ሁሉ ÷ የሜዶን ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ የቀረ ቡና ፡ የራቁ ÷ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ የሰሜን ፡ ነገሥታትንም ፡ ሁሉ ÷ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታትንም ፡ ሁሉ ፡ አጠጣኋቸው ፡ የሺሻክም ፡ ንጉሥ ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ይጠጣል ።

፳፮ አንተም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራ ዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመካከላችሁ ፡ ከምሰድደው ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ጠጡ ÷ ስከሩም ÷ አስታውኩም ፡ ውደቁም ÷ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አትነሡም ፡ በላቸው ።
፳፯ ይጠጡም ፡ ዘንድ ፡ ጽዋውን ፡ ከእጅህ ፡ ለመቀ በል ፡ እንቢ ፡ ቢሉ ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፈጽማችሁ ፡ ትጠ
፳፱ ጣላችሁ ፡ በላቸው ። እነሆ ÷ ስሜ ፡ የተጠራብ ትን ፡ ከተማ ፡ አስጨንቃት ፡ ዘንድ ፡ እጀምራ ለሁ ፡ በውኑ ፡ እናንተ ፡ ያልተቀጣችሁ ፡ ትሆናላ ችሁን ? በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሰይ ፍን ፡ እጠራለሁና ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ አትቀሩም ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ስለዚህም ፡ ይሁን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ትንቢት ፡ ፴፡
ትናገርባቸዋለህ ÷ እንዲህም ፡ ትላቸዋለህ ፦ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ይጮኻል ÷ በቅ ዱስ ፡ ማደሪያውም ፡ ሆኖ ፡ ድምፁን ፡ ያሰማል ፤ በበረቱ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ይጮኻል ÷ ወይንም ፡ እንደሚጠምቁ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይጮኻል ። እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡ ፴፩፡
ጋር ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ ድምፅ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይደርሳል ፤ ከሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ይፋረዳል ÷ ኃጢአተኞችንም ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብ ሔር ።

የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ፴፪፡
ይላል ፦ እነሆ ÷ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጣል ÷ ጽኑም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣል ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ፴፫፡
የእግዚአብሔር ፡ ግዳዮች ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ይሆናሉ ፡ አይለቀስላቸውም ፡ ፣ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይሆናሉ ፡ እንጂ ፡ አይከማቹም ፡ አይ ቀበሩምም ። ትታረዱና ፡ ትበተኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀና ፴፬፡
ችሁ ፡ ደርሶአልና ÷ እንደ ፡ ተወደደም ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ትወድቃላችሁና ፡ እናንተ ፡ አረኞች ÷ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፡ እናንተ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎች ÷ በአመድ ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለሉ ። ሸሽ ፴፭፡
ትም ፡ ከእረኞች ፡ ማምለጥም ፡ ከመንጋ ፡ አው ራዎች ፡ ይጠፋል ። እግዚአብሔር ፡ ማሰማር ፴፮፡
ያቸውን ፡ አጥፍቶአልና ፡ የእረኞች ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎችም ፡ ልቅሶ ፡ ሆኖአል ። ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የተ ፴፯፡
ነሣ ፡ የሰላም ፡ በረት ፡ ፈርሶአል ። እንደ ፡ አን ፴፰፡
በሳ ፡ መደቡን ፡ ለቅቆአል ፡ ከአስፈሌኖቁሙም ፡ ሰይፍና ፡ ከጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድራ ቸው ፡ በድማ ፡ ሆናለችና ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮ ፩፡
አቄም ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መጣ ። እግዚአብ ፪፡
ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ቁም ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ለሚመጡት ፡ ለይሁዳ ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ትንግራቸው ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝሁህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ተናገራቸው ፡ አንዳ ትም ፡ ቃል ፡ አታጕድል ። ምናልባት ፡ ይሰሙ ÷ ፫፡
ከክፉ ፡ መንገዳቸውም ፡ ይመለሱ ፡ ይሆናል ፤ እኔም ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ ክፋት ፡ ያሰብሁባቸ ውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እተዋለሁ ። እንዲህም ፡ በላ ፬፡
ቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በፊታችሁ ፡ በሰጠኋት ፡ ሕጌ ፡ ትኄዱ ፡ ዘንድ ፡ ፭፡
በትሰሙኝ ÷ ያልሰማችሁትን ፡ በማለዳ ፡ ተነ ሥቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የላክኋቸውን ፡ የባሪያዎ ቼን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ በትሰሙ ÷ ይህን ፡ ቤት ፡ ፮፡
እንደ ፡ ሴሎ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ይህችንም ፡ ከተማ ፡

ለምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እርግማን ፡ አደርጋ ታለሁ ።

፯ ካህናቱም ፡ ነቢያቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ኤር ምያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡
፰ ሲናገር ፡ ሰሙ ። ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ካህናትና ፡ ነቢ ያት ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፦ ሞትን ፡ ትሞታለህ ።
፱ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፦ ይህ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሴሎ ፡ ይሆናል ÷ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በድማና ፡ ወና ፡ ትሆናለች ፡ ብለህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትንቢት ፡ ተናገርህ ? ብለው ፡ ያዙት ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በኤርምያስ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ።

፲ የይሁዳም ፡ አለቆች ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጡ ÷ በአዲሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
፲፩ ደጅ ፡ መግቢያ ፡ ተቀመጡ ። ካህናቱና ፡ ነቢያ ቱም ፡ ለአለቆቹና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፦ በጆሮ አችሁ ፡ እንደ ፡ ሰማችሁ ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮአልና ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡
፲፪ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ኤርምያ ስም ፡ ለአለቆችና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦ በሰማችሁት ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በዚህች ፡ ቤትና ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትን
፲፫ ቢት ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልኮኛል ። አሁንም ፡ መንገዳችሁንና ፡ ሥራችሁን ፡ አሳ ምሩ ÷ የአምላካችሁንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረባች
፲፬ ሁን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ ይተዋል ። እኔ ፡ ግን ÷ እነሆ ÷ በእጃችሁ ፡ ነኝ ፡ በዓይናችሁ ፡ መልካ
፲፭ ምና ፡ ቅን ፡ የመሰለውን ፡ አድርጉብኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በጆሮአችሁ ፡ እና ገር ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልኮኛልና ፡ ብትገድሉኝ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ በራሳችሁና ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንድታመጡ ፡ በእርግጥ ፡ እወቁ ።

፲፮ አለቆቹና ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ለካህናትና ፡ ለነ ቢያት ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ስም ፡ ተናግሮናልና ፡ ሞት ፡ አይገባ
፲፯ ውም ፡ አሉ ። ከአገሩ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ለሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡
፲፰ ብለው ፡ ተናገሩ ። ሞሬሼትም ፡ ሚክያስ ፡ በይ ሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፡ ለይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጽዮን ፡ እንደ ፡ እርሻ ፡ ትታረሳለች ÷ ኢየሩሳሌምም ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ ትሆናለች ÷ የቤቱም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ከፍታ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡
፲፱ ተናገረ ። በውኑ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያ ስና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ገደሉትን ? በውኑ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ አልፈሩምን ? ወደ ፡ እግዚአብ ሔርስ ፡ አልተማለሉምን ? እግዚአብሔርስ ፡ የተናገረባቸውን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ አይተውምን ?

እኛም ፡ በነፍሳችን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ እና ደርጋለን ።

ደግሞም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ ፳፡
የተናገረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ የቂ ርያትይዓሪም ፡ ሰው ፡ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ አርዮ ፡ ይዓል ፡ ነበር ፡ በዚህችም ፡ ከተማ ፡ በዚህችም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ኤርምያስ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ ፳፩፡
ኃያላኑም ፡ ሁሉ ፡ አለቆቹም ፡ ሁሉ ፡ ቃሉን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሊገድለው ፡ ፈለገ ፡ አር ዮም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ገባ ። ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ የግ ፳፪፡
ከበርን ፡ ልጅ ፡ ኤልናታንን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ላካቸው ፡ ከግ ፳፫፡
ብጽም ፡ አርዮን ፡ አውጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኢዮአቄም ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፡ እርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ገደለው ፡ ሬሳውንም ፡ ከቡራን ፡ በል ሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መቃብር ፡ ጣለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፳፬፡
በሕዝቡ ፡ እጅ ፡ እንዳይሰጥና ፡ እንዳይገድሉት ፡ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃም ፡ እጅ ፡ ከኤርምያስ ፡ ጋር ፡ ነበረች ።

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአ ፩፡
ቄም ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ አስራትና ፡ ፪፡
ቀንበር ፡ ሥራ ፡ በአንገትህም ፡ ላይ ፡ አድርግ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ሴዶቅያስ ፡ ወደ ፫፡
አይራሳሌም ፡ በመጡት ፡ መልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሞዓብም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሲዶናም ፡ ንጉሥ ፡ ላካቸው ። ለጌቶቻቸውም ፡ እንዲነግሩ ፡ እን ፬፡
ዲህ ፡ ብለህ ፡ አዝዛቸው ፦ የእስራኤል ፡ አም ላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ ይላል ፦ ለጌቶቻችሁ ፡ እንዲህ ፡ በሉ ፦
፭ ምድሪቱን ፡ በሠርታም ፡ ፈት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎችንና ፡ እንስሶችን ፡ በታላቅ ፡ ኃይሌና ፡ በተ ዘረጋችው ፡ ክንዴ ፡ ፈጥሬአለሁ ፡ ለኃይሌም ፡ መልክም ፡ ለሆነው ፡ አሰጣታለሁ ። አሁንም ፡ ፮፡
እነዚህን ፡ ምድሮች ፡ ሁሉ ፡ ለባሪያዩ ፡ ለባቢ ሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ እጅ ፡ እሰልፌ ፡ ሰዋቸዋለሁ ፡ ደግሞም ፡ እንዲገዙለት ፡ ዘንድ ፡ የሠርጋ ፡ በዳ ፡ አራዊትንም ፡ ለማሞ ፡ ሰጥቼዋለሁ ። የገዛ ፡ ራሱም ፡ ፯፡
ምድር ፡ ጊዜ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱና ፡ ለልጁ ፡ ለልጅ ፡ ልጁም ፡ ይገ ዛሉ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላ ላቆች ፡ ነገሥታት ፡ እርሱን ፡ ያስገዙታል ። ለባ ፰፡
ቢሎን ፡ ንጉሥም ፡ ሉሪበነደንፆር ፡ የማይገዛ ውን ÷ ከዘሌሎችም ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ እንገቱን ፡ ዝቅ ፡ የማያደርገውን ፡ ሕዝብና ፡ መን ግሥት ፡ ያን ፡ ሕዝብ ፡ በእጁ ፡ እስከጠፋው ፡ ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እቀጣ

ሠ፡ ለሁ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። እናንተ ፣ ግን ፡— ለባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ አትገዙም ፣ የሚሉአችሁን ፣ ነቢያቶቻችሁንና ፣ ሞዋርተኞቻችሁን ÷ ሕልም ፣ አላሚዎቻችሁንና ፣ ቃላተኞቻችሁን ፣ መተተኞቻችሁንም ፣ አትስሙ ፣ ከምድራችሁ ፣ እንዲያርቁአችሁ ÷ እኔም ፣ እንዳሳድዳችሁ ፣ እናንተም ፣ እንድትጠፉ ፣ ሐሰተኛ ፣ ትንቢትን ፣ ይናገሩላችኋልና ። ነገር ፣ ግን ፣ ከባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ቀንበር ፣ በታች ፣ አንገታችሁን ፣ ጎብኝ ፣ የሚያደርገውንና ፣ የሚገዛለትን ፣ ሕዝብ ፣ በእገሩ ፣ ላይ ፣ እተወዋለሁ ፣ እነርሱም ፣ ያርሱአታል ፣ ይቀመጡበትማል ።

ሠ፣ ለይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ ለሰዴቅያስም ፣ በዚህ ፣ ቃል ፣ ተናገርሁ ፡— ከባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ቀንበር ፣ በታች ፣ አንገታችሁን ፣ ጎብቅ ፣ አድርጉ ፣ ለእርሱና ፣ ለሕዝቡም ፣ ተገዙላቸው ፣ በሕይወትም ፣ ኑሩ ። ለባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ይገዛ ፣ ዘንድ ፣ እንቢ ፣ ስላለ ፣ ሕዝብ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንደ ፣ ተናገረ ÷ አንተና ፣ ሕዝብህ ፣ በሰይፍና ፣ በራብ ፣ በቸነፈርም ፣ ለምን ፣ ትሞታላችሁ ? ሐሰተኛን ፣ ትንቢት ፣ ይናገሩላችኋልና ፡— ለባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ አትገዙም ፣ የሚሉአችሁን ፣ የነቢያትን ፣ ቃል ፣ አትስሙ ። እኔ ፣ አልላክኋቸውምና ፣ ነገር ፣ ግን ፣ እኔ ፣ እንዳሳድዳችሁ ÷ እናንተና ፣ ትንቢት ፣ የሚናገሩላችሁ ፣ ነቢያትም ፣ እንድትጠፉ ፣ በስሜ ፣ ሐሰተኛ ፣ ትንቢትን ፣ ይናገራሉ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ።

ሠ፣ ለካህናትም ፣ ለዚህም ፣ ሕዝብ ፣ እንዲህ ፣ ብዬ ፣ ተናገርሁ ፡— እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— ሐሰተኛውን ፣ ትንቢት ፣ ይናገሩላችኋልና ፡— የእግዚአብሔር ፣ ቤት ፣ ዕቃ ፣ በቅርብ ፣ ጊዜ ፣ ከባቢሎን ፣ ይመለሳል ፣ የሚሉአችሁን ፣ የነቢያቶቻችሁን ፣ ቃል ፣ አትስሙ ። እነርሱም ፣ አትስሙ ፣ ለባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ተገዙ ፣ በሕይወትም ፣ ኑሩ ። ይህችስ ፣ ከተማ ፣ ስለ ፣ ምን ፣ በድማ ፣ ትሆናለች ? እነርሱ ፣ ግን ፣ ነቢያት ፣ ቢሆኑ ÷ የእግዚአብሔርም ፣ ቃል ፣ በእነርሱ ፣ ዘንድ ፣ ቢኖኝ ÷ በእግዚአብሔር ፣ ቤትና ፣ በይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ ቤት ፣ በኢየሩሳሌም ፥ የቀረችው ፣ ዕቃ ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ እንዳትሄድ ፣ ወደ ፣ ሠራዊት ፣ ጌታ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ይማለሉ።

ሠ፣ ፡ የባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ናቡከደነፆር ፣ የይሁዳን ፣ ንጉሥ ፣ የኢዮአቄምን ፣ ልጅ ፣ ኢኮንያንንና ፣ የይሁዳንና ፣ የኢየሩሳሌምን ፣ ከበርቴዎች ፣ ሁሉ ፣ ማርኮ ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ በፈለሳቸው ፣ ጊዜ ፣ ስላልወሰዳቸው ፣ ዓምዶች ፣ ስለ ፣ ሁሪውም ፣ ስለ ፣ መቀመጫዎቹም ፣ በዚህችም ፣ ከተማ ፣ ስለ ፣ ቀረች ፣ ዕቃ ፣ ሁሉ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላልና ፣ በእግዚአብሔር ፣ ቤትና ፣ በይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ ቤት ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ ስለ ፣ ቀረች ፡ ዕቃ ፡ የአሦራውያን ፣ ንጉሥ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— ወደ ፣ ባቢሎን ፣ ትወሰዳለች ፣ እስከምጐበኛትም ፣ ቀን ፣ ድረስ ፣ በዚያ ፣ ትኖራለች ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ በዚያን ፣ ጊዜም ፣ አወጣታለሁ ፣ ወደዚህም ፣ ስፍራ ፣ እመልሳታለሁ ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

በዚያም ፣ ዓመት ÷ በይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ በሰዴቅያስ ፣ መንግሥት ፣ መጀመሪያ ÷ በአራተኛው ፣ ዓመት ፣ በእምስተኛው ፣ ወር ፣ ነቢዩ ፣ የጎባያን ፣ ሰው ፣ የዓዙር ፣ ልጅ ፣ ሐናንያ ፣ በእግዚአብሔር ፣ ቤት ፣ በካህናትና ፣ በሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ፊት ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ተናገረኝ ፡— የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ይናገራል ፡— የባቢሎንን ፣ ንጉሥ ፣ ቀንበር ፣ ሰብሬአለሁ ። የባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ናቡከደነፆር ፣ ከዚህች ፣ ስፍራ ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ የወሰዳትን ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቤት ፣ ዕቃ ፣ ሁሉ ፣ በሁለት ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ ወደዚህች ፣ ስፍራ ፣ እመልሳታለሁ ፣ ወደ ፣ ባቢሎንም ፣ የሄዱትን ፣ የይሁዳን ፣ ንጉሥ ፣ የኢዮአቄምን ፣ ልጅ ፣ ኢኮንያንንና ፣ የይሁዳን ፣ ምርኮ ፣ ሁሉ ፣ ወደዚህች ፣ ስፍራ ፣ እመልሳቸዋለሁ ፣ የባቢሎንን ፣ ንጉሥ ፣ ቀንበር ፣ እሰብራለሁና ።

ነቢዩ ፣ ኤርምያስም ፣ በካህናቱና ፣ በእግዚአብሔር ፣ ቤት ፣ በቆሙት ፣ ሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ፊት ፣ ለነቢዩ ፣ ለሐናንያ ፣ ተናገረ ። ነቢዩም ፣ ኤርምያስ ፣ እንዲህ ፣ አለ ፡— አሜን ÷ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ያድርግ ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቤት ፣ ዕቃ ፣ ምርኮውንም ፣ ሁሉ ፣ ከባቢሎን ፣ ወደዚህ ፣ ስፍራ ፣ በመመለስ ፣ እግዚአብሔር ፣ የተናገርኸውን ፣ ትንቢት ፣ ይፈጽም ። ነገር ፣ ግን ፣ በጆሮህና ፣ በሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ጆሮ ፣ የምናገረውን ፣ ይህን ፣ ቃል ፣ ስማ ፣ ከጥንት ፣ ከእኔና ፣ ከአንተ ፣ በፊት ፣ የነበሩ ፣ ነቢያት ፣ በብዙ ፣ አገርና ፣ በታላላቅ ፣ መንግሥታት ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ሰልፍና ፣ ስለ ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ ስለ ፣ ቸነፈርም ፣ ትንቢት ፣ ተናገሩ ። ስለ ፣ ሰላም ፣ የተናገረ ፣ ነቢይ ÷ የነቢዩ ፣ ቃል ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ÷ እግዚአብሔር ፣ በእውነት ፣ የሰደደው ፣ ነቢይ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ይታወቃል ።

ነቢዩም ፣ ሐናንያ ፣ ቀንበሩን ፣ ከነቢዩ ፣ ከኤርምያስ ፣ አንገት ፣ ወስዶ ፣ ሰበረው ። ሐናንያም ፣ በሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ፊት ፡— እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— እንዲሁ ፣ በሁለት ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ የባቢሎንን ፣ ንጉሥ ፣ የናቡከደነፆርን ፣ ቀንበር ፣ ከአሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ አንገት ፣ እሰብራለሁ ፣ አለ ። ነቢዩም ፣ ኤርምያስ ፣ መንገዱን ፣ ሄደ ።

ነቢዩም ፣ ሐናንያ ፣ ቀንበሩን ፣ ከነቢዩ ፣ ከኤርምያስ ፣ አንገት ፣ ከሰበረ ፣ በኋላ ÷ የእግዚአብሔር ፣ ቃል ፣ ወደ ፣ ኤርምያስ ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ መጣ ፡— ሂድ ፣ ለሐናንያ ፣ እንዲህ ፣ ብለህ ፣ ንገረው ፡— እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— አንተ ፣ የእንጨትን ፣ ቀንበር ፣ ሰብረሃል ÷ እኔ ፣ ግን ፣ በእርሱ ፣ ፋንታ ፣ የብረትን ፣ ቀንበር ፣ እሠራለሁ ። የእስራኤልም ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላልና ፡— ለብቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ለናቡከደነፆር ፣ ይገዙለት ፣ ዘንድ ፣ የብረትን ፣ ቀንበር ፣ በእነዚህ ፣ አሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ አንገት ፣ ላይ ፣ አድርጌአለሁ ፣ እነርሱም ፣ ይገዙለታል ÷ የምድረ ፣ በዳ ፣ አራዊትን ፣ ደግሞ ፣ ሰጥቼዋለሁ ። ነቢዩም ፣ ኤርምያስ ፣ ነቢዩን ፣ ሐናንያን ፡— ሐናንያ ፣ ሆይ ÷ ስማ ፣ ይህ ፣ ሕዝብ ፣ በሐሰት ፣ እንዲታመን ፣ አድርገሃል ፣ እንጂ ፣ እግዚአብሔር ፣ አልላከህም ። ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— እነሆ ÷ ከምድር ፣ ላይ ፣ አስድድሃለሁ ፣ በእግዚአብሔር ፣ ላይ ፣ ዓመፅን ፣ ተናግረሃልና ፣ በዚህ ፣ ዓመት ፣ ትሞታለህ ፣ አለው ። ነቢዩም ፣ ሐናንያ ፣ በዚያው ፣ ዓመት ፣ በሰባተኛው ፣ ወር ፣ ሞተ ።

ምዕራፍ ፳፱ ።

ነቢዩ ፣ ኤርምያስ ፣ ወደ ፣ ተረፉት ፣ የምርኮ ፣ ሽማግሌዎች ÷ ወደ ፣ ካህናቱም ÷ ወደ ፣ ነቢያቱም ÷ ናቡከደነፆር ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ ማርኮ ፣ ወዳፈለሰውም ፣ ሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ የላከው ፣ የደብዳቤው ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ። ይህም ፣ የሆነው ፣ ንጉሡ ፣ ኢኮንያን ፣ እናቱም ፣ እቴጌይቱ ፣ ጃንደረቦቹም ፣ የይሁዳና ፣ የኢየሩሳሌምም ፣ አለቆች ፣ ጠራቢዎችና ፣ ብረት ፣ ሠራተኞችም ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ከወጡ ፣ በኋላ ፣ ነው ። ኤርምያስ ፣ የይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ ሴዴቅያስ ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ወደ ፣ ናቡከደነፆር ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ በላካቸው ፣ በሳፋን ፣ ልጅ ፣ በኤልዓሣና ፣ በኬልቅያስ ፣ ልጅ ፣ በገማርያ ፣ እጅ ፣ ደብዳቤውን ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ላከው ፡— የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ ላስማረክኋቸው ፡ ምርኮኞች ፣ ሁሉ ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— ቤት ፣ ሠርታችሁ ፣ ተቀመጡ ÷ አታክልትም ፣ ተክላችሁ ፣ ፍሬዋን ፣ ብሉ ። ተጋቡ ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ልጆችንም ፣ ውለዱ ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ልጆቻችሁንም ፣ አጋቡ ÷ እነርሱም ፣ ወንዶችንና ፣ ሴቶችንና ፣ ልጆች ፣ ይውለዱ ። ከዚያም ፣ ተበዙ ፣ ጥቂቶችም ፣ አትሁኑ ። በእርስዋ ፣ ሰላም ፣ ተላም ፣ ይሆንላችኋልና ፣ ወደ ፣ እርስዋ ፣ ላስማረክኋችሁ ፣ ከተማ ፣ ሰላምን ፣ ፈልጉ ÷ ስለ ፣ እርስዋም ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ጸልዩ ። የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላልና ፡— በመካከላችሁ ፣ ያሉት ፣ ነቢያቶቻችሁና ፣ ምዋርተኞቻችሁ ፣ አያታልሉአችሁ ÷ እናንተም ፣ የምታልሙትን ፣ ሕልም ፣ አትስሙ ። በስሜ ፣ ሐሰተኛ ፣ ትንቢትን ፣ ይናገሩላችኋልና ፣ እኔም ፣ አልላክኋቸውም ። እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— ለባቢሎን ፣ ሰባ ፣ ዓመት ፣ ከተፈጸመ ፣ ጊዜ ፣ እጐበኛችኋለሁ ፣ ወደዚህም ፣ ስፍራ ፣ እመልሳችሁ ፣ ዘንድ ፣ መልካሚቱን ፣ ቃሌን ፣ እፈጽምላችኋለሁ ። ለእናንተ ፣ የማስባትን ፣ አሳብ ፣ እኔ ፣ አውቃለሁ ፣ ፍጻሜና ፣ ተስፋ ፣ እሰጣችሁ ፣ ዘንድ ፣ የሰላም ፣ አሳብ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የክፉ ፣ ነገር ፣ አይደለም ። እናንተም ፣ ትጠሩኛላችሁ ÷ ሄዳችሁም ፣ ወደ ፣ እኔ ፣ ትጸልያላችሁ ÷ እኔም ፣ እሰማችኋለሁ ። እናንተ ፣ ትሹኛላችሁ ÷ በፍጹም ፣ ልባችሁም ፣ ከሻችኋኝ ፣ ታገኙኛላችሁ ። ከእናንተም ፣ ዘንድ ፣ እገኛለሁ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ÷ ምርኮአችሁንም ፣ እመልሳለሁ ÷ ከአሕዛብም ፣ ሁሉ ፣ ዘንድ ፣ እናንተንም ፣ ከሳደድኩበት ፣ ስፍራ ፣ ሁሉ ፣ እሰበስባችኋለሁ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፤ እናንተንም ፣ ለምርኮ ፣ ወዳፈለሳኩበት ፣ ስፍራ ፣ እመልሳችኋለሁ ።

እናንተም ፡— እግዚአብሔር ፣ በባቢሎን ፣ ነቢያትን ፣ አስነሥቶልናል ፣ ብላችኋልና ፣ እግዚአብሔር ፣ በዳዊት ፣ ዙፋን ፣ ስለ ፣ ተቀመጠ ፣ ንጉሥ ፣ ከእናንተም ፣ ጋር ፣ ስላልተማረኩት ፣ ወንድሞቻችሁ ÷ በዚህች ፣ ከተማ ፣ ስለሚኖሩ ፣ ሕዝብ ፣ ሁሉ ÷ እንዲህ ፣ ይላልና ፡— የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— እነሆ ÷ ሰይፍንና ፣ ራብን ፣ ቸነፈርንም ፣ እሰድድባቸዋለሁ ÷ ከክፋቱም ፣ የተነሣ ፣ ይበላ ፣ ዘንድ ፣ እንደማይቻል ፣ እንደ ፣ ክፉ ፣ በለስ ፣ አደርጋቸዋለሁ ። በሰይፍም ፣ በራብም ፣ በቸነፈርም ፣ አሳድዳቸዋለሁ ÷ በሳደድኩባቸውም ፣ አሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ ዘንድ ፣ ለዮሳቻና ፣ ለመደነቂያ ፣ ለማፍዋጫም ፣ ለመሰደቢያም ፣ እንዲሆኑ ፣ በምድር ፣ መንግሥታት ፣ ሁሉ ፣ ዘንድ ፣ ለመበተን ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣቸዋለሁ ። ይህም ፣ የሆነው ፣ ቃሌን ፣ አሳልፌ ፣ ሰሙ ፣ ነው ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ በማለዳ ፣ ተነሥቼ ፣ ባሪያዎቼን ፣ ነቢያትን ፣ ወደ ፣ እነርሱ ፣ ሰድጃለሁና ፣ እናንተ ፣ ግን ፣ አልሰማችሁም ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፣ ከኢየሩሳሌም ፣ ወደ ፣ ባቢሎን ፣ የሰደድኋችሁ ፣ ምርኮኞች ፣ ሁሉ ፣ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣ ስሙ ።

የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ በስሜ ፣ ሐሰተኛ ፣ ትንቢትን ፣ ስለሚናገሩላችሁ ፣ ስለ ፣ ቆላያ ፣ ልጅ ፣ ስለ ፣ አክዓብና ፣ ስለ ፣ መዕሤያ ፣ ልጅ ፣ ስለ ፣ ሴዴቅያስ ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፡— እነሆ ፣ በባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ በናቡከደነፆር ፣ እጅ ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣቸዋለሁ ÷ በዓይኖቻችሁም ፣ ፊት ፣ ይገድላቸዋል ። ከእነርሱም ፣ የተነሣ ፣ በባቢሎን ፣ ያሉ ፣ የይሁዳ ፣ ምርኮኞች ፣ ሁሉ ፡— የባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ በእሳት ፣ እንደ ፣ ጠበሰቻቸው ፣ እንደ ፣ ሴዴቅያስና ፣ እንደ ፣ አክዓብ ፣ እግዚአብሔር ፣ ያድርግህ ፣ እንጂ ፣ እኔም ፣ አውቃለሁ ፣ ምስክርም ፣ ነኝ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ። በእስራኤል ፣ ዘንድ ፣ ስንኖና ፣ አድርገዋልና ፣ ከባልንጀሮቻቸውም ፣ ሚስቶች ፣ ጋር ፣ አመንዝረዋልና ፣ ያላዘዝኋቸውንም ፣ ቃል ፣ በስሜ ፣ በሐሰት ፣ ተናግረዋልና ።

ለኔሔላማዊው ፣ ለሸማያ ፣ እንዲህ ፣ በል ፡— የእስራኤል ፣ አምላክ ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚ

አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኢየሩሳሌም ፡ ወዳለው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ÷ ወደ ፡ ካህኑም ፡ ወደ ፡ መዕሤያ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሶፎንያስ ÷ ወደ ፡ ካህናቱም ፡ ሁሉ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ በስምህ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ልከሃል ፦ አያበደ ፡ ትንቢት ፡ የሚናገርን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእግር ፡ ግንድና ፡ በዛንጅር ፡ ታኖረው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አሰቃ ፡ እንድትሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በካህኑ ፡ በዮዳሄ ፡ ፋንታ ፡ ካህን ፡ አድርጎሃል ። አሁንስ ፡ ትንቢት ፡ ተናጋሪውን ፡ የዓናቶቱን ፡ ሰው ፡ ኤርምያስን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትዘለፈውም ? እርሱ ፡ — ምርኮው ፡ የረዘመ ፡ ነውና ፡ ቤት ፡ ሠርታችሁ ፡ ተቀመጡ ÷ አታክልትንም ፡ ተክላችሁ ፡ ፍሬዋን ፡ ብሉ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ልከአልና ። ካህኑም ፡ ሶፎንያስ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ጆሮ ፡ አነበበው ። የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኔሔላማዊው ፡ ስለ ፡ ሸማያ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ ምር ከኞች ፡ ሁሉ ፡ ላክ ፦ እኔ ፡ ሳልልከው ፡ ሸማያ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮላችኋልና ÷ በሐሰተም ፡ እንድትታመኑ ፡ አድርጎአችኋልና ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ÷ ኔሔላማዊውን ፡ ሸማያንና ፡ ዘሩን ፡ እቀጣለሁ ፡ እኔም ፡ የማደርግላቸውን ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ የሚያይ ፡ ሰው ፡ በመካከላችሁ ፡ አይኖርላቸውም ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የነገርሁህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ጻፍ ። እነሆ ÷ የሕዝቤን ፡ የእስራኤልንና ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ የምመልስበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣልና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደ ፡ ሰጠኋት ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለሁ ÷ እነርሱም ፡ ይገዙአታል ።

እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስራኤልና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ — የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ ሰምተናል ፡ የፍርሃት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰላም ፡ አይደለም ። ጠይቁ ÷ ወንድ ፡ ይወልድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልከቱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ወላጅ ፡ እጁን ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ፊቱም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጥቁረት ፡ ተለውጠ ፡ አየሁ ? ወዮ ! ያ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ነውና ÷ እርሱንም ፡ የሚመስል ፡ የለምና ፡ ያ ፡ የያዕቆብ ፡ መከራ ፡ ዘመን ፡ ነው ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ ይድናል ። በዚያ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀንበርን ፡ ከአንገትህ ፡ እሰብራለሁ ÷ እስራትህንም ፡ እበጥሳለሁ ÷ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ለሌላ ፡ አትገዛም ፡ ለአምላ ክቸው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ለማስነሣላቸው ፡ ለንጉሣቸው ፡ ለዳዊትም ፡ ይገዛሉ ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አይገዙአቸውም ።

እነሆ ÷ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርህንም ፡ ከምርኮ ፡ አገር ፡ አድናለሁና ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ÷ አትፍራ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ አትደንግጥ ፡ ያዕቆብም ፡ ይመለሳል ፡ ያርፍማል ፡ ተዘልሎም ፡ ይቀመጣል ፣ ማንም ፡ አያስፈራውም ። አድንህ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተንም ፡ የበተንሁባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለሁ ÷ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋህም ፡ በመጠን ፡ እቀጣሃለሁ ÷ ያለ ፡ ቅጣትም ፡ ከቶ ፡ አልተውህም ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስብራትህ ፡ የማይፈወስ ፡ ቍስልህም ፡ ክፉ ፡ ነው ። ትጠንን ፡ ዘንድ ፡ ከርክርህን ፡ የሚፈርድልህ ፡ የለም ÷ ቍስልህንም ፡ የሚፈውስ ፡ መድኃኒት ፡ የለህም ። ውሽሞችህ ፡ ሁሉ ፡ ረስተውሃል ፡ አይፈልጉህምም ፡ በደልህ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኃጢአትህም ፡ ስለ ፡ በዛ ÷ በጠላት ፡ ማቁሰልና ፡ በጨካኝ ፡ ቅጣት ፡ አቍስዬሃለሁና ። ሕመምህ ፡ የማይፈወስ ፡ ሆኖልና ፡ ስለ ፡ ስብራትህ ፡ ለምን ፡ ትጮኻለህ ? በደልህ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኃጢአትህም ፡ ስለ ፡ በዛ ÷ ይህን ፡ አድርጌብሃለሁ ። ስለዚህ ፡ የሚውጡህ ፡ ሁሉ ፡ ይዋጣሉ ÷ ጠላቶችህም ፡ ሁላቸው ፡ ይማረካሉ ፡ የዘረፉህም ፡ ይዘረፋሉ ÷ የበዘበዙህንም ፡ ሁሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ። እኔ ፡ ጤናህን ፡ እመልስልሃለሁ ፡ ቍስልህንም ፡ እፈውሰለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ማንም ፡ የማይሻት ፡ የተጣለች ፡ ጽዮን ፡ ብለው ፡ ጠርተውሻልና ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ÷ የያዕቆብን ፡ ድንኳን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለሁ ÷ ለማደሪያውም ፡ እራራለሁ ፡ ከተማይቱም ፡ በገብታዋ ፡ ላይ ፡ ትሠራለች ÷ አዳራሹም ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ይሆናል ። ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ የምስጋናና ፡ የዘፋኞች ፡ ድምፅ ፡ ይወጣል ፤ እኔም ፡ አበዛቸዋለሁ ፡ አያንሱምም ÷ እኔም ፡ አከብራቸዋለሁ ፡ ታናንሽም ፡ አይሆኑም ። ልጆቻቸውም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ይሆናሉ ÷ ማኅበራቸውም ፡ በፊቴ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ የሚያስጨንቋቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አቀጣለሁ ። አለቃቸው ፡ ከእነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ይሆናል ÷ ገዢአቸውም ፡ ከመካከላቸው ፡ ይወጣል ፡ እኔ ፡ አቀርበዋለሁ ፡ እርሱም ፡ ይቀርባል ፡ ይህስ ፡ በይሆን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚደፍር ፡ ማን ፡ ነው ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትሆኑኛላችሁ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናችኋለሁ ።

እነሆ ÷ የእግዚአብሔር ፡ ሀውሎ ፡ ነፋስ ÷ እርሱም ፡ ቀጣው ÷ የሚያገለባብጥ ፡ ሀውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወጥቶአል ፡ የዓመፀኞችንም ፡ ራስ ፡ ይገለባብጣል ። የእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የልቡን ፡ አሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመለስም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ታስተውሉታላችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

በዚያን ፡ ዘመን ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ ለእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ እሆናለሁ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይሆኑኛል ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — እስራኤል ፡ ማረፊያ ፡ ሊሻ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ከሰይፍ ፡ የተረፈው ፡ ሕዝብ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞገስ ፡ አገኘ ። እግዚአብሔርም ፡ ከሩቅ ፡ ተገለጠልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ — በዘላለም ፡ ፍቅር ፡ ወድጀሻለሁ ፡ ስለዚህ ፡ በቸርነት ፡ ሳብሁሽ ። የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ÷ እንደ ፡ ገና ፡ እሠራሻለሁ ፡ አንቺም ፡ ትሠሪያለሽ ፤ እንደ ፡ ገናም ፡ ከበሮሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ከዘፋኞች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዘፈን ፡ ትወጪአለሽ ። እንደ ፡ ገናም ፡ በሰማርያ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ በታዎችን ፡ ትተክያለሽ ፤ ትተክልተኞች ፡ ይተክላሉ ፡ ፍሬአውም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። በኤፍሬምም ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጠባቆች ፦ ተነሡ ÷ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንውጣ ፡ ብለው ፡ የሚጮኹበት ፡ ቀን ፡ ይመጣልና ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ስለ ፡ አሕዛብም ፡ አለቆች ፡ እልል ፡ በሉ ፡ አውሩ ÷ አመስግኑ ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ የእስራኤልን ፡ ቅሬታ ፡ አድኖአል ፡ በሉ ። እነሆ ÷ ከሰሜን ፡ አገር ፡ አመጣቸዋለሁ ÷ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ እሰበስባቸዋለሁ ÷ በመካከላቸውም ፡ ዕውሩና ፡ አንካሳው ፡ ያረገዘችና ፡ የወለደችም ፡ በአንድነት ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ሆነው ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ። በልቅሶ ፡ ወጡ ፡ እኔም ፡ በማጽናናት ፡ አመጣቸዋለሁ ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በቅን ፡ መንገድ ፡ አስኪዳቸዋለሁ ÷ በእርሱም ፡ አይሰናከሉም ። እኔ ፡ ለእስራኤል ፡ አባት ፡ ነኝና ÷ ኤፍሬምም ፡ ዘሩ ፡ ነውና ።

አሕዛብ ፡ ሆይ ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ÷ በሩቅም ፡ ላሉ ፡ ደሴቶች ፡ አውሩና ፡ — አስራኤልን ፡ የበተነ ፡ እርሱ ፡ ይሰበስበዋል ÷ እረኛም ፡ መንጋውን ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ይጠብቀዋል ፡ በሉ ። እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ተቤዣቸዋታል ÷ ከበረቱበትም ፡ እጅ ፡ አድኖታል ። ይመጣሉ ፡ በጽዮንም ፡ ተራራ ፡ እልል ፡ ይላሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጎኑት ÷ ወደ ፡ እህልና ፡ ወደ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ወደ ፡ ዘይትም ÷ ወደ ፡ በጎችና ፡ ወደ ፡ ላሞች ፡ ይሰበሰባሉ ፡ ነፍሳቸውም ፡ እንደ ፡ ረከች ፡ ገነት ፡ ትሆናለች ÷ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አያዝኑም ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ድንግሊቱ ፡ በዘፈን ፡ ደስ ፡ ይላታል ÷ ጕበዛዝቱና ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ልቅሶአቸውንም ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ እመልሳለሁ ÷ አጽናናቸውማለሁ ÷ ከኀዘናቸውም ፡ ደስ ፡ አሰኛቸዋለሁ ። የካህናቱንም ፡ ነፍስ ፡ በብዛት ፡ አረካታለሁ ፡ ሕዝቤም ፡ በጎኑቴን ፡ ይጠግባል ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — የዋይታና ፡ የመራራ ፡ ልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ በራማ ፡ ተሰማ ፤ ራሔል ፡ ስለ ፡ ልጆችዋ ፡ አለቀሰች ፤ የሉምና ፡ ስለ ፡ ልጆችዋ ፡ መጽናናትን ፡ እንቢ ፡ አለች ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — ድምፅሽን ፡ ከልቅሶ ፡ ዓይንሽንም ፡ ከእንባ ፡ ከልክይ ። ለሥራሽ ፡ ዋጋ ፡ ይሆናልና ÷ ከጠላትም ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ። ለፍጻሜሽም ፡ ተስፋ ፡ አለ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ ልጆችሽም ፡ ወደ ፡ ዳርቻቸው ፡ ይመለሳሉ ። ኤፍሬም ፦ — ቀጣኸኝ ፡ እኔም ፡ እንዳልተገራ ፡ ወይፈን ፡ ተቀጣሁ ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ነህና ፡ መልሰኝ ፡ እኔም ፡ እመለሳለሁ ። ከተመለስሁ ፡ በኋላ ፡ ተጸጸትሁ ÷ ከተገሠጽሁም ፡ በኋላ ፡ ጭኔን ፡ ጸፋሁ ፡ የብላቴንነቴንም ፡ ስድብ ፡ ተሸክሜአለሁና ፡ አፈርሁ ÷ ተዋረድሁም ፡ ብሎ ፡ ሰ ፤ያለቅስ ፡ ሰማሁ ። በእውነት ፡ ኤፍሬም ፡ ለእኔ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ የተወደደ ፡ ሕፃን ፡ ነውን ? በእርሱ ፡ ላይ ፡ በተናገርሁ ፡ ቍጥር ፡ አስበዋለሁ ፡ ስለዚህ ፡ አንጀቴ ፡ ታወከችለት ፡ ርኅራኄንም ፡ እራራለታለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ለራስሽ ፡ የመንገድ ፡ ምልክት ፡ አድርጊ ÷ መንገድንም ፡ የሚመሩ ፡ ዓምዶችን ፡ ትክዪ ÷ ልብሽንም ፡ ወደ ፡ ሄድሽበት ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ጥርጊያው ፡ አቅኚ ፡ አንቺ ፡ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ÷ ተመለሺ ÷ ወደ ፡ እነዚህም ፡ ወደ ፡ ከተሞችሽ ፡ ተመለሺ ። አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ እስከ ፡ መቼ ፡ ትቅበዘበዣለሽ ? እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ፈጥሮ ፡ አልና ፡ ሴት ፡ ወንድን ፡ ትከብባለች ።

የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — ምርከአቸውን ፡ በመለስሁ ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ በከተሞችዋ ፦ — የጽድቅ ፡ መደሪያ ፡ ሆይ ፡ የቅድስና ፡ ተራራ ፡ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ፡ የሚሉን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይናገራሉ ። በይሁዳ ፡ ከተሞችና ፡ በእገሩ ፡ ሁሉ ፡ ከገበሬዎችና ፡ መንጋን ፡ ይዘው ፡ ከሚዘሩ ፡ ጋር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይገኙሉ ። የደከመችውን ፡ ነፍስ ፡ አርክቻለሁና ÷ ያዘንችውንም ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ አጥግቤአለሁና ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነቃሁ ፡ ተመለከትሁም ÷ እንቅልፌም ፡ ጣፋጭ ፡ ሆነልኝ ።

የእስራኤልን ፡ ቤትና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ በሰው ፡ ዘርና ፡ በእንስሳ ፡ ዘር ፡ የምዘራበት ፡ ዘመን ÷ እነሆ ÷ ይመጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እንዲህም ፡ ይሆናል ፡ አፈርሰቸውና ፡ ከፋ ፡ አደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጋሁባቸው ÷ እንዲሁ ፡ እሠራቸውና ፡ እተክላቸው ፡ ዘንድ ፡ እተጋለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ዳሞኛ ፡ እንዲህ ፡ አይልም ፦ አባቶች ፡ ጨርቋ ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ በሉ ÷ የልጆችም ፡ ጥር

፴፩ ሶች ፡ ጠረሱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በገዛ ፡ በደሉ ፡ ይሞታል ፡ መራራውን ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ የሚበላ ፡ ሁሉ ፡ ጥርሶቹ ፡ ይጠርሰሉ ።

፴፩ እነሆ ፥ ከእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የምገባበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡

፴፪ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ በያዝሁበት ፡ ቀን ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ገባሁት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አይደለም ፡ እነርሱ ፡ በኪዳኔ ፡ አልጸኑምና ÷ እኔም ፡ ችል ፡

፴፫ አልኋቸው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ከእነዚያ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ የም ገባው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነውና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ አኖራለሁ ፡ በልባቸውም ፡ እጽፈዋለሁ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናቸዋለሁ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይሆኑኛል ።

፴፬ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባልንጀራውን ÷ እያንዳንዱም ፡ ወንድሙን ፡ — እግዚአብሔርን ፡ እወቅ ፡ ብሎ ፡ አያስተምርም ፡ ከታናሹ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡ ያውቁኛልና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በደላቸውን ፡ እምራቸዋለሁና ÷ ኃጢአታቸውንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስብምና ።

፴፭ ስሙ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ የሚባል ÷ ፀሐይን ፡ በቀን ፡ የጨረቃንና ፡ የከዋክብትን ፡ ሥርዓት ፡ በሌሊት ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ የሚሰጥ ÷ እንዲ ተምሙም ፡ የበሕርን ፡ ሞገዶች ፡ የሚያናውጥ ፡

፴፮ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ይህ ፡ ሕግ ፡ ከፊቴ ፡ ቢወገድ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የእስራኤል ፡ ዘር ፡ በፊቴ ፡

፴፯ ሕዝብ ፡ እንዳይሆን ፡ ለዘላለም ፡ ይቀራል ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ሰማይ ፡ በላይ ፡ ቢከነዳ ÷ የምድርም ፡ መሠረት ፡ በታች ፡ ቢመረመር ÷ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስላደረጉት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤልን ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ እጥላለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፴፰ ከሐናኤል ፡ ግንብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማዕዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ከተማ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመን ÷ እነሆ ÷ ይመጣል ÷ ይላል ፡

፴፱ እግዚአብሔር ። የተለካበትም ፡ ገመድ ፡ ወደ ፡ ጋራብ ፡ ከረብታ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይሄዳል ÷ ወደ ፡ ጎዓም ፡ ይዘራል ። የሬሳም ፡ ሸለቆ ፡ ሁሉ ፡ የአመድም ፡ እርሻ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስከለው ፡ እስከ ፡ ፈረሰ ፡ በር ፡ ማዕዘን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆናል ፡ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ለዘላለም ፡ አይነቀልም ፡ አይፈርስምም ።

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

፩ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በአሥረኛው ፡ ዓመት ÷ በናቡከደነፆር ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ÷ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፪ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከብቦ ፡ ነበር ፡ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በነበረው ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡ ታስሮ ፡ ነበር ። ፫ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አስጠብቆት ፡ ነበርና ፡— ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ትንቢት ፡ ትናገራለህ ፡— እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ፡ እርሱም ፡ ይይዛታል ፡ ፬ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በእውነት ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አልፎ ፡ ይሰጣል ፡ እኛ ፡ ለአፍም ፡ ይናገረዋል ÷ ዓይኑም ፡ ዓይኑን ፡ ያያል ፡ እንጂ ፡ ከከለዳውያን ፡ እጅ ፡ አያመልጥም ፡ እርሱም ፡ ሴዴቅያስን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሰዋል ፡ እኔም ፡ እስከ ፡ ብኋኋ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ይኖራል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ከከለዳውያን ፡ ጋር ፡ ብትዋጉ ፡ ምንም ፡ አትረቡም ።

፮ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ፯ እነሆ ÷ የአጐትህ ፡ የሰሎም ፡ ልጅ ፡ አናምኤል ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መጥቶ ፡— ትገዛው ፡ ዘንድ ፡ መቤዠቱ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፡ በኃናቶት ፡ ያለውን ፡ እርሻዬን ፡ ግዛ ፡ ርስቱ ፡ የአንተ ፡ ነውና ÷ መቤዠቱም ፡ የአንተ ፡ ነውና ፡ ለአንተ ፡ ግዛው ፡ አለኝ ። ፰ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቅሁ ። በኃናቶትም ፡ ያለውን ፡ እርሻ ፡ ከአጐቴ ፡ ልጅ ፡ ከአናምኤል ፡ ገዛሁ ÷ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ሰቅል ፡ ብርም ፡ መዘንሁለት ። ፱ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ፈረምሁ ፡ አተምሁትም ፡ ምስክሮችንም ፡ ጠርቼ ፡ ብሩን ፡ በሚዛን ፡ መዘንሁለት ። ፲ የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወሰድሁ ፡ የአጐቴም ፡ ልጅ ፡ አናምኤል ፡ የውሉንም ፡ ወረቀት ፡ የፈረሙ ፡ ምስክሮች ÷ በግዞትም ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡ የተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ እያዩ ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ለመሕሚያ ፡ ልጅ ፡ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠሁት ። ፲፩ በፊታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ባሮክን ፡ አዘዝሁት ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ብዙ ፡ ቀን ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ ይህን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወስደህ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አኑራቸው ። ፲፪ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— ሰዎች ፡ በዚህች ፡ ምድር ፡ ቤትንና ፡ እርሻን ፡ የወይን ፡ ቦታንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይገዛሉ ።

፲፫ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክም ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ከሰጠሁት ፡ በኋላ ÷ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለይሁ ፡— ፲፬ አቤቱ ፡ ጌታ ፡ እግ

ዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ እነሆ ÷ አንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በታላቅ ፡ ኃይልህና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድህ ፡ ፈጥረሃል ÷ ከአንተም ፡ የሚያቅት ፡ ነገር ፡ የለም ። ፲፭ ለብዙ ፡ ሺህ ፡ ምሕረት ፡ ታደርጋለህ ÷ የአባቶችንም ፡ በደል ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ በልጆቻቸው ፡ ብብት ፡ ትመልሳለህ ፡ ስምህ ፡ ታላቅና ፡ ኃያል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ፲፮ በምክር ፡ ታላቅ ፡ በሥራም ፡ ብርቱ ፡ ነህ ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ መንገዱና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ዓይኖችህ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ተገልጠዋል ። ፲፯ አንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በታላቅ ፡ ኃይልህና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድህ ፡ ፈጥረሃል ÷ ከአንተም ፡ የሚያቅት ፡ ነገር ፡ የለም ። ፲፰ ለብዙ ፡ ሺህ ፡ ምሕረት ፡ ታደርጋለህ ÷ የአባቶችንም ፡ በደል ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ በልጆቻቸው ፡ ብብት ፡ ትመልሳለህ ፡ ስምህ ፡ ታላቅና ፡ ኃያል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ፲፱ በምክር ፡ ታላቅ ፡ በሥራም ፡ ብርቱ ፡ ነህ ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ መንገዱና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ዓይኖችህ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ተገልጠዋል ። ፳ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ምልክትንና ፡ ድንቅን ፡ ነገር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ደግሞም ፡ በእስራኤልና ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አድርገሃል ÷ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ለአንተ ፡ ስም ፡ አድርገሃል ። ፳፩ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፥ በብርቱ ፡ እጅና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድ ፡ በታላቅም ፡ ግርማ ፡ ሕዝብህን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣህ ። ፳፪ ትሰጣቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልህላቸውን ፡ ምድር ÷ ወተትና ፡ ማርንም ፡ የምታፈስሰውን ፡ ምድር ÷ ሰጠሃቸው ። ፳፫ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ ወረሱአት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቃልህን ፡ አልሰሙም ፡ በሕግህም ፡ አልሄዱም ÷ ያደረጉም ፡ ዘንድ ፡ ካዘዝሃቸው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ አላደረጉም ፡ ስለ ዚህ ፡ ይህን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አመጣህባቸው ። ፳፬ እነሆ ፡ የአፈር ፡ ድልድል ፡ ተ ሊይዙአትም ፡ እስከ ፡ ከተማይቱ ፡ ድረስ ፡ ቀርበዋል ፡ ከሰይፍና ፡ ከራብ ፡ ከቸነፈርም ፡ የተነሣ ፡ ከተማይቱ ፡ የሚዋጉአት ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ÷ የተናገርኸውም ፡ ሆኖአል ፡ እነሆም ÷ አንተ ፡ ታየዋለህ ። ፳፭ አንተም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡— አርሻውን ፡ በብር ፡ ግዛ ፡ ምስክሮች ንም ፡ ጥራ ፡ አልኸኝ ፡ ከተማይቱ ፡ ግን ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ።

፳፮ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ፳፯ እነሆ ፡ እኔ ፡ የሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ በውኑ ፡ እኔን ፡ የሚያቅተኝ ፡ ነገር ፡ አለን ? ፳፰ ስለ ዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅና ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ÷ እርሱም ፡ ይይዛታል ። ፳፱ ይህችን ፡ ከተማ ፡ የሚጠ ፡ ከለዳውያን ፡ መጥተው ፡ በእሳት ፡ ያነድዱአታል ፤ ያስቈጡኝም ፡ ዘንድ ፡ በሰገነታቸው ፡ ላይ ፡ ለበኣል ፡ ካጠኑባቸው ÷ ለሌሎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርብን ፡ ካፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ ያቃጥሉአታል ። ፴ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከታናሽነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ በፊቴ ፡ ክፋ ፡ ነገርን ፡ ብቻ ፡ አድርገዋልና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እኔን ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ከማስቈጣት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አላደረጉምና ። ፴፩ ከፊቴ ፡ እስወግዳት ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ከሠሩአት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ቍጣዬንና ፡ መዓቴን ፡ ለማነሣሣት ፡ ሆናለችና ፡ ይህም ፡ እኔን ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ እነርሱና ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ አለቆቻቸውም ፡ ካህናቶቻቸውም ፡ ነቢያቶቻቸውም ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ÷ ስላደረጉት ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ልጆችና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ፴፪ ፊታቸውንም ፡ ሰደቡኝ ፡ ጀርባቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መለሱ ፡ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ሰስ ተምሬቸው ፡ ተግሣጽን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ አልሰሙም ። ፴፫ ያረከሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኖሩ ። ፴፬ ይሁዳን ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ እንዲያገቡት ÷ ይህንን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ እኔ ፡ ያላዘዝሁትንና ፡ በልቤ ፡ ያላሰብሁትን ፡ ነገር ÷ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የበእልን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠሩ ።

፴፭ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡— በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈረም ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ ስለምትላት ፡ ከተማ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍቴ ፡ እነርሱን ፡ ከሰደድሁበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ እሰበስባቸዋለሁ ÷ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለሁ ፡ ተዘልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አደርጋለሁ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይሆኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናቸዋለሁ ። ፴፰ ለእነርሱም ፡ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ ለልጆቻቸው ፡ መልካም ፡ ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ እንዲፈሩኝ ፡ አንድ ፡ ልብና ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ እሰጣቸዋለሁ ። ፴፱ ለእነርሱም ፡ ከማደርገው ፡ በጎ ፡ ነት ፡ አልመለስም ፡ ስል ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የዘላለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እገባለሁ ፡ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳይሉ ፡ መፈራቴን ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አኖራለሁ ። ፵ ለእነርሱም ፡ መልካም ፡ ያደርጉላቸው ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡ ነፍሴ ፡ በዘሀይ ፡ ምድር ፡ እተክላቸዋለሁ ። ፵፩ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— እነሆ ÷ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅና ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ÷ እርሱም ፡ ይይዛታል ። ፵፪ ይህችን ፡ ከተማ ፡ የሚጠ ፡ ከለዳውያን ፡ መጥተው ፡ በእሳት ፡ ያነድዱአታል ፤ ያስቈጡኝም ፡ ዘንድ ፡ በሰገነታቸው ፡ ላይ ፡ ለበኣል ፡ ካጠኑባቸው ÷ ለሌሎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርብን ፡ ካፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ ያቃጥሉአታል ። ፵፫ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከታናሽነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ በፊቴ ፡ ክፋ ፡ ነገርን ፡ ብቻ ፡ አድርገዋልና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እኔን ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ከማስቈጣት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አላደረጉምና ። ፵፬ ከፊቴ ፡ እስወግዳት ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ከሠሩአት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ቍጣዬንና ፡ መዓቴን ፡ ለማነሣሣት ፡ ሆናለችና ፡ ይህም ፡ እኔን ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ እነርሱና ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ አለቆቻቸውም ፡ ካህናቶቻቸውም ፡ ነቢያቶቻቸውም ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ÷ ስላደረጉት ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ልጆችና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ፵፭ ፊታቸውንም ፡ ሰደቡኝ ፡ ጀርባቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መለሱ ፡ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ሰስ ተምሬቸው ፡ ተግሣጽን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ አልሰሙም ። ፵፮ ያረከሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኖሩ ። ፵፯ ይሁዳን ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ እንዲያገቡት ÷ ይህንን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ÷ እኔ ፡ ያላዘዝሁትንና ፡ በልቤ ፡ ያላሰብሁትን ፡ ነገር ÷ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የበእልን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠሩ ።

፵፮ እነግዲህ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ ስለምትላት ፡ ከተማ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍቴ ፡ እነርሱን ፡ ከሰደድሁበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ እሰበስባቸዋለሁ ÷ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለሁ ፡ ተዘልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አደርጋለሁ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይሆኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆናቸዋለሁ ። ፵፯ ለእነርሱም ፡ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ ለልጆቻቸው ፡ መልካም ፡ ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ እንዲፈሩኝ ፡ አንድ ፡ ልብና ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ እሰጣቸዋለሁ ። ፵፰ ለእነርሱም ፡ ከማደርገው ፡ በጎ ፡ ነት ፡ አልመለስም ፡ ስል ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የዘላለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እገባለሁ ፡ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳይሉ ፡ መፈራቴን ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አኖራለሁ ። ፵፱ ለእነርሱም ፡ መልካም ፡ ያደርጉላቸው ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡ ነፍሴ ፡ በዘሀይ ፡ ምድር ፡ እተክላቸዋለሁ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— እነሆ ÷ እኔ ፡ በዚህች ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳመጣሁ ፡ እንዲሁ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የተናገርሁላቸውን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አመጣላቸዋለሁ ። ፶ በዚህች ፡ ምድር ፡ ሜዳ ፡ ይገዛሉ ፡ እናንተም ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ የምትሉአት ፡ ባድማ ፡ ናት ፡ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ በምትሉአት ፡ ምድር ፡ እርሻን ፡ ይገዛሉ ። ፶፩ ምርኮኞቻቸውንም ፡ እመልሳለሁና ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ በሉ ፡ ስፍራዎች ፡ በይሁዳም ፡ ከተሞች ፡ በደጋውም ፡ በሉ ፡ ከተሞች ፡ በቄላውም ፡ በሉ ፡ ከተሞች ፡ በደቡብም ፡ በሉ ፡ ከተሞች ÷ ሰዎች ፡ እርሻውን ፡ በብር ፡ ይገዛሉ ፡ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ፈርመው ፡ ያትማሉ ፡ ምስክሮችንም ፡ ይጠራሉ ።

ምዕራፍ ፴፫

፩ ኤርምያስ ፣ ገና ፣ በግዞት ፣ ቤት ፣ አደባባይ ፣ ታስሮ ፣ ሰለ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ቃል ፣ ሁለተኛ ፣
፪ ጊዜ ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ መጣለት ፦— ስሙ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሆነ ÷ ያደረገው ፣ እግዚአብሔር ÷
ያጸናውም ፣ ዘንድ ፣ የሠራው ፣ እግዚአብሔር ፣
፫ እንዲህ ፣ ይላል ፦— ወደ ፣ እኔ ፣ ጩኽ ÷ እኔም ፣
እመልስልሃለሁ ፤ አንተም ፣ የማታውቀውን ፣
፬ ታላቅና ፣ ኃይለኛ ፣ ነገርን ፣ አሳይሃለሁ ። የእስ
ራኤል ፣ አምላክ ፣ እግዚአብሔር ፣ ለአፈር ፣ ድል
ድልና ፣ ለምሽግ ፣ ስለ ፣ ፈረሱ ፣ ስለዚህች ፣ ከተማ ፣
ቤቶች ÷ ስለ ፣ ይሁዳም ፣ ነገሥታት ፣ ቤቶች ፣
፭ እንዲህ ፣ ይላልና ፦— ከለዳውያን ፣ ለመዋጋት ፣
መጥተዋል ፤ ነገር ፣ ግን ፣ በቍጣዬና ፣ በመዓቴ ፣
በገደልኋቸው ፣ ሰዎች ፣ ሬሳዎች ፣ ሊሞሉአቸው ፣
ነው ÷ ስለ ፣ ክፋታቸው ፣ ሁሉ ፣ ፊቴን ፣ ከዚ
፮ ህች ፣ ከተማ ፣ ሰውሬአለሁና ። እነሆ ÷ ፈውስ
ንና ፣ መድኃኒትን ፣ አመጣላታለሁ ÷ እፈውሳቸ
ውማለሁ ፤ የሰላምንና ፣ የእውነትን ፣ ብዛት ፣ አገ
፯ ልጥላቸዋለሁ ። የይሁዳን ፣ ምርኮና ፣ የእስራ
ኤልንም ፣ ምርኮ ፣ እመልሳለሁ ÷ ቀድሞም ፣
፰ እንደ ፣ ነበሩ ፣ አድርጌ ፣ እሠራቸዋለሁ ። እኔ
ንም ፣ ከበደሉበት ፣ ኃጢአት ፣ ሁሉ ፣ እነጻቸዋ
ለሁ ፣ እኔንም ፣ የበደሉኝን ፣ ያመፁብኝንም ፣
፱ ኃጢአታቸውን ፣ ሁሉ ፣ ይቅር ፣ እላለሁ ። ይህ
ችም ፣ ከተማ ፣ እኔ ፣ የምሠራላቸውን ፣ በጎነት ፣
ሁሉ ፣ በሚሰሙ ፣ እኔም ፣ ስለመጣሁላቸው ፣
በጎነትና ፣ ሰላም ፣ ሁሉ ፣ በሚፈሩና ፣ በሚደነ
ግጡ ፣ አሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ ፊት ፣ ለደስታ ፣ ስም ፣
ለምስጋናም ፣ ለክብርም ፣ ትሆናለች ።

፲ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— እናንተ ፣—
ያለ ፣ ሰውና ፣ ያለ ፣ እንስሳ ፣ ያለች ፣ በድማ ፣ ናት ፣
በምትሉአት ፣ በዚህች ፣ ስፍራ ÷ የሚቀመጥባ
ቸው ፣ በሌላ ÷ ያለ ፣ ሰውና ፣ ያለ ፣ እንስሳ ፣
በድማ ፣ በሆኑ ፣ በይሁዳ ፣ ከተሞችና ፣ በኢየ
፲፩ ሩሳሌም ፣ አደበባይ ÷ የሐሤት ፣ ድምፅና ፣ የደ
ስታ ፣ ድምፅ ÷ የወንድ ፣ ሙሽራ ፣ ድምፅና ፣
የሴት ፣ ሙሽራ ፣ ድምፅ ፦— እግዚአብሔር ፣
ቸር ፣ ነውና ÷ ምሕረቱም ፣ ለዘላለም ፣ ነውና ፣
የሠራዊትን ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔርን ፣ አመስ
ግኑ ፣ የሚሉ ፣ ድምፅ ÷ ወደ ፣ እግዚአብሔርም ፣
ቤት ፣ የምስጋናን ፣ መሥዋዕት ፣ የሚያመጡት ፣
ድምፅ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ይሰማል ። የምድርን ፣
ምርኮ ፣ ቀድሞ ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ አድርጌ ፣ እመል
ሳለሁና ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ።

፲፪ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣
ይላል ፦— በድማ ፣ ሆኖ ÷ ያለ ፣ ሰውና ፣ ያለ ፣ እን
ስሳ ፣ ባለው ፣ በዚህ ፣ ስፍራ ፣ በከተሞችም ፣
ሁሉ ፣ መንጎቻቸውን ፣ የሚያሳርፉት ፣ የአረ
፲፫ ኞች ፣ መናሪያ ፣ ይሆናል ። በደጋው ፣ ላይ ፣
ባሉ ፣ ከተሞች ፣ በቈላውም ፣ ባሉ ፣ ከተሞች ፣
በደቡብም ፣ ባሉ ፣ ከተሞች ÷ በብንያምም ፣
አገር ፣ በኢየሩሳሌምም ፣ ዙሪያ ፣ ባሉ ፣ ስፍራ
ዎች ÷ በይሁዳም ፣ ከተሞች ፣ መንጎቹ ፣ በተቈጣ
ጣሪው ፣ እጅ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ያልፋሉ ÷ ይላል ፣
እግዚአብሔር ።

፲፬ እነሆ ÷ ስለ ፣ እስራኤል ፣ ቤትና ፣ ስለ ፣ ይሁዳ ፣
ቤት ፣ የተናገርሁትን ፣ መልካም ፣ ቃል ፣ የምፈ
ጽምበት ፣ ዘመን ፣ ይመጣል ÷ ይላል ፣ እግዚአ
ብሔር ። በዚያም ፣ ዘመን ፣ በዚያም ፣ ጊዜ ፣ ለዳ
፲፭ ዊት ፣ የጽድቅን ፣ ቍጥጥር ፣ አበቅልለታለሁ ፣
እርሱም ፣ ፍርድንና ፣ ጽድቅን ፣ በምድር ፣ ያደ
ርጋል ። በዚያም ፣ ዘመን ፣ ይሁዳ ፣ ይድናል ፣
ኢየሩሳሌምም ፣ ተዘልላ ፣ ትቀመጣለች ፣ የም
ትጠራበትም ፣ ስም ፦— እግዚአብሔር ፣ ጽድቃ
ችን ፣ ተብሎ ፣ ነው ። እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣
፲፮ ይላልና ፦— በእስራኤል ፣ ቤት ፣ ዙፋን ፣ ላይ ፣
የሚቀመጥ ፣ ሰው ፣ ከዳዊት ፣ ዘንድ ፣ አይታ
ጣም ፤ የሚቃጠለውንም ፣ መሥዋዕት ፣ የሚያ
፲፯ ቀርብ ፣ የእህሉንም ፣ ቍርባን ፣ የሚያቃጥል ፣
ሁልጊዜም ፣ የሚሠዋ ፣ ሰው ፣ ከሌዋውያን ፣ ከህ
ናት ፣ ዘንድ ፣ በእኔ ፣ ፊት ፣ አይታጣም ።

፲፰ የእግዚአብሔርም ፣ ቃል ፣ ወደ ፣ ኤርምያስ ፣
፲፱ እንዲህ ፣ ሲል ፣ መጣ ፦— እግዚአብሔር ፣ እን
ዲህ ፣ ይላል ፦— ቀንና ፣ ሌሊት ፣ በወራቱ ፣ እንዳ
ይሆን ፣ የቀን ፣ ቃል ፣ ኪዳኔንና ፣ የሌሊት ፣ ቃል ፣
ኪዳኔን ፣ ማፍረስ ፣ ብትችሉ ÷ በዙፋኑ ፣ ላይ ፣
፳፩ የሚነግሥ ፣ ልጅ ፣ እንዳይሆንለት ፣ ከባሪያዬ ፣
ከዳዊት ፣ ጋር ÷ ከአገልጋዮቼም ፣ ከሌዋውያን ፣
ከህናት ፣ ጋር ፣ ያለው ፣ ቃል ፣ ኪዳኔ ፣ ደግሞ ፣
፳፪ ይፈርሳል ። የሰማይን ፣ ሠራዊት ፣ መቍጠር ፣
የባሕርንም ፣ አሸዋ ፣ መስፈር ፣ እንደማይቻል ÷
እንዲሁ ፣ የባሪያዬን ፣ የዳዊትን ፣ ዘርና ፣ የሚያ
ገለግሉኝን ፣ ሌዋውያንን ፣ አበዛለሁ ።

፳፫ የእግዚአብሔርም ፣ ቃል ፣ ወደ ፣ ኤርምያስ ፣ እን
፳፬ ዲህ ፣ ሲል ፣ መጣ ፦— ይህ ፣ ሕዝብ ፦— እግዚአ
ብሔር ፣ የመረጣቸውን ፣ ሁለቱን ፣ ወገን ፣ ጥሎ
አቸዋል ፣ ያለውን ፣ ነገር ፣ አትመለከትምን ?
እንዲሁ ፣ በፊታቸው ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣
ሕዝብ ፣ እንዳይሆን ፣ ሕዝቤን ፣ አቃልለዋል ።
፳፭ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— የቀንና ፣
የሌሊት ፣ ቃል ፣ ኪዳኔን ፣ የሰማይንና ፣ የምድ
፳፮ ርንም ፣ ሥርዓት ፣ ያላጸናሁ ፣ እንደ ፣ ሆነ ÷ እኔም ፣
ደግሞ ፣ በአብርሃምና ፣ በይስሐቅ ፣ በያዕቆብም ፣
ዘር ፣ ላይ ፣ ገዦች ፣ ይሆኑ ፣ ዘንድ ፣ ከዘሩ ፣ እንዳ
ልወስድ ÷ የያዕቆብንና ፣ የባሪያዬን ፣ የዳዊትን ፣
ዘር ፣ እጥላለሁ ። ምርከአቸውን ፣ እመልሳለ
ሁና ÷ እምራቸውማለሁና ።

ምዕራፍ ፴፬

፩ የባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ ናቡከደነፆርና ፣ ሠራ
ዊቱ ፣ ሁሉ ፣ ከእርሱም ፣ ግዛት ፣ በታች ፣ ያሉ ፣ የም
ድር ፣ መንግሥታት ፣ ሁሉ ፣ አሕዛብም ፣ ሁሉ ፣
ኢየሩሳሌምንና ፣ ከተሞችዋን ፣ ሁሉ ፣ ይወጉ ፣
በነበረ ፣ ጊዜ ÷ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ወደ ፣
፪ ኤርምያስ ፣ የመጣ ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ። የእስ
ራኤል ፣ አምላክ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣

፫ ይላል ፦— ሂድ ፣ ለይሁዳም ፣ ንጉሥ ፣ ለሴዴቅ
ያስ ፣ ተናገር ፣ እንዲህም ፣ በለው ፦— እግዚአብ
ሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— እነሆ ÷ ይህችን ፣
ከተማ ፣ በባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ እጅ ፣ አሳልፌ ፣
፬ እሰጣለሁ ÷ በእሳትም ፣ ያቃጥላታል ፣ አንተም ፣
በእርግጥ ፣ ትያዛለህ ፣ በእጁም ፣ አልፈህ ፣ ትሰ
ጣለህ ፣ ኣንጂ ፣ ከእጁ ፣ አታመልጥም ፣ ዓይን
ህም ፣ የባቢሎንን ፣ ንጉሥ ፣ ዓይን ÷ ታያለች ÷
እርሱም ፣ ከአንተ ፣ ጋር ፣ አፍ ፣ ለአፍ ፣ ይናገ
፭ ራል ÷ ወደ ፣ ባቢሎንም ፣ ትገባለህ ። ነገር ፣
ግን ÷ የይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ ሴዴቅያስ ፣ ሆይ ÷ የእ
ግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣ ስማ ፣ እግዚአብሔር ፣
ስለ ፣ አንተ ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— በሰይፍ ፣ አት
፮ ሞትም ፣ በሰላም ፣ ትሞታለህ ፣ እንጂ ፣ ከአ
ንተ ፣ በፊት ፣ እንደ ፣ ነበሩ ፣ እንደ ፣ ዳሮ ፣ ነገ
ሥታት ፣ እንደ ፣ አባቶችህ ፣ መቃጠል ÷ እን
ዲሁ ፤ ያቃጥሉሃልና ፦— ወየው ! ጌታ ፣ ሆይ ፣
እያሉ ፣ ያለቅሱልሃል ፣ እኔ ፣ ቃልን ፣ ተናግሬአ
፯ ለሁና ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ።
፰ የባቢሎንም ፣ ንጉሥ ፣ ሠራዊት ፣ ኢየሩሳሌ
ምንና ፣ የቀሩትን ፣ የይሁዳን ፣ ከተሞች ፣ ሁሉ ÷
ከተመሸጉት ፣ ከይሁዳ ፣ ከተሞች ፣ የተረፉትን ፣
ለኪሶንና ፣ ዓዜቃን ፣ በወጋ ፣ ጊዜ ÷ ነቢዩ ፣
ኤርምያስ ፣ ይህን ፣ ቃል ፣ ሁሉ ፣ ለይሁዳ ፣
፱ ንጉሥ ፣ ለሴዴቅያስ ፣ በኢየሩሳሌም ፣ ነገረው ።
፲ ሰው ፣ ሁሉ ፣ ሰብራሪ ፣ የሆነውን ፣ ወንድ ፣ ባሪ
ያውንና ፣ ሰብራሪት ፣ የሆነች ፣ ሴት ፣ ባሪያውን ፣
አርነት ፣ እንዲያወጣ ÷ አይሁዳዊ ፣ ወንድሙ
ንም ፣ ማንም ፣ እንዳይገዛ ÷ ስለ ፣ አርነታቸው ፣
አዋጅ ፣ እንዲነገር ፣ ንጉሡ ፣ ሴዴቅያስ ፣ በኢየ
ሩሳሌም ፣ ከነበሩ ፣ ሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ጋር ፣ ቃል ፣
ኪዳን ፣ ከደረገ ፣ በኋላ ÷ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣
ወደ ፣ ኤርምያስ ፣ የመጣው ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ።
፲፩ ሰው ፣ ሁሉ ፣ ወንድ ፣ ባሪያውንና ፣ ሴት ፣ ባሪያውን ፣
አርነት ፣ እንዲያወጣ ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህም ፣
ማንም ፣ እንዳይገዛቸው ፣ ወደ ፣ ቃል ፣ ከ ፣ ሃሉ ፣
የገቡ ፣ አለቆች ፣ ሁሉና ፣ ሕዝቡ ፣ ሁሉ ፣ ሰሙ ፣
፲፪ አርነትም ፣ አወጡአቸው ። ነገር ፣ ግን ፣ ከዚያ ፣
በኋላ ፣ ተመልሰው ፣ አርነት ፣ ያወጡአቸውን ፣
ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ባሪያዎቻቸውን ፣ አስመ
ለሱ ÷ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ባሪያዎችም ፣ አደር
፲፫ ገው ፣ ገዙአቸው ። ስለዚህ ፣ የእግዚአብሔር ፣
ቃል ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ ወደ ፣ ኤርምያስ ፣
፲፬ እንዲህ ፣ ሲል ፣ መጣ ፦— የእስራኤል ፣ አምላክ ፣
እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— አባቶቻች
ሁን ፣ ከባርነት ፣ ቤት ፣ ከግብጽ ፣ አገር ፣ በወጣ
ኋቸው ፣ ቀን ፣ ከእነርሱ ፣ ጋር ፣ እንዲህ ፣ ብዬ ፣
፲፭ ቃል ፣ ኪዳን ፣ አደረግሁ ፦— ሰባት ፣ ዓመት ፣
በተፈጸመ ፣ ጊዜ ÷ የተሸጠላችሁን ፣ ስድስት ፣
ዓመት ፣ የተገዛላችሁን ፣ ሰብራሪ ፣ ወንድማች
ሁን ፣ እያንዳንዳችሁ ፣ አርነት ፣ ታወጡታላ
ችሁ ÷ እያንዳንዱም ፣ ያወጣዋል ፣ አባቶቻችሁ ፣
ግን ፣ አልሰሙኝም ፣ ጆሮአቸውንም ፣ አላዘነበ
፲፮ ሉም ። እናንተም ፣ ዛሬ ፣ ተመልሳችሁ ፣ ሰው ፣
ሁሉ ፣ ባልንጀራውን ፣ አርነት ፣ ለማውጣት ፣
አዋጅ ፣ በመንገር ፣ ለኃይኔ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝን ፣
ነገር ፣ አድርጋችሁ ፣ ነበር ÷ በስሜም ፣ በሚጠራ
በት ፣ ቤት ፣ ሙስዋ ፣ በፊቴ ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ አድ
ርጋችሁ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ተመልሳችሁ ፣ ፲፯፣
ስሜን ፣ አስነቀፋችሁ ÷ እያንዳንዳችሁም ፣ በፈ
ቃዳቸው ፣ እንዲሄዱ ፣ አርነት ፣ ያወጣችኋቸ
ውን ፣ ወንድና ፣ ሴት ፣ ባሪያዎቻችሁን ፣ አስመ
ለሳችሁ ÷ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ባሪያዎችም ፣
እንዲሆኑላችሁ ፣ ገዛችኋቸው ።

ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦— ፲፯፣
ሰው ፣ ሁሉ ፣ ለወንድሙና ፣ ለባልንጀራው ፣
የአርነት ፣ አዋጅ ፣ ለመንገር ፣ እኔን ፣ አልሰማች
ሁም ፣ እነሆ ፣ እኔ ፣ ለሰይፍና ፣ ለቸነፈር ፣ ለራ
ብም ፣ የአርነት ፣ አዋጅ ፣ እናገር፣ ብችኋለሁ ÷
ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ በምድርም ፣ መንግሥ
ታት ፣ ሁሉ ፣ መከከል ፣ እንድትበተኑ ፣ አደርጋ
ችኋለሁ ። ቃል ፣ ኪዳኔንም ፣ የተላለፋችኁ ፣ ፲፰፣
ሰዎች ፣ እንቦሳውንም ፣ ቈርጠው ፣ በቍራጩ ፣
መካከል ፣ ባለፉ ፣ ጊዜ ፣ በፊቴ ፣ ያደረጉትን ፣
የቃል ፣ ኪዳንን ፣ ቃል ፣ ያልፈጸሙትን ÷ የይ ፲፱፣
ሁዳን ፣ አለቆችና ፣ የኢየሩሳሌምን ፣ አለቆች ፣
ጃንደረቦችን ፣ ካህናትንም ፣ በእንቦሳም ፣
ቍራጭ ፣ መካከል ፣ ያለፉትን ፣ የእንፋን ፣
ሕዝብ ፣ ሁሉ ፣ ለጠላቶቻቸው ፣ እጅ ፣ ነፍሳቸ ፳፣
ውንም ፣ ለሚሹአት ፣ እጅ ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣ
ለሁ ፣ ሬሳቸውም ፣ ለሰማይ ፣ ወፎችና ፣ ለም
ድር ፣ አራዊት ፣ መብል ፣ ይሆናል ። የይሁዳ ፳፩፣
ንም ፣ ንጉሥ ፣ ሴዴቅያስንና ፣ አለቆቹን ፣ ለጠላ
ቶቻቸው ፣ እጅ ፣ ነፍሳቸውንም ፣ ለሚሹአት ፣
እጅ ፣ ከእናንተም ፣ ለተመለሱት ፣ ለባቢሎን ፣
ንጉሥ ፣ ሠራዊት ፣ እጅ ፣ አሳልፌ ፣ እሰጣለሁ ።
እነሆ ፣ እገዘለሁ ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ÷ ፳፪፣
ወደዚህችም ፣ ከተማ ፣ እመልሳቸዋለሁ ፣ እርስ
ዋንም ፣ ይወጋሉ ፣ ይይዙአትማል ፣ በእሳትም ፣
ያቃጥሉአታል ፣ የይሁዳንም ፣ ከተሞች ፣ ሰው ፣
የሌለበት ፣ ባድማ ፣ አደርጋቸዋለሁ ።

ምዕራፍ ፴፭

፩ በይሁዳ ፣ ንጉሥ ፣ በኢዮስያስ ፣ ልጅ ፣ በኢ
ዮአቄም ፣ ዘመን ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣
ወደ ፣ ኤርምያስ ፣ የመጣ ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ፦—
፪ ወደ ፣ ሬካባውያን ፣ ቤት ፣ ሂደህ ፣ ተናገራቸው ÷
ወደ ፣ እግዚአብሔርም ፣ ቤት ፣ ከንዳምቹ ፣ ወደ ፣
አንዱቱ ፣ አግባቸው ፣ የወይን ፣ ጠጅም ፣ አጠ
ጣቸው ። የከባስንን ፣ ልጅ ፣ የኢርምያስን ፣ ፫፣
ልጅ ፣ ያዝንያን ፣ ወንድሞቹንም ፣ ልጆቹንም ፣
ሁሉ ፣ የሬካባውያንን ፣ ወገን ፣ ሁሉ ፣ ወሰድኋ
ቸው ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔርም ፣ ቤት ፣ በበረ ፬፣
ኛው ፣ በሰሎም ፣ ልጅ ፣ በመሶሜያ ፣ ዓዳ ፣ በላይ ፣
ባለው ፣ በአለቆች ፣ ዓዳ ፣ አጠገብ ፣ ወዳለው ፣
ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሰው ፣ ወደ ፣ ጌደልያ ፣
ልጅ ፣ ወደ ፣ ሐናን ፣ ልጆች ፣ ዓዳ ፣ አገበኋቸው ።
በሬካባውያንም ፣ ልጆች ፣ ፊት ፣ የወይን ፣ ጠጅ ፣ ፭፣

የሞላባቸውን ፥ ማድጋዎችንና ፥ ጽዋዎችን ፥
አኑሬ ፡፡ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ ጠጡ ፡ አልኋቸው ።
፮ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡ — የወይኑን ፡
ጠጅ ፡ አንጠጣም ፡ አባታችን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡
ኢዮናዳብ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዝዞናልና ፡ —
እናንተና ፡ ልጆቻችሁ ፡ ለዘላለም ፡ የወይን ፡
፯ ጠጅ ፡ አትጠጡ ። በምትኖሩባት ፡ ምድር ፡
ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንድትኖሩ ፡ በዕድሜአ
ችሁ ፡ ሙሉ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፡
እንጂ ፡ ቤትን ፡ አትሥሩ ፡ ዘርንም ፡ አትዝሩ ፡
ወይንም ፡ አትትከሉ ፡ አንዳችም ፡ አይሁንላ
፰ ችሁ ። እኛም ፡ የአባታችንን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡
የኢዮናዳብን ፡ ቃል ፡ በዘዘን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ታዝዘናል ። እኛም ፡ ሚስቶቻችንም ፡ ወንዶ
ችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ ዕድሜአችንን ፡
፱ ሙሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አልጠጣንም ። የምን
ቀመጥበትንም ፡ ቤት ፡ አልሠራንም ፡ የወይን ፡
፲ ቦታና ፡ እርሻ ፡ ዘርም ፡ የለንም ። በድንኳንም ፡
ውስጥ ፡ ተቀምጠናል ፡ ታዝዘናል ፡ አባታች
ንም ፡ ኢዮናዳብ ፡ ያዘዘንን ፡ ሁሉ ፡ አድርገናል ።
፲፩ ነገር ፡ ግን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
ወደዚህች ፡ ምድር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ — ኑ ፡ ከከለ
ዳውያን ፡ ሠራዊትና ፡ ከሶርያ ፡ ሠራዊት ፡ ፊት ፡
የተነሣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንሂድ ፡ አልን ፡
እንዲሁም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጥን ።
፲፪ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡
፲፫ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡ — የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡ — ሂድና ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላ
ቸው ፡ — ቃሌን ፡ ትሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ተግሣጽን ፡
አትቀበሉምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፲፬ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ልጆቹ ፡ የወይን ፡
ጠጅ ፡ እንዳይጠጡ ፡ ያዘዛቸው ፡ ቃል ፡ ተፈ
ጸመ ፡ ለአባታቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ታዝዘዋልና ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አይጠጡም ። እኔም ፡ በማ
ለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናግሬአችኋለሁ ፡ ተናገርሁ ፡
፲፭ ሆኖም ፡ አልሰማችሁኝም ። ደግሞም ፡ — እያ
ንዳንዳችሁ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችሁ ፡ ተመለሱ ፡
ሥራችሁንም ፡ አሳምሩ ፡ ታመልኩአቸውም ፡
ዘንድ ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ፡ ለአ
ናንተና ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ በሰጠሁት ፡ ምድር ፡
ትቀመጣላችሁ ፡ እያልሁ ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡
በሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ሁሉ ፡ ልኬባችሁ ፡
ነበር ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ጆሮአችሁን ፡ አላዘነበላ
፲፮ ችሁም ፡ እኔንም ፡ አልሰማችሁኝም ። የሬካብ ፡
ልጅ ፡ የኢዮናዳብ ፡ ልጆች ፡ አባታቸው ፡ ያዘዘ
ቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽመዋልና ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡
፲፯ ግን ፡ አልሰማኝምና ፡ ስለዚህ ፡ የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡ — እነሆ ፡ በተናገርኋቸው ፡
ጊዜ ፡ አልሰሙምና ፡ ዘመራኋቸውም ፡ ጊዜ ፡
አልመለሱልኝምና ፡ የተናገርሁባቸውን ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡
በሚቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አመጣባቸዋለሁ ።
፲፰ ኤርምያስም ፡ ሬካብውያንን ፡ እንዲህ ፡ አላ
ቸው ፡ — የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — ለአ
በታችሁ ፡ ለኢዮናዳብ ፡ ትእዛዝ ፡ ታዝዛችኋ
ልና ፡ ትእዛዙንም ፡ ሁሉ ፡ ጠብቃችኋልና ፡
፲፱ ያዘዛችሁንም ፡ ፈጽማችኋልና ፡ ስለዚህ ፡ በፊቴ ፡
የሚቆም ፡ ሰው ፡ ከሬካብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮናዳብ ፡
ወገን ፡ ለዘላለም ፡ አይታጣም ።

ምዕራፍ ፡ ፴፮ ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስ
፩ ያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡
ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤር
ምያስ ፡ መጣ ። አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክርታስ ፡
፪ ውሰድ ፡ ለእንተም ፡ ከተናገርሁበት ፡ ቀን ፡ ከኢ
ዮስያስ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ የተናገርሁህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ጻፍበት ።
፫ ምናልባት ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ — እኔ ፡ አደርግባቸ
ዋለሁ ፡ ያልሁትንና ፡ ያሰብሁትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ይሰሙ ፡ ይሆናል ፡ ከክፉ ፡ መንገዳ
ቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ በደላቸው
ንና ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ እል ፡ ዘንድ ።
፬ ኤርምያስም ፡ የኔርያን ፡ ልጅ ፡ ባሮክን ፡ ጠራ ፡
ባሮክም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእርሱ ፡ የተናገረ
ውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመጽ
ሐፉ ፡ ክርታስ ፡ ጻፈ ። ኤርምያስም ፡ ባሮክን ፡
፭ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ፡ — እኔ ፡ ተግገርአለሁ ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አል
ችልም ። አንተ ፡ ግን ፡ ሂድ ፡ ከአፌም ፡ የጻፍ
ኸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በጾም ፡ ቀን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ በክር
ታሱ ፡ አንብብ ፤ ደግሞም ፡ ከከተሞቻቸው ፡
በሚወጡ ፡ በይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ አን
ብበው ። እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
የተናገረው ፡ ቍጣውና ፡ መዓቱ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፡
ምናልባት ፡ ጸሎታቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
፮ ትወድቅ ፡ ይሆናል ፡ ሁሉም ፡ ከክፉ ፡ መንገዱ ፡
ይመለስ ፡ ይሆናል ። የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡
፯ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ ፡
በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።
፰ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስ
ያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡
በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡ ፡
ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ከይሁዳም ፡ ከተሞች ፡ ወደ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፡ የመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ለመጾም ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ። ባሮክም ፡
፱ የኤርምያስን ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
በላይኛው ፡ አደባባይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
በአዲሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ባለው ፡ በጸሐፊው ፡
በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በገማርያ ፡ ጓዳ ፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።

፲ የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የገማርያ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከመጽሐፉ ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጸሐ
ፊው ፡ ጓዳ ፡ ወረደ ፤ እነሆም ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡
ጸሐፊው ፡ ኤሊሳማ ፡ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ ድላያ ፡
የዓከቦር ፡ ልጅ ፡ ኤልናታን ፡ የሳፋን ፡ ልጅ ፡
ገማርያ ፡ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ አለቆ
ቹም ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ሚክ
ያስም ፡ በሰማ ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ ባነ
በበ ፡ ጊዜ ፡ የሰማውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው ።
፲፩ አለቆቹም ፡ ሁሉ ፡ — በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ ያነበብኸ
ውን ፡ ክርታስ ፡ በእጅህ ፡ ይዘህ ፡ ና ፡ የሚል ፡
መልእክት ፡ በኑሪ ፡ ልጅ ፡ በይሁዲ ፡ ልጅ ፡ በና
ታንያ ፡ ልጅ ፡ በይሁዲ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ በሮክ ፡
ላኩ ። የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ክርታሱን ፡
፲፪ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ። እነር
ሱም ፡ — እስኪ ፡ ተቀመጥ ፡ ፥ በጆሮአችንም ፡
አንብብ ፡ አሉት ። ባሮክም ፡ በጆሮአቸው ፡ አነ
በበው ። ቃሉንም ፡ ሁሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈር
ተው ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ ተመካከሩ ፥ ባሮክ
ንም ፡ — ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ ለን
ጉሡ ፡ እንናገራለን ፡ አሉት ። ባሮክንም ፡ —
ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከአፉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡
ጻፍኸው ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። ባሮ
ክም ፡ — ይህን ፡ ቃል ፡ ከአፉ ፡ ይነግረኝ ፡ ነበር ፥
እኔም ፡ በመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ በቀለም ፡ እጽፍ ፡
ነበር ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። አለቆቹም ፡ ባሮ
ክን ፡ — አንተና ፡ ኤርምያስ ፡ ሂዱ ፥ ተሸሸጉ ፥
ወዴትም ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፡
አሉት ።
፲፱ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ገቡ ፥
ክርታሱንም ፡ በጸሐፊው ፡ በኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡
አኑረውት ፡ ነበር ፡ ቃሉንም ፡ ሁሉ ፡ በንጉሡ ፡
ጆሮ ፡ ተናገሩ ። ንጉሡም ፡ ክርታሱን ፡ ያመጣ ፡
ዘንድ ፡ ይሁዲን ፡ ላከ ፥ እርሱም ፡ ከጸሐፊው ፡
ከኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡ ወሰደው ፡ ይሁዲም ፡ በንጉ
ሡና ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ በቆሙት ፡ አለቆች ፡
ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ አነበበው ። ንጉሡም ፡ በዘጠነ
ኛው ፡ ወር ፡ በክረምት ፡ ቤት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥
በፊቱም ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ይነድድ ፡
ነበር ። ይሁዲም ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡
ዓምድ ፡ ያህል ፡ በነበበ ፡ ቀኖር ፥ ንጉሡ ፡
በካራ ፡ ቀደደው ፡ ክርታሱም ፡ በምድጃ ፡
ውስጥ ፡ በለው ፡ እሳት ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪ ፡ ቃ
ጠል ፡ ድረስ ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ወዳለው ፡
እሳት ፡ ጣለው ። ንጉሡም ፡ ይህንም ፡ ቃል ፡
ሁሉ ፡ የሰሙ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ አልፈሩም ፡
ልብሶቻቸውንም ፡ አልቀደዱም ። ነገር ፡ ግን ፡
ኤልናታንና ፡ ድላያ ፡ ገማርያም ፡ ክርታሱን ፡
እንዳያቃጥል ፡ ንጉሡን ፡ ለመኑት ፥ እርሱ ፡
ግን ፡ አልሰማቸውም ። ንጉሡም ፡ ጸሐፊውን ፡
ባሮክንና ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡
የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ይረሕምኤልንና ፡ የዓዝርኤ
ልን ፡ ልጅ ፡ ሠራያን ፡ የዓብድኤልንም ፡ ልጅ ፡
ሰሌምያን ፡ አዘዘ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰወ
ራቸው ።
፳ ንጉሡም ፡ ክርታሱንና ፡ በሮክ ፡ ከኤርምያስ ፡
አፍ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ከቃጠለ ፡ በኋላ ፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ መጣ ፡ — ዳግመኛም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡
፳፩ ውሰድ ፥ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በቃ
ጠለው ፡ ክርታስ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የቀድሞ
ውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ጻፍበት ። የይሁዳንም ፡
፳፪ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፡ — እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — አንተ ፡ — የባ
ቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእርግጥ ፡ ይመጣል ፡ ይህች
ንም ፡ አገር ፡ ያፈርሰታል ፡ ከሰውና ፡ ከእንስ
ሳም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋታል ፡ ብለህ ፡ ለምን ፡ ጻፍህ
በት ? ብለህ ፡ ይህን ፡ ክርታስ ፡ አቃጥለሃል ።
፳፫ ስለዚህም ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኢዮአ
ቄም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — በዳ
ዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀማጭ ፡ አይኖርለትም ፡
ሬሳውም ፡ በቀን ፡ ለትኩሳት ፡ በሌሊትም ፡ ለው
ርጭ ፡ ይጣላል ። ስለ ፡ ኃጢአታቸውም ፡ እር
፳፬ ሱንና ፡ ዘሩን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ እቀጣለሁ ፡ እነር
ሱም ፡ አልሰሙምና ፡ የተናገርሁባቸውን ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእነርሱ ፡ ላይና ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በሚቀመጡ ፡ በይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አመ
ጣለሁ ።
፳፭ ኤርምያስም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡ ወሰደ ፡ ለኔር
ያም ፡ ልጅ ፡ ለጸሐፊው ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠው ፡ እር
ሱም ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በእሳት ፡
ያቃጠለውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከኤር
ምያስ ፡ አፍ ፡ ጻፈበት ፡ ደግሞም ፡ እንደ ፡ ቀድ
ሞው ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ ተጨመረበት ።

ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በይ
፩ ሁዳ ፡ ያነገሠው ፡ የኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅ
ያስ ፡ በኢዮአቄም ፡ ልጅ ፡ በኢኮንያን ፡ ፋንታ ፡
፪ ነገሠ ። እርሱም ፡ ሆነ ፡ ባሪያዎቹ ፡ የአገሩም ፡
ሕዝብ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ እጅ ፡ የተናገረ
ውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።
፫ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ — ወደ ፡ አምላኬችን ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልይ ፡ ብሎ ፡
የሰሌምያን ፡ ልጅ ፡ የኮልንና ፡ ካህኑን ፡ የመዕ
ሤያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ ፡ ላከ ። እርሱንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ገና ፡
፬ አላገቡትም ፡ ነበርና ፡ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡
መካከል ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ነበር ። የፈርዖንም ፡
፭ ሠራዊት ፡ ከግብጽ ፡ ወጣ ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡
ከብበዋት ፡ የነበሩ ፡ ከለዳውያን ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡
በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።
፮ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡
፯ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡ — የእስራ
ኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡ — ከእኔ ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ የላካችሁን ፡
የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፡ — እነሆ ፥

ሊረዳችሁ ፡ የወጣው ፡ የፈርዖን ፡ ሠራዊት ፡
፰ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳል ። ከለዳውያንም ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ይዋጉ
አታል ፡ ይይዙአትማል ፡ በእሳትም ፡ ያቃጥሉአ
፱ ታል ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ — አይ
ሄዳሚና ፦ — ከለዳውያን ፡ በእርግጥ ፡ ከእኛ ፡
ዘንድ ፡ ይጒዳሉ ፡ ብላችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ አታ
፲ ታልሉ ። እናንተንም ፡ የሚዋጉትን ፡ የከለዳ
ውያንን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ብትመቱት ፡ ኖሮ ÷
ከእነርሱም ፡ የተወጉት ፡ ብቻ ፡ ቢቀሩ ፡ ኖሮ ÷
ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በድንኳኑ ፡ ተነሥቶ ፡ ይህ
ችን ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ በቃጠሉአት ፡ ነበር ።
፲፩ የከለዳውያንም ፡ ሠራዊት ፡ ከፈርዖን ፡ ሠራ
ዊት ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በተመ
፲፪ ለሰ ፡ ጊዜ ÷ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡
የርስቱን ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ከዚያ ፡ ይቀበል ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ አገር ፡ ሊሄድ ፡ ከኢየሩሳ
፲፫ ሌም ፡ ወጣ ። በብንያምም ፡ በር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡
የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ የሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ የረያ ፡ የተ
ባለ ፡ የዘበኞች ፡ አለቃ ፡ በዚያ ፡ ነበረ ፡ አር
ሁም ፦ — ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ መኰብለልህ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ያዘው ።
፲፬ ኤርምያስም ፦ — ሐሰት ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ከለዳው
ያን ፡ መኰብለሌ ፡ አይደለም ፡ አለ ፡ አርሁ ፡ ግን ፡
አልሰማውም ÷ የሪያም ፡ ኤርምያስን ፡ ይዞ ፡
፲፭ ወደ ፡ አለቆች ፡ አመጣው ። አለቆችም ፡ ተቈጥ
ተው ፡ ኤርምያስን ፡ መቱት ÷ የጸሐፊውንም ፡
የዮናታንን ፡ ቤት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ አድርገውት ፡
ነበርና ፡ በዚያ ፡ አኖሩት ።
፲፮ ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡
ጓዳም ፡ ገባ ፡ ኤርምያስም ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡
፲፯ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡
አስመጣው ÷ ንጉሡም ፡ በቤቱ ፦ — በውኑ ፡ ከእ
ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አለን ? ብሎ ፡
በቂይታ ፡ ጠየቀው ። ኤርምያስም ፦ — አዎን ፡
አለ ። ደግሞም ፦ — በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡
፲፰ አልፈህ ፡ ትሰጣለህ ፡ አለ ። ኤርምያስም ፡ ደግሞ ፡
ንጉሡን ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ —
በግዞት ፡ ቤት ፡ የማላችሁኝ ፡ አንተን ፡ ወይስ ፡
ባሪያዎችህን ፡ ወይስ ፡ ሕዝብህን ፡ ምን ፡ በድያ
፲፱ ችሁ ፡ ነው ? የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእናንተና ፡
በዚህች ፡ አገር ፡ አይመጣባችሁም ፡ ብለው ፡
ትንቢት ፡ ይናገሩላችሁ ፡ የነበሩ ፡ ነቢያቶቻ
፳ ችሁ ፡ ወዴት ፡ አሉ ? ንጉሡ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡
እንድትሰማኝ ፡ አሁን ፡ አለምንሃለሁ ፤ አባክህ ÷
ልመናዬ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይድረስ ፡ በዚያ ፡ እንዳ
ልሞት ፡ ወደ ፡ ጸሐፈው ፡ ወደ ፡ ዮናታን ፡ ቤት ፡
፳፩ አትመልሰኝ ። ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ አዘዘ ÷
ኤርምያስንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡ አኖ
ሩት ÷ እንጀራም ፡ ሁሉ ፡ ከከተማ ፡ እስኪጠፋ ፡
ድረስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡
ከጋጋሪዎች ፡ መንገድ ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። እን
ዲሁም ፡ ኤርምያስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡
ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የተናገረውን ፡ ፩
ቃል ፡ የማታን ፡ ልጅ ፡ ስፋጥያስ ÷ የጳስኮርም ፡
ልጅ ፡ ጎዶልያስ ÷ የሰሌምያም ፡ ልጅ ፡ ዩኳል ÷
የመልክያም ፡ ልጅ ፡ ጳስኮር ፡ ሰሙ ። ኤርምያስ ፡ ፪
እንዲህ ፡ ብሎአልና ፡ — እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፦ — በዚህች ፡ ከተማ ፡ የሚቀመጥ ፡
በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታል ፡
ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ግን ፡ የሚወጣ ፡ በሕይወት ፡
ይኖራል ÷ ነፍሱም ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ትሆንለታ ፫
ለች ÷ በሕይወትም ፡ ይኖራል ። እግዚአብ
ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ — ይህች ፡ ከተማ ፡
በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ እጅ ፡ በእርግጥ ፡
ትሰጣለች ÷ እርሱም ፡ ይይዛታል ። አለቆቹም ፡ ፬
ንጉሡን ፦ — ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቃል ፡ ሲነግራ
ቸው ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ የቀሩትን ፡ የሰልፈኞቹን ፡
እጅ ፡ የሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ያደክማልና ፡
ይህ ፡ ሰው ፡ እንዲገደል ፡ እንለምንሃለን ፤ ይህ ፡
ሰው ፡ ክፋትን ፡ እንጂ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምን ፡
አይመኝለትምና ፡ አሉት ። ንጉሡም ፡ ሴዴቅ ፭
ያስ ፦ — ንጉሡ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ሊያ
ደርግ ፡ አይችልምና ፡ እነሆ ÷ በእጃችሁ ፡ ነው ፡
አለ ። ኤርምያስንም ፡ ወሰዱት ፡ በግዞት ፡ ፮
ቤቱም ፡ አደባበይ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡
ንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ መልክያ ፡ ጕድጓድ ፡
ውስጥ ፡ ጣሉት ። ኤርምያስንም ፡ በገመድ ፡
አወረዱት ። በጕድጓዱም ፡ ውስጥ ፡ ጭቃ ፡
እንጂ ፡ ውኃ ፡ አልነበረበትም ፡ ኤርምያስም ፡
ወደ ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።
በንጉሡም ፡ ቤት ፡ የነበረው ፡ ጃንደረባ ፡ ፯
ኢትዮጵያዊው ፡ አቤሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፡ በጕ
ድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳኖሩት ፡ ሰማ ። ንጉሡም ፡
በብንያም ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። አቤሜሌ ፰
ክም ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ንጉሡን ፡ እን
ዲህ ፡ አለው ፦ — ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ እነ ፱
ዚህ ፡ ሰዎች ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ በጕድጓድ ፡
ውስጥ ፡ በመጣላቸው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በማይ
ረጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ክፋ ፡ አድርገዋል ፤ በከተማይ
ቱም ፡ ውስጥ ፡ እንጀራ ፡ ስለሌለ ፡ በዚያ ፡ በራብ ፡
ይሞታል ። ንጉሡም ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ አቤ ፲
ሜሌክን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡
ከዚህ ፡ ውሰድ ÷ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ ሳይ
ሞት ፡ ከጕድጓዱ ፡ አውጣው ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።
አቤሜሌክም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሰዎችን ፡ ይዞ ፲፩
ሄደ ÷ ከቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ በታች ፡ ወደ ፡
ነበረው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ገባ ÷ ከዚያም ፡
አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ እላቂ ፡ ልብስ ፡ ወሰደ ÷ ወደ ፡
ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ በገመድ ፡
አወረዳው ። ኢትዮጵያዊውም ፡ አቤሜሌክ ፲፪
ኤርምያስን ፦ — ይህን ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ እላቂ
ውን ፡ ልብስ ፡ በብብትህ ፡ ከገመዱ ፡ በታች ፡
አድርግ ፡ አለው ፡ ኤርምያስም ፡ እንዲሁ ፡ አደ
ረገ ። ኤርምያስንም ፡ በገመዱ ፡ ጕተቱት ፡ ፲፫

ከጕድጓዱም ፡ አወጡት ÷ ኤርምያስም ፡ በግ
ዞት ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡ ተቀመጠ ።
፲፬ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ መግ
ቢያ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ አስ
መጣው ፡ ንጉሡም ፡ ኤርምያስን ፦ — እንዲት ፡
ነገር ፡ አጠይቅሃለሁ ፡ ምንም ፡ አትሸሽገኝ ፡
፲፭ አለው ። ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ — ብነግ
ርህ ፡ በውኑ ፡ አትገድለኝምን ? ብመክርህም ፡
አትሰማኝም ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ —
ይህችን ፡ ነፍስ ፡ የፈጠረልን ፡ ሕያው ፡ እግዚአ
ብሔርን ! አልገድልህም ፡ ነፍስህንም ፡ ለሚሹ ፡
ለእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጥህም ፡
ብሎ ፡ በቂይታ ፡ ለኤርምያስ ፡ ማለ ።
፲፮ ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ — የአስራኤል ፡
አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ — ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡
አለቆች ፡ ብትወጣ ÷ ነፍስህ ፡ በሕይወት ፡ ትኖ
ራለች ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ አትቃጠ
ልም ፡ አንተም ፡ ቤትህም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራ
፲፯ ላችሁ ። ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡
ባትወጣ ፡ ግን ÷ ይህች ፡ ከተማ ፡ በከለዳውያን ፡
እጅ ፡ ትሰጣለች ÷ በእሳትም ፡ ያቃጥሉአታል ፡
አንተም ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፡ አለው ።
፲፰ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፦ — ወደ ፡
ከለዳውያን ፡ በኩበለሉት ፡ በአይሁድ ፡ እጅ ፡
አሳልፈው ፡ ይሰጡኛል ፡ እነርሱም ፡ ያፌዙብ
፲፱ ኛል ፡ ብዬ ፡ እፈራለሁ ፡ አለው ። ኤርምያስም ፡
እንዲህ ፡ አለው ፦ — አሳልፈው ፡ አይሰጡህም ።
እኔ ፡ የምነግርህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ÷
አባክህ ፡ ስማ ፤ ይቀናሃል ፡ ነፍስህም ፡ በሕይ
፳ ወት ፡ ትኖራለች ። ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡
ብትል ፡ ግን ÷ እግዚአብሔር ፡ ያሳየኝ ፡ ቃል ፡
፳፩ ይህ ፡ ነው ። እነሆ ÷ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡
የቀሩትን ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ ያወጣሉ ፡ እነዚያም ፡ ሴቶች ፦
፳፪ ባለምዋሎችህ ፡ አታልለውሃል ፡ አሸንፈውህ
ማል ፡ እግሮችህ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በጭቃ ፡
ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ እነርሱ ፡ ከእንተ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡
፳፫ ተመልሰዋል ፡ ይላሉ ። ሚስቶችህንና ፡ ልጆ
ችህንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ያወጣሉ ፡
አንተም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ትያዛለህ ፤
እንጂ ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፡ ይህችም ፡
ከተማ ፡ በእሳት ፡ ትቃጠላለች ።
፳፬ ሴዴቅያስም ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ —
ይህን ፡ ቃል ፡ ማንም ፡ አይወቅ ÷ አንተም ፡
አትሞትም ። አለቆቹ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከእንተ ፡
፳፭ ጋር ፡ እንደ ፡ ተነጋገርሁ ፡ ቢሰሙ ፡ ወደ ፡ እን
ተም ፡ መጥተው ፦ — ለንጉሡ ፡ ያልኸውን ፡
ንገረን ፡ አትሸሽገንም ÷ እኛም ፡ እንገድልህም ፡
ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ ያለህን ፡ ንገረን ፡ ቢሉህ ÷
፳፮ አንተ ፦ — በዚያ ፡ እሞት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የና
ታን ፡ ቤት ፡ አትመልሰኝ ፡ ብዬ ፡ በንጉሡ ፡
፳፯ ፊት ፡ ለመንሁ ፡ በላቸው ። አለቆቹም ፡ ሁሉ ፡

ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁ ፤ ንጉ
ሡም ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡
ነገራቸው ። ነገሩም ፡ አልተሰማምና ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ መነጋገርን ፡ ተዉ ። ኤርምያስም ፡ ፳፯
ኤሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ተያዘችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባበይ ፡ ተቀመጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

ኢየሩሳሌምም ፡ በተያዘች ፡ ጊዜ ÷ በይሁዳ ፡ ፩
ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡
በአሥረኛው ፡ ወር ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከ
ደነፆርና ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
መጥተው ፡ ከበቡአት ። በሴዴቅያስም ፡ በአ ፪
ሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡
ከወሩም ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ ከተማይቱ ፡ ተሰ
በረች ። የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ÷ ፫
ኤርጌል ፡ ሳራ-ስር ÷ ሳምጋርናቦ ÷ ሠርሰኪም ÷
ራፌስ ÷ ኤርጌል ፡ ሳራ-ስር ÷ ራብማግ ÷ ከቀ
ሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
ገብተው ፡ በመካከለኛው ፡ በር ፡ ውስጥ ፡ ተቀ
መጡ ።
የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሰልፈኞቹም ፡ ፬
ሁሉ ፡ በዩአቸው ፡ ጊዜ ፡ ከበለሉ ÷ በሌሊትም ፡
በንጉሡ ፡ አትክልት ፡ መንገድ ፡ በሁለቱ ፡ ቅጥር ፡
መካከል ፡ ከነበረው ፡ ደጅ ፡ ከከተማይቱ ፡ ወጡ ፤
በዓረባም ፡ መንገድ ፡ ወጡ ። የከለዳውያንም ፡ ፭
ሠራዊት ፡ ተከታተላቸው ÷ ሴዴቅያስንም ፡ በኢ
ያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ አገኙት ፡ ይዘውም ፡ በሐማት ፡
ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ ወደ ፡ ባቢ
ሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነፆር ፡ አመጡት ፡
እርሱም ፡ ፍርድን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ።
የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በዓ ፮
ይኑ ፡ ፊት ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ፡ የባቢሎንም ፡
ንጉሥ ፡ የይሁዳን ፡ ከበርቴዎች ፡ ሁሉ ፡ ገደለ ።
የሴዴቅያስንም ፡ ዓይን ፡ አወጣ ÷ ወደ ፡ ባቢሎ ፯
ንም ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ።
ከለዳውያንም ፡ የንጉሡንና ፡ የሕዝቡን ፡ ቤቶች ፡ ፰
በእሳት ፡ አቃጠሉ ÷ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡
አፈረሱ ። የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ፱
በከተማይቱ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ እር
ሱም ፡ የኰበለሉትን ፡ ሰዎች ፡ የቀረውንም ፡ የሕ
ዝቡን ፡ ቀሬታ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረከቸው ።
አንዳች ፡ ከሌላቸው ፡ ከሕዝቡ ፡ ድሆች ፡ ግን ፡ ፲
የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡
ተዋቸው ÷ የወይኑን ፡ ቦታና ፡ እርሻውን ፡ በዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ ሰጣቸው ።
የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ስለ ፲፩፡፲፪
ኤርምያስ ፡ ፡ — ውሰዶውና ፡ በመልካም ፡ ተመል
ከተው ÷ የሚሻውንም ፡ ነገር ፡ አድርግለት ፡
እንጂ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አታድርግበት ፡ ብሎ ፡ የዘ
በኞቹን ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳንን ፡ አዘዘ ። የዘበኞ ፲፫
ቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ላከ ÷ ናቡሽዝባ
ንም ፡ ራፋስቂስም ፡ ኤርጌል ፡ ሳራ-ስርም ፡ ራብ
ማግም ፡ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለ

፲፬ ቆች ፡ ሁሉ ፡ ላኩ ፤ ኤርምያስንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አመጡት ÷ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ይመ
ስደው ፡ ዘንድ ፡ ለሳፋን ፡ ልጅ ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ሰጡት ፡ እንዲህም ፡ በሕ
ዝብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።

፲፭ በግዞትም ፡ ቤት ፡ እያለባይ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡
፲፮ ኤርምያስ ፡ መጣ ፦— ሂድ ፡ ለኢትዮጵያዊው ም ፡ ለአቤሜሉክ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦— የእስራኤል
አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ÷ ለበጎነት ፡ ሳይሆን ፡
ለክፋት ፡ ቃሉን ፡ በዚህች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ እመ
ጣለሁ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ በፊትህ ፡ ይፈጸማል ።
፲፯ በዚያ ፡ ቀን ፡ አድንሃለሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በምትፈራቸው ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አልሰጥ
፲፰ ሀም ። ፈጽሜ ፡ አድንሃለሁ ፡ ነፍስህም ፡ እንደ ፡
ምርኮ ፡ ትሆንልሃለች ፡ እንጂ ፡ በሰይፍ ፡ አትወ
ድቅም ፡ ና በእኔ ፡ ታምነሃልና ÷ ይላል ፡ እግዚአ
ብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

፩ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በተማረኩት ፡ በኢየሩሳሌ
ምና ፡ በይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ መካከል ፡ የዘበ
ኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በሰንሰለት ፡ አስሮ ፡
በወሰደው ፡ ጊዜ ፡ ከራማ ፡ ከለቀቀው ፡ በኋላ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡
፪ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡
ኤርምያስን ፡ ወሰደው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡—
አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡
፫ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ አመጣው ፡ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ አደ
ረገ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ ሠር
ታችኋልና ÷ ቃሉንም ፡ አልሰማችሁምና ፡ ይህ ፡
፬ ነገር ፡ ዘነበቸው ። እሁንም ÷ እነሆ ፡ በእጅህ ፡
ከለችው ፡ ሰንሰለት ፡ ዛሬ ፡ ፈታሁህ ። ከእኔ ፡
ጋር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡ መልካም ፡
መስሎ ፡ ቢታይህ ÷ ና ÷ እኔም ፡ በመልካም ፡ አይ
ሃለሁ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡
መልካም ፡ መስሎ ፡ በይታይህ ፡ ግን ÷ ተቀመጥ ፡
እነሆ ÷ አገሪቱ ፡ ሁሉ ፡ በፊትህ ፡ ናት ፡ ትኼድ ፡
ዘንድ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ወደሚታይህ ፡ ይሰ
፭ ወደሚያሰኝህም ፡ ስፍራ ፡ ሂድ ። እርሱም ፡
ገና ፡ ሳያመለስ ፡— የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በይ
ሁዳ ፡ ከተሞች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሾመው ፡ ወደ ፡
ሳፋን ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶ
ልያስ ፡ ተመለስ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ በሕዝቡ ፡
መካከል ፡ ተቀመጥ ፡ ወይም ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡
ይሰ ፡ ወደሚያሰኝህ ፡ ስፍራ ፡ ሂድ ፡ አለው ።
የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ስንቅና ፡ ስጦታ ፡ ሰጥቶ ፡
፮ አሰናበተው ። ኤርምያስም ፡ የአኪቃም ፡ ልጅ ፡
ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ሄደ ፡ ከእ
ርሱም ፡ ጋር ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ በተናቱት ፡ ሕዝብ ፡
መካከል ፡ ተቀመጠ ።
፯ በየሜዳውም ፡ የነበሩት ፡ የሎሩራ ፡ አለቆ

ችና ፡ ሰዎቻቸው ፡ ሁሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡
የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ ሾመ ÷ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች
ንም ÷ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያልተማረኩትን ፡ የም
ድርን ፡ ድሆች ÷ እንዳስጠበቀ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
፰ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ÷ የቃሬያም ፡
ልጆች ፡ ዮሐናንና ፡ ዮናታን ÷ የተንሑሜትም ፡
ልጅ ፡ ሠራያ ÷ የነጦፋዊውም ፡ የዮሪ ፡ ልጆች ÷
የማዕክታዊውም ፡ ልጅ ፡ ያእዝንያ ፡ ከሰዎቻ
ቸው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡
መጡ ። የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎ
፱ ዶልያስ ፡ ለእነርሱና ፡ ለሰዎቻቸው ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ ማለ ፡— ለነሐዳውያን ፡ ትገዙ ፡ ዘንድ ፡
አትፍሩ ፡ በምድር ፡ ተቀመጡ ፡ ለባቢሎንም ፡
ንጉሥ ፡ ተገዙ ÷ መልካምም ፡ ይሆንላችኋል ።
፲ እኔም ÷ እነሆ ÷ ወደ ፡ እናንተ ፡ በሚመጡት ፡ ከለ
ዳውያን ፡ ፊት ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በምጽጳ ፡ እኖ
ራለሁ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ወይንንና ፡ የበጋ ፡ ፍሬ ፡
ዘይትንም ፡ አከማቹ ÷ በየዕቃችሁም ፡ ውስጥ ፡
ከተቱ ÷ በያዘችኋቸውም ፡ ከተሞቻችሁ ፡ ተቀ
መጡ ። በሞዓብም ፡ በአሞንም ፡ ልጆች ፡ መካ ፲፩
ከል ፡ በኤዶምያስም ፡ በምድርም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
የንበሩ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የይ
ሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ እንዳስቀረ ÷ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡
የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በላያቸው ፡
እንደ ፡ ሾመው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ÷ አይሁድ ፡ ፲፪
ሁሉ ፡ ከተሰደዱበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ተመለሱ ÷
ወደ ፡ ይሁዳም ፡ አገር ፡ ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡
ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ÷ ወይንና ፡ የበጋንም ፡
ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ አከማቹ ።
፲፫ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ በየሜዳውም ፡ ፲፫
የነበሩ ፡ የሎሩራ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጎዶ
ልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጥተው ፡— የአሞን ፡
፲፬ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ በአሊስ ፡ ይገድልህ ፡ ዘንድ ፡
የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ እንደ ፡ ሰደደ ፡
ታውቃለህን ? አሉት ። የአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶ
ልያስ ፡ ግን ፡ አላመነላቸውም ። የቃሬያም ፡ ፲፭
ልጅ ፡ ዮሐናን ፡— እባክህ ÷ ልሂድ ፡ ማንም ፡
ሳያውቅ ፡ የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ ልግ
ደለው ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አይሁድ ፡
ሁሉ ፡ እንዲበተኑ ፡ የይሁዳም ፡ ቅሬታ ፡ እንዲ
ጠፋ ፡ ነፍስህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይገድላል ? ብሎ ፡
በምጽጳ ፡ በቆይታ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ተናገረ ። የአ
ኪቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ግን ፡ የቃሬያን ፡
ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡— በእስማኤል ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡
ተናግረሃልና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፵፩ ።

፩ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከመንግሥት ፡ ወገንና ፡
ከንጉሡ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡ የኤሊ
ሳማ ፡ ልጅ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከአ
ሥር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ወደ ፡ አኪ
ቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ መጣ ፤ በዚያም ፡
በምጽጳ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ እንጀራ ፡ በሉ ። የና ፪

ታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡
የነበሩት ፡ አሥሩ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ የሳፋ
ንን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡
በሰይፍ ፡ መቱ ÷ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በአገሩ ፡
ላይ ፡ የሾመውን ፡ ገደሉ ። እስማኤልም ፡ ከነ ፫
ዶልያስ ፡ ጋር ፡ በምጽጳ ፡ የነበሩትን ፡ አይሁድ ፡
ሁሉ ÷ በዚያም ፡ የተገኙትን ፡ የከለዳውያንን ፡
ሰልፈኞች ፡ ሁሉ ፡ ገደላቸው ።
፬ ጎዶልያስን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ ፭
በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ጠ.ማቸውን ፡ ላጭተው ፡
ልብሳቸውንም ፡ ቀድደው ፡ ገላቸውንም ፡ ነድ
ተው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያቀርቡ ፡
ዘንድ ፡ የእህል ፡ ቍርባንና ፡ ዕጣን ፡ በእጃቸው ፡
እየያዙ ÷ ሰማንያ ፡ ሰዎች ፡ ከሴኬምና ፡ ከሴሎ ፡
፮ ከሰማርያም ፡ መጡ ። የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስ
ማኤል ፡ ከምጽጳ ፡ ወጥቶ ፡ እያለቀሰ ፡ ሊገናኛ
ቸው ፡ ሄደ ፡ በተገናኛቸውም ፡ ጊዜ ፡— ወደ ፡
አኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ኑ ፡ አላቸው ።
፯ ወደ ፡ ከተማም ፡ መካከል ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የና
ታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነ
በሩ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉአቸው ÷ በጉድጓድም ፡
፰ መካከል ፡ ጣሉአቸው ። በመካከላቸውም ፡ እስ
ማኤልን ፡— በሚጫ ፡ የተሸሸገ ፡ ስንዴና ፡ ገብስ ፡
ዘይትና ፡ ማርም ፡ አለንና ፡ አትግደለን ፡ የሚ
ሉት ፡ አሥር ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ። እርሱም ፡ ተዋ
ቸው ÷ ከወንድሞቻቸውም ፡ ጋር ፡ አልገደላቸ
ውም ። እስማኤልም ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋር ፡ የገደ
ላቸውን ፡ የሰዎች ፡ ሬሳ ፡ ሁሉ ፡ የጣለበት ፡ ጉድ
ጓድ ፡ ንጉሡ ፡ አሳ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ ባአ
ሳን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ የሠራው ፡ ጉድጓድ ፡ ነበረ ፡
የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ የገደላቸውን ፡
፲ ሞላበት ። እስማኤልም ፡ በምጽጳ ፡ የነበረውን ፡
የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ሁሉ ÷ የንጉሡን ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ለአ
ኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ የሰጠውን ፡ በም
ጽጳ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ማረከቸው ፡
የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ማርኮ ፡ ወደ ፡
አሞን ፡ ልጆች ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ።
፲፩ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡
የነበሩ ፡ የሎሩራ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ የናታንያ ፡
ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ያደረገውን ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡
፲፪ በሰሙ ፡ ጊዜ ÷ ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ከናታ
ንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ጋር ፡ ሊዋጉ ፡ ሄዱ ÷
በገባዖንም ፡ በለው ፡ በታላቁ ፡ ውኃ ፡ አጠገብ ፡
፲፫ አገኙት ። ከእስማኤልም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡
ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የቃሬያን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡ ከአ
ርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ የሎሩራ ፡ አለቆችን ፡
፲፬ ሁሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። እስማኤ
ልም ፡ ከምጽጳ ፡ የማረከቸው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
ዘወር ፡ ብለው ፡ ተመለሱ ፡ ወደ ፡ ቃሬያም ፡
፲፭ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮሐናን ፡ ሄዱ ። የናታንያ ፡ ልጅ ፡
እስማኤል ፡ ግን ፡ ከስምንት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከዮ
ሐናን ፡ አመለጠ ፡ ወደ ፡ አሞንም ፡ ልጆች ፡
ሄደ ።

፲፮ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡
የነበሩት ፡ የሎሩራ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ የአኪቃ
ምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምጽጳ ፡ ከገደለው ፡
በኋላ ፡ ከናታንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ያስመለሰ
አቸውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ሁሉ ÷ ከገባዖን ፡
ያስመለሰአቸውን ፡ ሰልፈኞች ÷ ሴቶችንም ÷
ልጆችንም ÷ ጃንደረቦችንም ÷ ወሰዱ ፡ ተነሥ ፲፯
ተውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡
ሌሔም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በጌሮት ፡ ከመዓም ፡
ተቀመጡ ። እስማኤል ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በአ ፲፰
ገሩ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡
ጎዶልያስን ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ከለዳውያንን ፡ ፈር
ተዋልና ።

ምዕራፍ ፡ ፵፪ ።

፩ የሎሩራ ፡ አለቆችም ፡ ሁሉ ፡ የቃሬያም ፡
ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የሆሻያም ፡ ልጅ ፡ ያእዝንያ ፡
ሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ከታናሹ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፪ቡ፫
ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ቀረቡ ÷ ነቢዩንም ፡ ኤርምያ
ስን ፡— ዓይኖችህ ፡ እንዳዩን ፡ ከብዙ ፡ ጥቂት ፡
ቀርተናልና ፡ ልመናችን ፡ እባክህ ÷ በፊትህ ፡
፫ ትድረስ ፡ አምላክህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የምንሄ
ድበትን ፡ መንገድና ፡ የምናደርገውን ፡ ነገር ፡
፬ ያሳየን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ÷ ስለዚህ ፡ ቀሬታ ፡
ሁሉ ÷ ወደ ፡ አምላክህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጸልይ ፡ አሉት ። ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡— ሰምቻ ፭
ችኋለሁ ፡ እነሆ ÷ እንደ ፡ ቃላችሁ ፡ ወደ ፡ አም
ላካችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለሁ ፡
እግዚአብሔርም ፡ የሚመልስላችሁን ፡ ሁሉ ፡
እነግራችኋለሁ ÷ ከእናንተም ፡ ምንም ፡ አልሸሽ
ግም ፡ አላቸው ። ኤርምያስንም ፡— አምላክህ ፡ ፮
እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ የላ
ከውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በናይርግ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በመከከላችን ፡ እውነተኛና ፡ ታማኝ ፡ ምስ
ክር ፡ ይሁን ። የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔ ፯
ርን ፡ ቃል ፡ በመስማታችን ፡ መልካም ፡ እንዲ
ሆንልን ÷ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ቢሆን ÷
አንተን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ የምንልከህ ፡ የአምላካ
ችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንሰማለን ፡
አሉት ።
፰ ከአሥር ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፱
ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ። የቃሬያንም ፡ ልጅ ፡ ፲
ዮሐናንን ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ የሎ
ሩራ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ከታናሹ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ÷
እንዲህም ፡ አላቸው ፡— ጸሎታችሁን ፡ በፊቱ ፡ ፲፩
አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ የላካችሁኝ ፡ የእ
ስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦— ስላደረግሁባችሁ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸ
ጽቻለሁና ፡ በዚህች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡
እሠራችኋለሁ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሰችሁም ÷ እተ ፲፪
ክላችኋለሁ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላችሁም ። ከም
ትፈሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትፍሩ ፡ አድ
ናችሁ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁም ፡ አስጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡

እኔ ፥ ከእናንተ ፥ ጋር ፥ ነኝና ፥ አትፍሩ ÷ ይላል ፥
፲፪ እግዚአብሔር ። እርሱ ፥ እንዲምራችሁ ፥ ወደ ፥ አገራችሁም ፥ እንዲመልሳችሁ ፥ እኔ ፥ እምራች ኋለሁ ። እናንተ ፥ ግን ፥ — በዚህች ፥ ምድር ፥ አንቀመጥም ፥ ብትሉ ፥ የአምላካችሁንም ፥ የእ
፲፫ ግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ ባትሰሙ ÷ እናንተም ፥ — አይደለም ፥ ሰልፍ ፥ ወደማናይበት ፥ የመለከትም ፥ ድምፅ ፥ ወደማንሰማበት ፥ ወደማንራብበትም ፥ ወደ ፥ ግብጽ ፥ ምድር ፥ እንሄዳለን ፥
፲፬ በዚያም ፥ እንቀመጣለን ፥ ብትሉ ÷ እናንተ ፥ የይሁዳ ፥ ቅሬታ ፥ ሆይ ÷ አሁን ፥ እንግዲህ ፥ የእ ግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ ስሙ ፥ የእስራኤል ፥ አም ላክ ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላል ፥ — ወደ ፥ ግብጽ ፥ ትገቡ ፥ ዘንድ ፥ በዚ
፲፭ ያም ፥ ትቀመጡ ፥ ዘንድ ፥ ፈታ ችሁን ፥ በሚያቀኑ ፥ ሰዎች ፥ ሁሉ ፥ እንዲህ ፥ ይሆንባቸዋል ፥ በሰይፍና ፥ በራብ ፥ በቸነፈርም ፥ ይሞታሉ ፥ እኔም ፥ ከማመጣባቸው ፥ ክፉ ፥ ነገር ፥ ማንም ፥ አይቀርም ÷ ማንም ፥ አያመልጥም ።
፲፮ የእስራኤል ፥ አምላክ ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላልና ፥ — ቍጣዬና ፥ መዓቴ ፥ በእ.የሩሳሌም ፥ በሚኖሩ ፥ ላይ ፥ እንደ ፥ ፈሰሰ ÷ እንዲሁ ፥ ወደ ፥ ግብጽ ፥ በገባችሁ ፥ ጊዜ ፥ መዓቴ ፥ ይፈስብባችኋል ፥ እናንተም ፥ ለዋ ላቻና ፥ ለመደነቂያ ፥ ለመረገሚያና ፥ ለመሰደቢያ ፥ ትሆናላችሁ ÷ ይህንም ፥ ስፍራ ፥ ከእንግ
፲፱ ዲህ ፥ ወዲህ ፥ አታዩትም ። እናንተ ፥ የይሁዳ ፥ ቅሬታ ፥ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፥ — ወደ ፥ ግብጽ ፥ አትግቡ ፥ ብሎ ፥ ተናግሮባችኋልና ፥ ዛሬ ፥ እን
፳ ዳስጠነቀቅኋችሁ ፥ በእርግጥ ፥ እወቁ ። እና ንተ ፥ — ስለ ፥ እኛ ፥ ወደ ፥ አምላካችን ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ጸልይ ÷ አምላካችንም ፥ እግዚ አብሔር ፥ የሚናገርህን ፥ ሁሉ ፥ ንገረን ፥ እኛም ፥ እናደርገዋለን ፥ ብላችሁ ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥
፳፩ ወደ ፥ አምላካችሁ ፥ ልካችሁኝ ፥ ነበርና ፥ ራሳ ችሁን ፥ አታልላችኋል ። እኔም ፥ ዛሬ ፥ ነግሬአ ችኋለሁ ÷ ወደ ፥ እናንተም ፥ በላከኝ ፥ ነገር ፥ ሁሉ ፥ የአምላካችሁን ፥ የእግዚአብሔርን ፥
፳፪ ቃል ፥ አልሰማችሁም ። አሁንም ፥ ሄዳችሁ ፥ እንድትቀመጡ ፥ በወደዳችሁበት ፥ ስፍራ ፥ በሰ ይፍና ፥ በራብ ፥ በቸነፈርም ፥ እንድትሞቱ ፥ በእ ርግጥ ፥ እወቁ ።

ምዕራፍ ፥ ፵፫ ።

፩ የአምላካቸውን ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ ሁሉ ÷ ለእነርሱ ፥ አምላካቸው ፥ እግዚአብሔር ፥ የላከውን ፥ ይህን ፥ ቃል ፥ ሁሉ ÷ ኤርምያስ ፥ ለሕዝቡ ፥ ሁሉ ፥ መናገርን ፥ በፈጸመ ፥ ጊዜ ÷
፪ የሆሻያ ፥ ልጅ ፥ ዓዛርያስ ፥ የቃሬያም ፥ ልጅ ፥ ዮሐናን ፥ ትዕቢተኞችም ፥ ሰዎች ፥ ሁሉ ፥ ኤር ምያስን ፥ — ሐሰት ፥ ተናግረሃል ፥ አምላካችን ፥ እግዚአብሔር ፥ — በዚያ ፥ ትቀመጡ ፥ ዘንድ ፥ ወደ ፥ ግብጽ ፥ አትግቡ ፥ ብሎ ፥ አልላከህም ፥ ነገር ፥
፫ ግን ፥ ከለዳውያን ፥ እንዲገድሉን ፥ ወደ ፥ በቢ ሎንም ፥ እንዲማርኩን ፥ በእጃቸው ፥ አሳልፈህ ፥ ትሰጠን ፥ ዘንድ ፥ የኔርያ ፥ ልጅ ፥ ባሮክ ፥ በላያ ችን ፥ ላይ ፥ አነሣሥቶሃል ፥ አሉት ። የቃሬያም ፥
፬ ልጅ ፥ ዮሐናን ፥ የሮከፍራ ፥ አለቆችም ፥ ሁሉ ፥ ሕዝቡም ፥ ሁሉ ፥ በይሁዳ ፥ ምድር ፥ ይቀመጡ ፥ ዘንድ ፥ የእግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ አልሰሙም ።
፭ የቃሬያም ፥ ልጅ ፥ ዮሐናን ፥ የሮከፍራ ፥ አለቆ ችም ፥ ሁሉ ፥ በይሁዳ ፥ ምድር ፥ ለመቀመጥ ፥ ከተሰደዱባቸው ፥ ከአሕዛብ ፥ ሁሉ ፥ የተመለሱ ትን ፥ የይሁዳን ፥ ቅሬታ ፥ ሁሉ ÷ ወንዶችንና ፥
፮ ሴቶችን ፥ ልጆችንም ፥ የንጉሡንም ፥ ሴቶች ፥ ልጆች ÷ የዘበኞቹም ፥ አለቃ ፥ ናቡዘረዳን ፥ ከሰ ፋን ፥ ልጅ ፥ ከአኪቃም ፥ ልጅ ፥ ከነዶልያስ ፥ ጋር ፥ የተዋቸውን ፥ ሰዎች ፥ ሁሉ ÷ ነቢዩንም ፥ ኤር ምያስን ፥ የኔርያንም ፥ ልጅ ፥ ባሮክን ፥ ወሰዱ ፥ የእግዚአብሔርንም ፥ ቃል ፥ አልሰሙምና ፥ ወደ ፥
፯ ግብጽ ፥ ምድር ፥ ገቡ ÷ እስከ ፥ ጣፍናስ ፥ ድረስ ፥ መጡ ።

በጣፍናስም ፥ የእግዚአብሔር ፥ ቃል ፥ ወደ ፥
፰ ኤርምያስ ፥ እንዲህ ፥ ሲል ፥ መጣ ፥ — ታላላቆ
፱ ችን ፥ ድንጋዮች ፥ በእጅህ ፥ ውሰድ ÷ የይሁ ዳም ፥ ሰዎች ፥ እያዩ ፥ በጣፍናስ ፥ ባለው ፥ በፈር ዖን ፥ ቤት ፥ ደጅ ፥ መግቢያ ፥ ሸሽጋቸው ፥ እንዲ
፲ ህም ፥ በላቸው ፥ — የእስራኤል ፥ አምላክ ፥ የሠ ራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላል ፥ — እነሆ ÷ ልኬ ፥ ባሪያዬን ፥ የባቢሎንን ፥ ንጉሥ ፥ ናቡከደነፆርን ፥ አመጣለሁ ÷ ዙፋኑንም ፥ እኔ ፥ በሸሸግኋቸው ፥ በእነዚህ ፥ ድንጋዮች ፥ ላይ ፥ አኖራለሁ ፥ እርሱም ፥ ማለፊያውን ፥ ድንኳኑን ፥ በላያቸው ፥ ይዘረጋል ። መጥቶም ፥ የግብጽን ፥
፲፩ ምድር ፥ ይመታል ÷ ለሞትም ፥ የሚሆነውን ፥ ለሞት ÷ ለምርኮም ፥ የሚሆነውን ፥ ለምርኮ ÷ ለሰይፍም ፥ የሚሆነውን ፥ ለሰይፍ ፥ ይሰጣል ። በግብጽም ፥ አማልክት ፥ ቤቶች ፥
፲፪ አሳትን ፥ ያነድዳል ፥ ያቃጥላቸውማል ፥ ይማር ካቸውማል ፥ አረኖም ፥ ደበሎውን ፥ እንደሚደ ርብ ፥ እንዲሁ ፥ የግብጽን ፥ አገር ፥ ይደርበል ፥ ከዚያም ፥ በሰላም ፥ ይወጣል ። በግብጽም ፥
፲፫ ምድር ፥ ያለውን ፥ የፀሐይ.ቱን ፥ ከተማ ፥ ሐው ልቶች ፥ ይሰብራል ÷ የግብጽንም ፥ አማልክት ፥ ቤቶች ፥ በእሳት ፥ ያቃጥላል ።

ምዕራፍ ፥ ፵፬ ።

፩ በግብጽ ፥ ምድር ፥ በሚኖዶልና ፥ በጣፍናስ ፥ በሚምፎስም ፥ በጳትሮስም ፥ አገር ፥ ስለ ፥ ተቀ መጡ ፥ አይሁድ ፥ ሁሉ ፥ ወደ ፥ ኤርምያስ ፥ የመጣ ፥ ቃል ፥ ይህ ፥ ነው ። የእስራኤል ፥ አም
፪ ላክ ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እን ዲህ ፥ ይላል ፥ — በኢ.የሩሳሌምና ፥ በይሁዳ ፥ ከተ

ሞች ፥ ሁሉ ፥ ያመጣሁትን ፥ ክፉ ፥ ነገር ፥ ሁሉ ፥ አይታችኋል ፥ እነሆ ÷ ዛሬ ፥ በድማ ፥ ሆነዋል ÷
፫ የሚቀመጥባቸውም ፥ የለም ። ይህም ፥ የሠ ነው ፥ ያስቈጡኝ ፥ ዘንድ ፥ ስላደረጉት ፥ ክፋት ÷ ለማያውቁአቸውም ፥ ለሌሎች ፥ አማልክት ፥ ያጥኑ ፥ ዘንድ ፥ ያመልኩአቸውም ፥ ዘንድ ፥ ስለ ፥
፬ ሄዱ ፥ ነው ። በማለዳም ፥ ተነሥቼ ፥ ባሪያዎቼን ፥ ነቢያትን ፥ ሁሉ ፥ ሰደድኩባችሁና ፥ — እንደ ዚህ ፥ እንደ ፥ ጠላሁት ፥ ያለ ፥ ርኩስ ፥ ነገር ፥ አታ
፭ ድርጉ ፥ አልኋችሁ ። ነገር ፥ ግን ፥ አልሰሙም ፥ ከክፋታቸውም ፥ ተመልሰው ፥ ለሌሎች ፥ አማ ልክት ፥ እንዳያጥኑ ፥ ጆሮአቸውን ፥ አላዘነበ
፮ ሉም ። ስለዚህ ፥ መዓቴና ፥ ቍጣዬ ፥ ፈሰሰ ÷ በይሁዳም ፥ ከተሞችና ፥ በኢ.የሩሳሌም ፥ አይ ባበይ ፥ ነደዱ ፥ ዛሬም ፥ እንደ ፥ ሆነው ፥ ፈረሱ ፥
፯ ባድማም ፥ ሆኑ ። አሁንም ፥ የእስራኤል ፥ አም ላክ ፥ የሠራዊት ፥ አምላክ ፥ እግዚአብሔር ፥ እን ዲህ ፥ ይላል ፥ — ከይሁዳ ፥ ወገን ፥ ቅሬታ ፥ እንዳይ ቀርላችሁ ÷ ወንድንና ፥ ሴትን ፥ ብላቴናንና ፥
፰ ሕፃንን ፥ ከመካከላችሁ ፥ ታጠፋ ፥ ዘንድ ፥ ይህን ፥ ታላቅ ፥ ክፋት ፥ በራሳችሁ ፥ ላይ ፥ ለምን ፥ ታደ
፱ ርጋላችሁ ? ሰውነታችሁንም ፥ ታጠፉ ፥ ዘንድ ፥ በምድርም ፥ አሕዛብ ፥ ሁሉ ፥ መካከል ፥ መረገ ሚያና ፥ መሰደቢያ ፥ ትሆኑ ፥ ዘንድ ÷ ለመቀ መጥ ፥ በገባችሁባት ፥ በግብጽ ፥ ምድር ፥ ለሴ ሎች ፥ አማልክት ፥ በማጠናችሁ ፥ በእጃችሁ ፥
፲ ሥራ ፥ ለምን ፥ ታስቈጡኛላችሁ ? በውኑ ፥ በይ ሁዳ ፥ ምድርና ፥ በኢ.የሩሳሌም ፥ አደባባይ ፥ ያደረጉትን ፥ የአባቶቻችሁን ፥ ክፋት ÷ የይሁ ዳንም ፥ ነገሥታት ፥ ክፋት ÷ የሚስቶቻቸው ንም ፥ ክፋት ÷ የእናንተንም ፥ ክፋት ÷ የሚ ስቶቻችሁንም ፥ ክፋት ፥ ረስታችሁታልን ?
፲፩ እስከ ፥ ዛሬ ፥ ድረስ ፥ አልተዋረዱም ፥ አልፈሩ ምም ÷ በእናንተና ፥ በአባቶቻችሁም ፥ ፊት ፥ ባኖርሁት ፥ ሕጌና ፥ ሥርዓቴ ፥ አልሄዱም ።
፲፪ ስለዚህም ፥ የእስራኤል ፥ አምላክ ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላል ፥ — እነሆ ÷ ይሁዳን ፥ ሁሉ ፥ አጠፋ ፥ ዘንድ ፥ ፊቴን ፥ ለክ
፲፫ ፋት ፥ በላያችሁ ፥ አደርጋለሁ ። ወደ ፥ ግብጽም ፥ ይገቡ ፥ ዘንድ ፥ በዚያም ፥ ይቀመጡ ፥ ዘንድ ፥ ፊታቸውን ፥ ያቀኑትን ፥ የይሁዳን ፥ ቅሬታ ፥ እመ ስዳለሁ ÷ ሁሉም ፥ ይጠፋሉ ÷ በግብጽም ፥ ምድር ፥ ይወድቃሉ ፥ በሰይፍና ፥ በራብ ፥ ይጠ ፋሉ ! ከታናሹም ፥ ጀምሮ ፥ እስከ ፥ ታላቁ ፥ ድረስ ፥ በሰይፍና ፥ በራብ ፥ ይሞታሉ ፥ ለጥላ ቻና ፥ ለመደነቂያ ፥ ለመረገሚያና ፥ ለመሰደቢያ ፥
፲፭ ይሆናሉ ። ኢየሩሳሌምንም ፥ እንደ ፥ ቀባሁ ÷ እንዲሁ ፥ በግብጽ ፥ ምድር ፥ የሚኖሩትን ፥ በሰ
፲፬ ይፍና ፥ በራብ ፥ በቸነፈርም ፥ እቀጣለሁ ። በዚያ ፥ ለመቀመጥ ፥ ወደ ፥ ግብጽ ፥ ምድር ፥ ከሄዱ ÷ ወደ ፥ ይሁዳ ፥ አገር ፥ ተመልሰው ፥ በዚያ ፥ ይቀ መጡ ፥ ዘንድ ፥ ከሚወድዱ ፥ ከይሁዳ ፥ ቅሬታ ፥ ወገን ፥ የሚያመልጥና ፥ የሚቀር ፥ ወደዚያም ፥ የሚመለስ ፥ የለም ፣ ከሚያመልጥም ፥ በቀር ፥ ማንም ፥ አይመለስም ።

፲፭ ሚስቶቻቸውም ፥ ለሌሎች ፥ አማልክት ፥ ማጠ ናቸውን ፥ ያወቁ ፥ ሰዎች ፥ ሁሉ ፥ በዚያም ፥ የቆሙ ፥ ሴቶች ፥ ሁሉ ÷ በግብጽ ፥ ምድር ፥ በጳ ትሮስ ፥ የተቀመጡ ፥ ሕዝብ ፥ ሁሉ ÷ ታላቅ ፥ ጉባኤ ፥ ሆነው ፥ ለኤርምያስ ፥ መለሱለት ፥ እን ዲህም ፥ አሉ ፥ — አንተ ፥ በእግዚአብሔር ፥ ስም ፥
፲፮ የነገርኸንን ፥ ቃል ፥ እንሰማህም ። ነገር ፥ ግን ፥ እኛና ፥ አባቶቻችን ፥ ነገሥታቶቻችንም ፥ አለ ቆቻችንም ፥ በይሁዳ ፥ ከተሞች ፥ በኢ.የሩሳሌም ፥ አደባባይ ፥ እናደርገው ፥ እንደ ፥ ነበረ ÷ ለሰ ማይ ፥ ንግሥት ፥ እናጥን ፥ ዘንድ ፥ የመጠጥንም ፥ ቍርባን ፥ እናፈስስላት ፥ ዘንድ ፥ ከእፍኝ ፥ የወ ጣውን ፥ ቃል ፥ ሁሉ ፥ በእርግጥ ፥ እናደርጋለን ፥ በዚያን ፥ ጊዜም ፥ እንጀራ ፥ እንጠግብ ፥ ነበር ÷ መልካምም ፥ ይሆንልን ፥ ክፉም ፥ አናይም ፥
፲፯ ነበር ። ለሰማይ ፥ ንግሥት ፥ ማጠንን ፥ ለእርስ ዋም ፥ የመጠጥን ፥ ቍርባን ፥ ማፍሰስን ፥ ከተ ውን ፥ ወዲህ ፥ ግን ÷ እኛ ፥ በሁሉ ፥ ነገር ፥ ተቸ ግረናል ÷ በሰይፍና ፥ በራብ ፥ አልቀናል ። እኛስ ፥
፲፰ ለሰማይ ፥ ንግሥት ፥ ባጠንንላት ፥ የመጠጥንም ፥ ቍርባን ፥ ባፈሰስንላት ፥ ጊዜ ÷ በውኑ ፥ ያለ ፥ ባሎቻችን ፥ ምስልዋን ፥ ለማበጀት ፥ እንጉቻ ፥ አድርገንላት ፥ ኖሮአልን ? የመጠጥንም ፥ ቍር ባን ፥ አፍስሰንላት ፥ ኖሮአልን ?

ኤርምያስም ፥ ይህን ፥ ቃል ፥ ለመለሰለት ፥
፲፱ ሕዝብ ፥ ሁሉ ÷ ለወንዶቹና ፥ ለሴቶቹ ፥ ለሕዝ ቡም ፥ ሁሉ ÷ መለሰላቸው ፥ እንዲህም ፥ አለ ፥ — እናንተና ፥ አባቶቻችሁ ፥ ነገሥታቶቻችሁም ፥
፳፩ አለቆቻችሁም ፥ የምድርም ፥ ሕዝብ ፥ በይሁዳ ፥ ከተሞችና ፥ በኢ.የሩሳሌም ፥ አደባባይ ፥ ያጠና ችሁትን ፥ ዕጣን ፥ እግዚአብሔር ፥ ያሰበው ፥ በል ቡም ፥ ያኖረው ፥ አይደለምን ? እግዚአብሔርም ፥
፳፪ ከእንግዲህ ፥ ወዲህ ፥ የሥራችሁን ፥ ክፋትና ፥ ያደረጋችሁትን ፥ ርኵሰት ፥ ይታገሥ ፥ ዘንድ ፥ አልቻለም ፥ ስለዚህ ፥ ምድራችሁ ፥ በድማ ፥ መደ ነቂያም ፥ መረገሚያም ፥ ሆናለች ፥ ዛሬም ፥ እንደ ፥ ሆነ ፥ የሚኖርባት ፥ የለም ። ስላጠናችሁ ÷ በእ
፳፫ ግዚአብሔርም ፥ ላይ ፥ ስለ ፥ በደላችሁ ÷ የእግዚ አብሔርንም ፥ ቃል ፥ ስላልሰማችሁ ፥ በሕጉና ፥ በሥርዓቱም ፥ በምስክሩም ፥ ስላልሄዳችሁ ÷ ስለ ዚህ ፥ ዛሬ ፥ እንደ ፥ ሆነ ፥ ይህች ፥ ክፉ ፥ ነገር ፥ አግ ኝታችኋለች ።

ኤርምያስም ፥ ለሕዝቡ ፥ ሁሉ ፥ ለሴቶቹም ፥
፳፬ ሁሉ ፥ እንዲህ ፥ አለ ፥ — በግብጽ ፥ ምድር ፥ የም ትኖሩ ፥ ይሁዳ ፥ ሁሉ ÷ የእግዚአብሔርን ፥ ቃል ፥ ስሙ ። የእስራኤል ፥ አምላክ ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥
፳፭ እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላል ፥ — እናንተና ፥ ሚስቶቻችሁ ፥ በአፋችሁ ፥ — ለሰማይ ፥ ንግ ሥት ፥ እናጥን ፥ ዘንድ ፥ የመጠጥንም ፥ ቍርባን ፥ እናፈስስላት ፥ ዘንድ ፥ የተሳልነውን ፥ ስእለታች ንን ፥ በእርግጥ ፥ እንፈጽማለን ፥ አላችሁ ፥ በእጃች ሁም ፥ አደረጋችሁት ፥ እንግዲህ ፥ ስእለታች ሁን ፥ አጽኑ ፥ ስእለታችሁንም ፥ ፈጽሙ ። እና ፳፮

ንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ይሁዳ ፡ ሁሉ ÷ ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ በሚኖር ፡ በይሁዳ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አፍ ፡ ስሜ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡— ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! ተብሎ ፡ እንዳይጠራ÷ እነሆ ÷ በታላቅ ፡ ስሜ ፡ ምያለሁ ÷ ይላል ፡ እግ ፳፯። ዚአብሔር ። እነሆ ÷ ለመልካም ፡ ሳይሆን ፡ ለክ ፋት ፡ እተጋባቸዋለሁ ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ያሉት ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እስኪጠፉ ፡ ፳፰። ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ያልቃሉ ። ከሰይፍም ፡ የሚያመልጡ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ሆነው ፡ ከግ ብጽ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ፡ ሊ ቀመጡም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ የገቡት ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ሁሉ ፡ ከእኔ ፡ ወይም ፡ ከእነ ርሱ ፡ የማናችን ፡ ቃል ፡ እንዲጸና ፡ ያውቃሉ ። ፳፱። ቃሌም ፡ በላያችሁ ፡ ለክፋት ፡ እንዲጸና ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህች ፡ ስፍራ ፡ እንድቀጣችሁ ፡ ምል ክታችሁ ፡ ይህ ፡ ነው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፴፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ጠላቱ ፡ ለሆነው ፡ ነፍሱ ንም ፡ ለፈለገው ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከ ደነፆር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እንደ ፡ ሰጠሁት ÷ እን ዲሁ ÷ እነሆ ÷ የግብጽን ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ሐፍራን ፡ ለጠላቶቹ ፡ ነፍሱንም ፡ ለሚፈልጉ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፮ ።

፩፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሶርስያስ ፡ ልጅ ፡ በአ ሞጽቋም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የነቢያ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ እንዘሀን ፡ ቃሎች ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመ ጽሐፍ ፡ በጻፋቸው ፡ ጊዜ ÷ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ፪፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ባሮክ ፡ ሆይ ÷ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ፫፡ ይልሃል ፡— አንተ ፡— እግዚአብሔር ፡ በሕመሜ ፡ ላይ ፡ ኀዘንን ፡ ጨምሮብኛልና ፡ ወዮልኝ ! በል ቅሶዬ ፡ ጩኸት ፡ ደክሚአለሁ ÷ ዕረፍትንም ፡ ፬፡ አላገኘሁም ፡ ብለሃል ። እንዲህ ፡ በለው ፡— እግ ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ የሠራ ሁትን ፡ አፈርሰለሁ ÷ የተከልሁትንም ፡ እነቅላ ፭፡ ለሁ ፡ ይኸውም ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ነው ። ለራ ስህ ፡ ታላቅን ፡ ነገር ፡ ትፈልጋለህን ? በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ÷ እነሆ ÷ ክፋ ፡ ነገርን ፡ አመ ጣለሁና ፡ አትፈልገው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሄድህበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ነፍስ ህን ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ አድርጌ ፡ እሰጥሃለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፯ ።

፩፡ ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ፪፡ ስለ ፡ ግብጽ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በከርከሚሽ ፡ ስለ ፡ ነበረው ÷ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተ ኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነ ፆር ፡ ስለ ፡ መታው ፡ ስለ ፡ ግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ፈርዖን ፡ ኀከው ፡ ሠራዊት ።

፫፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ፡ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ቅረቡ ። ፬፡ ፈረሰኞች ፡ ሆይ ÷ ፈረሶችን ፡ ለጕሙና ፡ ውጡ ÷ ራስ ፡ ቊርንም ፡ ይኖታችሁ ፡ ቁሙ ፡ ጦርንም ፡ ሰንግሉ ፡ ጥሩርንም ፡ ልበሱ ። ፭፡ ፈርተው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲመለሱ ÷ ኃያላኖቻቸውም ፡ ሲደበደቡ ፡ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ ሳይመለከቱ ፡ ፈጥነው ፡ ሲሸሹ ፡ ለምን ፡ አየሁ ? በዚህና ፡ በዚያ ፡ ድን ጋጤ ፡ አለ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ፮፡ ፈጣኑ ፡ አያመልጥም ፡ ኃያሉም ፡ አይድንም ፡ በሰሜን ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ተሰናክለው ፡ ወደቁ ። ፯፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ የሚ ነሣ ፡ ውኃውም ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ የሚናወጥ ፡ ማን ፡ ነው ? ግብጽ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ይነሣል ፡ ውኃውም ፡ እንደ ፡ ወንዙ ፡ ይናወ ጣል ። ፰፡ እርሱም ፡— እነሣለሁ ፡ ምድርንም ፡ ሁሉ ፡ እከድናለሁ ፡ ከተሞችንና ፡ የሚኖሩባቸ ውን ፡ አጠፋለሁ ፡ ብሎአል ። ፱፡ ፈረሶች ፡ ሆይ ÷ ውጡ ፡ ሰረገሎችም ፡ ሆይ ÷ ንጉሱ ፡ ጋሻም ፡ የሚ ያነግቡ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የፉጥ ፡ ኃያላን ÷ ቀስት ንም ፡ ይዘው ፡ የሚሸቡ ፡ የሉድ ፡ ኃያላን ፡ ይውጡ ። ፲፡ ያ ፡ ቀን ፡ ጠላቶቹን ፡ የሚበቀልበት ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የበቀል ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ሰይፍ ፡ በልቶ ፡ ይጠግባል ፡ በደማቸውም ፡ ይሰክራል ÷ ለሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ መሥ ዋዕት ፡ አለውና ። ፲፩፡ ድንግሊቱ ፡ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ውጪ ፡ የሚቀበንም ፡ መድኃኒት ፡ ውሰጂ ፡ መድኃኒትን ፡ ያበዛሽው ፡ በከንቱ ፡ ነው ፡ መዳን ፡ የለሽም ። ፲፪፡ ኃያሉ ፡ በኃ ያሉ ፡ ላይ ፡ ተሰናክሎ ፡ ሁለቱ ፡ በአንድነት ፡ ወድቀዋልና ፡ አሕዛብ ፡ ኮስሞኗልና ። ፲፫፡ ሰምተ ዋል ÷ ልቅሶሽም ፡ ምድርን ፡ ሞልቶአታል ።

፲፫፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ እንዲመ ጣና ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ እንዲመታ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ለነቢዩ ፡ ለኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲፬፡ በግብጽ ፡ ተናገሩ ÷ በሚግዶልም ፡ አሰሙ ÷ በሜምፎስና ፡ በጣፍናስ ፡ አሰሙ ፡ ሰይፍ ፡ በዙ ሪያህ ፡ ያለውን ፡ በልቶአልና ፡— ተነሥ ፡ ተዘጋ ጅም ፡ በሉ ። ፲፭፡ ኃይለኛዎችህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተወ ገዱ ? እግዚአብሔር ፡ ስላደከማቸው ፡ አልቆ ሙም ። ፲፮፡ ብዛታቸውም ፡ ተሰናክለ ÷ ሰውም ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ እነርሱም ፡— ተነሡ ÷ ከማያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ወገ ናችን ፡ ወደ ፡ ተወለድንባት ፡ ምድር ፡ እንመለስ ፡ አሉ ። ፲፯፡ በዚያም ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፡— ሰዓቱን ፡ የሚያሰልፍ ፡ ጕረኛ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ። ፲፰፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በተራሮች ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ታቦር ፡ በባሕርም ፡ አጠገብ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ቀርሜሎስ ÷ እንዲሁ ፡ በእውነት ፡ ይመጣል ÷ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሠራ ዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ። ፲፱፡ አንቺ ፡ በግብጽ ፡ የምትቀመጪ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷

ሜምፎስ ፡ በድማ ፡ ትሆናለችና ÷ ትቃጠልማ ለችና ÷ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝምና ፡ ለም ፳፡ ርከ ፡ የሚሆን ፡ ዕቃ ፡ አዘጋጂ ። ፳፩፡ ግብጽ ፡ የተዋ በች ፡ ጊደር ፡ ናት ፤ ጥፋት ፡ ግን ፡ ይመጣል ፤ ፳፪፡ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ይመጣበታል ። በእርስዋም ፡ ያሉ ፡ የተቀጠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንደ ፡ ሰቡ ፡ ወይፈኖች ፡ ናቸው ፡ የጥፋታቸው ፡ ቀንና ፡ የመጐብኘታቸው ፡ ጊዜ ፡ መጥቶባቸዋልና ፡ ተመለሱ ÷ በአንድነትም ፡ ሸሹ ÷ አልቆመ ፳፫፡ ም ። ከሠራዊትም ፡ ጋር ፡ ይጌዳሉና ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ይተምማል ፤ እንደ ፡ እንጨት ፡ ቈራጮችም ፡ በምሰር ፡ ይመጡበታል ። ፳፬፡ ይቄ ጠሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻሉትን ፡ የዱርዋን ፡ ዛፎች ፡ ይቈርጣሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከአንበጣ ፡ ይልቅ ፡ በዝተዋልና ፡ ቊጥርም ፡ የላቸውምና ። ፳፭፡ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ታፍራለች ፤ በሰሜን ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ አልፋ ፡ ትሰጣለች ። የእስራኤል ፡ አም ላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ የኖ ፡ አሞንን ÷ ፈርዖንንም ÷ ግብጽንም ÷ አማልክቶችዋንና ፡ ነገሥታቶች ዋንም ÷ ፈርዖንና ፡ በእርሱም ፡ የሚታመኑትን ፳፮፡ እቀጣለሁ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ በሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ÷ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ እጅ ÷ በባሪያዎቹም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸ ዋለሁ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ዘመን ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትሆናለች ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፳፯፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ÷ አትፍራ ÷ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ አትደ ንግጥ ፤ እነሆ ÷ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርህንም ፡ ከተ ማረከባት ፡ ምድር ፡ አድናለሁ ፤ ያዕቆብም ፡ ተመልሶ ፡ ያርፋል ፡ ተዘልሎም ፡ ይቀመጣል ÷ ማንም ፡ አያስፈራውምም ። ፳፰፡ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ÷ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። አንተንም ፡ ያሰደድሁባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለሁና ÷ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋ ሃም ፤ በመጠን ፡ እቀጣሃለሁ ÷ ያለ ፡ ቅጣትም ፡ አልተውሃም ።

ምዕራፍ ፡ ፵፯ ።

፩፡ ፈርዖንም ፡ ጋዛን ፡ ሰደመቃ ፡ ስለ ፡ ፍልስጥኤ ማውያን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመ ጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። እግ ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ ውኃ ፡ ከሰሜን ፡ ይነሣል ÷ የሚያጥለቀልቅም ፡ ፈሳሽ ፡ ይሆናል ፤ በአገሪቱና ፡ በመላዋ ፡ ሁሉ ፡ በከተማ ፡ ይቱና ፡ በሚኖሩባት ፡ ላይ ፡ ይጮርፋል ፤ ሰዎቹም ፡ ይጮኻሉ ÷ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ያለቅ ፫፡ ሳሉ ። ከኃይለኞች ፡ ፈረሶች ፡ ከኰቴያቸው ፡ መጠ ብጠብ ፡ ድምፅ ፡ ከሰረገሎቹም ፡ መትመም ፡ የተነሣ ፡ አቧ ራቸው ፡ በእጃቸው ፡ ድክም ፡ ምክንያት ፡ ፈታቾ ውን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ልጆቻቸው ፡ አይመለ ከቱም ። ፬፡ ይህም ፡ የሚሆነው ፡ ፍልስጥኤማው ያንን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የቀሩትንም ፡ ረዳ ቶች ፡ ሁሉ ፡ ከጪርስና ፡ ከሰዶና ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚመጣው ፡ ቀን ፡ ነው ። እግዚአ ብሔር ፡ ፍልስጥኤማውያንና ፡ የከፍቶርን ፡ ደሴት ፡ ቅሬታ ፡ ያጠፋልና ። ፭፡ ቡዙነት ፡ በጋዛ ፡ ላይ ፡ መጥቶአል ፡ አስቀሎና ፡ ጠፋች ፡ የሜናቅ ፡ ቅሬ ታዎች ፡ ሆይ ! እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ገላችሁን ፡ ትነጫላችሁ ? አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ፮፡ ሆይ ÷ ዝም ፡ የማትለው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? ወደ ፡ ሰገባህ ፡ ግባ ፡ ጸጥ ፡ ብለህም ፡ ዕረፍ ። እግዚአብሔር ፡ በአስቀሎናና ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ፯፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶአልና ÷ በዚያም ፡ አዘጋጅ ቶታልና ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ትላለህ ?

ምዕራፍ ፡ ፵፰ ።

፩፡ ስለ ፡ ሞዓብ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራ ዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ናባው ፡ ጠፍታለችና ፡ ወዮላት ! ቂርያታ ይም ፡ አፍራለች ፡ ተይዛማለች ፤ ሚሥጋብ ፡ አፍራለች ፡ ደንግጣማለች ። ፪፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሞዓብ ፡ ትምክሕት ፡ የለም ! በሐሴ ቦን ፡ ላይ ፡— ኑ ፡ ሕዝብ ፡ እንዳትሆን ፡ እናጥ ፋት ፡ ብለው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አስበውበታል ። መድሜን ፡ ሆይ ÷ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትጠፊአለሽ ፤ ሰይፍም ፡ ያሳድድሻል ። ፫፡ መፍረስና ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ የሚል ፡ የፊጩኽት ፡ ቃል ፡ ከሐሮናይም ፡ ተሰማ ። ፬፡ ሞዓብ ፡ ጠፍታለች ÷ ልጆችዋም ፡ ጩኽትን ፡ አሰምተዋል ። በሉሒት ፡ ዓቀበት ፡ ልቅሶ ፡ እያለቀሱ ፡ ይወጣሉና ÷ በሐሮናይምም ፡ ቀላልዓለት ፡ የጥፋትንና ፡ የመበቦትን ፡ ጩኽት ፡ ሰምተዋል ። ፭፡ ሸሽታችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ አድኑ ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቊጥቋጦ ፡ ሁኑ ። ፮፡ በሥ ራሽና ፡ በመዝገብሽ ፡ ታምነሽልና ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትያዢያለሽ ፤ ካሞሽም ፡ ከካህናቱና ፡ ከአለቆቹ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይማረካል ። እግ ዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ÷ አጥፊ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሁሉ ፡ ይመጣል ፡ አንዲትም ፡ ከተማ ፡ አትድንም ፡ ሸለቆውም ፡ ይጠፋል ፡ ሜዳውም ፡ ይበላሻል ። ፰፡ በርራ ፡ እንድትወጣ ፡ ለሞዓብ ፡ ክንፍ ፡ ስጡአት ፡ ከተሞችዋም ፡ በድማና ፡ ወና ፡ ይሆናሉ ። የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ፱፡ ብቻልታ ፡ የሚያደርግ ፡ ርጉም ፡ ይሁን ÷ ሰይ ፍንም ፡ ከደም ፡ የሚከለክል ፡ ርጉም ፡ ይሁን ።

ሞዓብ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ቀምጥል ፡ ፲፩፡ ነበረ ÷ በአምቡላውም ፡ ላይ ፡ ዐርፎአል ÷ ከዕ ቃውም ፡ ወደ ፡ ዕቃ ፡ አልተገላበጠም ÷ ወደ ፡ ምርኮም ፡ አልሄደም ፡ ስለዚህ ፡ ቃናው ፡ በእ ርሱ ፡ ውስጥ ፡ ቀርቶአል ÷ መዓዛውም ፡ አልተ ለወጠም ። ፲፪፡ ስለዚህ ÷ እነሆ ÷ የሚያገላብጡትን ፡ የምልክበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ÷ ይላል ፡ እግ ዚአብሔር ÷ እንርሱም ፡ ያገላብጡታል ፤ ጋሮ ቹንም ፡ ባዶ ፤ ያደርጋሉ ÷ መስቴዎቹንም ፡ ይሰ ብራሉ ። የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ይታመንበት ፡ ፲፫፡

ከነበረው ፥ ከቤቴል ፥ እንዳፈረ ÷ እንዲሁ ፥
፲፫ ሞዓብ ፥ ከካሞሽ ፥ ያፍራል ። እናንተ ፥— እኛ ፥
ኃያላን ፥ በሰልፍም ፡ ጽኑዓን ፥ ነን ፥ እንዴት ፥
፲፬ ትላላችሁ ? ሞዓብ ፥ ፈርሰአል ÷ ከተሞቹም ፥
ጠፍተዋል ÷ የተመረጡትም ፥ ጕልማሶች ፥
ወደ ፡ መታረድ ፡ ወርደዋል ÷ ይላል ፥ ስሙ ፥
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ።
፲፭ የሞዓብ ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣ ፡ ቀርቦአል ፡ መከራ
፲፮ ውም ፡ እጅግ ፡ ይፈጥናል ። በዙሪያው ፡ ያላ
ችሁ ፡ ሁሉ ፡ ስሙንም ፡ የምታውቁ ፡ ሁሉ ፡—
ብርቱው ፡ በትር ÷ የከበረው ፡ ሽመል ÷ እን
፲፯ ዴት ፡ ተሰበረ ! ብላችሁ ፡ አልቅሱለት ። በዳ
ቦን ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ÷ ሞዓብን ፡ የሚያጠፋ ፡
ወጥቶብሻልና ÷ አምባሽንም ፡ ሰብሮአልና ፡ ከከ
፲፱ ብርሽ ፡ ውረጂ ፡ በጥማትም ፡ ተቀመጪ ። በአ
ሮዔር ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ÷ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡
ቆመሽ ፡ ተመልከቺ ፡ የሸሸውንና ፡ ያመለጠች
ሸ ውን ፡— ምን ፡ ሆኖአል ? ብለሽ ፡ ጠይቂ ። ሞዓ
ብም ፡ ፈርሶአልና ፡ አፈረ ፡ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፡
ሞዓብ ፡ እንደ ፡ ተዘረፈ ፡ በአርኖን ፡ አጠገብ ፡
፳፩ አውሩ ። በሜዳ ፡ ላይ ፡ በሖሎን ÷ በያሳ ፡ በሜ
፳፪ ፍዓት ፡ ላይ ፡ በዲቦን ÷ በናባው ፡ በቤት ፡ ዲብ
፳፫ ላታይም ፡ ላይ ፡ በቂርያታይም ፡ በቤት ፡ጋሙል ፡
፳፬ በቤትምዖን ፡ ላይ ፡ በቂርዮት ÷ በባሶራ ፡ በሞ
ዓብም ፡ ምድር ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ቅርብና ፡
፳፭ ሩቅ ፡ በሆኑ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ መጥቶአል ። የሞ
ዓብ ፡ ቀንድ ፡ ተቈረጠ ፡ ክንዱም ፡ ተሰበረ ÷
ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፳፮ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርቶአልና ፡ እስክ
ሩት ፡ ሞዓብም ፡ በትፋቱ ፡ ላይ ፡ ይንከባለላል ÷
፳፯ ደግሞም ፡ መሳቂያ ፡ ይሆናል ። እስራኤል ፡
ለእንተ ፡ መሳቂያ ፡ አልሆነምን ? ወይስ ፡ በሌ
ቦች ፡ መከከል ፡ ተገኝቶአልን ? ስለ ፡ እርሱ ፡ በተ
፳፰ ናገርህ ፡ ጊዜ ፡ ራስህን ፡ ትነቀንቃለህ ። እናንት ፡
በሞዓብ ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ÷ ከተሞችን ፡ ትታ
ችሁ ፡ በዓለት ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ÷ በገደል ፡ አፋ
ፍም ፡ ቤትዋን ፡ እንደምትሠራ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡
፳፱ ሁኑ ። እጅግ ፡ እንደ ፡ ታበየ ፡ ስለ ፡ ሞዓብ ፡ ትዕ
ቢት ፡ ስለ ፡ ትምክህቱም ፡ ስለ ፡ ዅራቱም ፡ ስለ ፡
መጓደዱም ፡ ስለ ፡ ልቡም ፡ ትዕቢት ፡ ሰምተ
፴ ናል ። ቍጣው ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቃ
ለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፋከራው ፡ ምንም ፡
፴፩ አልሠራም ። ስለዚህ ፡ ለሞዓብ ፡ አለቅሳለሁ ፡
ለሞዓብም ፡ ሁሉ ፡ እጮኻለሁ ፡ ለቂርሔሬስ ፡
፴፪ ሰዎች ፡ አለቅሳለሁ ። እንቺ ፡ የሴብማ ፡ ወይን ፡
ሆይ ÷ ከኢያዜር ፡ ልቅሶ ፡ ይልቅ ፡ ለእንቺ ፡
አለቅሳለሁ ፡ ቅርንጫፎችሽ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረ
ዋል ÷ ወደ ፡ ኢያዜርም ፡ ባሕር ፡ ደርሰዋል ፤
አጥፊው ፡ በሰብልሽና ፡ በወይንሽ ፡ ላይ ፡ መጥ
፴፫ ቶአል ። ሐሤትና ፡ ደስታ ፡ ከፍሬያማው ፡ እር
ሻና ፡ ከሞዓብ ፡ ምድር ፡ ጠፍተዋል ፡ ጠጁን ፡
ከመጥመቂያው ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ጠማቂውም ፡
በእልልታ ፡ አይጠምቅም ÷ እልልታቸውም ፡
፴፬ እልልታ ፡ አይሆንም ። ከሐሴቦን ፡ ጩኸት ፡
ኤሌያሊና ፡ እስከ ፡ ያሀጽ ፡ ድረስ ፡ ድም
ፃቸውን ፡ ሰጥተ ፡ ል ፡ ከዞዓር ፡ እስከ ፡ ሖሮና
ይምና ፡ እስከ ፡ ዔግላት ፡ ሸሊሺያ ፡ ድረስ ፡ ይደ
ርሰል ፡ የኔምሬም ፡ ውኃ ፡ ደግሞ ፡ ይደርቃል ።
በከረብታው ፡ መስገጃ ፡ ላይ ፡ የሚሥዋውን ፡ ፴፭
ለአማልክቱም ፡ የሚያጥነውን ፡ ከሞዓብ ፡ አጠ
ፋለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
ያተረፈው ፡ ትርፋ ፡ ጠፍቶበታልና ፡ ስለዚህ ፡ ፴፮
ልቤ ፡ ለሞዓብ ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ይጮኻል ÷
ልቤም ፡ ለቂርሔሬስ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንቢ
ልታ ፡ ይጮኻል ። ራስ ፡ ሁሉ ፡ መላጣ ፡ ጠ ፡ ም ፡ ፴፯
ሁሉ ፡ የተላጨ ፡ ነውና ፡ በእጅም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ክትፋት ፡ በወገብም ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ አለና ። ሞዓ ፴፰
ብን ፡ እንደማይወደድ ፡ ዕቃ ፡ ሰብሬአለሁና ፡
በሞዓብ ፡ ሰገነት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በአደባባዩም ፡ ላይ ፡
በሁሉም ፡ ቦታ ፡ ልቅሶ ፡ አለ ÷ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ። እንዴት ፡ ተገለበጠ ! በእፍረትም ፡ የተ
ነሣ ፡ ሞዓብ ፡ ጀርባውን ፡ እንዴት ፡ መለሰ ! ብላ ፴፱
ችሁ ፡ አልቅሱ ። ሞዓብም ፡ በዙሪያው ፡ ላሉት ፡
ሁሉ ፡ መሳቂያና ፡ ድንጋጤ ፡ ይሆናል ።
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— እነሆ ÷ ፵
እንደ ፡ ንስር ፡ ይበርራል ፡ ክንፉንም ፡ በሞዓብ ፡
ላይ ፡ ይዘረጋል ። ከተሞቹ ፡ ተይዘዋል ÷ አም ፵፩
ባዎቹም ፡ ተወስደዋል ÷ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሞ
ዓብ ፡ ኃያላን ፡ ልብ ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡
ልብ ፡ ይሆናል ። ሞዓብም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፵፪
ላይ ፡ ኰርቶአልና ፡ ሕዝብ ፡ ከመሆን ፡ ይጠፋል ።
በሞዓብ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ÷ ፍርሃትና ፡ ጕድ ፵፫
ጓድ ፡ ወጥመድም ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ አለ ÷ ይላል ፡
እግዚአብሔር ። በሞዓብ ፡ ላይ ፡ የመጕብኘ ፵፬
ትን ፡ ዓመት ፡ አመጣበታለሁና ÷ ይላል ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በፍርሃት ፡ የሸሸ ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡
ይወድቃል ÷ ከጉድጓድም ፡ የወጣ ፡ በወጥመድ ፡
ይያዛል ። የሸሹ ፡ ደክመው ፡ ከሐሴቦን ፡ ጥላ ፡ ፵፭
በታች ፡ ቆመዋል ፡ እሳት ፡ ከሐሴቦን ፡ ነበልባ
ልም ፡ ከሲዖን ፡ ወጥቶአል ፡ የሞዓብንም ፡ ማዕ
ዘን ፡ የሚትንም ፡ ልጆች ፡ እናት ፡ በልቶአል ።
ሞዓብ ፡ ሆይ ÷ ወዮልህ ! የካሞሽ ፡ ወገን ፡ ጠፍ ፵፮
ቶአል ፡ ወንዶች ፡ ልጆችህ ፡ ተማርከዋልና ÷
ሴቶች ፡ ልጆችህም ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ሄደዋልና ።
፵፯ ግን ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሞዓብን ፡
ምርኮ ፡ እመልሳለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
የሞዓብ ፡ ፍርድ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፵፱ ።

ስለ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ፩
ዲህ ፡ ይላል ፡— ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የሉት
ምን ? ወይስ ፡ ወራሽ ፡ የለውምን ? ስለ ፡ ምን ፡
ሚልኮም ፡ ጋድን ፡ ወረሰ ? ሕዝቡስ ፡ በከተ
ሞቹ ፡ ላይ ፡ ሰፈረ ? ስለ ፡ ምን ፡ ተቀመጠ ? ስለዚህ ÷ ፪
እነሆ ÷ በእሞን ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ በረባት ፡ ላይ ፡
የሰልፍ ፡ ውካታን ፡ የማሰማበት ፡ ዘመን ፡ ይመ
ጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። የኰርስራሽ ፡
ከምርም ፡ ትሆናለች ፡ ሴቶች ፡ ልጆችዋም ፡

በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ÷ እስራኤልም ፡ የወረሱ ፫
ትን ፡ ይወርሳል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ሐሴ
ቦን ፡ ሆይ ÷ ኃይ ፡ ፈርሳለችና ፡ አልቅሺላት ፡
እናንተም ፡ የረባት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ÷
ሚልኮም ፡ ካህናቱና ፡ አለቆቹም ፡ በአንድነት ፡
ይማረካሉና ፡ ጩኹ ÷ ማቅም ፡ ታጠቁ ÷ አል
ቅሱም ÷ በቅጥሮችም ፡ መካከል ፡ ተርመጥመጡ ።
ማን ፡ ይመጣብኛል ፡ ብለሽ ፡ በመዝገብሽ ፡ የታ ፬
መንሽ ፡ አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ በሸለቆ
ችሽ ÷ ውኃ ፡ በሚያረካቸው ፡ ሸለቆችሽ ÷ ስለ ፡
ምን ፡ ትመኪ ፡ ያለሽ ? እነሆ ÷ በዙሪያሽ ፡ ከሉት ፡ ፭
ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ፍርሃትን ፡ አመጣብሻለሁ ÷ ይላል ፡
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እያንዳንዳ
ችሁም ፡ በፊታችሁ ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ ትሰደ
ዳላችሁ ÷ የሚሸሹትንም ፡ የሚሰበስብ ፡ የለም ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የአሞንን ፡ ልጆች ፡ ፮
ምርኮ ፡ እመልሳለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአ ፯
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በውኑ ፡ በቴማን ፡
ጥበብ ፡ የለምን ? ከብልሃተኞችስ ፡ ምክር ፡ ጠፍ
ቶአልን ? ጥበባቸውስ ፡ አልቆአልን ? እናንተ ፡
በድዳን ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ÷ የጎሳውን ፡ ጥፋት ÷
የምጐበኝበትን ፡ ጊዜ ÷ አመጣበታለሁና ፡ ሽሹ ÷
ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ÷ በጥልቅም ፡ ውስጥ ፡ ተቀ ፰
መጡ ። ወይን ፡ ለቃሚዎች ፡ ቢመጡብህ ÷
ቃርሚያውን ፡ አይተዉልህምን ? ሌቦችስ ፡ በሌ
ሊት ፡ ቢመጡ ÷ የሚያጠፉት ፡ እስኪበቃቸው ፡
ድረስ ፡ አይደለምን ? እኔ ፡ ግን ፡ ዔሳውን ፡ ዐራ ፱
ቈትሁት ፡ የተሸሸጉትንም ፡ ስፍራዎች ፡ ገለ
ጥሁ ÷ ይሸሸግም ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ዘራም ፡
ወንድሞቹም ፡ ጎረቤቶቹም ፡ ጠፍተዋል ፡ እር ፲፩
ሱም ፡ የለም ። ድህ ፡ አደጎችህን ፡ ተው ÷ እኔም ፡
በሕይወት ፡ አኖራቸዋለሁ ፡ መበለቶችህም ፡
በእኔ ፡ ይታመኑ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፲፪
ይላልና ፡— እነሆ ÷ ጽዋውን ፡ ያልተገባቸው ፡
ሰዎች ፡ ጠጥተውታል ፡ አንተም ፡ ሳትቀጣ ፡ ቅቀ
ራለህን ? በእርግጥ ፡ ትጠጣለህ ፡ እንጂ ፡ ያለ ፡
ቅጣት ፡ አትቀርም ። በሶራ ፡ መደነቂያና ፡ መሰ
ደቢያ ፡ መረገሚያም ፡ እንድትሆን ፡ በራሴ ፡
ምያለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተሞች
ዋም ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለም ፡ በድማ ፡ ይሆናሉ ።
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምቻለሁ ፡ ፲፬
በአሕዛብም ፡ መካከል ፡— ተሰብሰቡ ÷ በእርስ
ዋም ፡ ላይ ፡ ኑ ፡ ለሰልፍም ፡ ተነሡ ፡ የሚል ፡
መልእክተኛ ፡ ተልከአል ። እነሆ ÷ በአሕዛብ ፡ ፲፭
ዘንድ ፡ የተጠቃህ ÷ በሰዎችም ፡ ዘንድ ፡ የተና
ቅህ ፡ አድርጌሃለሁ ። በዓለት ፡ ንቃቃት ፡ ውስጥ ፡
የምትቀመጥ ÷ የተራራውን ፡ ከፍታ ፡ የምት
ይዝ ፡ ሆይ ÷ ድፍረትህና ፡ የልብህ ፡ ኵራት ፡
አታልለውሃል ። ቤትህን ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ንስር ፡
ከፍ ፡ ብታደርግ ፡ ከዚያ ፡ አወርድሃለሁ ÷ ይላል ፡
እግዚአብሔር ። ኤዶምያስም ፡ መደነቂያ ፡ ትሆ ፲፯
ናለች ÷ የሚያልፍበትም ፡ ሁሉ ፡ ይደነቃል ÷
ስለ ፡ መጣበትም ፡ መቅሠፍት ፡ ሁሉ ፡ ያፍዋጭ

ከዳርቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ አመጣባቸዋ
ለሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። አሶርም ፡ የቀ
በር ፡ መናፈያና ፡ የዘላለም ፡ በድማ ፡ ትሆናለች ፡
በዚያም ፡ ሰው ፡ አይኖርም ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡
አይቀመጥባትም ።

፵፩ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሰዲቅያስ ፡ መንግሥት ፡
መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ኤላም ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡
ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
፵፪ ይህ ፡ ነው ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ ዋና ፡ የኃይላቸው ፡
መሣሪያ ፡ የሆነውን ፡ የኤላምን ፡ ቀስት ፡ እሰብራ
፵፫ ለሁ ። ከአራቱም ፡ ከሰማይ ፡ ማዕዘናት ፡ አራ
ቱን ፡ ነፋሳት ፡ በኤላም ፡ ላይ ፡ አመጣለሁ ፥
ወደ ፡ እነዚያም ፡ ነፋሳት ፡ ሁሉ ፡ እበትናቸዋለሁ ፤
ከኤላም ፡ የተሰደዱ ፡ ሰዎች ፡ የማይደርሱበት ፡
፵፬ ሕዝብ ፡ አይገኝም ። በጠላቶቻቸውና ፡ ነፍሳ
ቸውን ፡ በሚሹአት ፡ ፊት ፡ ኤላምን ፡ አስደነግ
ጣለሁ ፤ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እርሱም ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ
ዬን ፡ አመጣባቸዋለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤
እስክጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ በኋላቸው ፡ ሰይፍ ፡
፵፭ እሰድድባቸዋለሁ ፤ ዙፋኔንም ፡ በኤላም ፡ አና
ራለሁ ፡ ከዚያም ፡ ንጉሡንና ፡ አለቆቹን ፡ አጠ
፵፮ ፋለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ነገር ፡ ግን ፡
በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የኤላምን ፡ ምርኮ ፡ እመል
ሳለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፶ ።

፩ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ከለዳውያን ፡ ምድር ፡
ስለ ፡ ባቢሎን ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ የተናገ
፪ ረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። በአሕዛብ ፡ መካከል ፡
ተናገሩ ፡ አውሩም ፥ ዓላማውንም ፡ አንሡ ፤
አውሩ ፥ አትደብቁ ፦ ባቢሎን ፡ ተወሰደች ፥
ቤል ፡ አፈረ ፥ ሜሮዳክ ፡ ደነገጠ ፤ ምስሎችዋ ፡
፫ አፈሩ ፥ ጣዖታትዋ ፡ ደነገጡ ፡ በሉ ። ሕዝብ ፡
ከሰሜን ፡ ወጥቶበታል ፡ ምድርዋንም ፡ በድማ ፡
ያደርጋል ፥ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝም ፡
ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ሸሽ
፬ ተው ፡ ሄደዋል ። በዚያም ፡ ወራት ፡ በዚያም ፡
ጊዜ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡
ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ሆነው ፡
ይመጣሉ ፥ እያለቀሱም ፡ መንገዳቸውን ፡ ይሄ
ዳሉ ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈ
፭ ልጋሉ ። ፊታቸውንም ፡ ወደዚያ ፡ አቅንተው ፡ ፦
ኑ ፥ ከቶ ፡ በማይረሳ ፡ በዘላለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠጉ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡
ጽዮን ፡ መንገድ ፡ ይጠይቃሉ ።

፮ ሕዝቤ ፡ የጠፉ ፡ በጎች ፡ ሆነዋል ፤ እረኞቻ
ቸው ፡ አሳቱአቸው ፥ በተራሮችም ፡ ላይ ፡ የተ
ቀበዘበዙ ፡ አደረጉአቸው ፤ ከተራራ ፡ ወደ ፡ ኮረ
፯ ብታ ፡ አለፉ ፥ በረታቸውንም ፡ ረሱ ። ያገኙአ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ በሉአቸው ፥ ጠላቶቻቸውም ፡ ፦
በድያቸዋ ፡ ማደሪያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፥ በአ
ባቶቻቸው ፡ ተስፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
ኃጢአት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እኛ ፡ አልበደልንም ፡
አሉ ። ከባቢሎን ፡ መካከል ፡ ሽሹ ፥ ከከለዳው
ያንም ፡ ምድር ፡ ውጡ ፥ በመንጎችም ፡ ፊት ፡
፰ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ሁኑ ። እነሆ ፥ ከሰ
ሜን ፡ ምድር ፡ የታላላቅ ፡ አሕዛብን ፡ ጉባኤ ፡
አስነሣለሁ ፡ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋ
ለሁ ፡ በእርስዋም ፡ ላይ ፡ ይሰለፋሉ ፥ ከዚያም ፡
ትወሰዳለች ፡ ፍላጻቸውም ፡ በዶውን ፡ እንደማ
፱ ይመለስ ፡ እንደ ፡ ብልህ ፡ ጀግና ፡ ፍላጻ ፡ ናቸው ።
የከላውያንም ፡ ምድር ፡ ትበዘበዛለች ፥ የሚ
፲ በዘብዙአትም ፡ ሁሉ ፡ ይጠግባሉ ፥ ይላል ፡ እግ
ዚአብሔር ።

፲፩ ርስቴን ፡ የምትበዘብዙ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ደስ
ብሎአችኋልና ፥ ሐሤትንም ፡ አድርጋችኋልና ፥
በመስክ ፡ ላይም ፡ እንዳለች ፡ ጊደር ፡ ሆናችሁ ፥
ተቀናጥታችኋልና ፥ እንደ ፡ ብርቱዎችም ፡ ፈረ
፲፪ ሶች ፡ እሸክክታችኋልና ፥ እናታችሁ ፡ እጅግ ፡
ታፍራለች ፥ የወለደቻትም ፡ ትጐሰቍላለች ፤
እነሆ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኋለኛይቱ ፡ ትሆ
ናለች ፤ ምድረ ፡ በዳና ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ በረሀም ፡
፲፫ ትሆናለች ። ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡
ሰው ፡ አይቀመጥባ
ትም ፤ በባቢሎንም ፡ በኩል ፡ የሚያልፍ ፡ ሁሉ ፡
ይደነቃል ፡ በመጣባትም ፡ መቅሠፍት ፡ ሁሉ ፡
፲፬ ያፍጫል ። እናንተ ፡ ቀስትን ፡ የምትገትሩ ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ በዙሪያዋ ፡ ተሰ
ለፉ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርታ
ለችና ፡ ወርውሩባት ፡ ፍላጻችንም ፡ አትንፈጉ ።
፲፭ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ነውና ፤ በዙሪያዋ ፡
ጩኹባት ፤ እጅዋን ፡ ሰጠች ፤ ግንቦችዋ ፡ ወደቁ ፡
ቅጥሮችዋም ፡ ፈረሱ ፤ እርስዋን ፡ ተበቀሉ ፡
እንደ ፡ ሠራችው ፡ ሥሩባት ። ዘሪውን ፡ ከባቢ
፲፮ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ማጭድ ፡ የሚይዘውን ፡ ከባቢ
ሎን ፡ አጥፉ ፤ ከሚያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡ ፊት ፡
እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለሳል ፡ እያንዳ
ንዱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሸሻል ።

፲፯ እስራኤል ፡ የበዛ ፡ በግ ፡ ነው ፡ አንበሶች ፡ አሳ
ደዱት ፡ መጀመሪያ ፡ የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ በላው ፥
በመጨረሻም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደ
ነፆር ፡ አጥንቱን ፡ ቈረጠመው ። ስለዚህ ፡
፲፰ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሦርን ፡
ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ቀጣሁ ፡ እንዲሁ ፡ እነሆ ፥ የባ
ቢሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ምድሩን ፡ እቀጣለሁ ። ፲፱ እስ
ራኤልንም ፡ ወደ ፡ ማሰማርያው ፡ እመልሳለሁ ፥
በቀርሜሎስና ፡ በባሳንም ፡ ላይ ፡ ይሰማራል ፥
ሰውነቱም ፡ በኤፍሬም ፡ ተራራና ፡ በገለዓድ ፡
ላይ ፡ ትጠግባለች ። እነዚህን ፡ ያስቀረኋቸውን ፡
፳ ይቅር ፡ እላቸዋለሁና ፡ በዚያን ፡ ወራት ፡ በዚ
ያም ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራ
ኤል ፡ በደል ፡ የይሁዳም ፡ ኃጢአት ፡ ይፈለጋል ፡
ግንም ፡ አይገኝም ።

፳፩ በምራታይም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በፋቁድም ፡ በሚ
ኖሩት ፡ ላይ ፡ ውጣ ፡ ግደላቸው ፡ ፈጽመህም ፡
አጥፋቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንዳዘዝ

፳፪ ሁህም ፡ ሁሉ ፡ አድርግ ። የሰልፍና ፡ የታላቅ ፡
፳፫ ጥፋት ፡ ውካታ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አለ ። የም
ድር ፡ ሁሉ ፡ መዶሻ ፡ እንዴት ፡ ደቀቀ ፡ እንዴትስ ፡
ተሰበረ ! ባቢሎንስ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እን
፳፬ ዴት ፡ በድማ ፡ ሆነች ! ባቢሎን ፡ ሆይ ፥ አጥ
ምጄብኻለሁ ፡ አንቺም ፡ ሳታውቂ ፡ ተይዘሻል ፤
ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተዋጋሽ ፡ ተገኝተ
፳፭ ሻል ፡ ተይዘሽማል ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በክለዳውያን ፡ ምድር ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡
ሥራ ፡ አለውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ ቤቱን ፡
ከፍቶ ፡ የቍጣውን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ አውጥቶአል ።
፳፮ ከየበኩሉ ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፥ ጉተራዎ
ችዋንም ፡ ክፈቱ ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ አድርጓት ፥
ፈጽማችሁም ፡ አጥፉአት ፥ አንዳችም ፡ አታስ
፳፯ ቀሩላት ። ወይፈኖችዋን ፡ ሁሉ ፡ እረዱ ፥ ወደ ፡
መታረድም ፡ ይውረዱ ፤ ቀናቸው ፥ የመጐብኘ
፳፰ ታቸው ፡ ጊዜ ፥ ደርሶአልና ፡ ወዮላቸው ! የአ
ምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በቀል ፡ የመ
ቀደሱንም ፡ በቀል ፡ በጽዮን ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ፡
ሸሽተው ፡ ከባቢሎን ፡ አገር ፡ ያመለጡት ፡
ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቶአል ።

፳፱ ቀስትን ፡ የሚገትሩትን ፡ ቀስተኞችን ፡ ሁሉ ፡
በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ጥሩአቸው ፤ በዙሪያዋ ፡ ስፈ
ሩበት ፡ አንድም ፡ አያምልጥ ፤ በአስራኤል ፡
ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርታለ
ችና ፡ እንደ ፡ ሥራዋ ፡ መጠን ፡ መልሱላት ፥
፴ እንዳደረገችም ፡ ሁሉ ፡ አድርጉበት ። ስለዚህ ፡
ጕበዛገቱዋ ፡ በአደባባይዋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፥
በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፈኞችዋ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉ ፥
፴፩ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ትዕቢተኛው ፡ ሆይ ፥
የመጐብኘትህ ፡ ጊዜ ፡ ቀንህ ፡ ደርሶአልና ፤
እነሆ ፥ በአንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ትዕቢተኛው ፡ ተሰና
ክሶ ፡ ይወድቃል ፡ የሚያነሣውም ፡ የለም ፤ በከ
ተሞቹም ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አነድዳለሁ ፥ በዙሪ
ያውም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ትበላለች ።

፴፪ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡
ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ተገፍተዋል ፥ የማረኳቸ
ውም ፡ ሁሉ ፡ በኃይል ፡ ይይዙአቸዋል ፥ ይለቅቁ
፴፫ አቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ። ተቤዣቸ
ው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ምድርንም ፡ ያሰርፍ፡
ዘንድ ፡ በባቢሎንም ፡ የሚኖሩትን ፡ ያውክ ፡
ዘንድ ፡ መግታቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ይምዋገታል ።
፴፬ ሰይፍ ፡ በከለዳውያንና ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩ ፡
ላይ ፥ በአለቆችዋና ፡ በጥበበኞችዋ ፡ ላይ ፡ አለ ፥
፴፭ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ሰይፍ ፡ በሚጓደዱት ፡
ላይ ፡ አለ ፡ ሰነፎችም ፡ ይሆናሉ ፥ ሰይፍም ፡
በኀያላኖችዋ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ እነርሱም ፡ ይደነግ
፴፮ ጣሉ ። ሰይፍ ፡ በፈረሶቻቸውና ፡ በሰረገሎቻ
ቸው ፡ ላይ ፡ በመካከልዋም ፡ ባሉት ፡ በልዩ ፡
በልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ እነርሱም ፡
እንደ ፡ ሴቶች ፡ ይሆናሉ ፥ ሰይፍም ፡ በመዝገ
ብዋ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ለብዝበዛም ፡ ይሆናል ።
፴፯ እርስዋ ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ ምድር ፡ ናት ፥
እነርሱም ፡ በጣዖታት ፡ ይመከሩና ፡ ድርቅ ፡
በውኆችዋ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፤ እነርሱም ፡ ይደር
፴፰ ቃሉ ። ስለዚህ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ከተ
ኩላዎች ፡ ጋር ፡ ይቀመጡበታል ፥ ሰጐኖችም ፡
ይቀመጡበታል ፡ ሰውም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ለዘ
ላለም ፡ አይቀመጥባትም ፥ አስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅም ፡
ድረስ ፡ የሚኖርበት ፡ የለም ። ሰዶምንና ፡ ገሞ
፴፱ ራን ፡ በአጠገባቸውም ፡ የነበሩትን ፡ ከተሞች ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ገለበጣቸው ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ እንዲሁ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ አይቀ
መጥም ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ አይኖርበትም ።

፵ እነሆ ፥ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ ይመጣል ፥ ታላቅ ፡
፵፩ ሕዝብና ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡
ይነሣሉ ። ቀስትንና ፡ ጦርን ፡ ይይዛሉ ፤ ጨክ
፵፪ ኞች ፡ ናቸው ፡ ምሕረትም ፡ አያደርጉም ፤ ድም
ፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ይተምማል ፡ በፈረሶ
ችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ የባቢሎን ፡ ሴት ፡
ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡
እያንዳንዳቸው ፡ በእንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ። የባቢ
፵፫ ሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወሬአቸውን ፡ ሰምቶአል ፡ ፥
እጁም ፡ ደከማለች ፡ ጭንቀትም ፡ ይዘታል ፡
ምጥ ፡ ወላጅ ፡ ሴትን ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡
፵፬ ይዘታል ። እነሆ ፥ ከእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ በቆሎ ፡
አባርራቸዋለሁና ፡ በጠነከረው ፡ አምባ ፡ ላይ ፡
ከዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡
ይወጣል ፡ የተመረጠውንም ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡
እሾመዋለሁ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ?
ወይስ ፡ ለእኔ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው ፡ ? ወይስ ፡
ፊቴን ፡ የሚቃወም ፡ እረኛ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ? ስለ
፵፭ ዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ የመከ
ረባትን ፡ ምክር ፡ በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡
ላይ ፡ ያሰባትን ፡ አሳብ ፡ ስሙ ፤ በእውነት ፡ የመ
ንጋ ፡ ትንንሾች ፡ ይጐትቷቸው ፤ በእውነት ፡ ማደ
፵፮ ሪያቸውን ፡ በድማ ፡ ያደርግባቸዋል ። ከባቢ
ሎን ፡ መያዝ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወ
ጠች ፥ ጩኸትም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተሰማ ።

ምዕራፍ ፡ ፶፩ ።

፩ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥
በባቢሎን ፡ ላይና ፡ በነለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚ
ኖሩት ፡ ላይ ፡ አጥፊውን ፡ ነፋስ ፡ አስነሣለሁ ።
፪ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚያዘሩትን ፡ ሰዎች ፡ እሰድ
ዳለሁ ፡ እነርሱም ፡ ያዘሩአታል ፥ ምድርዋንም ፡
ባዶ ፡ ያደርጋሉ ፤ በመከራም ፡ ቀን ፡ በዙሪያዋ ፡
ይከብቡአታል ። በወርዋሪው ፡ ላይ ፡ በጥሩርም ፡
፫ በሚነሣው ፡ ላይ ፡ ቀስተኛው ፡ ቀስቱን ፡ ይገ
ትር ፡ ለጕበዝነትዋ ፡ አትዘኑ ፡ ሠራዊትዋንም ፡
ሁሉ ፡ አጥፉ ። በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ተገ
፬ ድለው ፥ በሚዳዎም ፡ ላይ ፡ ተወግተው ፡ ይወ
ድቃሉ ።

፭ ምድራቸው ፡ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በተ

ሠራው ፡ በደል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተሞላች ፡
ብትሆን ÷ እስራኤልም ፡ ሆነ ፡ ይሁዳ ፡ በእም
ላኩ ፡ በሠራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
፭ ፡ አልተጣለም ። ከባቢሎን ፡ ውስጥ ፡ ሽሹ ÷ እያ
ንዳንዳችሁም ፡ ነፍሳችሁን ፡ አድኑ ፤ በበደልዋ ፡
አትጥፉ ÷ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ጊዜ ፡
ነውና ÷ እርሱም ፡ ብድራትዋን ፡ ይከፍላታ
፮ ፡ ልና ። ባቢሎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡
ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያሰከረች ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ነበ
ረች ÷ አሕዛብም ፡ ከጠጅዋ ፡ ጠጥተዋል ፡ ስለ
፯ ፡ ዚህ ፡ አሕዛብ ፡ አብደዋል ። ባቢሎን ፡ በድን
ገት ፡ ወድቃ ፡ ጠፍታለች ፡ አልቅሱላት ÷ ትፈ
ወስም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለቊስልዋ ፡ መድኀኒት ፡
፰ ፡ ውሰዱላት ። ባቢሎንን ፡ ፈወስናት ÷ እርስዋ ፡
ግን ፡ አልተፈወሰችም ፡ ፍርድዋ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡
ደርሶአልና ÷ እስከ ፡ ደመናም ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ብሎአልና ፡ ትታችኋት ፡ እያንዳንዳችን ፡
፱ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንሂድ ። እግዚአብሔር ፡
ጽድቃችንን ፡ አውጥቶአል ፡ ኑ ÷ በጽዮን ፡ የአ
ምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ እንናገር ።
፲ ፡ ፍላጾችን ፡ ሳሉ ፡ ጋሻዎችንም ፡ አዘጋጁ ፤ እግ
ዚአብሔር ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ አሳቡ ፡ በባቢ
ሎን ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ የሚዶንን ፡ ነገሥታት ፡ መን
ፈስ ፡ አስነሥቶአል ፤ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡
፲፩ ፡ የመቅደሱ ፡ በቀል ፡ ነውና ። በባቢሎን ፡ ቅጥር ፡
ዓላማውን ፡ አንሡበት ÷ ጥበቃን ፡ አጽኑ ÷ ተመ
ልካቾችን ፡ አቁሙ ÷ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ።
እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡
የተናገረውን ፡ አስቦአልና ÷ አድርጎአልምና ።
፲፪ ፡ አንቺ ፡ በብዙ ፡ ውኃ ፡ አጠገብ ፡ የምትኖሪ ÷
በመዝገብም ፡ የበለጠግሽ ፡ ሆይ ÷ እንደ ፡ ስስ
፲፫ ፡ ትሽ ፡ መጠን ፡ ፍጻሜሽ ፡ ደርሶአል ። የሠራ
ዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
በራሱ ፡ ምሎአል ፦ በእውነት ፡ ሰዎችን ፡ እንደ ፡
አንበጣ ፡ እሞላብሻለሁ ÷ እነርሱም ፡ ጩኸት ፡
ያነሡብሻል ።
፲፬ ፡ ምድርን ፡ በኃይሉ ፡ የፈጠረ ÷ ዓለሙን ፡ በጥ
በቡ ፡ የመሠረተ ÷ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡
፲፭ ፡ የዘረጋ ፡ እርሱ ፡ ነው ። ድምፁን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ውኆች ፡ በሰማይ ፡ ይታወክሉ ÷ ከምድርም ፡
ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፡ ለዝናብም ፡
መብረቅን ፡ ያደርጋል ÷ ነፋስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛ
፲፮ ፡ ግብቱ ፡ ያወጣል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እውቀት ፡
አጥቶ ፡ ሰንፎአል ÷ አንጥረኛም ፡ ሁሉ ፡ ከቀረ
ጸው ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡ አፍሮአል ፤ ቀልጦ ፡
የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ÷ እስትንፋ
፲፯ ፡ ስም ፡ የላቸውምና ። እነርሱም ፡ ምናምንቴና ፡
የቀልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፡ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡
፲፰ ፡ ይጠፋሉ ። የያዕቆብ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡
እነዚህ ፡ አይደለም ÷ እርሱ ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡
ነውና ፤ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፡ ነገድ ፡ ነው ÷
ስሙም ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።
፲፱ ፡ አንቺ ፡ መዶሻዬና ፡ የጦር ፡ መሣሪያዬ ፡ ነሽ ፤
በአንቺ ፡ አሕዛብን ፡ እሰባብራለሁ ፤ በአንቺም ፡
መንግሥታትን ፡ አጠፋለሁ ፤ በአንቺ ፡ ፈረሱ
፳ ፡ ንና ፡ ፈረሰኛውን ፡ እሰባብራለሁ ፤ በአንቺም ፡
፳፩ ፡ ሰረገላውንና ፡ በላዩ ፡ የሚቀመጠውን ፡ እሰባብ
ራለሁ ፥ በአንቺም ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ እሰባብ
ራለሁ ፥ በአንቺም ፡ ሽማግሌውንና ፡ ብላቴና
ውን ፡ እሰባብራለሁ ፥ በአንቺም ፡ ጕልማሳውን
፳፪ ፡ ና ፡ ቆንጆይቱን ፡ እሰባብራለሁ ፤ በአንቺም ፡
እረኛውንና ፡ መንጋውን ፡ እሰባብራለሁ ፥ በአን
ቺም ፡ አራሹንና ፡ ጥማዱን ፡ እሰባብራለሁ ፥
በአንቺም ፡ አለቆችንና ፡ ሹማምቶችን ፡ እሰባ
፳፫ ፡ ብራለሁ ። በጽዮን ፡ በዓይናችሁ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡
ሠሩት ፡ ክፋታቸው ፡ ሁሉ ፡ በባቢሎንና ፡ በከ
ለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ፍዳ
ቸውን ፡ እከፍላለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፳፬ ፡ አንተ ፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ የምታጠፋ ፡ አጥፊ ፡
፳፭ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ÷ እነሆ ÷ እኔ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷
ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እጄንም ፡ እዘረጋብሃ
ለሁ ÷ ከድንጋዮችም ፡ ላይ ፡ እንከባልልሃለሁ ÷
የተቃጠለም ፡ ተራራ ፡ አደርግሃለሁ ። ከእን
፳፮ ፡ ተም ፡ ለማዕዘንና ፡ ለመሠረት ፡ የሚሆን ፡ ድን
ጋይ ፡ አይወስዱም ÷ ለዘላለምም ፡ በድማ ፡ ትሆ
ናለህ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
፳፯ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዓላማን ፡ አንሡ ፡ በአሕዛብም ፡
መካከል ፡ መለከት ፡ ንፉ ÷ አሕዛብንም ፡ አዘጋ
ጁበት ፡ የአራራትንና ፡ የሚኒን ፡ የአስከናዝ
ንም ፡ መንግሥታት ፡ ሰብስቡባት ፡ አለቃንም ፡
በላይዋ ፡ አቁሙ ፤ እንደ ፡ ጠጕራም ፡ ኩብኩባ ፡
፳፰ ፡ ፈረሶችን ፡ በላይዋ ፡ አውጡ ። አሕዛብን ፡ የሜ
ዶንንም ፡ ነገሥታት ፡ አለቆችንም ፡ ሹማምቶ
ችንም ፡ ሁሉ ፡ የግዛታቸውንም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡
አዘጋጁባት ። ማንም ፡ እንዳይቀመጥባት ፡ የባ
፳፱ ፡ ቢሎንን ፡ ምድር ፡ በድማ ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፡
የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ጸን
ቶአልና ፡ ምድር ፡ ተናውጣለች ፡ ታመመችም ።
፴ ፡ የባቢሎን ፡ ኃያላን ፡ መዋጋትን ፡ ትተዋል ፡ በአ
ምባዎቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ኃይ
ላቸውም ፡ ጠፍቶአል ፡ እንደ ፡ ሴቶችም ፡ ሆነ
ዋል ፤ ማደሪያዎችዋም ፡ ነድደዋል ፡ መወርወ
፴፩ ፡ ሪያዎችዋም ፡ ተሰብረዋል ። ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ከተማው ፡ እንደ ፡ ተያዘች ÷ መል
ክዎችዋም ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ ቅጥርዋም ፡ በእ
ሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ÷ ሰልፈኞችም ፡ እንደ ፡
ደነገጡ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ይነግር ፡ ዘንድ ፡
ወሬኛው ፡ ወሬኛውን ፡ መልእክተኛውም ፡ መል
እክተኛውን ፡ ሊገናኝ ፡ ይሮጣል ።
፴፪ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ አውድማን ፡ እንደ ፡
ተረገጠ ፡ ጊዜ ÷ እንዲሁ ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡
ናት ፡ ጥቂት ፡ ቈይታ ፡ የመከር ፡ ጊዜ ፡ ይደርስ
፴፫ ፡ ባታል ። የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡
በላኝ ÷ ከፋፈለኝም ÷ እንደ ፡ ባዶ ፡ ዕቃም ፡
አደረገኝ ÷ እንደ ፡ ዘንዶም ፡ ዋጠኝ ÷ ከሚጣፍ
ጠውም ፡ ምግቤ ፡ ሆዱን ፡ ሞላ ÷ እኔንም ፡
ጣለኝ ። በጽዮን ፡ የምትቀመጥ ፡ — በእኔና ፡
፴፬ ፡ በሥጋዬ ፡ የተደረገ ፡ ግፍ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡
ይሁን ፡ ትላለች ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ — ደሜ ፡ በነ
ለዓውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ይሁን ፡
፴፭ ፡ ትላለች ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ እነሆ ÷ እምዋገትልሻለሁ ፡ በቀልሽ
ንም ፡ እበቀልልሻለሁ ፤ ባሕርዋንም ፡ ድርቅ ፡
አደርገዋለሁ ፡ ምንጮዋንም ፡ አደርቃለሁ ።
፴፮ ፡ ባቢሎንም ፡ የድንጋይ ፡ ቍልልና ፡ የቀበሮ ፡
ማደሪያ ፡ መደነቂያም ፡ ማፍዋጫም ፡ ትሆናለች ÷
፴፯ ፡ የሚቀመጥባትም ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። በእን
ድነትም ፡ እንደ ፡ አንበሶች ፡ ያገሣሉ ÷ እንደ ፡
፴፰ ፡ አንበሳም ፡ ደቦሎች ፡ ያኵረመርማሉ ። በሞቃ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ ለዘላለምም ፡
እንቀላፋተው ፡ እንዳይነቁ ፡ የመጠጥ ፡ ግብዣ ፡
አደርግላቸዋለሁ ፡ አሰክራቸውማለሁ ÷ ይላል ፡
፴፱ ፡ እግዚአብሔር ። እንደ ፡ ጠቦቶችና ፡ እንደ ፡
አውራ ፡ በጎች ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎችም ፡
ወደ ፡ መታረድ ፡ አወርዳቸዋለሁ ።
፵ ፡ ሼሻክ ፡ እንዴት ፡ ተያዘች ! ፤ የምድርም ፡
ሁሉ ፡ ምስጋና ፡ እንዴት ፡ ተወሰደች ! ፤ ባቢሎ
ንም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ መደነቂያ ፡ እንዴት ፡
፵፩ ፡ ሆነች ! ፤ ባሕር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ በሞገ
፵፪ ፡ ዱም ፡ ብዛት ፡ ተከደነች ። ከተሞችዋ ፡ በድማና ፡
ደረቅ ፡ ምድር ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ሰውም ፡ የማ
ይቀመጥባት ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ የማያልፍባት ፡
፵፫ ፡ ምድር ፡ ሆኑ ። በባቢሎንም ፡ ውስጥ ፡ ዘልን ፡
አቀጣለሁ ፡ የዋጠውንም ፡ ከአፉ ፡ አስተፋዋለሁ ፡
አሕዛብም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አይሰ
በሰቡም ፡ የባቢሎንም ፡ ቅጥር ፡ ይወድቃል ።
፵፬ ፡ ሕዝቤ ፡ ሆይ ÷ ከመካከልዋ ፡ ውጡ ፡ እያንዳ
ንዳችሁም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቊጣ ፡
፵፭ ፡ ራሳችሁን ፡ አድኑ ። በምድርም ፡ ከሚሰማ ፡
ወሬ ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፡ ልባችሁም ፡ የዝለ ፡
አይሁን ፤ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ወሬ ፡ ይመጣል ÷
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሌላው ፡ ዓመት ፡ ወሬ ÷ በም
ድርም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ይመጣል ÷ አለቃም ፡ በአ
፵፮ ፡ ለቃ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ። ስለዚህ ፡ እነሆ ÷ የተቀ
ረጹትን ፡ የባቢሎን ፡ ምስሎች ፡ የምቀጣበት ፡
ዘመን ፡ ይመጣል ÷ ምድርዋም ፡ ሁሉ ፡ ታፍራ
ለች ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱት ፡ ሁሉ ፡ በመካከ
፵፯ ፡ ልዋ ፡ ይወድቃሉ ። አጥፊዎች ፡ ከሰሜን ፡ ይመ
ጡባታልና ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በእነርሱም ፡
ያለው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ እልል ፡ ይላሉ ÷
፵፰ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በባቢሎንም ፡ ከእስራ
ኤል ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ እንዲወድቁ ፡
እንዳደረገች ÷ እንዲሁ ፡ በባቢሎን ፡ ከምድሩ ፡
ሁሉ ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ ይወድቃሉ ።
፵፱ ፡ ከሰይፍ ፡ ያመለጣችሁ ፡ ሆይ ÷ ሂዱ ÷ አትቁ
ሙ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሩቅ ፡ አስቡ ÷ ኢየ
፶፩ ፡ ሩሳሌምንም ፡ በልባችሁ ፡ አስቡ ። ስድብን ፡
ስለ ፡ ሰማን ፡ አፍረናል ፡ ባዕዳን ፡ ሰዎችም ፡

ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተዋ
ልና ፡ ነውር ፡ ፊታችንን ፡ ከደኖታል ። ስለዚህ ÷ ፶፪
እነሆ ÷ የተቀረጹትን ፡ ምስሎችዋ ፡ የምቀጣ
በት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ÷ ይላል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በምድርዋም ፡ ሁሉ ፡ የተወጉት ፡ ያንቋ
ርራሉ ። ባቢሎን ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብት ፶፫
ወጣ ፡ የኀይልዋንም ፡ ከፍታ ፡ ብታጸና ÷ ከእኔ ፡
ዘንድ ፡ አጥፊዎች ፡ ይመጡባታል ÷ ይላል ፡ እግ
ዚአብሔር ።
ከባቢሎን ፡ ጩኸት ÷ ከከለዳውያንም ፡ ፶፬
ምድር ፡ የታላቅ ፡ ጥፋት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቶ
አል ። እግዚአብሔር ፡ ባቢሎንን ፡ አጥፍቶአታ ፶፭
ልና ÷ ከእርስዋም ፡ ታላቁን ፡ ድምፅ ፡ ዝም ፡ አሰኝ
ቶአልና ፤ ሞገዳቸውም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውኆች ፡
ይተመማል ÷ የድምፃቸውም ፡ ጩኸት ፡ ተሰ
ምቶአል ። ነዋሪው ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ መጥ ፶፮
ቶባታልና ÷ ኃያላኖችዋ ፡ ተያዙ ፡ ቀስታቸ
ውም ፡ ተሰበበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍዳን ፡ የሚ
ከፍል ፡ አምላክ ፡ ነውና ÷ ፍዳንም ፡ በእርግጥ ፡
ይከፍላል ። መሳፍንቶችዋንና ፡ ጥበበኞችዋ ፶፯
ንም ÷ አለቆችዋንና ፡ ሹማምቶችዋን ፡ ኃያ
ላኖችዋንም ፡ አሰክራለሁ ÷ ለዘላለምም ፡ እን
ቀላፍተው ፡ እይነቁም ÷ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሠራ
ዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ። ፶፰
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ሰፊው ፡ የባቢሎን ፡ ቅጥር ፡ ፈጽሞ ፡
ይፈርሳል ፡ ረጃጅሞችም ፡ በሮችዋ ፡ በእሳት ፡
ይቃጠላሉ ፡ የወገኖችም ፡ ድካም ፡ ከንቱ ፡ ትሆ
ናለች ÷ የአሕዛብም ፡ ሥራ ፡ ለእሳት ፡ ትሆና
ለች ፤ እነርሱም ፡ ይደክማሉ ።
የመሕሚያ ፡ ልጅ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ሠራያ ፡ ፶፱
የሄዱን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ ፡ በአራተ
ኛው ፡ ዓመት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘው ፡ ቃል ፡
ይህ ፡ ነው ። ሠራያም ፡ የቤት ፡ አዛዥ ፡ ነበረ ።
በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ ፷
ሁሉ ÷ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ የተጻፈውን ፡ ይህን ፡
ቃል ፡ ሁሉ ÷ ኤርምያስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ላይ ፡
ጻፈው ። ኤርምያስም ፡ ሠራያን ፡ እንዲህ ፡ ፷፩
አለው ፦ — ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በገባህ ፡ ጊዜ ፡ እይ ÷
ይህንም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ አንብብና ፦ — አቤቱ ÷ ፷፪
ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡
እንዳይቀመጥባት ÷ ለዘላለምም ፡ በድማ ፡ እን
ድትሆን ፡ ታጠፋት ፡ ዘንድ ፡ በዚህች ፡ ስፍራ ፡
ላይ ፡ ተናግረሃል ፡ በል ። ይህንም ፡ መጽሐፍ ፡ ፷፫
ማንበብ ፡ ከፈጸምህ ፡ በኋላ ÷ ድንጋይን ፡ እሰ
ርበት ፡ በኤፍራጥስም ፡ ውስጥ ፡ ጣለው ፤ አን ፷፬
ተም ፦ — እኔ ፡ ከማመጣባት ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ የተ
ነሣ ፡ እንዲሁ ፡ ባቢሎን ፡ ትሰጥማለች ፡ አትነሣ
ምም ፡ በል ።
የኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፶፪ ።

፩ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሀያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ÷ በኢየሩሳሌም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እና ፪ ቱም ፡ አሚጣል ፡ የተባለች ፡ የሊብና ፡ ሰው ፡ የኤር ምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ኢዮአቄምም ፡ እንዳደረገ ፡ ፫ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ። ፬ ከፈቱም ፡ አውጥቶ ፡ እስኪጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ይሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሆኖአልና ፤ ሴዴቅያስም ፡ በባቢ ሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ። ፭ ሴዴቅያስም ፡ በነገሠ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በአሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆርና ፡ ሠራ ዊቱ ፡ ሁሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ ከበቡአት ፡ በዙሪያዋም ፡ ዐርድ ፡ አደረገ ። ፮ ከተማይቱም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ተከ ፯ ብባ ፡ ነበር ። በአራተኛውም ፡ ወር ፡ በዘጠነ ኛው ፡ ቀን ፡ በከተማይቱ ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ÷ ለአገሩም ፡ ሰዎች ፡ እንጀራ ፡ ታጣ ። ፰ ከተማይ ቱም ፡ ተሰበረች ÷ ሰልፈኞችም ፡ ሁሉ ፡ ሸሹ ÷ በሁለቱም ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አትክልት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በሌሊት ፡ ከከተማይቱ ፡ ወጡ ። ከለዳውያንም ፡ በከተማይቱ ፡ ዙሪያ ፡ ነበሩ ፡ በዓረባም ፡ መን ፱ ገድ ፡ ሄዱ ። የከለዳውያንም ፡ ሠራዊት ፡ ንጉ ሡን ፡ ተከታተሉት ÷ በኢያሪኮም ፡ ሜዳ ፡ ሴዴ ቅያስን ፡ ያዙ ፡ ሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ፲ ዘንድ ፡ ተበትነው ፡ ነበር ። ንጉሡንም ፡ ይዘው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ አመጡት ፡ እርሱም ፡ ፍርድን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ። ፲፩ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ገደላቸው ÷ የይሁዳንም ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፲፪ ደግሞ ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ። የሴዴቅያስንም ፡ ዓይኖች ፡ አወጣ ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሰን ሰለት ፡ አሰረው ፡ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ወሰደው ÷ እስኪሞትም ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አኖረው ። ፲፫ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ በአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በአምስተኛው ፡ ወር ፡ ከወ ሩም ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ የቆመው ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ፲፫ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ። የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ አቃጠለ ፤ የኢየሩሳሌ ምንም ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ÷ ታላላቆችን ፡ ቤቶች ፡ ፲፬ ሁሉ ÷ በእሳት ፡ አቃጠለ ። ከዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ የከለዳውያን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡ ሁሉ ፡ ዙሪያዋን ፡ አፈ ፲፭ ረሱ ። የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ የሕዝ ቡን ፡ ድኆች ÷ በከተማም ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ሕዝብ ÷ ሸሽተውም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የተጠጉትን ÷ የሕዝቡንም ፡ ቅሬታ ፡ አፈለሰ ። ፲፮ ከለዳውያንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነ በሩትን ፡ የናስ ፡ ዓምዶች ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የነበሩትን ፡ መቀመጫዎችና ፡ የናሱን ፡ ኩሬ ፡ ሰባበሩ ÷ ናሱንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱ ። ፲፯ ምንቸቶቹንና ፡ መሣሪያዎችንም ፡ መኰ ስተሪያዎችንና ፡ ድስቶችን ፡ ጭልፋዎችንም ፡ የሚያገለግሉበትን ፡ የናስ ፡ ሰቃ ፡ ሁሉ ፡ ወሰዱ ። ፲፰ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ጽዋዎቹንና ፡ ማንደጃዎቹን ፡ ድስቶቹንና ፡ ምንቸቶችን ፡ መቅረዘችንና ፡ ጭል ፋዎቹን ፡ መንቀሎችንም ÷ የወርቁን ፡ ሰቃ ፡ በወ ርቅ ÷ የብሩንም ፡ ሰቃ ፡ በብር ፡ አድርጎ ÷ ወሰደ ። ፲፱ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያሠራቸውን ፡ ሁለቱን ፡ ዓምዶች ÷ አንዱንም ፡ ሱራ ÷ ከመቀመጫዎቹም ፡ በታች ፡ የነበሩትን ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ የናስ ፡ በሬዎች ፡ ወሰደ ፡ ለእ ፳ ነዚህ ፡ ሰቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ናስ ፡ ሚዛን ፡ አልነበ ረም ። ፳፩ ዓምዶቹም ÷ የአንዱ ፡ ዓምድ ፡ ቁመት ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ÷ የዙሪያውም ፡ መጠን ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ውፍ ረቱም ፡ አራት ፡ ጣት ፡ ያህል ፡ ነበረ ÷ በዶሙ ፡ ነበረ ። ፳፪ የናሱም ፡ ጕልላት ፡ በላዩ ፡ ነበረ ፤ የአ ንዱም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ÷ በጕልላቱም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ሁሉ ፡ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ መረበብና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ በት ፤ በሁለተኛውም ፡ ዓምድ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለ ፡ ነገርና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩበት ። ፳፫ በስተ ፡ ውጭም ፡ ዘጠና ፡ ስድስት ፡ ሮማኖች ፡ ፳፬ ነበሩ ። በመረበቡም ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩ ፡ ሮማኖች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

፳፭ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ሠራ ያን ፡ ሁለተኛውንም ፡ ካህን ፡ ሰፎንያስን ፡ ሦስ ቱንም ፡ በረኞች ፡ ወሰደ ። ከከተማይቱም ፡ ፳፮ በሰልፈኞች ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ከነበሩት ፡ አን ዱን ፡ ጃንደረባ ÷ በከተማይቱም ፡ ከሚገኙት ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከሚቆሙት ፡ ሰበቱን ፡ ሰዎች ÷ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያሰልፈውን ፡ የሠራ ዊቱን ፡ አለቃ ፡ ጸሐፊ ÷ በከተማይቱም ፡ ከተ ገኙት ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስድሳ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ። ፳፯ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወስዶ ፡ የባ ቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ አመ ጣቸው ። ፳፰ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ መታቸው ÷ በሐማትም ፡ ምድር ፡ በሪብላ ፡ ገደ ላቸው ። እንዲሁ ፡ ይሁዳ ፡ ከአገሩ ፡ ተማረከ ። ፳፱ ናቡከደነፆር ፡ የማረከው ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ነው ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሀያ ፡ ሦስት ፡ አይሁድ ፤ ፴ ናቡከደነፆርም ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ነፍስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርከአል ። ፴፩ በናቡከደነፆር ፡ በሀያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ከአይሁድ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ነፍስ ፡ ማርከ

አል ፤ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

፴፪ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ÷ በአ ሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሀያ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ÷ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ዮር ማሮዶክ ፡ በነገሠ ፡ በአንደኛው ፡ ዓመት ፡ የይ ፴፫ ሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የዮአኪንን ፡ ራስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፤ ከወህኒም ፡ አወጣው ፡ በመልካምም ፡ ተናገረው ÷ ዙፋኑንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በባቢ ሎን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ በላይ ፡ ፴፬ አደረገለት ። በወህኒም ፡ ውስጥ ፡ ለብሰት ፡ የነ በረውን ፡ ልብስ ፡ ለወጠለት ÷ ዮአኪንም ፡ በሕ ይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ እን ፴፭ ጀራ ፡ ይበላ ። ፤ ነበር ። የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የዘወትር ፡ ቀለብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ አሌፍ ። ሕዝብ ፡ ሞልቶበት ፡ የነበረች ፡ ከተማ ፡ ብቻዋን ፡ እንዴት ፡ ተቀመጠች ! በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ የነበረች ፡ እንደ ፡ መበለት ፡ ሆናለች ፤ በአውራጆች ፡ መካከል ፡ ልዕልት ፡ የነበረች ፡ ተገዢ ፡ ሆናለች ።

፪ ቤት ። በሌሊት ፡ እጅግ ፡ ታለቅሳለች ÷ እንባ ዋም ፡ በጕንጭዋ ፡ ላይ ፡ አለ ፤ ከውሽሞችዋ ፡ ሁሉ ፡ የሚያጽናናት ፡ የለም ፤ ወዳጆችዋ ፡ ሁሉ ፡ ወነጀሉአት ፡ ጠላቶችም ፡ ሆኑአት ።

፫ ጋሜል ። ይሁዳ ፡ ስለ ፡ መጨነቅና ፡ ስለ ፡ ባርነት ፡ ብዛት ፡ ተማረከች ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠች ፡ ዕረፍትም ፡ አላገኘችም ፤ የሚያስጨንቁአት ፡ ሁሉ ፡ ተጨንቃ ፡ አገኙአት ።

፩ ፡ ዳሌዋ ። ወደ ፡ ዓመት ፡ በዓልም ፡ የሚመጣ ፡ የለ
ምና ፡ የጽዮን ፡ መንገዶች ፡ አለቀሱ ፡
በሮችዋ ፡ ሁሉ ፡ ፈርሰዋል ፡ ከህናቶችዋም ፡
እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፡
ደናግሎችዋም ፡ ተጨነቁ ፡ እርስዋም ፡ በምሬት ፡
አለች ።
፭ ፡ ጌ ። ስለ ፡ ኃጢአትዋ ፡ ብዛት ፡ እግዚአብሔር ፡
አስጨንቆአታልና ፡
አስጨናቂዎችዋ ፡ ራስ ፡ ሆኑ ፡ ጠላቶችዋም ፡
ተከናወነላቸው ፤
ሕፃናቶችዋ ፡ በአስጨናቂዎች ፡ ፊት ፡ ተማርከ
ዋል ።
፮ ፡ ዋው ። ከጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ውበትዋ ፡ ሁሉ ፡
ወጥቶአል ፤
አለቆችዋ ፡ ማሰማርያ ፡ እንደማያገኙ ፡ ዋላዎች ፡
ሆኑ ፤
ከሚያዘርፋአቸው ፡ ፊት ፡ ተዳክመው ፡ ሄዱ ።
፯ ፡ ዛይ ። ኢየሩሳሌም ፡ በሞኑቅትዋና ፡ በመከራዋ ፡
ወራት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የነበረላትን ፡
የከበረን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሰበች ፡
ሕዝብዋ ፡ በአስጨናቂዎች ፡ እጅ ፡ በወደቀ ፡
ጊዜ ፡ የሚረዳትም ፡ በሌላት ፡ ጊዜ ፡
አስጨናቂዎች ፡ አዩአት ፡ በመሳፍረስዋም ፡ ሳቁ ።
፰ ፡ ሔት ። ኢየሩሳሌም ፡ እጅግ ፡ ኃጢአት ፡ ሠር
ታለች ፡ ስለዚህ ፡ ረከሰለች ፤
ያከብሩአት ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋዋን ፡
አያተዋታልና ፡ አቃለሱአት ፡
እርስዋም ፡ እየጮኸች ፡ ታለቅሰለች ፡ ወደ ፡
ኋላም ፡ ዘወር ፡ አለች ።
፱ ፡ ጤት ። አደፍዋ ፡ በልብስዋ ፡ ዘርፍ ፡ ነበረ ፡ ፍጻ
ሜዋን ፡ አላሰበችም ፡
ስለዚህ ፡ በድንቅ ፡ ተዋርዳለች ፡ የሚያጽናና
ትም ፡ የለም ፡
አቤቱ ፡ ጠላት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎአልና ፡ መከ
ራዬን ፡ ተመልከት ።
፲ ፡ ዮድ ። አስጨናቂው ፡ በከበረ ፡ ነገርዋ ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤
ወደ ፡ ጉባኤህ ፡ እንዳይገቡ ፡ ያዘዝሃቸው ፡ አሕ
ዛብ ፡
ወደ ፡ መቅደስዋ ፡ ሲገቡ ፡ አይታለችና ።
፲፩ ፡ ካፍ ። ሕዝብዋ ፡ ሁሉ ፡ እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፡
እንጀራም ፡ ይፈልጋሉ ፡
ሰውነታቸውን ፡ ለማበርታት ፡ የከበረ ፡ ሀብታ
ቸውን ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ሰጥተዋል ፡
አቤቱ ፡ ተጕሳኰ ፡ያለሁና ፡እይ ፡ ተመልከትም ።
፲፪ ፡ ላሜድ ። እናንተ ፡ መንገድ ፡ አላፊዎች ፡ ሁሉ ፡
በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለምን ?
እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ ቊጣው ፡ ቀን ፡ እኔን ፡
እንዳስጨነቀበት ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ እንደ ፡ እኔ ፡
መከራ ፡ የሚመስል ፡ መከራ ፡ እንዳለ ፡ ተመ
ልከቱ ፡ እዩ ።
፲፫ ፡ ሚም ። ከላይ ፡ አሳትን ፡ ወደ ፡ አጥንቴ ፡ ሰደደ ፡
በረታችበትም ፡
ለእግሬ ፡ ወጥመድ ፡ ዘረጋ ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡ መለ
ሰኝ ፡
አጠፋኝም ፡ ቀኑንም ፡ ሁሉ ፡ እያከሰኝ ።
፲፬ ፡ ኖን ። የኃጢአቶቼ ፡ ቀንበር ፡ በእጁ ፡ ተይዘለች ፡
ታስረው ፡ በእንገቴ ፡ ላይ ፡ ወጥተዋል ፡ ጕልበ
ቴን ፡ አደከመ ።
ጌታ ፡ በፈታቸው ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በማልችላ
ቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ሰጠኝ ።
፲፭ ፡ ሳምኬት ። ጌታ ፡ ኃያላኖቼን ፡ ሁሉ ፡ ከውስጤ ፡
አስወገዳቸው ፡
ጕልማሶቼን ፡ ያደቅቅ ፡ ዘንድ ፡ ጉባኤን ፡ ጠራ
ብኝ ፤
ጌታ ፡ ድንግሊቱን ፡ የይሁዳን ፡ ልጅ ፡ በመጥመ
ቂያ ፡ እንደሚረገጥ ፡ አድርጎ ፡ረገጣት ።
፲፮ ፡ ዓ ። የሚያጽናናኝ ፡ነፍሴንም ፡ የሚያበረታት ፡
ከእኔ ፡ ርቆአልና ፡
ስለዚህ ፡ አለቅሳለሁ ፡ ዓይኔ ፡ ዓይኔ ፡ ውኃ ፡ ያፈ
ስሳል ።
ጠላት ፡ በረትቶአልና ፡ ልጆቼ ፡ ጠፍተዋል ።
፲፯ ፡ ፌ ። ጽዮን ፡ እጅዋን ፡ ዘረጋች ፡ የሚያጽናናት ፡
የለም ፡
እግዚአብሔር ፡ በያዕቆብ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ እን
ዲያስጨንቁት ፡ አዘዘ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ በመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡
ነገር ፡ ሆነለች ።
፲፰ ፡ ጻዲ ። በእፉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ዓመፅ ፡ አድርጌአለ ፡
ሁና ፡ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ።
እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እባካችሁ ፡ ስሙ ፡
መከራዬንም ፡ ተመልከቱ ፤
ደናግሎቼና ፡ ጕበዛዝቴ ፡ ተማርከው ፡ ሄዱ ።
፲፱ ፡ ቆፍ ። ውሽሞቼን ፡ ጠራሁ ፡ እነርሱም ፡ አታለ
ሉኝ ፡
ካህናቶቼና ፡ ሽማግሌዎቼ ፡ ሰውነታቸውን ፡
ያዘረቱ ፡ ዘንድ ፡
መብል ፡ ሲፈልጉ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሞቱ ።
፳ ፡ ፈስ ። አቤቱ ፡ ተጨንቄአለሁና ፡ አንጀቴም ፡
ታውኩብኛልና ፡ ተመልከት ፡
ዓመፃን ፡ ፈጽሞ ፡ አደረጌአለሁና ፡ ልቤ ፡ በው
ስጠ ፡ ተገላበጠብኝ ፡
በሜዳ ፡ ሰይፍ ፡ ልጆቼን ፡ አጠፋ ፡ በቤትም ፡
ሞት ፡ አለ ።
፳፩ ፡ ሳን ። እኔ ፡ እየጮኸሁ ፡ እንደማሰኳስ ፡ ሰምተ
ዋል ፡ የሚያጽናኑኝ ፡ የለም ፡
ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መከራዬ ፡ ሰምተዋል ፡
አንተ ፡ አድርገኸዋልና ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡
ስለ ፡ እርሱ ፡ የተናገርኸውን ፡ ቀን ፡ ታመጣለህ ፡
እነርሱም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይሆናሉ ።
፳፪ ፡ ታው ። ልቅሶዬ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፡ ልቤም ፡ ደክ
ሞአልና ፡
ክፋታቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ፊትህ ፡ ይድረስ ፡
ስለ ፡ ኃጢአቴ ፡ ሁሉ ፡ እንዳደረግህብኝ ፡ አድር
ግባቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ አሌፍ ። ጌታ ፡ በቊጣው ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡
ልጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አደመናት !
የእስራኤልን ፡ ውበት ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡
ጣለ ፡
በቊጣውም ፡ ቀን ፡ የእግሩን ፡ መረገጫ ፡ አላሰ
በም ።
፪ ፡ ቤት ። ጌታ ፡ የያዕቆብን ፡ ማደሪያዎች ፡ ሁሉ ፡
ዋጠ ፡ አልራራም ፤
በመዓቱ ፡ የይሁዳን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አምባች ፡
አፈረሰ ፡
ወደ ፡ ምድርም ፡ አወረዳቸው ፡ መንግሥቱንና ፡
አለቆችዋን ፡ አረከሰ ።
፫ ፡ ጋሜል ። በጽኑ ፡ ቊጣው ፡ የእስራኤልን ፡ ቀንድ ፡
ሁሉ ፡ ቀጠቀጠ ፡
ቀኝ ፡ እጁን ፡ ከጠላት ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ ፡
በዙሪያውም ፡ እንደሚበላ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበ
ልባል ፡ ያዕቆብን ፡ አቃጠለ ።
፬ ፡ ዳሌዋ ። ቀስቱን ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ገተረ ፡ እንደ ፡
አስጨናቂ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ አጸና ፡
ለዓይንም ፡ የሚያምረውን ፡ ሁሉ ፡ ገደለ ፤
በጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ድንኳን ፡ መዓቱን ፡ እንደ ፡
እሳት ፡ አፈሰሰ ።
፭ ፡ ሄ ። ጌታ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ሆነ ፡ እስራኤልን ፡
ዋጠ ፡
አዳራሾችዋን ፡ ሁሉ ፡ ዋጠ ፡ አምባችዋን ፡
አጠፋ ፡
በይሁዳም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀዘንና ፡ ልቅሶን ፡ አበዛ ።
፮ ፡ ዋው ። ማደሪያውን ፡ እንደ ፡ አትክልት ፡ ነቀለ ፤
የበዓሉን ፡ ስፍራ ፡ አጠፋ ፤
እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ዓመት ፡ በዓሉንና ፡
ሰንበቱን ፡ አስረሳ ፡
በቊጣውም ፡ መዓት ፡ ንጉሡንና ፡ ካህኑን ፡ አቃ
ለለ ።
፯ ፡ ዛይ ። ጌታ ፡ መሠዊያውን ፡ ጣለ ፡ መቅደሱን ፡
ጠላ ፡
የአዳራሾችዋንም ፡ ቅጥር ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ አሳ
ልፎ ፡ ሰጠ ፤
ድምፃቸውን ፡ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በአ
ግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ።
፰ ፡ ሔት ። እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
ቅጥር ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ፡ አሰበ ፤
የመለኪያውን ፡ ገመድ ፡ ዘረጋ ፡ እጁን ፡ ከማጥ
ፋት ፡ አልመለሰም ፤
ምሽጉና ፡ ቅጥሩ ፡ እንዲያለቅሱ ፡ አደረገ ፤ በአ
ንድነት ፡ ደከሙ ።
፱ ፡ ጤት ። በሮችዋ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሰጠሙ ፡
መወርወሪያዎችዋን ፡ አጠፋ ፡ ሰበረም ፤
ንጉሥዋና ፡ አለቆችዋ ፡ ሕግ ፡ በሌለባቸው ፡
በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኖሉ ፤
ነቢያቶችዋም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ራእይ ፡
አላገኙም ።
፲ ፡ ዮድ ። የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሽማግሌዎች ፡
ዝም ፡ ብለው ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀምጠዋል ፤
ትቢያን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነሰነሱ ፡ ማቅም ፡
ታጠቁ ፤
የኢየሩሳሌም ፡ ደናግል ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡
ምድር ፡ አዘነበሉ ።
፲፩ ፡ ካፍ ። ሕፃኖና ፡ ጡት ፡ የሚጠቡ ፡ በከተማ ፡
ይቱ ፡ ጕዳና ፡ ላይ ፡ ሲዝሉ ፡
ዓይኔ ፡ በእንባ ፡ ደከመች ፡ አንጀቴም ፡ ታወከ ፤
ስለ ፡ ወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅዋቃጤ ፡ ጉበቴ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ ተዘረገፈ ።
፲፪ ፡ ላሜድ ። በከተማ ፡ ጕዳና ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡
ሰው ፡ በዛሉ ፡ ጊዜ ፡
ነፍሳቸውም ፡ በእናቶቻቸው ፡ ብብት ፡ በወጣች ፡
ጊዜ ፡
እናቶቻቸውን ፡— እህልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡
ወዴት ፡ አለ ? ይሉአቸዋል ።
፲፫ ፡ ሚም ። የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡
እመሰክርልሻለሁ ? በምንስ ፡ እመስልሻለሁ ?
ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ አጽናናሽ ፡
ዘንድ ፡ በምን ፡ አስተካክልሻለሁ ?
ስብራትሽ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፡ የሚ
ፈውስሽ ፡ ማን ፡ ነው ?
፲፬ ፡ ኖን ። ነቢያቶችሽ ፡ ከንቱና ፡ ሐሰተኛ ፡ ራእይ ፡
አይተውልሻል ፤
ምርኮሽንም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ በደልሽን ፡
አልገለጡም ፤
ከንቱና ፡ የማይረባ ፡ ነገርንም ፡ አይተውልሻል ።
፲፭ ፡ ሳምኬት ። መንገድ ፡ አላፊዎች ፡ ሁሉ ፡ እጃቸ
ውን ፡ ያጨበጭቡብሻልና ፡—
በውኑ ፡ የውበት ፡ ፍጻሜና ፡ የምድር ፡ ሁሉ ፡
ደስታ ፡ የሚሉአት ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናትን ?
እያሉ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ያፍዋጫሉ ፡
ራሳቸውንም ፡ ያንቃንቃሉ ።
፲፮ ፡ ዔ ። ጠላቶችሽ ፡ ሁሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብሽ ፡
እያፍዋጩና ፡ ጥርሳቸውን ፡ እያፋጩ ፡— ውጠ
ናታል ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ያደረግናት ፡ ቀን ፡ ይህች ፡
ናት ፡ አግኝተናታል ፡ አይተናትማል ፡ ይላሉ ።
፲፯ ፡ ፌ ። እግዚአብሔር ፡ ያሰበውን ፡ አደረገ ፤ በቀ
ድሞ ፡ ዘመን ፡ ያዘዘውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ ፤
አፈረሰ ፡ አልራራም ፡
ጠላትንም ፡ ደስ ፡ አሰኘብሽ ፡ የሚያስጨንቁሽ
ንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ።
፲፰ ፡ ጻዲ ። ልባቸው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ጮኸ ፤
የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥር ፡ ሆይ ፡ እንባሽን ፡
እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አፍስሺ ፤
ለሰውነትሽ ፡ ዕረፍት ፡ አትስጪ ፤ የዓይንሽ ፡
ብሌን ፡ አታቋርጥ ።
፲፱ ፡ ቆፍ ። ተነሺ ፡ በሌሊት ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡
ጩኺ ፡
በጌታም ፡ ፊት ፡ ልብሽን ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ አፍስሺ ፤
በጕዳና ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በራብ ፡ ደክመ ፡
ስለ ፡ ሕፃናትሽ ፡ ነፍስ ፡ እጆችሽን ፡ ወደ ፡

እርሱ ፡ አንሺ ።
፵፩ ፡ ሬስ ። አቤቱ ÷ እይ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ እንዳደረግህ ፡ ተመልከት ።
በውኑ ፡ ሴቶች ፡ ፍሬያቸውን ÷ ያቀማጠሉአቸውን ፡ ሕፃናት ÷ ይበላሉን ?
በውኑ ፡ ካህኑና ፡ ነቢዩ ፡ በጌታ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ይገደላሉን ?
፵፪ ፡ ሳን ። ብላቴናውና ፡ ሽማግሌው ፡ በመንገዶች ላይ ፡ ተጋደሙ ፡
ደናግሎቼና ፡ ጕበዛዝቴ ፡ በሰይፍ ፡ ወድቀዋል ፤
በቍጣህ ፡ ቀን ፡ ገደልሃቸው ፡ ሳትራራ ፡ አረድሃቸው ።
፵፫ ፡ ታው ። እንደ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ የሚያስፈሩኝን ፡ ከዙሪያዬ ፡ ጠራህ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ቀንም ፡ ያመለጠ ፡ ወይም ፡ የቀረ ፡ አልተገኘም ፡
ያቀማጠልኋቸውንና ፡ ያሳደግኋቸውን ፡ ጠላቴ ፡ በላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፡ አሌፍ ። በቍጣው ፡ በትር ፡ መከራ ፡ ያየ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
፪ ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ ሌለበት ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ መርቶ ፡ ወሰደኝ ።
፫ ፡ ዘወትር ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ እጁን ፡ በላዬ ፡ መለሰ ።
፬ ፡ ቤት ። ሥጋዬንና ፡ ቁርበቴን ፡ አስረጀ ÷ አጥንቴን ፡ ሰበረ ።
፭ ፡ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፡ በሐሞትና ፡ በድካምም ፡ ከበበኝ ።
፮ ፡ ቀድሞ ፡ ሞተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ በጨለማ ፡ አኖረኝ ።
፯ ፡ ጋሜል ። እንዳልወጣ ፡ በዙሪያዬ ፡ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፡ ሰንሰለቴን ፡ አከበደ ።
፰ ፡ በጠራሁና ፡ በጮኽሁ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎቴን ፡ ከለከለ ።
፱ ፡ መንገዴን ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ ዘጋ ÷ ጕዳናዬንም ፡ አጣመመ ።
፲ ፡ ዳሌጥ ። እንደሚሸምቅ ፡ ድብ ፡ እንደ ፡ ተሸሸገም ፡ አንበሳ ፡ ሆነብኝ ።
፲፩ ፡ መንገዴን ፡ ለወጠ ÷ ገነጣጠለኝም ፤ ባድማ ፡ አደረገኝ ።
፲፪ ፡ ቀስቱን ፡ ገተረ ፡ ለፍላጻውም ፡ እንደ ፡ ጊጤ ፡ አደረገኝ ።
፲፫ ፡ ሄ ። የሰገባውን ፡ ፍላጻዎች ፡ በኵላሊቴ ፡ ውስጥ ፡ ተከለ ።
፲፬ ፡ ለወገኔ ፡ ሁሉ ፡ ማላገጫ ፡ ቀኑንም ፡ ሁሉ ፡ መሳለቂያ ፡ ሆንሁ ።
፲፭ ፡ ምሬት ፡ ሞላብኝ ፡ በእሬትም ፡ አጠገበኝ ።
፲፮ ፡ ዋው ። ጥርሰን ፡ በጥንጫ ፡ ሰበረ ÷ በአመድም ፡ ከደነኝ ።
፲፯ ፡ ነፍሰን ፡ ከሰላም ፡ አራቅህ ፡ በን ፡ ነገርን ፡ ረሳሁ ።
፲፰ ፡ እኔም ፡— ኃይሌ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ተስፋዬ ፡ ጠፋ ፡ አልሁ ።
፲፱ ፡ ዛይ ። መከራዬንና ፡ ችግሬን ፡ እሬትንና ፡ ሐሞትን ፡ አስብ ።
፳ ፡ ነፍሴ ፡ እያሰበችው ፡ በውስጤ ፡ ፈዘዘች ።
፳፩ ፡ ይህችን ፡ በልቤ ፡ አኖራለሁ ÷ ስለዚህ ፡ እታገሣለሁ ።
፳፪ ፡ ሔት ። ያልጠፋነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፤ ርኅራኄው ፡ አያልቅምና ።
፳፫ ፡ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ አዲስ ፡ ነው ፤ ታማኝነትህ ፡ ብዙ ፡ ነው ።
፳፬ ፡ ነፍሴ ፡— እግዚአብሔር ፡ እድል ፡ ፈንታዬ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ተስፋ ፡ አደርገዋለሁ ፡ አለች ።
፳፭ ፡ ጤት ። እግዚአብሔር ፡ በተስፋ ፡ ለሚጠብቁት ፡ ለምትሻውም ፡ ነፍስ ፡ መልካም ፡ ነው ።
፳፮ ፡ ሰው ፡ ገሥ ፡ ብሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ ተስፋ ፡ ቢያደርግ ፡ መልካም ፡ ነው ።
፳፯ ፡ ሰው ፡ በታናኘነቱ ፡ ቀንበር ፡ ቢሸከም ፡ መልካም ፡ ነው ።
፳፰ ፡ ዮድ ። እርሱ ፡ አሸክሞታልና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ለብቻው ፡ ይቀመጥ ።
፳፱ ፡ ተስፋ ፡ የሆነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አፉን ፡ በአፈር ፡ ውስጥ ፡ ያኑር ።
፴ ፡ ጕንጩን ፡ ለሚመታው ፡ ይስጥ ÷ ስድብንም ፡ ይጥገብ ።
፴፩ ፡ ካፍ ። ጌታ ፡ ለዘላለም ፡ አይጥልምና ፤
፴፪ ፡ ቢያሳዝንም ፡ እንደ ፡ ምሕረቱ ፡ ብዛት ፡ ይራራልና ፤
፴፫ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ከልቡ ፡ አያስጨንቅም ÷ አያሳዝንምም ።
፴፬ ፡ ላሜድ ። በምድር ፡ የተጋዙትን ፡ ሁሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ይረግጣቸው ፡ ዘንድ ÷
፴፭ ፡ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ በልዑል ፡ ፊት ፡ ያመልስ ፡ ዘንድ ÷
፴፮ ፡ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ ያጣምም ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እሺ ፡ አይልም ።
፴፯ ፡ ሜም ። ጌታ ፡ ያላዘዘውን ፡ የሚልና ፡ የሚፈጽም ፡ ማን ፡ ነው ?
፴፰ ፡ ከልዑል ፡ አፍ ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አይወጣምን ?
፴፱ ፡ ሕያው ፡ ሰው ፡ የሚያጕረመርም ÷ ሰው ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚያጕረመርም ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
፵ ፡ ኖን ። መንገዳችንን ፡ እንመርምርና ፡ እንፈትን ÷ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንመለስ ።
፵፩ ፡ ልባችንን ፡ ከእጃችን ፡ ጋር ፡ በሰማይ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንሣ ።
፵፪ ፡ በድለናል ፡ ሆም፡ዐናልም ÷ አንተም ፡ ይቅር ፡ አላልህም ።
፵፫ ፡ ሳምኪት ። በቍጣ ፡ ከደንኸን ፡ አሳደድኸንም ፡ ገደልኸን ÷ አልራራህም ።
፵፬ ፡ ጸሎት ፡ እንዳያልፍ ፡ ራስህን ፡ በደመና ፡ ከደንህ ።
፵፭ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ጕድፍና ፡ ውዳቂ ፡ አደረግኸን ።
፵፮ ፡ ዔ ። ጠላቶቻችን ፡ ሁሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብን ።
፵፯ ፡ ድንጋጤና ፡ ቍጣ ÷ ጥፋትና ፡ ቅጥቃጤ ፡ ሆነብን ።

፵፰ ፡ ስለ ፡ ወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ዓይኔ ፡ የውኃ ፡ ፈሳሽ ፡ አፈሰሰች ።
፵፱ ፡ ፩ ። እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ እስኪ ፡ ጕበኝና ፡ እስኪ ፡ መለከት ፡ ድረስ ፡
ዓይኔ ፡ ሳታቋርጥ ፡ ዝም ፡ ሳትል ፡ እንባ ፡ ታፈስ ፡ ሰለች ።
፶ ፡ ስለ ፡ ከተማዪ ፡ ቁንጮጅት ፡ ሁሉ ፡ ዓይኔ ፡ ነፍሴን ፡ አሳዘነች ።
፶፩ ፡ ጸዲ ። በከንቱ ፡ ነገር ፡ ጠላቶች ፡ የሆኑኝ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ማደንን ፡ አደኑኝ ።
፶፪ ፡ ሕይወቴን ፡ በጕድጓድ ፡ አጠፉ ÷ በላዩም ፡ ድንጋይ ፡ ጣሉ ።
፶፫ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ ውኖች ፡ ተከነበሉ ፡ እኔም ፡— ጠፋሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ።
፶፬ ፡ ቆፍ ። አቤቱ ÷ በጠለቀ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ሆኜ ፡ ስምህን ፡ ጠራሁ ።
፶፭ ፡ ድምፂን ፡ ሰማህ ፡ ጆሮህን ፡ ከልመናዬ ፡ አትመልስ ።
፶፮ ፡ በጠራሁህ ፡ ቀን ፡ ቀርበህ ፡— አትፍራ ፡ አልህ ።
፶፯ ፡ ሬስ ። ጌታ ፡ ሆይ ÷ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ተሟዋግተህ ፡ ሕይወቴን ፡ ተቤገርህ ።
፶፰ ፡ አቤቱ ÷ ጭንቀቴን ፡ አይተሃል ÷ ፍርዴን ፡ ፍረድልኝ ።
፶፱ ፡ በቀላቸውን ፡ ሁሉና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አሳባቸውን ፡ ሁሉ ፡ አየህ ።
፷ ፡ ሳን ። አቤቱ ÷ ስድባቸውንና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አሳባቸውን ፡ ሁሉ ÷
፷፩ ፡ የተነሡብኝን ፡ ሰዎች ፡ ከንፈሮች ፡ ቀኑንም ፡ ሁሉ ፡ ያሰቡብኝን ፡ አሳባቸውን ፡ ሰማህ ።
፷፪ ፡ መቀመጣቸውንና ፡ መነሣታቸውን ፡ ተመልከት ፡ እኔ ፡ መሳለቂያቸው ፡ ነኝ ።
፷፫ ፡ ታው ። አቤቱ ÷ እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ ፍዳቸውን ፡ ትከፍላቸዋለህ ።
፷፬ ፡ የልብ ፡ ዕውርነትንና ፡ እርግማንህን ፡ ትሰጣቸዋለህ ።
፷፭ ፡ አቤቱ ÷ በቍጣ ፡ ታሳድዳቸዋለህ ፡ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ታጠፋቸዋለህ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፡ አሌፍ ። ወርቁ ፡ እንዲት ፡ ደበሰ ! ጥሩው ፡ ወርቅ ፡ እንዲት ፡ ተለወጠ !
የመቅደሱ ፡ ድንጋዮች ፡ በጕዳና ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ተበተኑ ።
፪ ፡ ቤት ። ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስሉ ፡ የከበሩ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ÷
የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ እንዲት ፡ ተቁጠሩ !
፫ ፡ ጋሜል ። ቀበሮች ፡ እንኳ ፡ ጡታቸውን ፡ ገልጠው ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ አጠቡ ፡
የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰጕን ፡ ጨካኝ ፡ ሆነች ።
፬ ፡ ዳሌጥ ። ጡት ፡ የሚጠባው ፡ የሕፃን ፡ ምላስ ፡ ከጥም ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ትና ጋው ፡ ተጣበቀ ፤
ሕፃናት ፡ እንጀራ ፡ ለመኑ ፡ የሚቈርስላቸው ፡ አጡ ።
፭ ፡ ስለዚህ ፡ ጣፋጭ ፡ ሲበሉ ፡ የነበሩ ፡ በመንገድ ፡ ጠፉ ፡
በቀይ ፡ ግምጃ ፡ ያደጉ ፡ የነበሩ ፡ የፍግ ፡ ክምር ፡ አቀፉ ።
፮ ፡ ዋው ። የማንም ፡ እጅ ፡ ሳይወድቅበት ፡ ድንገት ፡ ከተገለበጠች ፡
ከሰዶም ፡ ኃጢአት ፡ ይልቅ ፡ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኃጢአት ፡ በዛች ።
፯ ፡ ዛይ ። አለቆችዋ ፡ ከበረዶ ፡ ይልቅ ፡ ጥሩ ÷ ከወተት ፡ ይልቅ ፡ ነጭ ፡ ነበሩ ፡
ገላቸው ፡ ከቀይ ፡ ሰንቋ ፡ ይልቅ ፡ ቀይ ፡ ነበረ ÷ መልካቸውም ፡ እንደ ፡ ሰንፔር ፡ ነበረ ።
፰ ፡ ሔት ። ፊታቸው ፡ ከጥቁሮ ፡ ይልቅ ፡ ጠቍሮ ፡ አል ÷ በመንገድም ፡ አልታወቁም ፡
ቁርበታቸው ፡ ወደ ፡ አጥንታቸው ፡ ተጣብቆ ፡ አል ፡ ደርቆአል ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ ሆኖአል ።
፱ ፡ ጤት ። በሰይፍ ፡ የሞቱ ፡ በራብ ፡ ከሞቱት ፡ ይሻላሉ ፡
እነዚህ ፡ የምድርን ፡ ፍሬ ፡ አጥተው ፡ ተወግተው ፡ ቀጥነዋል ።
፲ ፡ ዮድ ። የርኅሩኖች ፡ ሴቶች ፡ እጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ቀቅለዋል ፤
የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በመቀጥቀጥዋ ፡ መብል ፡ ሆኑአቸው ።
፲፩ ፡ ካፍ ። እግዚአብሔር ፡ መዓቱን ፡ ፈጽሞአል ÷ ጽኑ ፡ ቍጣውን ፡ አፍስሶአል ፤
እሳትን ፡ በጽዮን ፡ ውስጥ ፡ አቃጠለ ÷ መሠረትዋንም ፡ በላች ።
፲፪ ፡ ላሜድ ። የምድር ፡ ነገሥታት ፡ በዓለምም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡
አስጨናቂና ፡ ጠላት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ እንዳገባ ፡ አላመኑም ።
፲፫ ፡ ሚም ። የጻድቃንን ፡ ደም ፡ በውስጥዋ ፡ ስላፈሰሱ ፡
ስለ ፡ ነቢያቶችዋ ፡ ኃጢአትና ፡ ስለ ፡ ካህናቶች ፡ በደል ፡ ነው ።
፲፬ ፡ ኖን ። ታውረው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተቅበዘበዙ ፡
ልብሳቸው ፡ እንዳይዳሰስ ፡ በደም ፡ ረክሰዋል ።
፲፭ ፡ ሳምኬት ። እናንተ ፡ ርኩሳን ÷ ራቁ ÷ ርቃችሁም ፡ ሂዱ ÷ አትንኩ ፡ ብለው ፡ ጮኹባቸው ።
በሸሹና ፡ በተቅበዘበዙ ፡ ጊዜ ÷ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡— በዚህ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኖሩም ፡ ተባለ ።
፲፮ ፡ ዓ ። የእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በተናቸው ፡ እርሱም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለከታቸውም ፡
የካህናቱን ፡ ፊት ፡ አላፈሩም ÷ ሽማግሌዎቹንም ፡ አላከበሩም ።
፲፯ ፡ ፌ ። ዓይናችን ፡ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ረዳታችን ፡ ገና ፡ ሲመለከት ፡ ጠፍቶአል ፤
በመቆየታችን ፡ ማዳን ፡ የማይቻለውን ፡ ሕዝብ ፡ ጠብቀናል ።
፲፰ ፡ ጸዲ ። በእደበባያችን ፡ እንዳንሄድ ፡ ፍለጋች ፡

ንን ፡ ተከተሉ ፡
ፍጻሜያችን ፡ ቀርቦአል ÷ ዕድሜያችን ፡ አልቆ
አል ÷ ፍጻሜያችን ፡ ደርሶአል ።
፲፱ ቆፋ ። አሳዳጆቻችን ፡ ከሰማይ ፡ ንስር ፡ ይልቅ ፡
ፈጣኖች ፡ ሆኑ ፡
በተራሮች ፡ ላይ ፡ አሳደዱን ÷ በምድረ ፡ በዳ ፡
ሸመቁብን ።
፳ ፌስ ። ስለ ፡ እርሱ ፡— በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በጥ
ላው ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ፡ ያልነው ፡
በእግዚአብሔር ፡ የተቀባ ÷ የሕይወታችን ፡ እስ
ትንፋስ ÷ በጕድጓዳቸው ፡ ተያዘ ።
፳፩ ሳን ። በዖፅ ፡ ምድር ፡ የምትኖረ ፡ የኤዶምያስ ፡
ልጅ ፡ ሆይ ÷ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ሐሤትም ፡ አድ
ርጊ ፡
ጽዋው ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እንቺ ፡ ያልፋል ÷ እን
ቺም ፡ ትሰክሪአለሽ ፡ ትራቁቻለሽም ።
፳፪ ታው ። የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ የበደልሽ ፡ ቅጣት ፡
ተፈጸመ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያስማርክ
ሽም ።
የኤዶምያስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ በደልሽን ፡ ይቀጣል ፡
ኃጢአትሽን ፡ ይገልጣል ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ አቤቱ ÷ የሆነብንን ፡ አስብ ፡
ተመልከት ፡ ስድባችንንም ፡ እይ ።
፪ ርስታችን ፡ ለእንግዶች ÷
ቤቶቻችን ፡ ለሌሎች ፡ ሆኑ ።
፫ ድሀ ፡ አደጎችና ፡ አባት ፡ የሌለን ፡ ሆነናል ፡
እናቶቻችን ፡ እንደ ፡ መበለቶች ፡ ሆነዋል ።
፬ ውኃችንን ፡ በብር ፡ ጠጣን ፡
እንጨታችንን ፡ በዋጋ ፡ ገዛን ።
፭ አሳዳጆቻችን ፡ በአንገታችን ፡ ላይ ፡ ናቸው ፡
እኛ ፡ ደክመናል ፡ ዕረፍትም ፡ የለንም ።
፮ ለግብጻውያንና ፡ ለአሦራውያን ፡
እንጀራ ፡ እንጠግብ ፡ ዘንድ ፡ እጅ ፡ ሰጠን ።
፯ አባቶቻችን ፡ ኃጢአትን ፡ ሠሩ ፡ ዛሬም ፡ የሉም ፡
እኛም ፡ በደላቸውን ፡ ተሸከምን ።
፰ ባሪያዎች ፡ ሠልጥነውብናል ፡
ከእጃቸው ፡ የሚታደገን ፡ የለም ።
፱ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡
በሕይወታችን ፡ እንጀራችንን ፡ እናመጣለን ።
፲ ከሚያቃጥል ፡ ከራብ ፡ ትኩሳት ፡ የተነሣ ፡
ቁርበታችን ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ጠቁሯ ።
፲፩ በጽዮን ፡ ሴቶችን ÷
በይሁዳም ፡ ከተሞች ፡ ደናግልን ፡ አጐሰቈሉ ።
፲፪ አለቆች ፡ በእጃቸው ፡ ተሰቀሉ ፡
የሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ አልታፈረም ።
፲፫ ጕልማሶች ፡ ወፍጮን ፡ ተሸከሙ ÷
ልጆችም ፡ ከእንጨት ፡ በታች ፡ ተሰናከሉ ።
፲፬ ሽማግሌዎች ፡ ከአደባባይ ÷
ጕልማሶችም ፡ ከበገናቸው ፡ ተሻሩ ።
፲፭ የልባችን ፡ ደስታ ፡ ቀርቶአል ፡
ዘፈናችን ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ተለውጦአል ።
፲፮ አክሊል ፡ ከራሳችን ፡ ወድቆአል ፡
ኃጢአት ፡ ሠርተናልና ፡ ወዮልን !
፲፯ ስለዚህ ፡ ልባችን ፡ ታምሞአል ፡
ስለዚህም ፡ ነዝ ፡ ዓይናችን ፡ ፈዝዘአል ፡
፲፰ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ተራራ ÷ ባድማ ፡ ሆኖለችና ÷
ቀበሮችም ፡ ተመላልሰውበታልና ።
፲፱ አቤቱ ÷ አንተ ፡ ለዘላለም ፡ ትኖራለህ ፡
ዙፋንህ ፡ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ነው ።
፳ ስለ ፡ ምን ፡ ለዘላለም ፡ ትረሳናለህ ?
፳፩ ስለ ፡ ምንስ ፡ ለረጅም ፡ ዘመን ፡ ትተውናለህ ?
፳፪ አቤቱ ÷ ወደ ፡ አንተ ፡ መልሰን ፡ እኛም ፡ እንመ
ለሳለን ፡
ዘመናችንን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አድስ ።
፳፫ ነዝ ፡ ግን ፡ ፈጽመህ ፡ ጥለኸናል ፡
እጅግ ፡ ተቈጥተኸናል ።

ት ን ቢ ተ ፡ ሕ ዝ ቅ ኤ ል ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በሠላሳኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡
ከወሩም ፡ በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ በከቦር ፡ ወንዝ ፡
በምርኮኞች ፡ መካከል ፡ ሳለሁ ፡ ሰማያት ፡ ተከ
ፈቱ ÷ የእግዚአብሔርንም ፡ ራእይ ፡ አየሁ ።
፪ ንጉሡ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በአምስተኛው ፡
፫ ዓመት ፡ ከወሩም ፡ በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በከለዳውያን ፡ አገር ፡ በከ
ቦር ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ቡዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡
ወደ ፡ ሕዝቅኤል ፡ መጣ ። የእግዚአብሔርም ፡
፬ እጅ ፡ በዚያ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ሆነች ÷ እኔም ፡ አየሁ ÷
እነሆም ÷ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስና ፡
ታላቅ ፡ ደመና ፡ የሚበርቅም ፡ እሳት ፡ መጣ ÷
በዙሪያውም ፡ ፀዳል ፡ ነበረ ÷ በመካከልም ፡
በእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚብለጨለጭ ፡ የወርቅ ፡
፭ ምስያ ፡ ነበረ ። ከመካከልም ፡ የአራት ፡ እንስ
፮ ሶች ፡ አምሳያ ፡ ወጣ ። መልካቸውም ፡ እንደ
ዚህ ፡ ነበረ ÷ ሰውም ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። ለእያ
ንዳንዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ፊት ÷ ለእያንዳን
፯ ዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ክንፍ ፡ ነበሩት ። እግሮ
ቻቸውም ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ፡ የእግ
ራቸውም ፡ ኩቴ ፡ እንደ ፡ ጥጃ ፡ እግር ፡ ኩቴ ፡
፰ ነበረ ፡ እንደ ፡ ተወለወለ ፡ ናስም ፡ ይብለጨለጭ ፡
፱ ነበር ። በክንፎቻቸውም ፡ በታች ፡ በእያንዳቱ ፡
ጐድናቸው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ነበረ ፡ ለአራ
ቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ፊትና ፡ ክንፍ ፡ ነበሩአ
፲ ቸው ። ክንፎቻቸው ፡ እርስ ፡ በእርሱ ፡ የተያ
ያዘ ፡ ነበረ ፡ ሲሄዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ÷
፲፩ እያንዳንዱም ፡ ፊቱን ፡ አቅንቶ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ።
የፊታቸው ፡ አምሳያ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረ ÷
ለአራቱም ፡ በስተ ፡ ቀኛቸው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡
ፊት ÷ በስተ ፡ ግራቸውም ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ፊት ፡
ነበራቸው ÷ ለአራቱም ፡ ደግሞ ፡ የንስር ፡ ፊት ፡
፲፪ ነበራቸው ። ክንፋቸውም ፡ በላይ ፡ ተዘርግቶ ፡
ነበር ÷ የእያንዳንዱም ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ክን
ፋቸው ፡ የተያያዙ ፡ ነበሩ ÷ ሁለት ፡ ሁለቱም ፡
፲፫ ገላቸውን ፡ ይከድኑ ፡ ነበር ። እያንዳንዱም ፡
ወደ ፡ ፊት ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፤ መንፈ
ስም ፡ ወደሚሄድበት ፡ ሁሉ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ÷
፲፬ ሲሄዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ። በእንስሶቹ ፡
መካከል ፡ እንደሚነድድ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ ያለ ፡
ምስያ ፡ ነበረ ፤ በእንስሶች ፡ መካከል ፡ ወዲህና ፡
ወዲያ ፡ የሚሄድ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ያለ ፡ ምስያ ፡
፲፭ ነበረ ፤ ለእሳቱም ፡ ፀዳል ፡ ነበረው ÷ ከእሳቱም ፡
፲፮ መብረቅ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። እንስሶቹም ፡ እንደ ፡
መብረቅ ፡ ምስያ ፡ ይሮጡና ፡ ይመለሱ ፡ ነበር ።
፲፯ እንስሶችንም ፡ ስመለከት ÷ እነሆ ÷ በአራቱ ፡
እንስሶች ፡ አጠገብ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡
፲፰ አንድ ፡ መንኰራኵር ፡ አየሁ ። የመንኰራኵ
ራም ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ቢረሌ ፡ ነበረ ፤ አራቱም ፡
አንድ ፡ አምሳያ ፡ ነበሩ ፤ ሥራቸውም ፡ በመን
ኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ መንኰራኵር ፡
፲፱ ነበረ ። በእያራቱ ፡ ጐድናቸው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፤
፳ ሲሄዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ። ቁመታቸ
ውም ፡ የረዘመና ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበረ ፤ የአራ
ቱም ፡ ክበብ ፡ ዙሪያው ፡ በዓይን ፡ ተሞልቶ ፡
፳፩ ነበር ። እንስሶቹም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ መንኰራኵ
ሮቹ ፡ በአጠገባቸው ፡ ሄዱ ። እንስሶቹም ፡ ከም
ድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ መንኰራኵሮቹ ፡
፳፪ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ። መንፈሱ ፡ ወደሚሄድበት ፡
ሁሉ ፡ እነርሱ ፡ ሄዱ ፤ የእንስሶች ፡ መንፈስ ፡